በማሳመን "በ19ኛው ጉባኤ ላይ የወንበር ላይ ምሁራንን ገፍትረን የኢተማሰአን የመሪነት ቦታ መያዝ አለብን" አሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለም "The National Question In Ethiopia" "የብሔሮች ጥያቄ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ "ጥላሁን ታከለ" በሚል የብዕር ስም በብርሃነመስቀል ረዳ እና በኢያሱ አለማየሁ ተዘጋጅቶ የተላከውን የአልጀሪያ ቡድን አንድ ጽሁፍ በኢተማሰአ የኒዮርክ ቀበሌ ቅርንጫፍ ማኅበር መጽሔት በነበረው "The New York chapter Newsletter" በቅጽ 1 ቁጥር 3 ላይ በድብቅ አሳትመው በመጋቢት ወር 1963 ዓ.ም በመላው ዓለም ለሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራትና አባላት እንዲሰራጭ አደረጉ። ጽሁፉ የብሔረሰቦች ጥያቄ ይባል እንጂ ከማንም ያልመነጨና የራሳቸውን ዓላማ በብሔረሰቦች አስመስለው ያችኑ የራስን ዕድል በራስ መወሰን የምትለውን ጥያቄ ነው ያስተጋቧት። የከፋው ነገር ደግሞ ጽሁፉ በኢተማስአ ስም ታትሞ መውጣቱ ነበር።

በዚህ መልኩ አዞዎቹ የሰሜን አሜሪካውን የአዛዥነት ስልጣን የመጨበጥ መሠረትን ጣሉ። በኢተማሰአ ደንብ መሠረት የማኅበሩ ፕሬዝዳንት ምርጫ በየዓመቱ ይካሄድ ነበርና በ1963 ዓ.ም በ19ኛው የሎስአንጀለስ ጉባኤ ላይ በአንድነትና በትግል አጋርነት የተሰየሙት አባላት በተለሙት መሠረት ነበር አመራሮችን አውርደው በረቀቀ ዘዴያቸው የመሪነቱን ስልጣን የተረከቡት። የ12 ወር ወጥመዳቸው ሰራላቸው።

ራሳቸውንም "አዲሱ ኢተማሰአ" ብለው በመሰየማቸው አዲሱና አሮጌው ኢተማሰአ የሚል ነገር ተከተለ። በዚህ መሠረት ከ1963ቱ ጉባኤ በኋላ ዓለም አቀፉ የምሁራን የአመፅ እንቅስቃሴ የጀብሃና የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥያቄ በአንደኝነት፣ የአብዮትና የመደብ ጥያቄ በሁለተኝነት አጀንዳ ተይዘው ሊቀጥሉ ግድ ሆነ።

አዲሱና አሮጌው ኢተማሰአ ሁለት አንጃ ሆነው ቢናቆሩም፤ አዲሱ የበላይ ሆኖ መቀጠል ችሎ ነበርና "የፊላደልፊያውን አቋማችንን ለውጠናል" በማለት አዲስና አሮጌ የሚባል ነገር እንደሌለ አስመስለው፤ አዞዎቹ ከአልጀሪያው ቡድን ጋር ተመሳጥረው ያወጡትን ጽሁፍ "የመጨረሻ አቋማችን" በማለት ያንኑ የፖሊሲ አቋም በልዩ መጽሔታቸው አውጥተው በዓለም ላይ አሰራጩት።

የአውሮፓው ቡድን (ኢተማአ) ቀደም ሲልም የፊላደልፊያውን አቋም ተቃውሞ ነበርና አሁንም በኢተማሰአ ላይ የተደረገውን ኩዴታ በደስታ መቀበሉን ይፋ አደረገ። ሆኖም የአልጀሪያው ቡድንና አዲሱ ኢተማሰአ ኅብረት ፈጥረው የአውሮፓውን የመሪነት ስልጣን ለመያዝ የተለመደውን የአዞ ዘመቻ ጀመሩ። በ1964 ዓ.ም የኢተማአ 12ኛ ጉባዔ በፈረንሣይ አገር ሲካሄድ በአዞዎቹ ተዘጋጅቶ በቀረበ ጽሁፍ



በብርሃነመስቀል ረዳ የሚመራው የአልጀሪያ ቡድን የኢተማአ አመራሮችን ክፉኛ ነቀፏቸው።

አዞዎቹ በዚህም ሳይወሰኑ በዚሁ ጉባኤ ላይ የኢተማአ የራሱ አባላት ተወካዮች "የኢትዮጵያ ተማሪዎች የዓለም አቀፍ ማኅበር (ኢተዓአማ) ደንብና አሰራር የሚሻሻልበትን የውሣኔና የደንብ ረቂቅ በድርጅታዊ አሰራር አዘጋጅተን አቅርበናል" ብለው አቀረቡ። የቀረበውን ረቂቅ በእለቱ አዲሱ ኢተማሰአ እና የአልጀሪያው ቡድን ተወካዮች ተስማሙበት።

በዚህ መሠረት ዓለም አቀፉ የኢተዓአማ ጉባኤ በሚያዚያ ወር 1965 ዓ.ም በጀርመን በርሊን ከተማ መካሄድ ነበረበት። በበርሊኑ ጉባዔ ለኢተዓአማ ምስረታ የአባል ማኅበራት ውክልናና የምርጫ ስነ-ሥርዓት ጥያቄ ተነስቶ ለአንድ ሳምንት ተጨቃጨቁ።

ከዚህ ቀደም የነበሩት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ የአመፅ እንቅስቃሴ ማኅበራት አአዩተማ፣ ኢተማሰአ፣ ኢተማአ ነበሩ። በ1965ቱ ጉባዔ ላይ ግን ከብዙ ውዝግብ በኋላ ሦስት አዳዲስ ማኅበራት እንዲኖሩ ተወሰነና 1ኛ የአልጀሪያው ቡድን፣ 2ኛ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ሌባነን (ኢተማሌ) 3ኛ የኢትዮጵያ ሴቶች ዓለም አቀፍ ጥናት ክበብ (ኢሴዓአጥክ) እንዲሆኑ ተወሰነ።

በወቅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት የአአዩተማ ተወካዮች በነበረው የፖለቲካ ችግር ምክንያት በጉባዔው ላይ አልተገኙም። አሮጌው ኢተማሰአ ከአውሮፓውና ከአዲሶቹ ጋር የአላማ መለያየትና ፀብም ስለነበረ በጉባዔው አልተሳተፈም። በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ሦስቱ ማኅበራት ለዓለም አቀፉ የአመፅ እንቅስቃሴ ቅርንጫፍ ማኅበራት መሆናቸው ፀና።

በበርሊኑ ጉባኤ የአልጀሪያ ቡድን ተወካይ ሆነው የቀረቡት ስምንቱ ስደተኞች ሲሆኑ፤ በሌባነን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ተወካይ ተብለው የቀረቡት ደግሞ በመካከለኛው ምስራቅ በስደት የነበሩ 30 ተማሪዎች ናቸው።

ኢሴዓአጥክ ተብለው የተወከሉትና የአባልነትና የምርጫ መብት የተሰጣቸው የሴቶች ቡድንም አዲሡ ኢተማሰአ በአሜሪካን አገር ለማደራጀት ያሰበውን የሴቶች ማኅበር ለመመስረት ሲል የጣላቸው መሠረቶች ነበሩ።

በመሆኑም እነዚህ ግለሰቦች እንጂ በብዙሃኑ ተማሪ የተደራጁ ማኅበራት ተወካዮች አልነበሩም። ከኢተማሌ ውጪ ያሉት ሁለቱ ቡድኖች የጀብሃንና የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችን ጥያቄ በሚመለከት አንድ አይነት አቋም የያዙ ናቸው። የአዲሱ ኢተማሰአ እና የኢተማአን የአመራር ቦታ የያዙት አዞዎቹ ኢተአዓማን በአዲስ መልክ አዋቅረው

ሁሉንም ስልጣን በእዞ የትግል ስልት ጠቀለሉት፡፡ የአጠቃላዩና የብዙሃኑ የኢትዮጵያ ተማሪ ተወካይ ሆነው በድርጅት ስም ብቅ አሉ፡፡

በመጨረሻ ለተሻሻለው ኢተዓአማ ምስረታ ጉባኤ ላይ ከተገኙ አምስት አባል ማኅበራትና ቡድኖች ማለትም አዲሱ ኢተማሰአ፣ ኢተማአ፣ የአልጀሪያ ቡድን፣ ኢተማሌ፣ እና ኢሴዓአጥክ ውስጥ በጉባኤው የምርጫ ሂደትና ውጤት የኢተማአንና የኢተማሌን ተወካዮች በምርጫ ስነስርዓት በማሸነፍ እዞዎቹ በእቅዳቸው መሠረት ራሳቸውን በኅብረት "የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽን" (ኢተዓአፌ) ብለው ሰይመው በአዲስ መልክ መዋቀራቸውን ይፋ አደረጉ፡፡

በፌዴሬሽኑ ምርጫ የተሸነፉት የኢተማአ እና የኢተማሌ ተወካዮችም የጉባኤውን ውጤት ውድቅ አድርገው ወደየማኅበራቸው ተመለሱ፡፡

የኢትዮጵያ ተማሪዎች የአመፅ እንቅስቃሴ ሄዶ ሄዶ በእዞዎቹ ቁጥጥር ስር ሆኖ ኢተዓአፌ ላይ ተወስኖ ቀረ፡፡ በበርሊኑ ጉባኤ ያልተገኘው የአገር ውስጡ እአዩተማ ግን የፌዴሬሽኑ አካል ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ አዲሱና አሮጌው ኢተማሰአ ጠላትነታቸው ቀጠለ፡፡ ስለዚህም በአብዮቱ ዋዜማ የኢትዮጵያ ተማሪዎች የፌዴሬሽን፣ የኢተማአ እና የአሮጌው ኢተማሰአ አመራርና አባላት እርስ በርሳቸው ጎራ ለይተው በፖለቲካና በስልጣን ትግል ሲፋለሙ እንደቆዩ ሁሉም ባልጠበቁት ሁኔታና መንገድ ያሳበጡት አብዮት ሲፈነዳ ለሁሉም አስገራሚ ነበር፡፡

የጃንሆይ መንግስት የተማሪዎችን አመፅ ለማስቆም የተለያዩ እርምጃዎችን ለመውሰድ ቢሞክርም ሙሉ ለሙሉ መገደብ አልተቻለም፡፡ ይልቁንም የመንግስትን ተፅዕኖ መቋቋም ያልቻሉት ወደ ሌላ አገር እየተሰደዱ በውጭ አገር ያሉትን ማኅበራት እየተቀላቀሉ የየማኅበራቱን የሰው ኃይል እያጎለበቱ አመፁን አጠናክረው ቀጠሉ እንጂ ከስመው አልቀሩም፡፡ መንግስት በ1962 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ የግድያ ተግባር ከፈፀመ በኋላ የአገር ውስጡን ማኅበር ከነመጽሔቱ ሊያከስም ቢችልም፤ ከመጠነኛ ፋታ ያለፈ ዘላቂ ውጤት ስላልተገኘ በ1964 ዓ.ም ንጉሠነገስቱ፣ አልጋወራሹ፣ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ፣ የዘውድ አማካሪዎችና የካቢኔ ሚኒስትሮች ተሰብስበው በተማሪዎች ጉዳይ ላይ የሚያተኩር አዲስ የስራ መመሪያ ቀርፀው በተግባር እንዲተረጎም አዘዙ፡፡

ለዚህም አንድ ከፍተኛ ኮሚቴ በአገር ግዛት ሚኒስትር ሰብሳቢነት ተቋቋመና የአገር መከላከያ ሚኒስትር፣ የትምህርት ሚኒስትር፣ የጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹም፣ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ፣ የምድር ጦር ዋና አዛዥ፣ የፖሊስ ሠራዊት ዋና አዛዥ፣ የክቡር ዘበኛ ዋና አዛዥ፣ የህዝብ ፀጥታ ጥበቃ ዋና ሹም፣ የልዩ ካቢኔ ሹምና የዩንቨርሲቲው ፕሬዝዳንት



የኮሚቴው ተሳታፊ ሆነው፤ "የተማሪዎችን ፀጥታ ለማስከበር" በሚል ተከታዩን ውሣኔ አሳለፉ፡፡

"የኢትዮጵያ ተማሪዎች በየጊዜው እየተነሱ ትምህርት በማቆም በህዝብ ንብረትና ህይወት ላይ አደጋ በማድረስ ትምህርት ቤቶችን በመስበር፣ የትምህርት እድገት እንዲጨናጎል፣ የልጆች እድል እንዲሰናከል፣ ህዝብና የመንግስት ባለሥልጣን የሚዘልፍ ሕገወጥ ፖለቲካ አዘል የሆነ ልዩ ልዩ ጽሁፍ በመበተን ግርግርና ሽብር አድርገው ፀጥታ በመንሳታቸው ጉዳይ ግርማዊ ጃንሆይ፣ ልዑል አልጋወራሽ፣ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ክቡራን የዘውድ አማካሪዎችና የካቢኔ ሚኒስትሮች ባሉበት ስብሰባ ተደርጎ አጥፊ እንዲቀጣ፣ ትምህርት የሚፈልግ እንዲማር ፀጥታው በአስራ አራቱም ጠቅላይ ግዛቶች በሚገባ እንዲከበር ተብሎ በተወሰነው መሠረት ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ባለስልጣኖች ስለተማሪዎች ፀጥታ ማስከበር ቀደም ብለው ስለተቋቋሙ ጉባዔው ስብሰባ አድርጎ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት እንዲፈፀም ወስኗል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. "ማናቸውም የዩኒቨርሲቲ፣ የ2ኛ ደረጃና የግዛት ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንማራለን ካሉ ፀጥታ ነሾችን ለመከላከለ ፖሊስ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ እንዲጠብቅ፣
2. ብጥብጥ ያስነሱ የተማሪ መሪዎች እንዲያዙና እንዲቀጡ፣ ቅጣትም ከልማት ጋር የተያያዘ አድካሚ ስራ እንዲሆን፣ አንማርም ብለው ከትምህርት ቤት የወጡት ተማሪዎች ዳግመኛ እንዳይገቡና እንደወጡ እንዲቀሩ፣
3. ተማሪዎች በየጊዜው የሚያደርጉትን ሕገወጥ ስራ ህዝብና ወላጆች እንዲያውቁት በወላጆች ኮሚቴ በኩል በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ፣ በጋዜጣ፣ በገዥዎች ጭምር ያለማቋረጥ እንደሚገባ እንዲገለፅ፣
4. ሕገወጥ የሆኑ የዩንቨርሲቲ፣ የኮሌጅና የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ማኅበር ጥፋታቸው በፖሊስና በፀጥታ በኩል ተጣርቶ ለዩኒቨርሲቲ ቦርድና ለትምህርት ሚኒስትር እያቀረቡ ማኅበሩ እንዲፈርስ ማድረግ፣
5. ትዕዛዙን አክብረን እንማራለን ያሉ ተማሪዎች ጥቂትም ቢሆኑ ጥበቃ እየተደረገላቸው እንዲማሩ፤
6. በዚህ ቃለ ጉባዔ በቁጥር 2 የተመለከቱና፣ ከትምህርት ቤት ከወጡ በኋላ ጥፋታቸውን እየቀጠሉ የሚማሩትን እንዳይማሩ የሚያውኩ ለጥፋት ስራ የሚዘጋጁ ተማሪዎች ሲገኙ በ28ኛው ዓመት በቁጥር 13 በአንቀጽ 3 በፊደል "ሀ" መጋቢት 27 ቀን 1961 ዓ.ም በወጣው ነጋሪት ጋዜጣና ይኸው ፀንቶ

የሚቆይበትን ጊዜ በማስረዘም በ31ኛው ዓመት ቁጥር 5 በ"ሀ" ፊደል ታህሳስ 19 ቀን 1964 ዓ.ም በወጣው አዋጅ መሠረት ፖሊስ እየያዘ አስፈርዶ ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ ያደርጋል፡፡

7. አጥፊ ተማሪዎችን ፖሊስ እየሰበሰበ፣ ብዛታቸው ከፍ ያለ እንደሆነ በፀጥታ ማስከበሪያ አዋጅ መሠረት ለአገር ግዛት አቅርቦና አስወስኖ ለጦር ሠራዊትና ለክብር ዘበኛ ያከፋፍላል፡፡
8. ተማሪዎች በጥፋታቸው ሲቀጡ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ለሌሎችም ተማሪዎች የትምህርት ሚኒስትር ለምግብና ለሌላ ወጪ የሚሰጠውን ገንዘብ ተማሪዎች ለ·ተሰሩበት ክፍል ይከፍላል፡፡ ከዩኒቨርሲቲና ከትምህርት ሚኒስትር የሚገኘው ተመላሽ ባይበቃ በተለየ ቀርቦ እንዲፈቀድ ይደረጋል፡፡
9. እነዚህ ከዚህ በላይ የተመለከቱት ውሣኔዎች በአስራአራቱም ጠቅላይ ግዛቶች፣ አውራጃዎችና ወረዳዎች እንዲሰሩባቸው ስለተወሰነ ክቡራን ጠቅላይ ገዥዎችና የጠቅላይ ግዛት እንደራሴዎች፣ የጠቅላይ ግዛት ፖሊስና ዋና አዛዦች፣ የክብር ዘበኛና የብሔራዊ ጦር አዛዦች፣ የጠቅላይ ግዛቱ የትምህርት ስራ መሪ፣ የአውራጃና የወረዳ ትምህርት ቤቶች ስራ መሪዎች በአገረገዥዎች ኃላፊነት እየተሰበሰቡ በኅብረት ፕላን በትእዛዝ እያወጡ ያፈፃፀሙን ውጤት በየጊዜው እንዲሰጡ ማድረግ ነው፡፡

የሰብሳቢውና<br>የአባሎች ፊርማ<br>ያገር ግዛት<br>ሚኒስትር<br>ማሕተም"

አንድ የህዝብ አመፅ የተነሳበት መንግስት እንዲህ አይነት ውሣኔ ከማሳለፍ የተሻለ ምርጫ ይኖረዋል ብሎ ማሰብ ቢከብድም፤ የወረዳና የአውራጃ ገዥዎች እንዲሁም ውሣኔውን ለማስፈፀም የተፈቀደላቸው ሹሞች ግን ከዚህ ጠንካራ ውሣኔ ያለፈ ተጨማሪ በደል በየግዛቱ መፈፀም ጀመሩ፡፡ የአመፁ ተባባሪ ያልሆኑ የተማሪ ወላጆችን በሌላ ቂም በቀል "ተባባሪ ናቸው፣ አነሳስተዋል..." እያሉ በመወንጀል ማሰር፣ ማንገላታት፣ መዝረፍ፣ መግደል ሆነ ስራቸው፡፡

በውሣኔው ደስተኛ ያልነበሩ ተማሪዎች መኖራቸው ሳያንስ፤ ይህ መሰሉ ተደራቢ ሕገወጥ የሹማምንቱ ዝርፊያ በመጨመሩም የአውራጃና የወረዳ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እና መምህራን የየግዛቱን



ሹማምንት ሕገወጥ "የአመፅ ቅጣት"ን ተቃውመው ወደ አደባባይ መውጣት ጀመሩ፡፡

የከተማ ውስጡ ተመሳሳይ እርምጃም አመፁን የበለጠ የሚያጋግል እየሆነ ሄደ፡፡ አጠቃላዩ የአመፅ እንቅስቃሴ ሁኔታ የሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ትኩረት በመሳቡም ሁሉም የየራሱን ብሶት ይዞ ወደ አደባባይ እንዲወጣ የሚጋብዝ ነበር፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለም የኢትዮጵያ መንግስት ከዓለም ባንክ በተሰጠው የገንዘብ እርዳታ 30 የውጭ አገር፣ 51 የአገር ውስጥ የትምህርት ባለሙያዎችና 69 የመንግስት ሠራተኞች በጋራ ሆነው ብዙሃኑ መምህራን ባላወቀው መንገድ በሚስጥር አጥንተው ያቀረቡትና በ1967 ዓ.ም ሊተገበር የታሰበው አዲስ የትምህርት ፖሊሲ በመምህራን ማኅበር ዘንድ እንደተሰማ ተጨማሪ ከፍተኛ ቁጣ አስነሳ፡፡
በ150 ባለሙያዎች ለሁለት ዓመታት ተጠንቶ የቀረበው አዲስ የትምህርት ፖሊሲ "ሴክተር ሪቪው" የተሰኘው ሲሆን፤ ዓላማውም ከ1934-1965 ዓ.ም ድረስ የነበረው የኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲ ተደራሽነቱ አጥጋቢ አልነበረምና፤ ለህዝቡ የሙያ ትምህርት በዝቅተኛ ደረጃ በስፋትና በብዛት ማዳረስ ያስፈልጋል" የሚል ነው፡፡

ይህ ዓላማ ሊተገበር መሆኑን ዘግይተው የሰሙት መምህራን "ይህ አይነቱ ትምህርት አውሮፓውያን ለቅኝ ተገዥ አገራት ህዝቦች ያስተምሩት የነበረው ዝቅተኛ የሙያ ትምህርት ስለሆነ አያስፈልግም" በማለት የመንግስትን አቋም የሚያጣጥል የቅስቀሳ ዘመቻ ከፈቱ፡፡ የዚህ ዘመቻ መሪ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር /ኢመማ/ ሆነና፤ አዲሱን የትምህርት ስርዓት በመቃወምና የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄን በጥምረት በማንሳት አገዛዙን ተፈታተኑት፡፡ የ1ኛና የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎችም ከኢመማ ጎን ተሰለፉ፡፡

በ1941 ዓ.ም የተመሠረተው የኢትዮጵያ "መምህራን ኅብረት" የመጀመሪያው የሙያ ማኅበር የነበረና በ1958 ዓ.ም በመንግስት ዘንድ በይፋ ታውቆ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር /ኢመማ/ የሚል ስያሜ ይዞ የቀጠለ ማኅበር ነው፡፡

ኢመማ በብሔራዊ ደረጃ ከተደራጀ በኋላም እስከ 1964 ዓ.ም ድረስ የአባላቱን ቁጥር እና የገንዘብ አቅሙን እያዳበረ ሄዶ በ14ቱም ጠቅላይ ግዛቶች ቅርንጫፍ ማኅበራት ያሉት ግዙፍ ድርጅት ሆኖ ነበር፡፡ የመምህራን የመረዳጃ ድርጅት እስከመመስረትም ደርሷል፡፡ የአገሪቱን የፖለቲካ ጉዳይም በየዓመቱ በሚያካሂዱት ጉባዔ ላይ እያነሱ ሲወያዩበት ቆይተዋል፡፡

ኢመማ በመስከረም ወር 1966 ዓ.ም በአርባ ምንጭ ከተማ ባካሄደው በ8ኛው ዓመታዊ መደበኛ ጉባዔ ላይ የ"ሴክተር ሪቪው"ን ጉዳይ

በመቃወምና የደመወዝ ጭማሪን በማመላከት ተወያይተው ያሳለፉት ውሣኔ፤

"1. የእያንዳንዱ መምህር ደመወዝ አስር በመቶ እንዲያድግ፣ 2. መምህራን ከስራቸው በጡረታ እስኪገለሉ ድረስ በደሞዛቸው እድገት የጣራ ወሰን እንዳይደረግ፣ 3. በደሞዝ ጭማሪ ጉዳይ ለቀረበው ጥያቄ መንግሰት እስከ ህዳር 30 ቀን 1966 ዓ.ም ድረስ ተገቢውን የስምምነት መልስ እንዲሰጥ" የሚል ጠንካራ ጥያቄ ሲያቀርቡና ሲያሳስቡ፣ የትምህርት ስርዓቱን በሚመለከት ደግሞ፤

"1. የስርዓተ ትምህርቱ "ብሔራዊ ፍልስፍናው" በቅድሚያ ሳይገለፅ፣ 2. የስርዓተ ትምህርቱ ትምህርታዊ ጽሁፎችና መሣሪያዎች በደንብ ሳይዘጋጁ፣ 3. የግል ትምህርት ቤቶች በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መሠረት የሚሰሩ መሆናቸው በቅድሚያ ሳይታወቅ፣ 4. በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት እንዲከፈልበት መጠየቁ የማይገባ በመሆኑ እንዲሰረዝ፣ 5. በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ለመምህራኑ የስራ ዋጋ የተመደበው 153 ብር ካለው ሁኔታ ጋር የማይመጣጠን በመሆኑ "እስኪለወጥ ድረስ" የስርዓተ ትምህርቱን በሥራ ላይ መዋል በጥብቅ እንቃወማለን" በማለት ኢመማ አስጠነቀቀ፡፡

መንግስት የደሞዝ ጥያቄውን በሚመለከት በህዳር 30 ቀን 1966 ዓ.ም የሰጠውን መልስ የኢመማ አመራርና አባላት "ጥያቄያችን በከፊል እንጂ ሙሉ ለሙሉ ያልመለሰ ሆኖ ስላገኘነው ውድቅ አድርገናል" አሉ፡፡ ሲቀጥሉም፤ "ከታህሳስ እስከ የካቲት ድረስ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ የመምህራኑ የተስተካከለ የደሞዝ ጭማሪ ባይደረግ በፋሽዝም ሰማዕታት የዋዜማ በዓል ላይ የካቲት 11 ቀን 1966 ዓ.ም የአገሪቱ መምህራን በአገር አቀፍ ደረጃ ስራ እንደሚያቆሙ" ወስነው ተለያዩ፡፡ (የበዓሉ ዋዜማ ያሉት በየካቲት 12 ቀን በኢጣሊያ የተጨፈጨፉትን ሰማዕታት የመታሰቢያ እለት ማለታቸው ነው)

ኢመማ ታህሳስ 12 ቀን ያየነውን ውሣኔ ካሳለፈ በኋላ የትምህርት ሚኒስትር ጥያቄያቸውን ሳይመልስ አንድ ወር አለፈ፡፡

በእርግጥም አንዲት በሙስና ስትበዘበዝ የኖረችና እርቃኗን የቀረች አገር ይህን መሰሉን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል አቅም አልነበራትም፡፡

አንዴ እያምጣው ነውና በዚሁ ወቅት ደግሞ በወሎ የተከሰተውና ሊደበቅ የታሰበው ረሃብ በህዝቡ ዘንድ ታውቆ ሌላውን ኅብረተሰብ አስቆጣ፡፡ በዚሁ በታህሳስ ወርም የነዳጅ ዘይት ዋጋ በዓለም አቀፍ ደረጃ በመጨመሩ የንግድና ኢንደስትሪ ሚኒስትር ታህሳስ 30 ቀን 1966 ዓ.ም የ50 በመቶ ጭማሪ መደረጉን በዜና አውታሮች ሲያስታውቅ ህዝቡ እሪታው እየጎላ ሄደ፡፡ በጥቅሉ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ ከነበረው



የፖለቲካ ችግር ጋር ተዳምሮ ከቁጥጥር ውጭ ሆነ፡፡ ይህ የነዳጅ ጉዳይ ዓረቦችና እስራኤል ጦርነት በማድረጋቸውና የስዊዝ ቦይ እንዲዘጋ በመደረጉ በድንገት 45 ሣንቲም የነበረው አንድ ሌትር ነዳጅ 65 ሣንቲም እንደገባ በመገለፁ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ስለሚነካ፣ የሸቀጦች ዋጋ ጋርም ስለሚነካካ የእያንዳንዱን ቤት ለከፋ ችግር ማጋለጡ ግልፅ ነበር፡፡ ወዲያውም "የምንበላው እህልና የምንጠጣው ውሃ ከአፈር ጋር እየተቀላቀለ ተቸግረናል" በማለት ጥር 4 ቀን የአራተኛው ብርጌድ ወታደሮች በነገሌ ቦረና ያሉት በኑሮ ችግር ምክንያት ተማርረው በማመፅ የብርጌድ አዛዡን ጨምሮ ሁሉንም አለቆቻቸውን አሰሩ የሚል ወሬ ተሰማ፡፡ ጉዳዩን ለማጣራት ከአዲስ አበባ የተላኩት የምድር ጦር አዛዥ ጄኔራል ድረሴ ዱባለ ወደ ቦታው ሲሄድ እሳቸውንም አስረው የተበላሸውን እህል ውሃ እንዲበሉ አደረጓቸው፡፡ የሄደው ሁሉ እየታሰረ መቅረቱን ያዩት ጃንሆይ በመጨረሻ የአየር ኃይሉን አዛዥ ብ/ጄ/ል አበራን ላኩ፡፡ጄ/ሉ ጥያቄያቸው ሁሉ እንደሚመለስ የተላከውን መልዕክት ለጦሩ አንብበው ታጋቾቹን አስፈትተው ተመለሱ፡፡ የነገሌው ጦር ይህን ጥያቄ ደጋግሞ አመልክቶ የነበረ ቢሆንም፤ ጥያቄው ወደ መሀል አገር ሳይደርስ በአዛዦች ታፍኖ ቆይቶ ነበር፡፡ በእነዚህ ችግሮች ላይ ነው እንግዲህ የአዲስ አበባ ተማሪዎችና መምህራን ልዩ ልዩ ወረቀቶች አትመው እያሰራጩ ህዝቡ በአገዛዙ ላይ እንዲነሳ መቀስቀሳቸውን የቀጠሉት፡፡

የቅስቀሳ ጽሁፎች በኢመማ ጽ/ቤት እየታተሙ በየጎዳናው ለህዝቡ መድረሳቸውን ያስተዋሉት የፀጥታ ጠባቂዎች በፖሊስ ሠራዊት አዛዡ አቅራቢነት የኢመማ ፕሬዝዳንት ወደ ጃንሆይ ቀርበው ጉዳያቸውን በቀጥታ እንዲያመለክቱ ተደረገ፡፡

ለፀረ-መንግስት እንቅስቃሴው ዋና ማዕከል የሆነው ኢመማ ነው የሚባለው ሐሰት እንደሆነና፤ የኢመማ ጥያቄ የደመወዝና የአዲሱን ስርዓተ ትምህርት የሚመለከት ብቻ መሆኑን ፕሬዝዳንቱ ለጃንሆይ ገለፁ፡፡

ጃንሆይም ከሹማምንቱ የሰሙትና የኢመማ ፕሬዝዳንት ያስረዳው የተለያየ ሲሆንባቸው "የተባለውን ችግር በሚመለከት አስፈላጊውን ማስረጃ ይዘህ በማግስቱ ጥር 28 ቀን ከጠዋቱ 4 ሰዓት ወደ ታላቁ ቤተ-መንግስት እንድትቀርብ" አሉት ባረጀው አንደበታቸው፡፡

በማግስቱ ከጃንሆይ ጋር ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የአገር ግዛትና የትምህርት ሚኒስትሮች፣ የዘውድ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት፣ የእልፍኝ ዋና አስከልካይ፣ የክብር ዘበኛና የፖሊስ ዋና አዛዥ፣ የህዝብ ፀጥታ ጥበቃ ሹም በተገኙበት የኢመማ ተወካዮች ችግራቸውንና ጥያቄያቸውን አስረዱ፡፡ በእለቱ የትምህርት ሚኒስትር "የኢመማ ጥያቄ መሠረተ ቢስ" መሆኑን ሲገልፅ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደግሞ "የየካቲት 11ዱ ስራ የማቆም አድማ

ካልቀረ ተጠያቂዎቹ እናንተ የኢመማ አመራሮች ናችሁ" ብሎ ዛተ፡፡ የፖሊስ ሠራዊትና የክብር ዘበኛ አዛዦች ግን "ችግሩ ወደ ኅብረተሰቡም ተዛምቷልና ጥያቄአቸው አፋጣኝ መፍትሄ ማግኘት አለበት" በማለት የጠቅላይ ሚኒስትሩንና የትምህርት ሚኒስትሩን አካሄድ ተቃወሙ፡፡ ኢመማዎች በበኩላቸው "የኢመማ አመራር ኮሚቴ ብቻውን አቋሙን ለመለወጥ የሚያስችል ስልጣን የለውም" ብለው ገለፁ፡፡ ጃንሆይ "መምህራኑ ስራ እንዳያቆሙ የሚያደርግ ሌላ ውሣኔ አሳልፍልንና በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍትሄ እንፈልጋለን" አሉና ስብሰባው ተበተነ፡፡

ከሁለት ቀናት በኋላ የኢመማ የየግዛቱ ቅርንጫፍ ማኅበራት ተወካዮች ወደ አዲስ አበባ መጡ፡፡ በትምህርት ሚኒስትር እና በኢመማ መካከል ጥብቅ ክርክር የካቲት 2 ቀን ተካሄደ ለውጥ የለም፡፡ በመጨረሻ የኢመማ አመራርና የክፍለ አገር ተወካዮች በጽሁፍና በቃል ያንኑ ጥያቄያቸውን በኢዮቤልዩ ቤተ-መንግስት ለጃንሆይ በይበልጥ አስረዱ፡፡

ጃንሆይም "ይህ በንባብ ያቀረባችሁት ነገር እውነት ከሆነማ ከሚኒስትሮች ጋር በአንድነት ምክሩበትና ውጤቱን እንድናውቀው ይሁን" የሚል ትዕዛዝ ሰጥተው ሽማግሌው ንጉሠነገስት በማግስቱ ለአንድ ሳምንት ጉብኝት ወደ ኤርትራ ሄዱ፡፡ በንጉሠነገስቱ ትዕዛዝ መሠረት ከየካቲት 4 ቀን ጀምሮ ለተከታታይ ሦስት ቀናት በያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት የኢመማ ተወካዮችና የትምህርት ሚንስትር ከመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ኮሚሽን ባለሥልጣኖች ጋር ሆነው ያካሄዱት ስብሰባ ሁሉ ውጤት አልባ ሆነ፡፡

የባለሥልጣናቱ ትኩረት በጥያቄዎችና በሚቀርቡ የመፍትሄ ሀሳቦች ላይ ሳይሆን የየካቲት 11ን አድማ በተፅዕኖ ማስቀረቱ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ የኢመማ ተወካዮች የባለስልጣናቱን ተፅዕኖ ተቋቁመው ሲሟገቱ ሙግቱን ይከታተሉ የነበሩ የአዲስ አበባ ተማሪዎች በሚበትኑት ጽሁፍ የኢመማ አካሄድ ትክክል መሆኑን እየገለፁ ህዝቡን ይቀሰቅሱ ነበር፡፡ ከዚህም ባለፈ የመንግስትን የተደበቁ ገመናዎች ማጋለጥ ተጨማሪ ስራ አድርገው ያዙት፡፡

የካቲት 5 ቀን የደብረዘይት የአየር ኃይል አባሎች በአመፅ አዛዥ መኮንኖችን በቁጥጥር ስር አውለው የራሳቸውን የኑሮ ችግር ሲገልፁ ለመንግስት ሌላ ተፅዕኖ ሲሆን፤ ለኢመማ ግን ጥሩ እድል ሆኖ ተገኘ፡፡

የካቲት 7 ቀን የአዲስ አበባ ተማሪዎች ከኢመማ ጎን በመሰለፍ በጎዳናው ላይ በሚዘዋወሩ የመንግስት መኪኖች ላይ የድንጋይ ናዳ አወረዱ፡፡ ኢመማ የበለጠ የልብ ልብ ተሰማው፡፡ በዚህ እለት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የትምህርት ሚኒስትር ተከታዩን ጽሁፍ አትሞ አወጣ፤

"አዲሱን የትምህርት ስርዓት አጠቃላይ መንፈስ በሚገባ ያልተገነዘቡ አንዳንድ ሰዎች ይኖሩ ይሆናል፤ አያስገርምም፡፡ ማንኛውም



አዲስ ሀሳብ ለጊዜው ግራ የሚያጋባ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ አዲሱ የትምህርት አጠቃላይ ጥናት መንፈስና አላማ ዛሬ ያልገባቸው አንዳንድ ሰዎች ቢኖሩ ነገ ከፀፀት ላይ ይወድቁ ይሆናል፡፡ ዋናው ቁም ነገር ግን ካለማወቅ ለኢትዮጵያ የትምህርት እርምጃ እንቅፋት ከመሆን መቆጠብ ነው፡፡ በታሪክ ምዕራፍ ላይ ጥቁር ነጥብ ከጣሉ በኋላ መፀፀት ውጤት አያስገኝም፡፡ ትምህርትን ለማዳረስ የወጣውን እጅግ የሚያጓጓ እቅድ ስራ ላይ ለማዋል እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከፍተኛ መስዋዕት እንዲያደርግ የሚጠበቅበት ጊዜ ነው፡፡" (ረቡዕ የካቲት 7 ቀን 1966 ዓ.ም አዲስ ዘመን)

ሐሙስ የካቲት 8 ቀን የትምህርት ሚኒስትር ለኢመማ አመራር ኮሚቴ ' "የመምህራን ደመወዝና የስርዓተ ትምህርት ጥያቄዎችን በሚመለከት የሚወሰደው እርምጃ ከላይ ውሣኔ ሲሰጥበት በኢመማ በኩል ለመምህራን ይገለፃል" የሚል ደብዳቤ ልኮ ጉዳዩን ዘጋ፡፡

ኢመማ የትምህርት ሚኒስትሩን ውሣኔ በመቃወም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አስረዳ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩም "ጉዳዩ በትምህርት ሚኒስትር በኩል መልስ ካላገኘ ለግርማዊ ጃንሆይ ቀርቦ ተጠንቶ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ይሰጥበታል፡፡ ይህንንም ኢመማ ለሁሉም መምህራን ይግለፅ" ሲል የስርዓተ ትምህርቱን ጉዳይ ደግሞ "የትምህርት አጠቃላይ ጥናቱ እንደ ፕላን የሚቆጠር ስለሆነ በየጊዜው አስፈላጊ ማሻሻያ እየተደረገለት በስራ ላይ ይውላል እንጂ አይቀርም..." የሚል መልስ ሰጥቶ ነበር፡፡

ከዚያም የኢመማ ተወካዮች በጥበቃ ኃይሎች ተከበው 24 ሰዓት የፈጀ ስብሰባ አድርገው ተገደው ያሳለፉት ውሣኔ "የስራ ማቆም አድማው ቀርቷል" የሚል የነበረ ይሁን እንጂ፤ ጎን ለጎን ግን "ውሣኔው እንዳልቀረና ተገደን የተናገርነው ነው" የሚል መልዕክት በማስተላለፍና በኮድ መልዕክቶች በመጠቀም የየካቲት 11ዱን ቀጠሮ እውን አደረጉት፡፡ የመንግስት ባለሥልጣኖች ውሣኔውን ያስቀሩት መስሏቸው ተረጋግተው ነበር፡፡

ዕለተ ማክሰኞ የካቲት 11 ቀን የኢመማ መላው አባላት የስራ ማቆም አድማውን ተገበሩት፡፡ በዚያው እለት የአዲስ አበባ ታክሲ ሾፌሮች አገልግሎታቸውን አቆሙ፡፡ ከዚህች እለት ጀምሮ ምሁሩ፣ ነጋዴው፣ ሹፌሩ፣ ወታደሩ፣ ወዛደሩ ... ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ማለት ይቻላል ለተከታታይ ቀናት አገዛዙን እየተቃወመ ቀጠለ፡፡

ጃንሆይ "የደሃ ልጆችን ያገላልና ይህ የትምህርት ፖሊሲ (ሴክተር ሪቪው) መታጠፍ አለበት" የሚለውን የኢመማን ጥያቄ አመፁን ለመግታት ሲሉ አጠፉት፡፡ ቀጥለው የነዳጅ ዋጋ ጭማሪውን እንዲነሳ አስደረጉት፡፡ የደመወዝ ጭማሪውን እንደሚያጠኑት ቃል ገቡ፡፡ ግን ለውጥ የለም፡፡ የነገሌውን ጦር ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ ሰጡ፣ ለውጥ

የለም፡፡ ይልቁንም የንጉሡ "እሽ እሽ" ባይነት ዓላማው አመፁን ለማርገብ የተወሰደ እርምጃ አድርጎ ከማሰብ ይልቅ፤ እንደ ፍርሃት እየተቆጠረ ቀጠለና፣ ቀደም ሲል ከተማሪዎችና ከጅብሃ በስተቀር አንድም ፖለቲካዊ ጥያቄ ያላነሱትና ጥያቄያቸው ማኅበራዊ ጉዳዮችን ማለትም የኑሮ ችግር እንዲቃለል፣ ደመወዝ እንዲጨመር፣ አስፈላጊ ቁሳቁሶች እንዲሟሉ ይጠይቁ የነበሩት ሁሉ በተለይ ጦር ሠራዊቱ ቀስ በቀስ ጥያቄያቸውን ፖለቲካዊ ወደማድረግ አመሩ፡፡

የካቲት 18 ቀን 1966 ዓ.ም በኤርትራ አስመራ የነበረው የሁለተኛው ክፍለ ጦር አባላት የነገሌ ቦረናው ጦር በቀደደው ፈር በመጓዝ ጠንከር ያለ ጥያቄ ይዘው ተነሱ፡፡ ሁሉም ባለማዕረጎች ማዕረጋቸውን አውልቀው (በጦር ሠራዊት ሕግ መሠረት ጦሩ ሲያምፅ ከተገኘ ከተራ ወታደሩ ይልቅ መሪ መኮንኖች ከባድ ቅጣት ስለሚወሰንባቸው) ሁሉም ተራ መስለው ታጥቀው ወደ ከተማ በመውጣት የአስመራን የአየር ጣቢያ፣ የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያና ሌሎች ወሣኝ ቦታዎችን በቁጥጥር ስር በማድረግ የከፍተኛ መኮንኖችንና የሲቪል ባለሥልጣናትን እንቅስቃሴ በመግታት ጥያቄአቸውን በሬዲዮ ለንጉሡ አቀረቡ፡፡ ይህም እንደነገሌው የሠራዊቱን ብሶቶችና የኑሮ ችግሮችን የሚመለከት ጥያቄ ነበር፡፡

የጃንሆይ መንግስት አሁንም ለጦሩ ጥያቄ ፈጣን አዎንታዊ ምላሽ በእለቱ ሰጠ፡፡ ምክንያቱም በኤርትራ ያለው ጦር አመፀ ማለት ወይም የማይሆን እርምጃ ተወሰደበት ማለት የአካባቢውን የጅብሃ የትጥቅ ትግል አጎልብቶ ኢትዮጵያን አደጋ ላይ መጣል ማለት ነበርና ጃንሆይ አላንገራገሩም፡፡ ያመፀው ጦር ግን መሽቶ እንደነጋ የካቲት 19 ቀን የሚከተለውን አጀንዳ ለመንግስት በሬዲዮ አስተላለፈ፤ "1. የፖለቲካ ፓርቲ የማቋቋም ነፃነት፣ 2. የጠቅላይ ግዛት ገዥዎች በዴሞክራሲያዊ መንገድ በአካባቢው ነዋሪ ህዝብ እንዲመረጡ፣ 3. የተባባሰውን የዋጋ ግሽበት የሚቆጣጠር ደንብ እንዲወጣ፣ 4. የመሬት ይዞታ ለህዝብ በሚጠቅም መልኩ ተሻሽሎ እንዲወጣ፣ 5. ለመለዮ ለባሹ፣ ለመንግስትና ለፋብሪካ ሠራተኞች ወቅታዊውን የኑሮ ውድነት መቋቋም የሚያስችል የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግ፣ 6. የህዝብ ገንዘብ ያባከኑ ባለሥልጣናት በቁጥጥር ስር ውለው ለፍርድ እንዲቀርቡ፣ 7. እነዚህ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ እንዲያገኙ ተከታትሎ የሚያስፈፅም ከመንግስትና ከጦሩ የተውጣጡ አባላት የሚገኙበት የጋራ ኮሚቴ እንዲቋቋም..." የሚሉ የንጉሣዊ አገዛዙን የሚፈታተኑ ጥያቄዎች ቀረቡ፡፡

ይህ በሆነ በሁለተኛው ቀን የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሐብተወልድ በድንገት የስራ መልቀቂያ ደብዳቤ ለጃንሆይ አቀረቡ፡፡ ጃንሆይም የአክሊሉን ጥያቄ ተቀብለው ካቢኔውን አሰናበቱ፡፡



የሁለተኛ ክፍለ ጦር አባላት በመጀመሪያው ቀን 23 ያህል ጥያቄዎችን በሬዲዮ ለንጉሡ ሲገልፁ አንድም ፖለቲካዊ ጥያቄ አላቀረቡም ነበር፡፡ ከደመወዝ ጀምሮ እስከጡረታ ... ወዘተ የሚያትቱ ብቻ ነበር፡፡ ይህንንም "እሽ" ተብለው ሳለ በፍጥነት አገዛዙን የሚፈትን ከባድ ፖለቲካዊ ጥያቄ በማግስቱ ያስከተሉት ግን በጦሩ ብሶት ተከልለው የራሳቸውን ዙፋን የመንጠቅ (የመተካት) እቅድ የነበራቸው የንጉሡ የበታች ሹማምንት የሆኑ መሣፍንት ስለገፋፏቸው ነበር፡፡

በአንድ በኩል የግራ ክንፎች ሹማምንት ስር ነቀል ለውጥ የሚፈልጉ፤ በሌላ በኩል የቀኝ ክንፎች ጃንሆይን ከስልጣን አውርደው ሌላ ንጉሥ ለመተካት የሚያስቡት ናቸው፡፡

የጦሩ አመፅ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከፈለጉት መሣፍንት ውስጥ ዋናው አስተባባሪ ቀደም ሲል የኤርትራ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ የነበሩት ልዑል ራስ አስራት ካሣ ነበሩ፡፡ (ምስክርነት 2001 ዓ.ም)

የጦሩን ቅፅበታዊ የጥያቄ ለውጥና የጥያቄዎችን ይዘትና ጥልቀት የመረመሩ ምሁራንም የመሳፍንቱ ግፊት እንደነበረበት ያምናሉ፡፡ ይህ የውስጥ ለውስጥ የመሳፍንቱ የፖለቲካ ደባም ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሐብተወልድ ስልጣን ሲለቁ በምትካቸው ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው እንዲሾሙና አዲሱ ካቢኔ ተቋቁሞ፣ አዲስ ሹም ሽር ተደርጎ 19 አዳዲስ ሚኒስትሮች በየካቲት ማለቂያ ከጃንሆይ ፊት ቀርበው ቃለ-መሀላ ፈጽመው ስራቸውን እንዲጀምሩ አድርጓል፡፡

ምንም እንኳን ጃንሆይ ከዚህ ሹም ሽር በፊት ጄኔራል አብይ አበበን አዲስ ካቢኔ እንዲመሰርት አዘውት የነበረ ቢሆንም፤ የጄኔራል አቢይ ካቢኔ ገና ሳይመሠረት ተቃውሞ ስለገጠመው እንዲቀር ሆኗል፡፡

በመሆኑም የልጅ እንዳልካቸው መኮንን ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ መሾም በመሳፍንቱና በመኳንንቱ መካከል የነበረው የስልጣን ትግል መሳፍንቱ አሸንፈው በድል የተወጡበት ሆኖ ታዩ፡፡ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሐብተወልድ ከመሳፍንት ወገን ያልሆኑና ከታችኛው መደብ የተገኙ ነበሩና፡፡

ሆኖም ልጅ እንዳልካቸው ከልዑል ራስ አስራተ ካሣ ጋር ሽርክ ነው የሚለው ጉዳይ መሣፍንቱን ረፍት ሊሰጣቸው አልቻለም፡፡ በሌላ በኩልም የእነ ልዑል አስራተ ካሣ ተቀናቃኝ ሆነው በጦሩ ብሶት የራሳቸውን የስልጣን ጥም ለማርካት የሚሻኮቱት በአዲሱ ካቢኔ የግቢ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት የጃንሆይ የረጅም ጊዜ ታማኝ አገልጋይ ደጃዝማች ከበደ ተሠማ ነበሩ፡፡

ከመኳንንት ወገን ደጃዝማች ከበደ፣ ከመሳፍንት ወገን ልዑል ራስ አስራተ ካሣ ሆነው የስልጣን ገመድ ሲጓተቱ፣ ፍፁም እምነት የጣሉባቸውንና ለረጅም ዓመታት ያገለገሏቸውን፣ ያልበደሏቸውን

የጃንሆይን ጉዳይ እርግፍ አድርገው ትተዋል፡፡ በዚህ መካከል የህዝቡ አመፅ ጋብ ሊል ቀርቶ ይብሱን "ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም" እየተባለ ተባብሶ ቀጥሏል፡፡ ድምፁ ተሰምቶ የማያውቀው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን ውጤታማ የተባለውን ለተከታታይ አራት ቀናት የቆየ አጠቃላይ የስራ ማቆም አድማ አደረገ፡፡ ጥያቄያቸውም "የሠራተኛና አሠሪ ሕግ እንዲደነገግና በነፃነት የመደራጀት መብት እንዲከበር፤ እንዲሁም ደሞዝ እንዲጨመር" የሚል ነበር፡፡

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር "ፋታ ይሰጠኝ ሁሉንም ነገር አስተካክላለሁ" ቢሉም ሰሚ አጡ፤ ተዋከቡ፡፡ አዲሱ ካቢኔ ግን ተገቢ ስራዎችን በፍጥነት እያከናወነ ነበር፡፡ ለምሳሌ ካቢኔው ስራ በጀመረ በቀናት ውስጥ በጃንሆይ ትዕዛዝ ሕገመንግስቱን ለማሻሻል እቅድ ነደፈ፣ በመጋቢት ወር መጀመሪያ የመንግስት ሹማምንትን አለአግባብ መበልፀግ አጣርቶ ለፍርድ የሚያቀርብ የምርመራ ኮሚሽን ተቋቋመ፣ ቀጥሎ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ችግሮችን የሚያብራራና ወደመፍትሄው የሚያደርሰውን መንገድ የሚያሳየውን የእንግሊዝ አገር ፖሊሲን የተከተለውን ኋይት ፔፐር (ነጭ ሠነድ) የተሰኘውን መመሪያ ይፋ አደረገ፡፡ ነገር ግን "ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ" ተብሎ ተጮኸ፡፡ እነዚያን የመሳሰሉ ወሣኝ ወሳኝ ተግባራት የሚያዩ ኢትዮጵያዊ ዓይኖች የሉም፡፡ ረፍዷል፡፡ በዚያም ላይ የካቢኔው ሹማምንት የዚያው አገዛዝ ባለሥልጣን የነበሩ ስለሆኑ ከስራቸው ይልቅ የቀድሞ ታሪካቸው ነውና የሚታየው ስር ነቀል ለውጥ ለሚፈልግ ህዝብ ትኩረት ቢነፈጋቸው አይገርምም፡፡

ተቃውሞው ሄዶ ሄዶ ሚያዚያ 10 ቀን ከመቶ ሺ በላይ የሚገመት ህዝብ የተሳተፈበት ግዙፍ ሠላማዊ ሰልፍ ተካሄደ፡፡ በእለቱ የወጣው ህዝብ ከሁሉም ዓይነት የኅብረተሰብ ክፍል የተውጣጣ ሲሆን፤ የቤተ-ክህነትና የቤተ-መንግስት ቁርኝት እንዲቀር ከመጠየቅ ጀምሮ ባለሥልጣናትን በየቢሮአቸው እየቆለፉ ለቀናት ታሽገው እንዲቆዩ እስከማድረግ የደረሰ ነበር፡፡ ይህን ህዝባዊ ማዕበል መግታት የማይሞከር ሆነ፡፡ ያልተነሳ ጥያቄ አለ ማለት አይቻልም፡፡ በአጭሩ ሁሉንም ጥያቄዎች መመለስ ማለት ንጉሣዊ አገዛዙ ያብቃ የሚል የማያሻማ ትርጉም ያለው መሆኑ ግልፅ ነበር፡፡

አዲሱ ካቢኔ ግራ ሲጋባ በሚያዚያ 22 "ብሔራዊ የፀጥታ ኮሚሽን" አቋቁሞ ሰላምና ኃይልን ያጣመረ የአመፅ መግቻ ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ ሠራዊቱን ከካቢኔው ጎን ለማሰለፍ ሞከረ፡፡ ይህም ያስገኘው ውጤት የቀድሞው ካቢኔ ሚኒስትሮችንና ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናትን በሌላ አገላለፅ የልጅ እንዳልካቸውን ተቃዋሚዎች በኮሎኔል ዓለምዘውድ ተሠማ አማካኝነት (በኮሚቴው ውስጥ የመሪነት ስልጣን ተሰጥቶት ስለነበር) በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ማድረግን



ነበር፡፡ልጅ እንዳልካቸው በስተመጨረሻ ራሳቸውም ላይቀርላቸው በዙሪያቸው የነበሩ ተቃዋሚዎቻቸውን ሲያስለቅሙም የጃንሆይን ፈቃድ በመጠየቅ የነበረ ሲሆን፤ ንጉሡም "ይሁን ብያለሁ" ባይ ነበሩ፡፡

ከየካቲት ወር ጀምሮ እስከ ግንቦት ድረስ በነበረው ጊዜ የጦር ሠራዊቱ ጥያቄ በተለይም የደሞዝ ጭማሪው ተደርጎለት ጥያቄዎቹም ተመልሰውለት ነበርና ሰቪሉ ኅብረተሰብ "ወታደሩ የራሱን ጥቅም ብቻ አስከብሮ የህዝቡን እሮሮ አያገባኝም ያለ ከሃዲ ነው" እየተባለ መወረፍ ጀመረ፡፡ የዚህ ትችት አሰራጮች ለውጥ ፈላጊ ነን ያሉ ምሁራን ናቸው፡፡ በዚህም መለዮ ለባሹን ላላሰበውና ላልፈለገው ስልጣን መንገድ ጠረጉለት፡፡ ከምሁራኑ ባለፈም ቀደም ሲል ያየናቸው የግራና የቀኝ የቀድሞ የጃንሆይ ታማኝ ሹማምንት "ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል"ን መርህ አድርገው በወታደሩ አመፅ ሳቢያ ጃንሆይ ሲወርዱ ለመተካት አሰፍስፈውና የየራሳቸውን ስልጣን የመያዝ እቅድ ከግብ ለማድረስ ሲሉ አመፁ እንዲቀጣጠል እንጂ እንዲረግብ የወሰዱት ይህ ነው የሚባል ቀና እርምጃ አልነበረም፡፡ እውነታውን እያወቁትም ለጃንሆይ "አይዞዎት፤ ህዝቡም ጦሩም ለእርስዎ ያለው ታማኝነት ጽኑ ነው፤ የጠላው አንዳንድ ባለሥልጣናትን ነው፤ እነዚያ ባለሥልጣናት ከተሻሩ አመፁ ይቆማል" እያሉ ይደልሏቸው ነበር፡፡ በተለይ የግቢ ሚኒስትሩ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ታማኝም ስለነበሩ ለዚህ መሰሉ የማዘናጋት ተግባር በብርቱ ጥረዋል፡፡

ምሁራኑም ሆኑ መሣፍንቱ እንዲሁም መኳንንቱ በመለዮ ለባሹ ትግል ስልጣን ለመያዝ ሲያቅዱ፤ "ራሱ ጦሩ ስልጣኑን ቢይዘውስ?" ብለው ለማሰብ የሞከሩበት ሁኔታ የለም፡፡ ምናልባትም ያው ያደጉበትና ያረጁበት ራስን በዘር ሐረግ ከፍ አድርጎ የማየት አስተሳሰባቸው ወታደሩን እንዲንቁትና "ስልጣን ለእኔ አልተፈቀደም፤ አይገባኝም" ብሎ ያስባል ብለው ካላመኑ በቀር ይህን መጠርጠር ነበረባቸው፡፡ ከዚህ አንፃር የነሱ መነሻ ብዙ ላይገርም ይችላል፡፡ ነገር ግን ለዘመናት የፖለቲካ ትግል ሲያደርጉና "ስር ነቀል ለውጥ" እያሉ ሲያቀነቅኑ የኖሩት፤ የትኛው ርዕዮት ለኢትዮጵያ እንደሚሻላት ቀድመው ሲገልፁ የቆዩት ምሁራንና ምሁር ነን ባዮች፤ ስለ አብዮትም ብዙ ያነበቡት ሁሉ ያንን የመሰለ የህዝብ አመፅ ሲያስተውሉ ቢያንስ ተከታዩን ተግባር አውቀው አንዳችም ቅድመ ዝግጅት አለማድረጋቸው ያስገርማል፡፡

የዚያ ወቅት ምሁራንም ሆኑ ስልጣን ፈላጊዎች ያንን አመፅ ሲያጋግሉ አንድ አይነት ግብ ነበራቸው፡፡ "ጦሩ ንጉሡን በአመፅ ያወርዳል፤ ምክንያቱም ታጥቋልና፡፡ ከዚያ በኋላ ወታደር አገር መምራት ስለማይችል ጦሩ ወደ ክፍሉ ይመለሳል እኛ ስልጣን እንጨብጣለን" የሚል ነው፡፡ ቢያንስ የጎረቤት አገሯን የግብፅን የቅርብ አብዮት ማሰብ

አልፈለጉም፡፡ እንደተባለውም ያንን አብዮተኛ የህዝብ ማዕበል የሚያስተባብር አንድም አካል፣ አንድም የተደራጀ ቡድን ስላልነበረ የግድ ህዝቡን የሚያስተባብር አካል አስፈለገ፡፡ እርግጥ ነው ወቅቱም ሕጉም የፖለቲካ ፓርቲ መመስረትና መንቀሳቀስ የሚቻልበት አልነበረም፡፡ ነገር ግን በአደባባይ ማመፅ የቻለና ለውጥ የፈለገ ምሁር እንዳደረጉት ከአብዮት በኋላ ሳይሆን ከአብዮቱ በፊት ቢያንስ በጠሩ እየታገዘ መፈፀም የነበረበት የቤት ስራ መኖር ነበረበት፡፡ አልሆነም፡፡

ሁኔታው ያለቀለት መሆኑ ገሃድ ወጣ፡፡ አብዮቱ መያዝ ከሚገባው ትንፋሽ በላይ የያዘ የልጆች ፊኛ መስሎ ተወጥሯል፡፡ እንዳያስተነፍሱት በማይፈታ አስተሳሰር ከጫፍ ታስሯል፣ የቀረው መፈንዳት ነው፤ ለዚህ ደግሞ ቅንጣት ምክንያት ብቻ በቂ ነበር፡፡ ያላቸውን ኃይል ተጠቅመው ያሳበጡት በውጭ አገር ያሉት ለሥልጣን ሲባሉ ይህን የሚያስቡበት ጊዜ አጡ፤ በቅርብ ያሉትም ከፈነዳ በኋላ ስለሚነፉት አዲስ የልጆች ፊኛ ሲያውጠነጥኑ ነበር፡፡ በመሆኑም አገሪቱ በአስር አለቆች መመራትና ብዙ እልቂት መድረስ ነበረበት፡፡ በሌሎች ይሁንታ ያበጠውን አብዮት ማፈንዳት ለወታደሩ ቀላል ነበር፡፡ እናም "ለማስተባበር" በሚል መነሻ ከየጦር ክፍሉ ተውጣጥተው እንደቀልድ በላንድሮቨር መኪና ለስብሰባ መጡ፣ በዚያው ተባብረው፣ አስተባብረው፣ በዚያው ስልጣን ይዘው፣ ባላሰቡት መንገድ አገር መርተው፣ በዚያው ቀሩ፡፡ ለማንኛውም ባየነው መልኩ የኢትዮጵያ አብዮት አበጠ፡፡



አንበሳ አጉራሹ ጃንሆይ

*የደርግ ውልደትና እድገት*

በየካቲት ወር 1966 ዓ.ም ህዝባዊ አመፅ ሲቀጣጠል የተቋቋሙ የጦር ኃይሉ አባላት የተሰባሰቡባቸው ኮሚቴዎች ነበሩ፡፡

የመጀመሪያው ኮሚቴ የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግለት ለጃንሆይ ጥያቄ ባቀረበበት ወቅት የተቋቋመ ነበር፡፡ ይህ ኮሚቴ ወደ 200 የሚጠጉ



ባለሥልጣናትን በቁጥጥር ስር አድርጎ የነበረ ሲሆን፤ ጃንሆይ የጠሩን ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡት የታሰሩትን ከፍተኛ ባለሥልጣናት ፈትቶ ተበተነ፡፡

ሁለተኛው ኮሚቴም በተመሳሳይ ይሰበሰብና ኮሎኔል የዓለምዘውድ ተሠማን ሊቀመንበሩ አድርጎ ይመርጣል፡፡ በመኮንኖች ክበብ የሁተለኛው ኮሚቴ ስብሰባ ሲካሄድ ከዓለምዘውድ ሌላ ኮሎኔል ይገዙ ይመኔ፣ ሻለቃ አጥናፉ አባተና ሻምበል እንዳለ ተሠማ ተመርጠው ነበር፡፡ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ይህንን ኮሚቴ በዘመዳቸው በኮሎኔል የዓለምዘውድ መዳፍ ውስጥ በመሆኑ 20 ከፍተኛ ባለሥልጣናትን አስለቅመው ጎፋ ሰፈር እንዲታሰር ያደረጉት በዚህ በሁለተኛው ኮሚቴ አባላት አማካኝነት ነው፡፡ ልጅ እንዳልካቸው የኮሎኔል የዓለምዘውድን ኮሚቴ በዚህ አይነት ከተጠቀሙበት በኋላ፣ በጎን ያሴሩና በጄኔራል ወልደስላሴ በረካ አማካኝነት የኮሎኔል የዓለምዘውድን ኮሚቴ እራሳቸው ልጅ እንዳልካቸው ያስበትኑታል፡፡ ሁለቱ ኮሚቴዎች በዚህ ዓይነት ከተበተኑ በኋላ አንድ ወር ያህል ቆይቶ ሰኔ 20 ቀን አንድ ነገር ይከሰታል፡፡

ይህም ኮንጎና ኮርያ ዘምተው የተመለሱ የሠራዊቱ አባላት ያቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ እነዚህ 80 የሚሆኑ የኮንጎ ዘማች የበታች ሹሞች ሰኔ 20 ቀን 1966 ዓ.ም በቀጥታ ወደ ቤተመንግስት ይሄዱና ከንጉሠነገስቱ ፊት ቀርበው፤ "ጃንሆይ ከፊትዎ ዛሬ የቀረብነው የደከምንበት፣ ላብና ደማችን የፈሰሰበት፣ ከተባበሩት መንግስታት የተከፈለን ገንዘብ እንዲሰጠን ለግርማዊ ጃንሆይ ለማመልከት ነው" በማለት አቤቱታ አቀረቡ፡፡

- ጃንሆይ በጣም ተበሳጭተው "እናንተ ምቀኞች፤ ተንኮለኞች፣ የሠላም ፀሮች! ማዘጋጃ ቤቱም የተሰራው በእኛ ገንዘብ ነው ትላላችሁ! ለመሆኑ ይህን ህንፃ ለመስራት ኢትዮጵያ ገንዘብ አጥታ የናንተን ገንዘብ ወሰደች? እናንተ እርጉሞች! ገንዘቡን ብታገኙ እንኳን ልትጠጡበትና ልትሰክሩበት እንጂ ቁም ነገር አትሰሩበትም" የሚል መልስ ሲሰጧቸው፤ ከመካከላቸው አንዱ ሃምሳ አለቃ እሸቱ አያሌው "ጃንሆይ! ገንዘቡን የፈለግነው ከሐብታም ኩሽና ለመውጣት እንጂ ልንሰክርበት አይደለም" የሚል ምላሽ በመስጠት ሲሞግት ጃንሆይ "ቀጣፊ ዝም በል!" እንዳሉትና በሙግቱ መሐል ሌተናል ጄኔራል አቢይ አበበ ድንገት ሲደርሱ አቤቱታ አቅራቢዎች ሙግቱን ትተው እንደወጡና ጃንሆይም ሰድበው እንዳባረሯቸው ከአቤቱታ አቅራቢዎች አንዱ የነበረው ለሻምበል ተስፋዬ ርስቴ በእስር ቤት ውስጥ ገልጾላቸው በመፃህፋቸው አካተውት ይገኛል፡፡

እነዚህ ወታደሮች ከወጡ በኋላ ብንበታተን እየለቀሙ ያስሩናል በሚል ስጋት ጥያቄያቸው ምላሽ እስኪያገኝ ድረስ መበተን እንደሌለባቸው ይወስኑና የዚያኑ ዕለት በጋራ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው ቢሮ በመሄድ ጥያቄያቸውን ለጃንሆይ እንዳቀረቡና ጃንሆይም አዋርደው

እንዳባረሯቸው በመግለፅ አቤቱታቸውን ያሰማሉ፡፡ጠቅላይ ሚኒስትሩም የወታደሮቹን ቁጣ አብርደው፤ከንጉሡ ጋር ተመካክረው ለጥያቄያቸው አፋጣኝ ምላሽ እንደሚሰጡ ቃል ገብተው ያሰናብቷቸዋል፡፡

ከዚያ ወጥተውም መበታተኑን አልፈለጉምና ወታደራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ መነጋገር እንዳለባቸው ወስነው በቀጥታ ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ጠቅላይ መምሪያ ሄዱ፡፡ ዘማቾቹ 4ኛ ክፍለ ጦር ግቢ ውስጥ ተሰብስበው ሲነጋገሩ በመምሪያው ውስጥ የነበሩ የክፍለ ጦሩ አባላትም ተጨምረው "ለውጥ ማምጣት አለብን!" እያሉ ማጋጋል ያዙ፡፡

ከዚህ በፊት የነበረው ሁለተኛው የዓለምዘውድ ኮሚቴ ሲበተን ቅር የተሰኙ የነበሩት ሻለቃ አጥናፉ አባተ ይመኙት የነበረውን ለውጥ የማምጣት ሀሳብ በራሳቸው ክፍለ ጦር ጊቢ ውስጥ የሚጀምሩበትን አዲስ እድል አገኙ፡፡ ያ ኮሚቴ ከተበተነ በኋላም እነ ሻለቃ አጥናፉ ውስጥ ውስጡን በድብቅ እየተገናኙ ይዶልቱ ነበር፡፡

ስለዚህ ሻለቃ አጥናፉ አባተ፣ ሻምበል እንዳለ ተሠማ፣ ሃምሳ አለቃ ዓሊ ሙሣ፣ ሻምበል ወንድወሰን ብርሃኑ የተባሉ መኮንኖች ወደ እንግዶች ስብሰባ ተቀላቀሉ፡፡ የኮንጎ ዘማቾች የለውጥ ማምጣት ሀሳብ ካነሱ በኋላ ስብሰባቸው መልክ ይኖረው ዘንድ መሪ መምረጥ እንዳለባቸው ይወስናሉ፡፡ ተከታዩ ጥያቄ የሚመረጠው መሪ መኮንን ይሁን ወይስ የበታች ሹም? የሚል ነበርና ውይይቱ ቀጥሎ የጦሩ ሙሉ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ፣ የጦሩን አባላት አስተባብሮ ለመምራት ደግሞ የግድ መኮንን የሆነ መሪ እንደሚሻል፣ ነገር ግን ከፍተኛ መኮንን እንደማያስፈልግና ማዕረጉ ከሻለቃ መብለጥ እንደሌለበት ተስማሙ፡፡

ምክንያቱም ከፍተኛ መኮንኖች መሪ ከሆኑ የራሳቸውን ጥቅም አስከብረው የበታቹን ጥያቄ ቀብረው ያስቀሩት ስለነበር ነው፤ ከሻለቃ መብለጥ የለበትም የተባለው፡፡ በውሣኔው መሠረት ሻለቃ አጥናፉ አባተ የስብሰባው መሪ፣ ሃምሳ አለቃ አበራ አጋ ከፖሊስ ሠራዊት፣ ጁኒር ቴክኒሽያን ዮሐንስ ፍትዊ ከምድር ጦር አቪዬሽን ለኮሚቴው አባልነት ተሰየሙና ተሰብሳቢዎቹ በሻለቃ አጥናፉ መሪነት ወደ ስብሰባ አጀንዳ ተዛወሩ፡፡

ይህ ሦስተኛው ኮሚቴ የመጨረሻው መጀመሪያ ሊባል ይችላል፡፡ በእለቱ ከተሰብሳቢዎች ውስጥ ብዙዎቹ የ4ኛ ክፍለ ጦር አባላት ስለነበሩ እንዲቀነሱ ተደረገ፡፡ በስብሰባው የተለያዩ ሀሳቦችን እያነሱ እየጣሉ ቆይተው በመጨረሻ የደረሱበት ውሣኔ "1. የምድር ጦር ልዩ ልዩ ክፍሎች የአየርና ባህር ኃይል እንዲሁም የፖሊስ ሠራዊት የየራሳቸውን ወኪል መርጠው እንዲልኩ፣ 2. በአዲስ አበባ ያሉት የሬዲዮና የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ ቁልፍ ቦታዎችን በጦሩ እንዲጠበቁ ማድረግ፣ 3. የስጋት ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ የሲቪልና የጦር



አለቆችን በቁጥጥር ስል ማዋል፣ 4. ለመለዮ ለባሹ ሁሉ ለተጀመረው እንቅስቃሴ ድጋፍ እንዲሰጡ ጥሪ ማቅረብ፣ በተለይ ለኮሚቴው አባልነት አዲስ አበባ፣ አስመራና ሐረር ከሚገኙ ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች ማስመረጥና ማሳተፍ..." የሚሉ ሲሆን፤ ተወካዮች ከተላኩላቸው በኋላም ሁኔታዎችን የሚከታተል፣ የሚያስተባብርና ድጋፍ የሚያሰባስብ፣ ለንጉሡ ታማኝነትን የሚገልፅ  ኮሚቴ እንደሚሰይሙ ተወያይተው ተስማሙ፡፡ እነዚህ በ4ኛ ክፍለ ጦር የተሰባሰቡት 31 መለዮ ለባሾች በምርጫ ያልተወከሉ የመጀመሪያ የደርግ አንቀሳቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህን እቅዶች መርጠው ያስቀመጡትና በፍጥነትም በተግባር እንዲተረጎም ያደረጉት ሻለቃ አጥናፉ አባተ ሲሆኑ፤ከመኮንንነታቸው ባለፈ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቢዝነስ አድሚንስትሬሽን ተምረዋል፡፡

የዚያኑ ዕለት ምሽት ሁለት ሠዓት ከ4ኛ ክፍለ ጦር በተውጣጡ ወታደሮች አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት አጠገብ ይገኝ የነበረውን የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ፣ ማዘጋጃ ቤት ህንፃ ውስጥ የሚገኘውን የቴሌቪዥን ማሰራጫ ጣቢያ፣ ጌጃ ሠፈር የሚገኘውን የብስራተወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ፣ የቴሌኮሙኒኬሽንን መስሪያ ቤት፣ የመብራትና የውሃ አገልግሎት ማሰራጫዎችንና የአዲስ አበባ ከተማ መግቢያ መውጫ መንገዶችን በወታደር ጥበቃ ስር እንዲሆኑ አደረጉ፡፡ ለዚህም ከሻለቃ አጥናፉ ጋር የፖሊስ ሠራዊት አባሉ ሻለቃ እንየው ፈረደ (ለደርግ ምስረታ አስተዋፅኦ ቢያደርጉም ሻለቃ ፈረደ የደርግ አባል ግን አልሆኑም) ጦሩን በማንቀሳቀስና ለጥበቃ በመመደብ ተባብረዋል፡፡

ለመገናኛ ብዙሃኑም ሻለቃ አጥናፉ ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ጀምሮ 4ኛ ክፍለ ጦር ከተመሠረተው ኮሚቴ የሚሰጠውን ትዕዛዝ መፈፀም ተግባራቸው መሆኑን ለተረኛ ሹሞች ገለፁ፡፡ ወቅቱ ወታደራዊ ዲሲፒሊንም ሆነ የአዛዥና ታዛዡ ግንኙነት ቅጥ ያጣበት ነበርና እቅዱን ለማሳካት እንቅፋት አልነበረም፡፡ በመሆኑም ጦሩ በመስክ ሬዲዮ ያለገደብ እየተገናኘ መልዕክት እንደልቡ ይለዋወጥ ነበር፡፡ በኮሚቴው እቅድ መሠረትም በአገሪቱ ካሉት 40 ያህል ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች 3 አባላት መርጠውና ወክለው ወደ አዲስ አበባ 4ኛ ክፍለ ጦር ጠቅላይ መምሪያ ጊቢ እንዲልኩ መልዕክት ደረሳቸው፡፡ ከአራቱም ክፍለ ጦሮችና በክፍለ ጦሩ ስር ካሉ ልዩ ልዩ ክፍሎች ፖሊስ ሠራዊትን ጨምሮ ተመርጠው የተላኩ አባላት ፈጥነው ደረሱ፡፡ ገሚሱ "ሂድ እስቲ የሚባለውን ስማ" ተብሎ የመጣ ነበር እንጂ ለጉዳዩ ብዙዎች ትኩረት የሰጡ አልነበሩም፡፡ ብቻ ግን እንቅስቃሴው ሂደቱን ቀጥሎ ወደ ስኬት እያመራ ነው፡፡ ነገር ግን የደርግ አባላቱ በመጀመሪያ ተጠራርተው በ4ኛ ክፍለ ጦር ሲሰበሰቡ ሹፌሩም ምኑም ተጠራቅሞ ስለነበር 170 ነበሩ፡፡ ቆይቶ ሻለቃ መንግስቱ ሰብሳቢ ሆነው ከተመረጡ በኋላ የየክፍሉ ተወካይ አባላት በአግባቡ ስም

ዝርዝርራቸው እንዲመዘገብ ስለተደረገ 50ዎቹ ወደየክፍላቸው እንዲመለሱ ተደርጐ 120 ሆኑ፡፡ ሆኖም ቀስ በቀስ በመኪና አደጋ ከሞተው አንድ አባል በስተቀር 10 ያህሉ ገና ከጅምሩ መዝረፍ፣ መስከር፣ ቁማር መጫወት፣ አስገድዶ መድፈር፣ በሆነ ባልሆነው ታሳሪዎችን በእሳት እየለበለቡ በማሰቃየትና በሌሎች ወንጀሎች የደርግን ስም እያከፋት በመሄዳቸው የተገደሉ ናቸው፡፡ (ምስክርነት 2001 ዓ.ም)

በመሆኑም 109 አባላት ረዥም ጉዞ ተጉዘዋል፡፡

በሻለቃ አጥናፉ የሚመራው አስተባባሪ ኮሚቴ ሰኔ 21 ቀን 1966 በ4ኛ ክፍለ ጦር ጊቢ ውስጥ መቋቋሙን በሬዲዮ ይፋ አደረገ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ስብሰባዎች መካሄድ ቢጀምሩም፤ አባላቱ ተጠቃለው ለመግባት የቀናት እድሜ ወስዶባቸዋል፡፡ እነዚህ በጥሪ የመጡ አባላት አብረዋቸው ከመጡ አባላት ውጪ አይተዋወቁም፣ ለምን እንደመጡ፣ አላማቸው ምን እንደሆነ በውል የተረዱ አልነበሩም፡፡

ሰብሳቢው ሻለቃ አጥናፉ ስብሰባውን ሲከፍቱ በጦሩ ውስጥ ስላለው ያስተዳደር ጉድለት፣ በስልጣን የባለጉ ሹሞች መበርከታቸው፣ ስልጣንን ተገን አድርገው በሙስና የተሰማሩ በዝባዦች አገሪቱን እያራቆቷት እንደሆነ መተንተን ጀመሩ፡፡ ተሰብሳቢውም አገዛዙን እየወነጀለ የመሰለውን ይናገራል፡፡ ምን መደረግ አለበት? የሚለውን ግን የሚያስረዳ ጠፋ፡፡

እርግጥ ነው አስተባባሪ ኮሚቴው ምስረታውን በሬዲዮ ይፋ ሲያደርግ ህዝቡ "ጀግና! በርቱ!" የሚል ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ኮሚቴውም ዓላማዬ ብሎ ያቀረበው ማኑፌስቶ የመሰለ መግለጫው "የሠራዊቱን አባላት ደመወዝ ማስጨመር፣ የድርጅትና የትጥቅ መሟላትንና የአስተዳደር በደል እንዲወገድ፣ መለዮ ለባሹ ሲጠይቀው የቆየውን ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች እንዲሟሉና በአገሪቱ መሠረታዊ ለውጥ እንዲከሰት መጣር የኮሚቴው ዓላማ ነው" ብሏል፡፡

ነገር ግን በምን መልኩ? የሚለው አንኳር ጥያቄ አልተብራራም፡፡ ስለዚህም ከሰኔ 22 ጀምሮ ለ4 ቀናት ያህል ጥቂት የቀድሞው ባለሥልጣናትን እየመረጠ በ4ኛ ክፍለ ጦር ጊቢ ውስጥ ሲያስር ቆዬ፡፡ ኮሚቴው ሀሳቦችን ሲያነሳ ሲጥል ሠንብቶ ሰኔ 26 ቀን ከምስራቅ አንበሳው ክፍለ ጦር ተውጣጥተው ተመርጠው የተላኩ የ3ኛ ክፍለ ጦር አባላት ደረሱ፡፡ ከምስራቁ ክፍል ከመጡት 10 አባላት ውስጥ አንዱ ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም ነበሩ፡፡

የደረሱት ስብሰባው ላይ ነው፡፡ ሻለቃ መንግስቱ ስብሰባውን በፀጥታ ሲከታተሉ ቆይተው ግራ ተጋቡ፡፡ ሀሳቦች እየተነሱ እየተጣሉ፣ ማን ይታሰር፣ ማን ምን ይደረግ? ሲባባሉ አምሽተው ተለያዩ፡፡ በተከታዩ ቀን ሁሉም አባላት ተጠቃለው ገብተው የተለመደው ስብሰባ ተጀመረ፡፡



የሚባለውን በፀጥታ ሲያዳምጡ የቆዩት ሻለቃ መንግስቱ እጃቸውን አወጡ፡፡ ሻለቃ አጥናፉ እንዲናገሩ ፈቀዱላቸው፡፡ "... ለመሆኑ መለዮ ለባሹ ተወካዮቹን ወደ 4ኛ ክፍለ ጦር እንዲልክና ለምታደርጉትም እንቅስቃሴ ድጋፍ እንዲሰጥ ስትጠይቁት ምን እቅድ ይዛችሁ ነው? ምን ለመስራት ነው ዓላማችሁ?" የሚል ጥያቄ አነሱ፡፡ ፀጥታ ሰፍኖ ቆዬ፡፡ ከዚያም ሻለቃ አጥናፉ መልስ መስጠት ነበረባቸውና "እኛ ጥሪ ስናስተላልፍ የተጠናና የታቀደ ይህ ነው የምንለው የተለየ እቅድ ይዘን አይደለም፡፡ ሰቃይና መከራ ላንገላታው ርሐብና እርዛት ዕጣፈንታው ለሆነው ለኢትዮጵያ ህዝብ ተስፋ የሚሰጥ ለውጥ ለማምጣት ግን እንፈልጋለን፡፡ የአገርን ዳር ድንበር ለማስከበር የተሰማራው መለዮ ለባሽ ጎስቋላ ህይወትም ያሳስበናል፡፡ ተወክላችሁ የመጣችሁት መለዮ ለባሾች ምን እናድርግ? እንዴት እናድርግ? ዓላማችንስ ምን ይሁን? ምን መርህ እንከተል? ለሚሉት ጥያቄዎች በጋራ ተወያይታችሁ ከውሣኔ እንደሚደረስ ተስፋ አለን፡፡ ለአሁኑ ግን በጎ ምኞት እንጂ ይህ ነው የምንለው ልዩ እቅድ የለንም" ብለው መለሱ፡፡

በዚህ ጊዜ ሻለቃ መንግስቱ፤ "... ከምስራቅ መርቼ ያመጣኋቸው መለዮ ለባሾችና እኔ መሰብሰቡን የምንቀበለው አንድ እቅድ ኖሮ፣ ለህዝብ መሠረታዊ ለውጥ ለማስገኘት ዝግጅት ያለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ መለዮ ለባሹ ከግምጃ ቤት መሣሪያ እያወጣ ጥቃቅን ብሶቶችን እያወሳ ዘላቂነት የሌላቸው መልሶችን እየተቸረ ወደ ጦር ሠፈሩ መመለሱን አይደለም አሁን መመልከት ያለብን፡፡ ይህ አይነቱን ተግባር ለመፈፀም ከሆነ ከቡድኔ ጋር ወደ አንበሳው ክፍለ ጦር ሰፈር ሐረርጌ እመለሳለሁ፡፡ በጎ ምኞት ብቻ አይበቃም፤ መርህ ያስፈልጋል፤ ወደተግባር የሚለወጥ እቅድ ያስፈልጋል" በማለት የተናገሩት ንግግር በሁሉም ተሰብሳቢዎች ዘንድ ትኩረትን አስገኘላቸው፡፡

ስብሰባው ቀጠለ፡፡ በወቅቱ የነበሩት አባላት የዚያን ጊዜውን የመንግስቱን አንደበተርቱዕነት በመገረም ያስታውሱታል፡፡ በገነት አየለ "የመንግስቱ ትዝታዎች ቁጥር 1" ላይ ቃላቸውን ከሰጡት አባላት ውስጥ አንዱ "... ሁላችንም በንግግር ችሎታውና በሀሳቦቹ ጥልቀት ተደነቅን፡፡ ይህ ሰው የሚናገረውን የሚያውቅ መሆኑን ተረዳን፡፡..." ሲል፤ ሌላው ጓድ "...መንግስቱ ስማርት ነበር፡፡ ተራ ተሰጥቶት መናገር ሲጀምር ተሰብሳቢዎችን በመጠየቅ ነበር የጀመረው፡፡ ምንድን ነው ዓላማችን? ምን ማድረግ ነው የምንፈልገው? ግባችን ምንድነው? ሲል እርስ በርሳችን መተያየት ጀመርን፡፡ ብዙዎቻችን ይህን መሠረታዊና ዋና ጥያቄ አላጤንነውም፡፡ የመለሰም አልነበረም፡፡ መንጌ ቀጠለና "ይሄን ግልፅ ካላደረግን ብዙም ወደፊት ልንራመድ አንችልም ሲል አንዳንዶች በጦሩ የተመረጡ ተወካዮች መሆናቸውን አመለከቱ፡፡ ቢሆንስ? So what? ነበረ

መልሱ፡፡ ... እያለ ሁላችንም እንድናደንቀው ያደረገ ንግግር ተናገረ፡፡ ብዙዎቻችን ይህ ሰው ሊመራን ይችላል ብለን ሳንል አልቀረንም...” በማለት ያስታውሳሉ፡፡ ወዲያው ሻለቃ አጥናፉ “ለምን ከአሁኑ ሰዓት ጀምሮ ተወያይተን ውሣኔ ላይ አንደርስም? የኢትዮጵያ ህዝብ ግፍና መከራ ተሸካሚ ሆኗል፤ ለውጥ ይፈልጋል፣ የተሻለ ህይወት ይመኛል፣ ከስቃይና መከራ የሚያወጣው ይሻል፡፡ ስለዚህ እንወያይና ከአንድ ውሣኔ ላይ እንድረስ” ወደማለት አመሩ፡፡

እንደበተርቱው ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም ንግግራቸውን ካንበለበሉት በኋላ ሌሎች ተወካዮችም እየተነሱ ሀሳባቸውን መግለፅ ሲጀምሩ መንግስቱ ብድግ ብለው ግድግዳ ላይ ወደተሰቀለው ጥቁር ሰሌዳ አመሩና የአባላቱን ፍሬ ሀሳቦች ማስፈር ጀመሩ፡፡ የተለያዩ ሀሳቦች ካቀረቡ በኋላ፤ ለኢትዮጵያ የሚበጃትን የመንግስት ዓይነት በሚመለከት 1. ሕገ-መንግሰታዊ የዘውድ አገዛዝ፣ 2. ዴሞክራሲያዊ የሲቪል መንግስት፣ 3. ወታደራዊ መንግስት የሚሉ ነጥቦች ተመርጠው ተቀመጡ፡፡ ለብዙ ሺ ዓመታት ዘውዳዊ አስተዳደር ላራመደች አገር የቱ ተመራጭ እንደሚሆን ግልፅ ከመሆኑም በላይ፤ ዘውዱን ማስወገድ ለእነዚህ መለዮ ለባሾች ፈጽሞ በዚያ ወቅት የሚታሰብ አልነበረም፡፡ “ሀሳቡ ራሱ ያስፈራ ነበር” ይላሉ አባላቱ፡፡

ስለዚህ ሻለቃ መንግስቱ “ሕገ-መንግስታዊ የዘውድ አገዛዝ” የሚለውን በጠመኔ አከበቡትና ተቀመጡ፡፡ ሁሉም ተስማማ፡፡ ከ15 ደቂቃ ዕረፍት በኋላ ውይይቱ ሲቀጥል ከአባላቱ ውስጥ “አዲስ ፕሮግራምና መመሪያ የምናወጣ ከሆነ ለምን አዲስ ሊቀመንበር አንመርጥም?” የሚል ሀሳብ ተነሳ፡፡ ሻለቃ አጥናፉ አልተቃወሙም፡፡ በቅንነታቸው ብቻም ሳይሆን ሙሉ አባላቱ ከተሰባሰቡ በኋላ ሌላ የጋራ ምርጫ መደረጉ አግባብ ነበር፡፡

“ሻለቃ መንግስቱ” አለ አንዱ አባል፡፡የሁሉንም ቀልብ የሳቡ መንግስቱ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ሻለቃ አጥናፉ ራሳቸው በመንግስቱ ብቃት የተደነቁ ናቸው፡፡ ስለዚህ ያለአንዳች ተቃውሞ በሙሉ ድምፅ ሻለቃ መንግስቱ ሊቀመንበር፣ ሻለቃ አጥናፉ ምክትል ሊቀመንበር ሆነው ተመረጡ፡፡ ቀጥሎ ዋና ፀሐፊ ሊመርጡ ሲሉ መንግስቱ ተቃወሙና፤“ሊቀመንበር እንድሆን እምነት ጥላችሁብኝ ከመረጣችሁኝ ዋና ፀሐፊውን የምመርጠው እኔ መሆን አለብኝ” አሉ፡፡በዚያ አዳራሽ ውስጥ የመንግስቱን ሀሳብ የሚቃወም ቢኖር እንደ ጅል በተቆጠረ ነበር፡፡ ማንም አልተቃወመም፡፡መንግስቱ ጓደኛቸውን /ኮርስ ሚታቸውን/ ገብረየስ ወልደሃናን መረጡ፡፡ሻለቃ ብርሃኑ ባየህንም የእቅድ ኮሚቴው አባል እንዲሆን አደረጉ፡፡



ሻለቃ መንግስቱ በአንደበት ብቻ የአጥናፉን ቦታ ያለችግር ነጥቀው ሊቀመንበር /በዚያ ሰዓት በመሠረቱ ሊቀመንበር ሳይሆን ሰብሳቢ ነው ሊባል የሚችለው/ ከመሆናቸው ባለፈ ሁለት ጓደኞቻቸውን ፀሐፊና የእቅድ አውጪ ኮሚቴ አባል ማድረጋቸው ላዕላዩንም ታህታዩንም መዋቅር በራሳቸው እቅድና መንገድ የማስቀጠል እድላቸውን አመቻችተዋል፡፡ ይህ ኮሚቴ “የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስና የህዝባዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ” በሚል ራሱን ይፋ አድርጓል፡፡ ከየጦር ክፍሉ ተመርጠው የተላኩ አባላቱን መዝግቦ ጨርሷል፡፡ ስራውንም ንዑስ ኮሚቴዎችን በማቋቋም ሲጀምር 1. የፖለቲካና የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ፣ 2. የኢኮኖሚ ኮሚቴ፣ 3. የመከላከያ ኮሚቴ፣ 4. የሶሻል ጉዳይ ኮሚቴ፣ 5. የህዝብና ደህንነት ኮሚቴ፣ 6. የአስተዳደርና ሕግ ኮሚቴ፣ 7. የእስረኞች አስተዳደር ጉዳይ ኮሚቴ፣ 8. የስራ መቆጣጠሪያ ኮሚቴ፣ 9. የጽህፈት አገልግሎት ኮሚቴ የሚባሉትን አቋቋመ፡፡

ሻለቃ መንግስቱ የአስተባባሪው ኮሚቴ መሪ ስለሆኑ የእቅድ አውጪ ኮሚቴውን ሰብስበው ተከታዮቹን እቅድ አቀረቡ፡፡

1. የመለዮ ለባሹን አስተባብሮ ለለውጥ ማዘጋጀት፣ 2. ለውጥ ፈላጊውን ህብረተሰብ በተለይም ምሁራንን ከጎኑ አሰልፎ ረዳቱ ማድረግ፣ 3. ከጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን መንግስት ጋር ተባብሮ እንደሚሰራ መግለጫ እንዲያወጣ ማድረግና በአገሪቱ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት፣ 4. ለንጉሡ በተመረጡ አባሎች አማካኝነት ታማኝነትን መግለፅ የሚሉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከህዝቡ አስተያየቶችን መሰብሰብ የሚችሉበት የሀሳብ መስጫ ሳጥኖችን በየአደባባዩ ማዘጋጀት በሚሉት ነጥቦች ተወያይተው ኮሚቴው ይህንንም በሙሉ ድምፅ ተቀበለው፡፡

ቀጣዩ ጥያቄ “መርሃችንስ ምን ይሁን?” የሚል ነበር፡፡ ፈጣኑ መንግስቱ በቅፅበት “ኢትዮጵያ ትቅደም!” አሉ፡፡ ማንም አልተቃወመም፡፡ በእርግጥ ይህቺ መፈክር የአዶልፍ ሂትለር “ጀርመን ትቅደም” ናት፡፡ በኢትዮጵያ ምድር ግን የመንጌ ሆናለች፡፡ “እንዲያውም” ብለው ቀጠሉ መንግስቱ “ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም!” የአድናቆት ጭብጨባውን ተከትሎ ፀደቀ፡፡

ይህ አስተባባሪ ኮሚቴ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁለት ኢምንት አስተባባሪ ኮሚቴዎች የበለጠ ሆኖ በጠንካራ መሠረት ላይ ቆመ፡፡ወዲያውም ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አስተያየት ሲሰነዘርለት አንድ ግለሰብ የግዕዙን ቃል አጣቅሰው “ደርግ” የሚለውን ስያሜ አቀበሉ፡፡የአማርኛ ትርጉሙ ያው ኮሚቴ ማለት ነው፡፡ እናም “የጦር ኃይሎች፣የፖሊስና የህዝባዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ” የሚለው ቀርቶ “ደርግ” የሚለው መጠሪያው ሆኖ ቀረ፡፡የየጦር ክፍሉ ዋና አዛዦችም

ተወካዮቻቸው ተሳታፊ ስለነበሩ ከበስተጀርባ ሆነው ድጋፍ ይሰጧቸው ነበር፡፡

ደርግን በፓርላማ አይነት አወቃቀር ልንመስለው እንችላለን፡፡ ልዩነቱ የጦር ክፍሎች ለደርግ አባልነት ተወካዮቻቸውን መርጠው ከላኩ በኋላ ድጋሚ መሻር አለመቻላቸው ነው፡፡ ይህንን ቀድሞ ለማሰብም መሠረታዊ መነሻ አልነበራቸውም፤ ሊኖራቸውም አይችልም፡፡ "ተወካይ ላኩ" ተባሉ ላኩ፡፡ አበቃ፡፡ አባላቱ በዚያው ጭልጥ ብለው ባልተጠበቀ ሁኔታና ፍጥነት ስር ሰደዱ፡፡ መልሶ የመሻሩ ጉዳይ የሚጠበቅ ባይሆንም፤ በሃይልና በማስገደድ ሊሞከር ይችላል፡፡ ለዚህም ነው ከአብዮቱ በኋላ ብዙም ሳይቆይ መንግስቱ ኃይለማርያምን የያዙት አንባገነናዊ ሂደት ያልጣማቸው የሦስተኛ ክፍለ ጦር አዛዦች "ወደ ክፍልህ ተመለስ" ሲሏቸው "አብዮቱን አደጋ ላይ ጥዬ አልመጣም፣ ይህ የህዝብ አደራ ነው" ብለው ድርቅ ያሉት፡፡ ቢለመኑ ቢለመኑ አሻፈረኝ በማለታቸውም የመጡበት ክፍል አዛዦች የመንግስቱ ኃይለማርያምን ቤተሰቦች አገቱ፡፡ "በጭራሽ" አሉ መንጌ፡፡ ጦሩ ግን አማራጭ ሲያጣ የታገቱትን ቤተሰቦቻቸውን ለቀቀ፡፡ በዚህ መሰሉ አካሄድ ከፓርላማ ሲለይ፤ በተጨማሪም፣ ፓርላማ ሕግን ተከትሎ ሲሰራ ደርግ ግን አንዳንድ ጊዜ ምናልባትም ብዙ ጊዜ ከሕግ ውጪ በስብሰባና በጭብጨባ ብቻ አንኳር አንኳር ጉዳዮችን የሚመለከቱ ውሣኔዎች ያሳልፋል፡፡

ደርግ ቀደም ሲል ያየናቸውን እቅዶች በፍጥነት ተግባራዊ ወደማድረጉ አመራ፡፡ ከተለያዩ ወገኖችም ትኩረት አገኘ፡፡ በዋናነት የስልጣን ጥም ያለባቸውንና ለለውጥ ስንታገል ኖረናል የሚሉት ምሁራን ያቹን ያበቃላትን ወንበር ለመቅለብ ከደርግ ለመጣበቅ ሲጥሩ፤ በሌላ በኩል ልዑል ራስ አስራተ ካሣ እንዲሁም የመንግስቱ ስጋ ዘመድ ደጃዝማች ከበደ ለመንግስቱ ድጋፍና ሽር ጉድ ማድረግ ጀመሩ፡፡ ይህ ሽኩቻ ለደርግ ልዩ ጥቅም ነበረው፡፡ ሌሎች የደርግን ስር እየሠደደ መሄድ ያዩ ምሁራንም ኮሚቴው ስር ነቀል ለውጥ እንደሚያመጣ ቀድመው በመገመት ብቻም ሳይሆን በደርግ እቅድ መሠረት በስደት ውጭ አገር ያሉ ምሁራን ተጠርተው ስለነበር ተንጋግተው መጥተው የየራሳቸውን ጠንካራ ድርጅት ማዋቀር ሲችሉ ከዚህ የበለጠ ትኩረት ሰጥተው በግልና በጋራ የተንቀሳቀሱት ከደርግ ጋር ለመወዳጀት መሪውን እያጣሩ በአክብሮትና በልምምጥ ጎንበስ ቀና ማለትን ነበር፡፡ ደርግ የመንግስትን ስልጣን መቦርቦርን ነበር ቅድሚያ የሰጠው ተግባር፡፡ ይህንንም ሲያደርግ ለንጉሱ ያለውን ታማኝነት በተደጋጋሚ እየገለፀ የነበረ ሲሆን፤ ጃንሆይም እውቅና አልነፈጉትም፡፡

ደርግ ለጃንሆይ ያቀረባቸው የመጀመሪያ ጥያቄዎች "... የተረቀቀውን አዲስ ሕገ-መንግስት ባፋጣኝ በስራ ላይ እንዲውል (አዲሱ



ካቢኔ በህዝብ ጥያቄ ያረቀቀውን)፣ ለፖለቲካ እስረኞችና ስደተኞች አጠቃላይ ምህረት እንዲታወጅ፣ ለዚህም ሲባል ፓርላማው እንደቀድሞው ክረምት ላይ መዘጋቱ ቀርቶ በእነዚህ መሰል ጉዳዮች ላይ እንዲመክር" የሚሉ ነበሩ፡፡ ጃንሆይ ከሌላው አመፀኛ እነዚህ ትንንሾች ሳይሻሉኝ አይቀሩም፤ እንዲያውም ጄኔራል ቢሆን እንጂ ሃምሳ አለቃና አስር አለቃ መቸም ዙፋን አይመኝም ብለው ያሰቡ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ከጥቂት ማንገራገር በቀር እምቢ ያሉት ጉዳይ አልነበረምና፡፡

የደርጉ አባላትም በልዩ አክብሮት፣ እንክብካቤና ፍቅር ነበር ጥያቄያቸውን የሚያቀርቡት፡፡ የጃንሆይ አለማንገራገር ደግሞ ደርጎችን የበለጠ እያደፋፈራቸው ሄደና፤ ሌሎች ተከታታይ ጥያቄዎችን ማቅረብ ቀጠሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዋናው ደርግን የተረጋገጠ ህልውና እንዲኖረው ያደረገው ጥያቄ መመለሱ ሲሆን፤ ወደፊት የለውጥ እንቅፋት ይሆናሉ ተብለው የሚፈሩትን ታላላቅ ባለሥልጣናትና የጦር ጄኔራሎችን በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተጠይቆ ሳይውል ሳያድር እጃቸውን እንዲሰጡ ታዘው መታጎራቸው ነው፡፡ የዚያ ግዙፍ ግንድ ቅርንጫፎች ሁሉ ተመልምለው አለቁ፡፡ የደርጉ አባላት እጅ እየነሱ በጃንሆይ ፊት ቀርበው የሚጠይቋቸውና በይሁንታ የሚመለሱ ጥያቄዎች ሁሉ በመገናኛ ብዙሃን እንዲታዩና እንዲደመጡ የሚል ጥያቄም የተካተተበት ነውና ህዝቡ ክንውኑን እንዲከታተል ሆኗል፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን የደርግ ዓላማ ምን እንደሆነ ህዝቡ አልገባውም፡፡ ኮሚቴው ራሱ ያስቀመጠው ግብ በምን መልኩ እንደሚፈፀም ያወቀው አይመስልም፡፡ ብቻ ግን ምንጠራውን አጧጧፈው፡፡

ደርግ ምንም እንኳን ጦር ያዘምታሉ ያላቸውን ታላላቅ ባለሥልጣናት መልምሎ ቢጨርስም፤ የመለዮ ለባሹን ሙሉ ድጋፍ አላገኝ ይሆን? በሚል ስጋት ተወጥሯል፡፡ ስለዚህም በጦሩ ውስጥ እጅግ ታዋቂና ተወዳጅ ከፍተኛ መኮንን መርጦ የኮሚቴው መሪ ለማድረግ ፈለገ፡፡በርግጥም አስፈላጊ ነበር፡፡ተወዳጁ መኮንን ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም ነበሩና እርሳቸውን ከፊት ማስቀደሙ ለጊዜውም ቢሆን አስፈላጊ ነበርና ሊያሾሟቸው ወሰኑ፡፡ጄኔራል አማን ከስራ ገበታቸው ከመወሰኛ ምክር ቤት ተጠርተው የኮሚቴው ውሣኔ ሲነገራቸው ያለማወላወል ተቀበሉት፡፡ቀጣዩ ስራ ወደ ጃንሆይ ሄዶ "ይህን ሰው ይሹሙልን" ብሎ መጠየቅ ነበር፡፡ይህን ጥያቄ ከሌሎች ካልተመለሱ ጥያቄዎች ጋር አጣምረው፤ በንጉሠነገስቱ ፊት እንዲያነቡ የተላኩት የደርግ ልዑካን በሻለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳን እየተመሩ ሄዱ፡፡ሻለቃ ናደው ዘካርያስ ጽሁፉን እንዲያነቡ ተመድበዋል፡፡በሐምሌ ወር 1966 ዓ.ም ልዑካኑ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን፣ልዑል ራስ እምሩና ሌሎች ጥቂት የካቢኔ አባላት ከጃንሆይ ጋር አብረው ባሉበት ጥያቄዎች ተነበቡ፡፡

ጃንሆይ እጅግ ተቆጥተው "ለመሆኑ ጄኔራል አማንን ታውቁታላችሁ? ከሠራዊታችን ውስጥ ሌላ ሰው አጣችሁ? ፏሚና ሻሪስ እናንተ መሆናችሁ ነው?" አሉ፡፡ (ሌላ ሰው አጣችሁ? ያሉት ለምን እንደሆነ ግልፅ አይደለም፡፡ ምክንያቱም አማንን ጃንሆይ ይወዷቸዋል፣ ያከብሯቸዋል፣ ከስደት ሲመለሱ አማን ሱዳን ውስጥ በስደት ነበሩና አብረው እየተዋጉ የመጡ ናቸው፡፡ ብቻ ጃንሆይ በእርጅና ምክንያት አንዳንዴ የንግግር ውሉ ዝብርቅ ይልባቸው ስለነበር ይሆናል) ቀጠሉ ጃንሆይ፤ "... ደግሞስ ማን የሚባል የፖለቲካ እስረኛ ነው እንዲፈታላችሁ የምትፈልጉት? እስኪ አንድ የፖለቲካ እስረኛ ስም ጥሩ?" ብለው አፋጠጧቸው፡፡

አንባቢው ሻለቃ ናደው መልስ አጡ፡፡ሻለቃ ተስፋዬ ገ/ኪዳንም ፀጥ አሉ፡፡ የካድሬ ነገር ይሄው ነው፤የተሞላውን ከመናገር ያለፈ ጥልቅ ጥያቄ ቢመጣ መልስ የለውም፡፡ድጋሚ ሄዶ ተሞልቶ (ቻርጅ ተደርጎ) ካልመጣ ከየት አምጥቶ ይመልሳል? የካድሬ ትክክለኛ መገለጫ ወይም ትርጉም ይሄ ነው ለማለት ነው፡፡ጥያቄው የቀድሞ ምሁራን የሆኑና ከደርግ ለመጣበቅ አንዳንድ ሀሳቦችን ከርዕዮት አመራረጥ ጀምሮ በማቅረብ የግፊት ምክርም ይለግሱ ከነበሩ ምሁራን የመነጨ ነው፡፡

የሆነ ሆኖ የንጉሡን ጥያቄ መመለስ ስላልቻሉ ለደቂቃ ያህል ፀጥታ ሰፍኖ ከቆየ በኋላ ከአባላቱ አንዱ የነበረው እንዳለ ተሠማ "ግርማዊ ሆይ! እኛ ፏሚም ሻሪም አይደለንም፣ሠራዊቱ ለጃንሆይ የላከውን መልዕክት ይዘን የመጣን ነን፡፡ የእርሰዎ ዙፋን እንዲታፈር፣የኢትዮጵያ ዳር ድንበር እንዲከበር፣የተቀሰቀሰው ሠራዊትም መንፈስ እንዲረጋጋ፣ ጄኔራል አማንን ግርማዊነትዎ እንዲሾምልን ነው የጠየቅነው፤ጥያቄዎቹም የጦሩ እንጂ የእኛ አይደሉም"በማለት አለሳልሰው መመለሳቸውን የዓይን እማኙ ደበላ ዲንሳ ትውስታቸውን በምስክርነት መፃሀፍ ላይ ገልጠው እናያለን፡፡

ወዲያው ጃንሆይ ቀዝቀዝ ብለው "ይህ እንኳን ይሻላል፤ ሹሙልን ብሎ መጠየቅ ያባት ነው፤ ለሁሉም መልሱን ማታ በሁለት ሰዓት አዳምጡ" የሚል ምላሽ ሰጡ፡፡ ልዑካኑ ቁርጥ ያለ መልስ ይዘን ካልሄድን ጦሩ ይገድለናል እያሉ በልስላሴ ሞገቱ፡፡ "እኮ ማታ በሁለት ሰዓት ጠብቁ!" አሏቸው ተቆጥተው፡፡ ይህም አጥጋቢ መልስ አልነበረምና ተገትረው ሲቀሩ ልጅ እንዳልካቸው "እሺ ማለታቸው ነው" ብለው ልዑኩን አሰናበቱ፡፡ እዚህ ላይ ጃንሆይ ሙሉ ለሙሉ መረታታቸውን እንረዳለን፡፡ እንምከርበት፣ እናጥናው የሚሉ የተለመዱ ቃላቶቻቸው የሉም፡፡ የኮሚቴውንም ተፅዕኖ በድርቅናው ስንረዳ "እምቢ የሚል ቃል የመናገሪያ ጊዜዎ አልፏል" የሚል መልዕክት ያለው ነው፡፡በዘውዲቱ ጊዜ ተፈሪን ያንግሱልን የሚል ግፊት እንደነበረው ሁሉ አሁንም ታሪክ ራሱን ደግሞ



ማዕረጋቸው በማይፈቅድ ሰዎች ግፊት የተባለውን መፈጸም ግድ ሆነ፡፡ሰው የዘራውን ያጭዳልና፡፡

ጄኔራል አማን የደርጉ ሊቀመንበር ሆነው ተሾሙ፡፡ ደርግ ንጉሡን ማስወገድ የሚለው ሀሳብ አስደንጋጭ መስሎ እንዳልታየው ዛሬ ይህን መሰል ተግባር በኃይል ማስፈፀሙን ሲረዳ ዘውዱ እየቀለለበትና አስፈሪ ሀሳብም እንዳልሆነ በውል ተረዳ፡፡ ጃንሆይም እጅ መስጠታቸውን ለራሳቸው ከማሳመን በቀር ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም፡፡

ሻለቃ መንግስቱ አማንን ከፊት አስቀድመው አሯሯጭ አደረጓቸው፡፡ ደርግ አሁን በአማን ሹመት የጦሩን አይደግፈኝ ይሆን? ስጋት ካስወገደ በኋላ የቀረው የሲቪል ኅብረተሰቡን ድጋፍ ሊያስገኝለት የሚችል ተግባርን መፈፀም ነበርና ፋታ ቢስ ሆነው ለወራት በጠቅላይ ሚኒስትርነት ያገለገሉትን፣ ደርግንም ከመነሻው ሊበትኑት ሞክረው ያልተሳካላቸውን ልጅ እንዳልካቸው መኮንንን ሽሮ በሌላ ታዋቂ ግለሰብ መተካት አሰኘው፡፡ ለዚህ ስልጣን ታጭተው የነበሩት ሀዲስ አለማየሁ ነበሩ፡፡ ነገር ግን "እኔ የስነ-ጽሁፍ እንጂ የፖለቲካ ሰው አይደለሁም ይቅርብኝ" አሉ፡፡ እናም በጨዋነታቸው የሚታወቁት የራስ እምሩ ልጅ፤ ልጅ ሚካኤል እምሩ ለሹመቱ ታጩ፡፡

በአምባሳደርነት አገራቸውን ያገለግሉ ነበርና በአባታቸው በኩል ተልኮባቸው መጥተው ሁለተኛው ሲቪል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ፡፡ ደርግ ልጅ ሚካኤልን የመረጠበትን ምክንያት ሲገልፅም፤ ታማኝና በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ተወዳጅ፣ በሠራዊቱም ዘንድ የሚከበሩ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህንንም ህዝቡ በቀላሉ ተቀበለው፡፡ ምክንያቱም በተለይ አባታቸው ራስ እምሩ ከጃንሆይ ዘመን ባለሥልጣናት ውስጥ ብቸኛው በክፉ የማይነሱና ለደሃ አዛኝ፣ ያላቸውን ሐብት ለድሆች አከፋፍለው የሰጡና ምንም አይነት የዘረፋ ተግባር ያልፈፀሙ መሳፍንት መሆናቸው ይታወቃልና ነው፡፡ ከጃንሆይ ጋርም ከልጅነታቸው ጀምሮ አብረው በአንድ ላይ ያደጉ ነበሩ፡፡ ልጃቸውም በአባታቸው የወጡ መሆናቸው ስለሚታወቅ ጥሩ ዘዴ ነበር ደርግ የዘየደው፡፡ ከዚህም በላይ ሚካኤል እምሩ የተማሩ ናቸው፡፡ የአስተዳደር ችሎታና ልምድም ነበራቸው፡፡ ይህም ሲሆን ተሻሪው ሚኒስትር ልጅ እንዳልካቸው "ቦታዎ እስር ቤት ነው" ተባሉና አስለቅመው አሳስረዋቸው ከነበሩት ባለሥልጣናት ጋር ተቀላቀሉ፡፡

ልጅ ሚካኤል እምሩ ደርግ ፊት ቀርበው የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልጠው የጠቅላይ ሚኒስትርነት ስራቸውን ጀመሩ፡፡ አገሪቱ ከባድ ውጥረት ውስጥ ነበረችና የደርግ ዓላማ የተጠበቀውን ለውጥ እንደሚያመጣ ሂደቱ እየገለፀ መሆኑን በመረዳት የህዝብ ድጋፍ ይጎርፍ ጀመር፡፡

አሁን ለደርግ የቀረው እንቅፋት የለም፡፡ በጃንሆይ ዙሪያ የነበሩ ወፋፍራም ባለሥልጣናት ሁሉም ተለቅመው አልቀዋል፡፡ የቀሩት ጃንሆይና ጥቂት አሽከሮቻቸው ብቻ ናቸው፡፡ ጃንሆይ ሐምሌ 16 ቀን 1966 ዓ.ም የመጨረሻውን የልደት በዓላቸውን በቤተ-መንግስት ውስጥ አክብረዋል፡፡ ያውም ብቻቸውን፡፡ 82ኛ ዓመታቸውን መሆኑ ነው፡፡ አንዲት የልደት በዓል ትቀራቸው ይሆናል፡፡ እሷንም በእስር ያሳልፏታል፡፡
ጃንሆይ ፍዝዝ ... ብለዋል፡፡ባለሥልጣኖቻቸው ሁሉ ሲለቀሙ አንዲት የተቃውሞ ድምፅ አላሰሙም፡፡ ደርግ ሂደቱን ቀጥሏል፡፡ቅርንጫፎቹን መልምሎ ከጨረሰ በኋላ ወደ ሀብት ወረሳ አመራ፡፡ጃንሆይ በከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ይቆጣጠሩት የነበረውን የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካንና የአንበሳ አውቶቢሶችን ደርግ ወረሰ፡፡እነዚህንና ሌሎች መሰል የንጉሣዊ ቤተሰቡን የግል ሐብት ወደ ራሱ አዞረ፡፡ እነዚህንም ድርጊቶች ለህዝብ በሚዲያ እያሳዬ ጃንሆይን ህዝቡ እንዲጠላ አደረገ፡፡

ወደመጨረሻው ግድም ጥቂት የደርግ አባላት ወደ ቤተ-መንግስት ጎራ ብለው የእልፍኝ አስከለካያቸውን ጄኔራል አሠፋን ለማሰር ሲሞክሩ ከፈዘዙበት ነቃ በማለት ልዑካኑ ሰምተውት በማያውቁት ከባድ የቁጣ ጩኸት፤ "የፈለጋችሁትን ውሰዱ! እሱን ግን አትንኩም!" ብለው እንባረቁባቸው፡፡ "ለምን እሱን ትወስዳላችሁ? ምን አደረገ ነው የምትሉት? ተውት! ያለበለዚያ እኛንም እሰሩን!" አሉ፡፡ ደርግ "በቃ ይቅር" ብሎ ለጊዜው ተወላቸው፡፡ ጄኔራሉ ማታ ወደቤታቸው ሲሄዱ ግን ተይዘው ታሰሩ፡፡ ጃንሆይ በማግስቱ ሁኔታውን ሰሙ፡፡ ከማዘን በቀር ምንም አላሉም፡፡ በመጨረሻ አቶ ሽመልስ አዱኛ የተባሉት ሰው ለደርግ የምሰጠው ሚስጥር አለ አሉና የደርግ አባላቱ እንዲያይላቸው ጠየቁ፡፡አባላቱ ብቻ ተሰብስበው አዩት፡፡ ጆናታን ዲምቢልቢ የተባለው እንግሊዛዊ ጋዜጠኛ የቀረፀውን "የተደበቀ ረሃብ" የሚል ርዕስ የሰጠውን፤ የወሎ ህዝብ በረሃብ ሲረግፈ የሚያሳየውን ፊልም ነው፡፡ ፊልሙ እንግሊዝ አገር ታይቷል፡፡ይህን አሰቃቂ ፊልም ያዬ ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን፣ ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር እንባውን መቆጣጠር አይችልም፡፡ የደርጉ አባላት እየዘገነናቸው አይተው ጨረሱትና ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚያሳዩበትን ጊዜ መጠበቅ ጀመሩ፡፡ፊልሙን በጥንቃቄ ለጥቂት ጊዜያት አስቀምጠውም እንደመጨረሻ ጥይት ሊጠቀሙበት ፈለጉ፡፡ፊልሙ ብቻውን የጃንሆይን አገዛዝ ህዝቡ አንቅሮ እንዲተፋው የማድረግ ኃይል ቢኖረውም፤ ደርግ ግን የበለጠ ለማድረግ ሲል ከፊልሙ ጎን ለጎን ጃንሆይ ውሾቻቸውን በቅንጦት ሲመግቡና ሌሎች መሰል የቤተ-መንግስት ፌሽታዎችን አጣምሮ እያነፃፀር ለማቅረብ ፈለገ፡፡ ኤዲቲንጉም የተዋጣለት ሆነ፡፡የደርግ አባላት በነሐሴ ወር መጨረሻ ስለንጉሡ ቀጣይ



ዕጣ ፋንታ መወያየት ጀመሩ፡፡ምን እናድርጋቸው? በሚል፡፡ጳጉሜ 4 ቀን 1966 ዓ.ም አባላቱ ተሰብስበው በእጅ ብልጫ የወሰኑት ውሣኔ፤"ከዙፋን ማውረድ" የሚል ሆነ፡፡

ጳጉሜ 5 ቀን 1966 ዓ.ም ደግሞ አባላቱ "ስዊዝ ባንክ ብር አለዎትና ለኢትዮጵያ ህዝብ ይስጡ" ብለው ሞገቷቸው፡፡ "ገንዘብ የለንም" ብለው መለሷቸው፡፡ መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም ምሽት ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ የዘመን መለወጫ በዓልን አክብሮ ሁሉም በየቤቱ ሲከተት ደርግ "እኛ ለህዝብ የምንሰጠው ስጦታ የለንም፡፡ ያለን ይህ ነው" በማለት ያ ዘግናኝ ፊልም ለህዝቡ በቴሌቪዥን ተላለፈ፡፡ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የቁጣ እንባውን አነባ፡፡ ለንጉሡም ፍፁም ጥላቻ እንዲኖረው ሆነ፡፡ ደርግ ባየነው መልኩ ተመስርቶ ንጉሣዊ አገዛዙን ቦርቡሮ ቦርቡሮ እቅዶቹን ሁሉ በአግባቡ አከናውኖ እዚህ ደረጃ ደረሰ፡፡ በተወለደ በአጭር ጊዜ ውስጥ አደገ፡፡ ብዙዎቹ አዝጋሚ ሂደት ቢሉትም ከኢትዮጵያ ህዝብ ባህል እምነትና ንቃተ ህሊና አንፃር፣ እንዲሁም ከህዝቦች ታሪክና ልማድ ተነስቶ ሲመዘን (ምንም እንኳ ሁሉም ለውጥ ፈላጊ ሆኖ ቢታይም) ዘውዳዊውን ኢትዮጵያዊ ስርዓት በአንድ ጊዜ ደንፍቶ በደራሽ አብዮት ማስወገዱ ከፍተኛ የርስ በርስ ፍጅት ማስከተሉ የማይቀር ይሆን ነበር፡፡ በቀለም ትምህርት ብዙ ያልገፉት የደርግ አባላት የተጓዙበት መንገድ ግን በአዝጋሚነቱ ውስጥ ፈጣንነቱ የሚገለፅ ነው፡፡ በወቅቱም ተአማኒነትን ከሁሉም ዘንድ አስገኝቶላቸዋል፡፡ ለዚህ ሁሉ ሂደት ሻለቃ መንግስቱ ትልቁን ስራ ሰርተዋል፡፡ በእስር ላይ ያሉ አባላትም ይህንኑ ነው የሚሉት፡፡

ለደርግ ብዙ ምሁራን በግንባር እየቀረቡ ምክር ይለግሱና ንጉሡን እንዲያወርዱ ግፊት ያደርጉ ነበር፡፡ ከዚህም ባለፈ አንድ የደርግ አባል ምስክርነታቸውን ሲሰጡ "... በተለይ ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም ማታ ማታ ከለውጥ ፈላጊ ምሁራን ብቻ ሳይሆን፤ ከደጃዝማች ከበደ ተሠማ ጋር እየተገናኘ በተከታይ ቀን አዳዲስ ሀሳብ ይዞ ይመጣ ነበር፡፡ ሁላችንም በአንድ አስተባብሮ ከውሣኔ ያደረሰን ሻለቃ መንግስቱ ነበር" ብለዋል፡፡

ተጀምሮ እስኪጨረስ የሒደቱ አራማጅ "አባላቱ" ይባሉ እንጂ በአንድ መንግስቱ ሀሳብ፣ እቅድና ውሣኔ እንዲሁም የተግባር እርምጃ ብቻ ደርግ የደርግነቱን ህልውና ማግኘቱን የካደም የሚክድም አባል የለም፡፡

ከተለያዩ የጦር ክፍሎችና ከፖሊስ ሠራዊት ጭምር ተውጣጥተው፤ ተደራጅተው ደርግን የመሠረቱ አባላት ስም ዝርዝር የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የአባላቱን የቀለም ትምህርት በሚመለከት፤ ከፍተኛው የሻለቃ አጥናፉ አባተ 12+4፣ዝቅተኛው ምንም ያልተማረ ሲሆን፤ ብዙዎች 7 እና 8፣ እንዲሁም 11 እና 12ኛ ክፍል መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፤ 3ኛና 4ኛ ክፍሎችም ቀላል ቁጥር አልነበራቸውም፡፡ 12+3፣ 12+2 ድረስ የገፉም

ነበሩ፡፡ ይህም ሲባል ከደርግ ምስረታ በኋላ "በጣት የሚቆጠሩት" በአገር ውስጥና በውጭ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ መደረጉ መዘንጋት የለበትም፡፡

ደርግ ሲመሠረት የነበራቸውን ማዕረግና ስም ስናይ ከተለያዩ የጦር ክፍሎች መውጣጣታቸው እንዳለ ሆኖ፤ በየክፍላቸው የነበራቸው የስራ ድርሻም የተለያዩ እንደነበርና በየጊዜውም የማዕረግ እድገት እያገኙ እንደሄዱ ተረድተን እንቀጥል፡፡



1. ሻለቃ አጥናፉ አባተ
2. ሻለቃ አባተ መርሻ
3. ሻለቃ አበበ በላይነህ
4. ሻለቃ አስራት ደስታ
5. ሻለቃ ፋንታዬ ይህደጎ
6. ሻለቃ ጎሩይ ኃይለስላሴ
7. ሻለቃ ተስፋዬ ገብረኪዳን
8. ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም
9. ሻለቃ ዘለቀ በየነ
10. ሻለቃ አሥፋ መኮንን
11. ሻለቃ ሲሳይ ሐብቴ
12. ሻለቃ ብርሃኑ ባይህ
13. ሻለቃ ፍስሐ ደስታ
14. ሻለቃ ጌታቸው ሽበሺ
15. ሻለቃግርማ ኃይለገብርኤል
16. ሻለቃ ሐዲስ ተድላ
17. ሻለቃ ደምሴ ደሬሳ
18. ሻለቃ ከተማ አይተንፍሱ
19. ሻለቃ ኪሮስ አለማየሁ
20. ሻለቃ እንዳለ ተሰማ
21. ሻለቃ መኩሪያ ኃይሉ
22. ሻለቃ ናደው ዘካርያስ
23. ሻለቃ ነጋሽ ተስፋፅዮን
24. ሻለቃ ሽመልስ ሙሉጌታ
25. ሻለቃ ተካ ቱሉ
26. ሻለቃ ደበላ ዲንሳ
27. ሻለቃ መለሠ ኃይሌ
28. ሻለቃ ገብረየስ ወልደሃና
29. ሻምበል የማነ ተስፋንጉስ
30. ሻምበል ካሳሁን ታፈሰ
31. ሻምበል ካሣዬ አራጋው
32. ሻምበልሚካኤል ገብረንጉስ
33. ሻምበልሞገስ ወልደሚካኤለ
34. ሻምበል የኋላሸት ግርማ
35. ሻምበል ተፈራ ደነቀ
36. ሻምበል ውብሸት ደሴ
37. ሻምበል ንጉሴ ፋንታ
38. ሻምበል መለሰ ማሩ
39. መቶ አለቃ ዓለማየሁ ኃይሌ

40. መቶ አለቃ ተሰማ በላይ
41. መቶ አለቃ ዓሊ ሙሣ
42. መቶ አለቃ በላይ ቢተው
43. መቶ አለቃ በዕውቀቱ ካሣ
44. መቶ አለቃ ፍቅረስላሴ ወግደረስ
45. መቶ አለቃ መላኩ ተፈራ
46. መቶ አለቃ ገበየሁ ተመስገን
47. መቶ አለቃ ስለሺ በየነ
48. መቶ አለቃ ግርማ ፍስሃ
49. መቶ አለቃ ኃይሌ መለሰ
50. መቶ አለቃ አሸብር አማረ
51. መቶ አለቃ ተስፋዬ ተክሌ
52. መቶ አለቃ ስለሺ መንገሻ
53. መቶ አለቃ ግርማ አየለ
54. መቶ አለቃ ንጉሴ ነጋሣ
55. ሻ/ ባሻ ማንመክቶት ወንድማገኝ
56. ሻ/ል ባሻ ግዛው ወልደሚካኤል
57. ባሻ ታደሰ አደራ
58. ባሻ ከበደ ዓሊ
59. ማስተር ሠርጀንት ደሣለኝ በላይ /አየር ኃይል/
60. ሃምሳ አለቃ ጌታሁን አቦዬ
61. ጁኒየር ኤክማን ዮሐንስ ፍትዊ /አየር ኃይል/
62. ማስተር ሠርጀንት ማሞ እጅጉ /አየር ኃይል/
63. ሃምሳ አለቃ ተፈራ ወልደመስቀል
64. ሃምሳ አለቃ ከበደ ክብረት
65. ሃምሳ አለቃ ንጉሴ ፋንታ
66. ሃምሳ አለቃ ደመቀ ባንጃው
67. ሃምሳ አለቃ ጎሹ አለማየሁ
68. ሃምሳ አለቃ ታምራት ፈዬ
69. ሃምሳ አለቃ ኃይሌ ገበየሁ
70. ሃምሳ አለቃ አድማሱ አየለ
71. ሃምሳ አለቃ ጴጥሮስ ገብሬ
72. ሃምሳ አለቃ ተፈራ ጅፋር
73. ሃምሳ አለቃ ግዛው ወልደሚካኤል
74. ሃምሳ አለቃ ጥሩነህ ኃይለስላሴ
75. ሃምሳ አለቃ ገብረሀይወት ገብረፃድቅ
76. ሃምሳ አለቃ ከበደ አበጋዝ
77. ሃምሳ አለቃ አበራ አጋ
78. ሃምሳ አለቃ አክሊሉ በላይነህ



79. ሃምሳ አለቃ በቀለ ደጉ
80. ሃምሳ አለቃ ተገኝወርቅ ተስፋ
81. ሃምሳ አለቃ ለገሠ አሰፋው
82. ሃምሳ አለቃ ይልማ ከበደ
83. ፒቲ ኦፊሰር ትምራት ፈረደ /ባህር ኃይል/
84. ፒቲ ኦፊሰር ሚካኤል አስገዶም /ባህር ኃይል/
85. ሲኒየር ቴክኒሽያን ደምሰው ካሳዬ /አየር ኃይል/
86. ሲዲኒግ ቴክኒሽያን ገሠሠ ወልደኪዳን /አየር ኃይል/
87. አስር አለቃ አለማየሁ አየለ
88. አስር አለቃ ፍስሃ አንደቶ
89. አስር አለቃ በጋሻው ጉርሜሳ
90. አስር አለቃ ኃይሉ በላይ
91. አስር አለቃ ግርማ ቡርቃ
92. አስር አለቃ መንግስቱ ገመቹ
93. አስር አለቃ ንጉሴ ወልዴ
94. አስር አለቃ ሙሉጌታ አብርሃም
95. አስር አለቃ ግርማ አድማሱ
96. አስር አለቃ ገብረሀይወት ገብረእግዚአብሔር
97. አስር አለቃ ፍቅሬ ዘርጋባቸው
98. አስር አለቃ ጌታቸው አረጋ
99. አስር አለቃ ዳምጠው ገረመው
100. አስር አለቃ ጌታቸው ተቀባ
101. ም/ል አስር አለቃ አራጋው ይመር
102. ተራ ወታደር ደምሴ አብተው
103. ተራ ወታደር ደጀኔ ወንድምአገኘሁ
104. ተራ ወታደር ደምስ አላምረው
105. ተራ ወታደር ገዛኸኝ ወርቁ
106. ተራ ወታደር በጋሻው አታላይ
107. ተራ ወታደር ዓለማየሁ ከልካይ
108. ተራ ወታደር ፀጋዬ ጥሩነህ
109. ተራ ወታደር ገብረጊዮርጊስ ብርሃኔ

ደርግ በእነዚህ አባላት ስብሰብ ተመስርቶ፤ ነገር ግን ከጅምሩ አባል ያልሆኑትን ሁለት ጄኔራሎች የደርግ ሊቀመንበር አድርጎ አሳይቷል፡፡ በዚህ መሠረት ጄኔራል አማን 2 ወር፣ ጄኔራል ተፈሪ በንቲ 2 ዓመት በሊቀመንበርነት የቆዩ ሲሆን፤ ከዚያ በኋላ ያለውን ጊዜ መሪነቱን ይዘው የቀጠሉት ሻለቃ መንግስቱ ናቸው፡፡ ሁለቱ ጄኔራሎች ስለተጨመሩም ነው ብዙ ጊዜ የደርግ አባላት ቁጥራቸው 111 ተደርጎ ሲዘረዘር የምናየው፡፡

የደርጉ ሊቀመንበር መንግስቱ ግንቦት 19 ቀን 1933 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተወለዱ ናቸው፡፡ ውልደትና እድገታቸውን በሚመለከት ጥርት ያለ ትንታኔ አናገኝም፡፡ ብዙዎች የደጃዝማች ከበደ ልጅ ናቸው ሲሉ፤ ሌሎች ደጃዝማቹ አጎታቸው፣ አንዳንዶች የእናታቸው አባት አያታቸው፣ የቀሩት አጎታቸው አድርገው ጽፈውታል፡፡

ይህን ለማለት የሚያስችሉ በርካታ መነሻዎችም አሉ፡፡ ጥቂቶቹን ለመጠቃቀስ 1ኛ. ከዚያ ሁሉ የቀድሞው ሹማምንት ሳይታሰሩ የቀሩ መሆናቸው፣ ደጃዝማቹ የሞቱ እለት የቤተመንግስቱ ያማረ ምንጣፍ ሄዶ እንደተነጠፈላቸውና፤ መንግስቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀድሞው ባለሥልጣናት ሞተው ያለቀሱትና ለቅሶ የደረሱት እሳቸው ዘንድ መሆኑ፣ የጃንሆይ ታማኝ ሆነው ሳለ፤ ነገር ግን የንጉሱን ሚስጥር ዘክዝከው ለመንግስቱ መግለፃቸው ... ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡

ሃምሳ አለቃ ኃይለማርያም ወልዴ ሳይቀሩ አሳዳጊው ነኝ እንጅ አባቱ አይደለሁም የሚል ቃል እንደተናገሩ ተጽፏል፡፡ የመንግስቱ እናት ቤተመንግስት ውስጥ ዝቅ ያለ ሥራ እየሰሩ ይተዳደሩ ነበር መባሉም ለውዝግቡ በር ከፍቷል፡፡ ምንም ቢሆን ግን "ውልደትን" በተመለከተ ባለቤቱ የተናገረውን መቀበል የውዴታ ግዴታ ነውና እንዲህ ነው፤ እንዲያ ነው ብሎ መደምደሙ የአንድ ፀሐፊ ተግባር ስላልሆነ ትቼዋለሁ፡፡ ምክንያቱም ከላይ የተጠቃቀሱትን አይነት አንታኔዎች መንግስቱ "የሃሰት ወሬ ነው" ብለው ዛሬ ድረስ አስተባብለዋልና ነው፡፡ መንግስቱ እንዲታወቁ የፈለጉት በኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ እስከሆነ ድረስም ዘር መዘርዘሩ አስፈላጊ አይደለም፡፡

እናም በአዲስ አበባ ጊዎርጊስ ብተክርስቲያን አካባቢ ተወልደው እናታቸውን በ9 ዓመታቸው በሞት ያጡት መንግስቱ በጃንሆይ ጊዜ በውትድርና ተሰማርተው ከነበሩት ከአባታቸው ከሃምሳ አለቃ ኃይለማርያም ወልዴ ጋር ሲያድጉ፤ አባታቸው በየተመደቡበት አገር ከፋ፣ ጅማ፣ ድሬዳዋ፣ ሐረር፣ ... አብረው እየዞሩ የልጅነት ጊዜያቸውን ያሳለፉት የቀለም ትምህርታቸውን በመከታተል ነበር፡፡



ከዚያም የኢትዮጵያ ሠራዊት በእንግሊዞች አማካኝነት ሲደራጅ በቀረበው ሀሳብ መሠረት የጃንሆይ መንግስት ወጣት ልጆችን ከልጅነታቸው መልምሎ በወታደራዊና በቀለም ትምህርት አሳልብቶ በተለያዩ ዘርፎች እንዲያገለግሉ ማድረግ ሲጀምር ከእነዚህ ውስጥ አንዱ መንግስቱ መሆን ቻሉ፡፡

"የልጅ ወታደርነት" በሚል ስያሜው የሚታወቀው የዚያ ዘመን ምልመላ ከሞላ ጎደል መመዘኛው የነበረው ወላጆቻቸው በአርበኝነቱ ዘመን ያለቁባቸው፣ የባለሥልጣናቱ ይሁኝታና፣ በቀጣሪ መኮንኖች ዘንድ በቅርብ የሚታወቁ፣ እንዲሁም የወታደር ልጆችን ማዕከል ያደረገ ነበር፡፡ መንግስቱ የልጅ ወታደር ሆነው እንዲቀጠሩ ያስቻላቸው ተብሎ ሁለት ነገር ሲጠቀስ፤ አንዱ የወታደር ልጅ መሆናቸው፣ ሌላው በደጀአዝማች ከበደ ተሰማ እገዛና ይሁንታ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ብቻ ግን መንግስቱ በ1946 ዓ.ም ወደ ውትድርና ገብተው እስከ 1950 ዓ.ም ድረስ የዕጩ መኮንኖችን ኮርስ በሆለታ ገነት የጦር ትምህርት ቤት ተከታትለው ከ19ኛው ዙር ተመራቂዎች ውስጥ አንዱ ሆነው፣ የምክትል መቶ አለቃነት ማዕረጋቸውን ይዘው ስራቸውን ጀምረዋል፡፡ በተለያዩ ጊዜያቶችም ሁለት ጊዜ ያህል ለትምህርት ወደ አሜሪካ ተጉዘው ስለመሣሪያ ይዞታና አስተዳደር ተምረው ተመልሰዋል፡፡ በሌሎች የጦር ክፍሎች ተመድበው ቢሰሩም፤ በዋናነት ግን በመሣሪያ ግምጃ ቤት ውስጥ ነው ረጅም ዓመታት ያገለገሉት፡፡ በመጨረሻም ወደ ሦስተኛ ክፍለ ጦር ተዛውረው የመሣሪያ ግምጃ ቤቱ ኃላፊ ሆነው ሐረር ውስጥ በማገልገል ላይ ሳሉ በክፍለ ጦሩ አዛዥ ብርጋዴር ጄኔራል ጥላሁን ቢሻኔ ተመርጠው ከሌሎች አባሎቻቸው ጋር ከሐረር ተነስተው አዲስ አበባ 4ኛ ክፍለ ጦር ጊቢ ውስጥ ገቡ፡፡ እዚያም መሪ ሆኑ፤ ከዚያ ወጥተውም ቤተመንግስት ገቡ፤ እዚያም መሪ ሆኑ፡፡

*አብዮቱ ሲፈነዳ*

አቶ ብርሃኑ ድንቄ በቄሳርና አብዮት መፃሀፋቸው መደምደሚያ ላይ አብዮትን በተመለከተ ያሰፈሩትን ሐተታ ሳስቀድም፤ "... ሪቮሉውሽን /አብዮት/ በማስነሳት በአንድ አገር ውስጥ የሚገኘውን ኢፍትሀ፣ የመብት መነፈግ፣ ጭካኔ፣ ግፍ፣ የአስተዳደር ንቅዘት ለማረም በፍፁም የማይቻል ነው፡፡ የሰዎች ማኅበራዊ ድርጅት ከተቋቋመ ጀምሮ እስከዘመናችን ድረስ ብዙ ሪቮሊውሽኖች እንደተደረጉ በታሪክ አንብበናል፤ ጥቂቶቹንም በዘመናችን አይተናል፡፡ ግን ለሰው ልጅ ምን አተረፉለት?" ብለው በመጠየቅ መልሱን ከጆርጅ በርናንድ ሾው እንድንረዳ ይጋብዙናል፡፡ "Revolutions have never lighted the burden of tyranny: They have only shifted it to another shoulder." "አብዮቶች የጭካኔን ሸክም

አቃለው አያውቁም፤ ነገር ግን ወደ ሌላው ትክሻ ያዛውሩታል" እንደማለት፡፡

አምባሳደሩ ሲቀጥሉ፤ "ይህ እውነተኛ ቃል ነው፡፡ ግን የሰው ልጆች አትኩረው ሊመረምሩትና ሊጠቀሙበት አልቻሉም፡፡ ሰዎች እንደሰዎች ሊያስቡና እንደሰዎች ሊኖሩ የሚችሉበት አንድ ዘዴ መገኘት አለበት፡፡ በበኩሌ በመንፈሣዊ ሪቮሉሽን አምናለሁ፡፡ በርግጥ መንፈሣዊ ሪቮሉሽን የቤተ-ክርስቲያን ቋንቋ አይደለም፡፡ እኔ ከቋንቋው ጉዳይ የለኝም፡፡ ቋንቋ ገለባ ነው፡፡ እኛ መፈለግ ያለብን በገለባው ውስጥ የሚገኘውን ፍሬ ነው፡፡ እውነተኛ መንፈሣዊ ሪቮሉሽናሪ የናዝሬቱ እየሱስ መሆኑን አውቃለሁ፡፡ እርሱ በባዶ ቋንቋ መጠቀምን አይፈቅድም፡፡ እርሱ ስለእውነትና ስለፍትህ ተናገረ፡፡ በባዶ ቋንቋ የሚያምኑ ፈሪሳውያን ትምህርቱን ተቃወሙ፡፡ ግን ዓለም የርሱን ትምህርት መከተል እስካልቻለ ድረስ ፍትህ ማግኘት አይቻልም" በማለት ጽሁፋቸውን ይደመድማሉ፡፡ *(ቄሣርና አብዮት ገፅ 69)*

የደርግ አብዮትስ? ብለን እንጠይቅ፡፡ እንዲያውም ጠያቂው ራሳቸው ጃንሆይ ይሁኑና መላሹ ኮሎኔል ዳንኤል ይሁን፡፡ በመንግስቱ ትዝታዎች ቁጥር 1 መጽሐፍ ውስጥ ከአልባሾቻቸው አንዱ ጃንሆይ በእስር ላይ በነበሩ ጊዜ ኮሎኔሉን ጠርተው እንዲህ ማለታቸውን ያስታውሳል፤ "... አንድ ቀን ጃንሆይ "ኮሎኔል ዳንኤልን ለመሆኑ እናንተ ዓላማችሁ ምንድነው?" ብለው ቢጠይቋቸው፤ ኮሎኔል ዳንኤል "ዓላማችን ዝቅ ያለውን ከፍ፤ ከፍ ያለውን ዝቅ ማድረግ ነው" አሏቸው፡፡ንጉሡም "አይሆንላችሁማ!" ብለው መለሱላቸው፡፡"

አብዮት ማለት ይህ መሆኑን ስንረዳ በጆርጅ በርናንድ ሾው አባባል ለመስማማት እንገደዳለን፡፡ ሌላው እንግሊዛዊ ጆርጅ ኦርዌል ደግሞ "አብዮት በመጀመሪያ ሁሉንም እኩል ያደርጋል፤ ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ አንዳንዶች ይበልጥ እኩል መሆናቸውን ያውጃሉ" ብሏል፡፡ ኮሎኔል ዳንኤል "ዝቅ ያለውን ከፍ፤ ከፍ ያለውን ዝቅ" ሲሉ ከድጡ ወደ ማጡ ማለታቸው ነው ባይባልም፤ የእኩልነትን ፍልስፍና ገለፃቸው አያካትትም፡፡ ከፍ ያሉት ዝቅ ሲሉ ዝቅ ያሉት ከፍ ይሉና፤ ከፍ ብለው ይቀራሉ የማለት ያህል ነው፡፡ ስለዚህ በጆርጅ አርዌል አባባልም ልንስማማ እንገደዳለን፡፡ አብዮት የአንድ አገር ህዝብ የመንግስትን አገዛዝ ተቃውሞ፤ በትብብር አመፅ ያንን መንግስት በኃይል አስወግዶ በሌላ የመተካት ፍላጎትና ውጤት ነው፡፡ ከተሳካ በኋላ የሚተካው መንግስትም ያኛውን አገዛዝ ለመቃወም ያደረሱትን ብልሹ አሰራሮች አስወግዶ የተሻለ አስተዳደር ዘርግቶ ለውጥ ማምጣት ነው፡፡ ስለዚህ አብዮት ለውጥ ነውና አገርን ይለውጣል፡፡



የደርግ አብዮት ወደፊት እንደምናገኘው ያስገኛቸው ፍሬ ነገሮች አሉ፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ አብዮት ከሌላው አገር አብዮት የሚለይበት የስልጣን አብዮት ሆኖ መቅረቱ ነው፡፡ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም የደርግ ልዑካን ወደ ቤተ-መንግስት ሄደው ለጃንሆይ የአገዛዝ ዘመናቸው ማብቃቱን አረዷቸው፡፡

ደርጎች ገና ከጅምሩ በማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል እንዳይነቀፉ ልዩ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር፡፡ እያንዳንዷን እንቅስቃሴያቸውን አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ ነው ያከናወኑት፡፡ በጄኔራል አማን አሰማሪነት ሌሊቱን ሙሉ ጥበቃውን ሲያጠናክሩ አድረዋል፡፡ በቤተ-መንግስቱ ዙሪያ ታንክ ሳይቀር አጥምደው አስከብበዋል፡፡ በማለዳ ጃንሆይን ለማውረድ ሲሄዱም ሌላ ታሪክ ተፈጥሮ እንዳይወራባቸው ከጃንሆይ ጋር ራስ እምሩ በእማኝነት አብረው እንዲገኙ አድርገዋል፡፡ 13 ሆነው የሄዱት የደርግ ልዑካን፤ ቤተ-መንግስት የገቡት ማለዳ ላይ ነው፡፡ ጃንሆይ እንደተፈለጉ ተነግሯቸው ከፎቅ እየወረዱ ነውና ልዑካኑ ደንግጠው ጥቂት ጠበቁ፡፡ በዝግታ የመጡት ንጉሠነገስት በዙፋኑ አዳራሽ ባለው ወንበር ቀስ ብለው ተቀመጡ፡፡

ሻምበል ደበላ ዲንሳ የኮሚቴውን የውሣኔ ቃል ለጃንሆይ አነበቡ፤ "... ለአገርና ለህዝብ ደህንነት ሲባል በዛሬው ዕለት ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለስላሴ ከስልጣን ወርደዋል፤ ለደህንነትዎ ሲባልም አስተባባሪው ኮሚቴ ወዳዘጋጀልዎት ቦታ እንዲሄዱ ተወስኗል..." የሚል ጭብጥ ያለው ሃተታ ተነበበላቸው፡፡ አንባቢው ከማንበባቸው በፊት የሰጡትን ወታደራዊ ሠላምታ አንብበው ከጨረሱ በኋላም ደገሙት፡፡ ጃንሆይ በዝምታ ተውጠው ደቂቃዎች አለፉ፡፡ ደርግ ንጉሱን ከስልጣን ለማውረድ በወሰነ ጊዜ አዋጅ አውጥቶ አዋጁንም በወታደራዊ ማርሽ ታጅቦ በመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

"በኢትዮጵያ የኖረው ዘውድ በህዝቡ ዘንድ በቅን ልቦና የአንድነት ምልክት ሆኖ ታምኖበት ቢቆይም ለ50 ዓመታት አገሪቱን የመሩት ንጉስ ከህዝብ የተሰጣቸውን ስልጣን ለራሳቸውና በአካባቢያቸው ለሚገኙ ሰዎች በማዋል አገሪቱን አሁን ካለችበት ከፍተኛ ችግር ላይ በመጣላቸው፣

አሁን በእድሜ መግፋት ሳቢያ ይህን ከፍተኛ አገር የመምራት ኃላፊነት ሊሸከሙ የማይችሉ መሆኑን በመረዳት፣

ያለው የህዝብ ምክር ቤት አመራረጥ ዴሞክራሲን ያልተከተለ፣እስካሁን ያገለገለውም ለህዝብ ሳይሆን ለዘውዳዊው ስርዓት በመሆኑ፤የአገሪቱ መሠረታዊ ችግር የሆነው የመሬት ይዞታን የሚያሻሽል ሕግ ከማውጣት የተቆጠበ፤አባላቱም ከህዝብ የተሰጣቸውን ከፍተኛ ስልጣን ለግል መጠቀሚያ አድርገው በህዝብ ላይ ተጨማሪ ችግር እያደረሱ

በመሆኑና አሁን የምክር ቤቱ መኖር ለ"ኢትዮጵያ ትቅደም" መርህ እንቅፋት ስለሚሆን፣

የ1948ቱ ሕገ-መንግስት የተዘጋጀው ለንጉሱ የፈላጭ ቆራጭነት ስልጣን የሰጠ ለውጭው ዓለም ደግሞ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ያለ ያስመስላል እንጂ እውነተኛ ዴሞክራሲ የሌለበት፣ ለህዝብ ጥቅም ታስቦ ያልተዘጋጀ፣ለሰው ልጅ ተፈጥሮ የሰጠውን መብትም ከንጉሠነገስቱ የተሰጠ የሚል፤ ኢትዮጵያን ለማስቀደም ለተጀመረው ህዝባዊ እንቅስቃሴና የኢኮኖሚ፣የፖለቲካና የሶሻል እድገት መሻሻል ተፃራሪ በመሆኑ፣የነበረው የመሣፍንት አገዛዝ ስርዓት ባስከተላቸው ጉድለቶች አገሪቱን በኢኮኖሚ፣በማኅበራዊና ፖለቲካ አዘቅት ውስጥ ስለጣላትና ባለንበት የመሸጋገሪያ ወቅት ልዩ ልዩ የፀጥታ ችግሮች በመፍጠራቸው ችግሮችን አስወግዶ አገሪቱን ወደፊት ለማራመድ የሚያስችል ለህዝብ ጥቅም የተሰለፈ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ለመፍጠር በመታሰቡ" በሚል የአዋጁ መግቢያ ተነበበ፡፡

አንድ አዲስ ስልጣን ያዥ ኢትዮጵያዊ መንግሰት የተለመደውን ህዝብን የመሸንገል ተግባሩን ለማከናወን ከዚህ የተሻሉ ቃላትን መቀሸርና ማንበብ የሚጠበቅበት አይመስልም፡፡ "ስልጣን የህዝብ ነው" ይሉናል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ስልጣን የህዝብ ሆኖ ያዩ ትውልድ ካለ ይመናቸው እንጂ በኢትዮጵያ ከዘውዳዊ አገዛዙ ማከተም በኋላ ሆኖ አያውቅም፡፡ ስንመለስ አዋጁ፤

1ኛ. ንጉሡን ከስልጣን ማውረድና በአልጋወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋወሰን መተካት፣

2ኛ. ንጉሡን የሚተኳቸው ንጉስ ከርዕሰብሔርነት ውጪ ምንም የፖለቲካና የአስተዳደር ስልጣን እንደማይኖራቸው፣(ሁለቱ አዋጆች ተግባራዊ አልሆኑም)

3ኛ. የሕግ መምሪያና መወሰኛ ምክር ቤት መዘጋቱን፣

4ኛ. የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስ ሠራዊትና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ የመንግስትን አመራር መያዙን፣

5ኛ. የኢትዮጵያ ትቅደም መርህን የሚቃወም፣ የስራ ማቆም አድማና ሠላማዊ ሰልፍ ያለፈቃድ ማድረግና የህዝብን ፀጥታና ሠላም የሚነሳ ተግባር መፈፀም መከልከሉን፣

6ኛ. የኢትዮጵያ ትቅደምን መርህ ተቃውመው ወንጀል የሚፈጽሙትንና በቀድሞው መንግስት የዳኝነትና የአስተዳደር በደል የፈፀሙትን ያለአግባብ የመበልፀግ ወንጀል የፈፀሙትን ሰዎች ጉዳይ የሚመለከት ይግባኝ የሌለበት ፍርድ ቤት መቋቋሙን ደንግጓል፡፡

ወደጀመርነው ወዳጃንሆይ ዝምታ እንመለስ፡፡





ጃንሆይ የደርጉን ንባብ ሲያደምጡ

ደበላ ዲንሳ ለጃንሆይ ያነበቡትን በአንዲት ዓረፍተነገር የተዋቀረች መርዶ ያደመጡት ንጉስ ከደቂቃዎች ድንዛዜያቸው እንደመንቃት ብለው አንባቢውን ትኩር ብለው ማየት ጀመሩ፡፡ አልሄድም ቢሉስ? የሚል ውጥረት ይዟቸዋል ልዑካኑ፡፡ መልስ ሲጠፋ አንባቢው ወደራስ እምሩ ቀረብ አሉና "ልዑልነትዎ አንድ ያድርጉ እንጂ፡፡ ሰዓት እያለቀብን ነው፤ ግርማዊነታቸውን ፍጠኑ ማለት አልችልም" አሉ በአክብሮት፡፡

ራስ እምሩም ቁጭት ላይ ነበሩ፡፡ ምክንያቱም በተደጋጋሚ ለአብሮ አደጋቸው ጃንሆይ በቀና መንፈስ ለውጥ እንዲያደርጉ፣ ሕገ-መንግስቱ እንዲሻሻል፣ ስርዓቱ እንዲለወጥ ወንድማዊ ምክራቸውን ሲለግሱ የኖሩ ናቸው፡፡ ጃንሆይ ግን እንዲህ ያለውን ጉትጎታ አይወዱትም ነበርና በአምባሳደርነት እየሾሙ ያርቋቸው ነበር፡፡ ቁጭታቸው ከዚህ የመነጨ ነው፡፡ አሁን ግን ራስ እምሩ ወደ ጃንሆይ ጠጋ ብለው "እንዳሉት ማድረግ ነው እንግዲህ፤ ሁሉም ነገር አልቆለታል፤ ሌላ አማራጭ የለንም" አሏቸው፡፡ ጃንሆይ ወደ አብሮአደጋቸው ቀና አሉና በማይሰማ ሹክሹክታ ጥቂት ቃላት ተለዋወጡ፡፡

በመጨረሻም ንጉሡ መናገር ጀመሩ፤ "ያነበባችሁትን ሠምተናል፤ የኢትዮጵያ ንጉሠነገስት ስንሆን ስም ብቻ አይደለም፤ ቢሆንም በየጊዜው የሚለዋወጠው ነገር ደግሞ ለአገር የሚጠቅም ነገር እስካለበት .... ያነበባችሁትን ሰምተናል፡፡ የኢትዮጵያን ታሪክ ጠብቃችሁ ማልማት ከቻላችሁ የእኛ ታሪክ እዚህ ላይ ያበቃል፤ ካልቻላችሁ የናንተ ታሪክ እዚያ ላይ ይቆምና የእኛ ይቀጥላል፡፡ አገራችንንና ህዝባችንን በምንችለው አገልግለናል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ እድል የእኛን መወገድ የሚጠይቅ ከሆነ

ግን ስራችንን አቁመን ማንኛውንም ነገር ለመቀበል ዝግጁ ነን፡፡ አሁን ተራው የእኛ ነው ካላችሁ ኢትዮጵያን ጠብቁ" ብለው አበቁ፡፡ (ጃንሆይ እውነትም ነብይ ቢባሉ ያንሳቸዋል፡፡ ያሉት አልቀረም ደርግ ከነርዕዮቱ ወድቆ የቀድሞው የጃንሆይ ዘመኑ ካፒታሊዝም እንደወረደ በኢትዮጵያ እየተሰራበት ይገኛል፡፡)



ይህ ሁሉ ሲሆን የቴሌቪዥን ጋዜጠኞች ካሜራቸውን ተክለው እየቀረፁ ነው፡፡ አንባቢው ደበላ ዲንሳ ለገነት አየለ የገለፁትን እና በቁጥር 1 ትዝታዎች የተካተተውን ጽሁፍ መሠረት አድርገን እንቀጥል፤

"መልስ አልሰጠናቸውም፤ ልባችን ተነክቷል፡፡ እኛም አገራችንን በቅንነት ለማገልገል ስለሆነ የተነሳነው ባሉት ሙሉ በሙሉ የምንስማማ ነበርን፡፡ ለህዝብና ለአገር ያለንን ቀና አስተሳሰብ ባንጠራጠርም፤ በአንፃሩ ወጣቶችና ልምድ አልባዎች በመሆናችን የወደፊቱ አካሄዳችን ሳያሳስበን አልቀረም" ብለዋል፡፡ ጃንሆይ ንግግራቸውን ከጨረሱ በኋላ ሌላ ፀጥታ ተከተለ፡፡

"ግርማዊ ሆይ፤ እባክዎን ይከተሉን፤ እንሂድ"

"የት ነው የምንሄደው? የት ነው የምትወስዱን?" አሉ ቆጣ ብለው፡፡

"ለግርማዊነትዎ ማረፊያ ልዩ ስፍራ ተዘጋጅቷል"

"እኮ የት ነው እሱ?"

"እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ ነው ግርማዊ ሆይ፡፡ ለደህንነትዎ ተብሎ በምስጢር የተያዘ ቦታ ስለሆነ ትክክለኛ ስፍራውን ለመንገር አልተፈቀደልኝም"

"አንድ አሽከር ሊከተለን ይችላል?"

"አዎን ግርማዊ ሆይ፤ ሊከተልዎት ይችላል፡፡ ማንን ነው የሚፈልጉት? ስሙ ማን ነው?"



"ስሙን ምን አስጠየቀህ? አንድ አሽከር ነው የምንፈልገው ካልን አይበቃም" ቆጣ አሉ፡፡"ወሰኔ" ብለው ተጣሩ፡፡ ወሰኔ በፍጥነት ቀርቦ እጅ ነሣ፡፡ ጃንሆይ ጥያቄያቸውን ቀጠሉ፡፡ "መፃህፍትስ ይዘን መሄድ እንችላለን?" አይ ቀን! ፈቃጅ ፈቃድ ሲጠይቅ፤

"የፈለጉትን ያህል ግርማዊ ሆይ፡፡ የፈለጉትን ያህል መውሰድ ይችላሉ" አሏቸው፡፡ ጃንሆይ እንደመነሳት ሲሉ፤ ትሁቱ ራስ እምሩ "እኔስ ልከተላቸው እችላለሁ?" ብለው አስፈቀዱ፡፡ ለጊዜው እንደማይቻልና ወደፊት እየመጡ ማየት እንደሚችሉ ሲነገራቸው ቀሩ፡፡ ጃንሆይ በዝግታ መራመድ ጀመሩ፡፡ በመርዶ ነጋሪያቸው መሐል ሲያልፉ የመሣሪያ አያያዙን አይተው፤

"ለምንድነው መሣሪያህን እንዲህ አንጠልጥለህ የያዝከው?" ብለው ጠየቁ በእርጋታ፡፡

"ለአያያዝ እንዲመቸኝ ነው ግርማዊ ሆይ"

"እኛን ለመያዝ?"

"አይደለም ግርማዊ ሆይ መሣሪያውን ማለቴ ነው" የሚል መልስ ሲያገኙ ፈገግ ብለው በእርጋታ ጉዟቸውን ቀጠሉ፡፡ ከአዳራሹ ወጥተው በረንዳው ላይ እንደደረሱ ያቺን ያማረች ሮልስ ሮይስ መኪናቸውን በዓይናቸው ያማትሯት ገቡ፤ የለችም፡፡ የሞተረኞች እጀባም የለም፡፡ "የት አለች መኪናዋ?" ብለው ጠየቁ፡፡ ከደረጃው ስር የቆመችውን ያረጀች ሠማያዊ ቮልስዋገን ጠቆሟቸው፡፡

ደርግ ይህን ያደረገው ከተማዋ ውጥረት ላይ ስለነበረች ትኩረት ላለመሳብ ሲል ብቻ ነው፡፡ ሆነ ብለው ክብራቸውን ለመንካት ነው እያሉ የፃፉ ፀሐፍት አሉ፡፡ ነገር ግን ደርጎች መፈንቅለ መንግስት እንደመሆኑ መጠን ንጉሡን በቁጥጥር ስር ማዋል ግዴታቸው የነበረ ዋና ነጥብ መሆኑ ግልፅ ነውና ሂደቱን እስከ እስር ቀጥለውበታል፡፡ በስተመጨረሻ ታመው ውጭ አገር ሂደው ካልታከሙ የሚል ነገር ሲነሳ ለደርግ አጣብቂኝ ሆኖ አፍነው እስኪገድሏቸው ድረስ የነበረው አያያዝና እንክብካቤ ጥሩ የነበረ መሆኑን ስናጤን፤ ገና ከወዲሁ የንጉሡን ክብር ዝቅ በማድረግና ስሜታቸውን በመጉዳት አረመኔነታቸውን ይፋ ለማድረግ አይሞክሩም፡፡ ጊዜው ካለፈ በኋላም ይህን ጉዳይ በተመለከተ የሁሉም አባላት ቃል መነሻ ምክንያቱ "ዓይን ውስጥ ላለመግባት" የሚል ነው፡፡ ያን በማድረግ የሚገኝ ፖለቲካዊ ትርፍም በወቅቱ አይኖርም፡፡

ጃንሆይ በእርጅና ምክንያት ይሁን፤ ሁኔታውን ቀድመው በማወቃቸው ይሁን ለመገመት በሚቸግር መልኩ ፍፁም መረጋጋት ይታይባቸው ነበር፡፡ አልገረማቸውም፤ አልተረበሹም፤ የደነገጠ ሰው የሚያሳየው የፊት ገፅታ አልታየባቸውም፤ እልህ፣ ቁጭት አብረዋቸው አልነበሩም፡፡ እነዚህን ስሜቶች ሆነ ብለው ደብቀዋቸው ከሆነ ከፍተኛ

ስሜትን የመደበቅና የማስመሰል ችሎታ አላቸው ከማለት በቀር ምንም ሊባል እንደማይችል ያልገለፀ የዓይን እማኝ ፈልገን አናገኝም፡፡



ጃንሆይ ከቤተመንግስታቸው ወጥተው ወደ 4ኛ ክ/ጦር ሲወሰዱ

በቀጥታ ተከፍታ ወደጠበቀቻቸው ቮልስ አመሩ፡፡ ሾፌሩ ዳንኤል አሰፋው ነው፡፡ አጠገቡ ፈርጣማ ወታደር ተቀምጧል፡፡ ጃንሆይ ከኋላ ተሳፈሩ፤ አሽከራቸው ወሰኔ ከጎናቸው ተቀመጠ፡፡ በዚያ ጊዜ በመንገድ ሲያልፉ መሬት ይስም የነበረው ህዝብ "ሌባ! ሌባ!" ይላቸው ነበር፡፡ "ህዝብ" ለማለት ባይቻልም ያልተለመደውን እንቅስቃሴ አይተው በቤተ-መንግስቱ አቅራቢያ ቆመው የነበሩ ሰዎች ቃሉን በጋራ ብለውታል፡፡ ጃንሆይ ለዚህ ቃል ጆሮ የሰጡት አይመስልም፡፡

መኪናዋ በፊት በር በኩል ነበርና የቆመችው፤ ጃንሆይን ይዛ በሒልተን ቁልቁለታማ ጎዳና ተፈትልካ 4ኛ ክፍለ ጦር ጊቢ አደረሰቻቸው፡፡ የደርግ አብዮት ተሳካ፡፡ የኢትዮጵያ አብዮት ፈነዳ፡፡ "አብዮት" የሚለው ቃልም ለኢትዮጵያውያን ዜጎች መጠሪያ ስም ሆኖ ከእነመንግስቱ ተርታ ተሰለፈ፡፡

በኢትዮጵያ ለ5,800 አመታት ያህል (የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ የሚለውን የዚህን መፃህፍ የመጀመሪያ ክፍል ልብ ይሏል) የዘለቀው ንጉሣዊ አገዛዝ ባየነው መልኩ አከተመ፡፡ ጃንሆይ የኢትዮጵያ 314ኛው ንጉሠነገስት ናቸው፡፡ ለረጅም ዓመታት በስልጣን ላይ በመቆየትም የሪከርድ ባለቤት ናቸው፡፡ የመጨረሻው ንጉሠነገስት በመሆንም በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ናቸው፡፡ ከኢትዮጵያዊ ንጉሠነገስቶች ውስጥም ብቸኛው የእድሜ ባለፀጋ ሆነው ረጅም እድሜ ምድር ላይ የኖሩት (83 ዓመት) ጃንሆይ ብቻ ናቸው፡፡


አስተዋዩ፣ ብልሁ፣ ስልጣኔ ናፋቂው፣ በበሰለ ንግግራቸው ነብይ የተሰኙት፣ የአፍሪካ አባት፣ የራስተፈሪያን አምላክ... ስልጡኑ የኢትዮጵያ መሪ ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለስላሴ.... በዚህ አይነት ከስልጣን ከወረዱና ከታገቱ በኋላ የእስር ጊዜያቸው ምን መስሎ ምን ያህል ቆዩ? እርጅናውስ እንዴት አደረጋቸው? አሟሟታቸውስ? የቀብር ስርዓቱስ?



የሚሉትን ነጥቦች በተከታዩ "ጃንሆይና ፍፃሜያቸው" በሚል ንዑስ ርዕስ ስር በአጭሩ አይተን እናልፋለን፡፡

*ጃንሆይና ፍፃሜያቸው*

ጃንሆይ ይሄ ሁሉ ሴራ ሲከናወንባቸው ደንዝዘው ያዩ የነበሩት ለምንድነው? የሚለው ጥያቄ ከብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ተሰንዝሯል፡፡ እንዲህ ያለ ጥያቄ ለማንሳት የተቻለውም እኒያ ጠላታቸውን ሁሉ በዘዴ ያንበረከኩ የነበሩት ብልሃተኛ ሰው ዛሬ ምን ነካቸውና እንቅስቃሴውን እያዩ ቻል አሉ? በሚል መነሻ ነው፡፡



ብርሃኑ ድንቄ እንዲህ ይላሉ "አፄ ኃይለስላሴ በሚያስደንቅ ችሎታ የውስጡንና የውጭውን የፖለቲካ ፉትቦል እንደተጫወቱ አያጠራጥርም፡፡ በዚህ የውስጥና የውጭ የፖለቲካ ኳስ ጨዋታ እርሳቸውን ያሸነፉ ተቃዋሚ ቡድኖች እነማን እንደሆኑ የሚጠይቀኝ ቢኖር ሁለት ብቻ እጠቅሳለሁ፤ 1ኛ. ወደፊት አርቆ የማስተዋል ስጦታ ጉድለት፣ 2ኛ. እርጅና" በማለት "አርቆ የማስተዋል ስጦታ ይጎድላቸዋል ስል አዋቂ አይደሉም ማለቴ አይደለም፡፡ ግን በተፈጥሮአቸው በእድል የሚያምኑ ስለሆኑ እለት በእለት ሊሰሩት የሚፈልጉትን ብቻ እየፈፀሙ የቀረውን ለእድል የተውት ይመስላል" ይሉናል፡፡ የፀሐፊው ድምዳሜ "ጃንሆይ ዛሬን በነገ ዓይን ማየት አልቻሉም" የሚል ነው፡፡ ጃንሆይ የፈለጉት ነገን በዛሬ ዓይን ማየት ነበርና፡፡

እንደተባለውም በተለይ በስተመጨረሻ ሁሉንም ነገር ለእድል ትተውት ነበር፡፡ ይህን ድምዳሜ የሚያጠናክር ሌላ ገለፃ እንይ፡፡ ፍቅረማርቆስ ደስታ "የበጋው መብረቅ" በሚል ርዕስ የጄኔራል ጃገማ ኪሎን የህይወት ታሪክ በፃፈበት መጽሐፍ ጄኔራሉ ጃንሆይ ያሏቸውን ለደራሲው ሲገልፁ፤ "... እግዜር የሰጠንን መንግስታችንን አንተም ብትጨመር የሚነቀንቅ የለም፤ እግዚአብሔር በቃ ካለ ደግሞ ማንም ቢረዳን መንግስታችን ሊቀጥል አይችልም" ብለዋቸዋል፡፡

ከዚህም በላይ በክቡር ዘበኛ አዛዡ በጄኔራል አበበ ተቀነባብሮ የነበረውን ደርግን የመበታተን ዘመቻ እንደ ነው ጃንሆይ "አንተ ሰው አርፈህ ተቀመጥ" ብለው ኣስተተዋቸዋል፡፡

ጃንሆይ የህዝብ አመፅ ከተነሳ በኋላ የሚወሰድ የኃይል እርምጃ መጨረሻው ታሪክን ማበላሸት መሆኑንም ያውቃሉ፡፡ ባለፈው ምዕራፍ አልጋወራሽ እያሉ በጃንሜዳ ለተሰበሰበው ህዝብ ጽፈው የላኩት መልዕክት ላይ ደጋግመው ሹሞቻቸውን ሲያስጠነቅቁ አንብበናል፡፡ "ለወደፊቱ ይህን የመሰለ የህዝብ መሰብሰብና በመንግስት ስራ መግባት የሚያስፈልግ አይደለም..." እያሉ የሩሲያን አብዮት ምሳሌ እየሰጡ ያስጠነቀቁትም ህዝብ ካመፀ መንግስት ዋጋ እንደሌለው ተረድተው ለማስረዳት የተጠቀሙት ምሳሌ ነበር፡፡ ከእነዚህ ነገሮችና ከወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር በመነሳት መንግስታቸው ማብቃቱን ስለተረዱት ቀሪውን ለእድል ብቻም ሳይሆን ለፈጣሪ ትተውታል ሊባል ይችላል፡፡ ምንም ቢሆን ግን ጃንሆይ በተፈጥሮ ባህሪያቸው ጠላታቸውን ካላንበረከኩ እንቅልፍ የማይተኙ ነበሩና አንድ ነገር ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቅ ነበር፡፡ ግን ምንም አላደረጉም፡፡ ለምን? አርጅተዋል ነው መልሱ፡፡

ጃንሆይ የቅርብ ሰዎችም እንደሚመሰክሩት በቀን 20 ሰዓት ያህል እየሰሩ የኖሩ ናቸው፡፡ እረፍትም ሆነ ከስልጣን ገለል ማለት አልፈለጉም፡፡

የጃንሆይ እርጅና ለውድቀታቸው እንደ አንድ ግብአት የሚቆጠር ነው፡፡ እሳቸው አርጅተው በወሣኝ ወሣኝ ጉዳዮች ላይ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ሲያቅታቸው በዙሪያቸው ያሉ ሹማምንት ሊያግዟቸው ይገባ የነበረ ቢሆንም፣ በጣት ከሚቆጠሩት በቀር ሌሎች ንቅዝ ስለነበሩ እንኳን የዙፋኑ ጠበቃ ሊሆኑ ለራሳቸው ህልውና እንኳ ጥብቅና የሚቆሙበት ደረጃ ላይ አይገኙም፡፡ ይህም ስለሆነ ሹማምንቱ "ከሸተቱ አይቀር ጥንብት ክርፍት" በሚል መርህ ንቅዘታቸውን አፋጥነው ቀጥለው የግል ሐብት ሲያጋብሱ በእሳት ላይ ቤንዚን እንደሚባለው አደረጉት፡፡ ጃንሆይ ብቻቸውን ነበሩ፡፡ በዚህም ላይ በእርጅና ምክንያት ፈዘዋል፡፡ ያለማንገራገር ታሰረዋል፡፡

የጃንሆይን እርጅና በሚመለከት ከዶ/ር ኃይለገብርኤል ደሣለኝ አንድ ገጠመኝ እንስማ፡፡ በመውደቂያቸው የመጨረሻ ወራት ላይ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሚካኤል እምሩ አዲሱን ተሿሚ መርጠው በጃንሆይ ለማሾም ወደቤተመንግስት ያመራሉ፡፡ ለትምህርት ሚኒስትርነት የተመረጡትን ዶ/ር ኃይለገብርኤልን ይዘው ጃንሆይ ፊት በመቅረብ "ጃንሆይ አዲሱ የትምህርት ሚኒስትር እነሆ" ሲሉ ጃንሆይ እንደመባነንም እንደመደንገጥም ብለው አንድ ጥያቄ ሠነዘሩ፡፡ "ትምህርት ምንድነው?" ተሿሚው ያልጠበቁት ጥያቄ ቢሆንም አንዳንድ ገለፃዎችን ስለ ትምህርት



ማድረግ ሲጀምሩ፣ ጃንሆይ "አይደለም!" ብለው አቋረጧቸው፣ ቀጠሉና "ትምህርት ማለት ምን ማለት ነው?" ካሉ በኋላ ራሳቸው ንጉሡ መልስ መስጠት ጀመሩ፡፡ ከንግግራቸው ውስጥ ግን አንዱም ቃል ከትምህርት ጋር የማይገናኝና ቅብጥርጥር ያለ የቅዥት ገለፃ ነበር፡፡ "ይህ አንድ ነገር አስረዳኝ" ይላሉ ምሁሩ ተሿሚ ዶ/ር ኃይለገብርኤል "ለካንስ ንጉሡ በእርጅና ምክንያት በትክክል ማሰብ አቅቷቸው ነበር" በማለት የተሰማቸውን ሐዘን እያስታወሱ ተርከዋል፡፡ (አዲስ ነገር 2001 ዓ.ም) ትምህርት ጥንቃቄ ያስፈልገዋል ብለው ለረጅም ዓመት የትምህርት ሚኒስትርን ስልጣን ራሳቸው ነበር የያዙት፡፡ በመጨረሻ ግን የቃሉ ትርጉም ሳይቀር ጠፋባቸው፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ የመርሳትና የመሳት ባህሪ በተደጋጋሚ ማሳየት የጀመሩት ገና ከስልጣን ሳይወርዱ ጀምሮ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ያለ ንጉስ ዘዴው ቢጠፋበት አይገርምም፡፡

ጃንሆይ ከቤተ-መንግስት ተወስደው 4ኛ ክፍለ ጦር ጊቢ በቁም እስር ላይ ቆይተው፣ እንደገና ደግሞ ወደቤተ-መንግስቱ ጊቢ ተመልሰው በአንድ መካከለኛ ቤት ገብተው እንዲኖሩ(እንዲታሰሩ) ከተደረገ በኋላ ፍፃሜያቸውም እዚያው ሆኗል፡፡

በቁም እስር ላይ በነበሩበት ጊዜም ምግብ ከቤተ-መንግስት እየሄደላቸው፣ አሽከሮቻቸው በስርዓቱ እያገለገሏቸው፣ ዘመዶቻቸው እየጠየቋቸው በክብር እንዲያዙ መደረጉን የደርግ አባላቱ መንግስቱን ጨምሮ ይገልፃሉ፡፡ እንዲያውም ልዕልት ተናኘወርቅ ከእኛ ጋር ትቀመጥ ስላሉ ደርግ ፈቅዶ አብረዋቸው እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

ደርግ ከ4ኛ ክፍለ ጦር ለቆ ወደ ታላቁ ቤተ-መንግስት በማምራት ቢሮውን የጃንሆይ ጽ/ቤት የነበረውን አድርጓል፡፡ በጊቢው ውስጥ አፄ ምኒልክ አሠርተው ይኖሩበት በነበረው አሮጌ የእንጨት ፎቅ ስር አንድ መለስተኛ ቪላ ነበርና ያ የጃንሆይ መኖሪያ እንዲሆን ተደረገ፡፡ በጊቢው ውስጥ አበቦችና አትክልቶች የሚገኙ ሲሆን፣ ለጃንሆይ የሚከፋ አልነበረም፡፡ አጥሩንም ሰፋ አድርገው ሠርተው እንዳይወጡ በጥብቅ ማስጠበቅ ጀምረዋል፡፡ ከደርግ አባላት ውስጥም ከ3 የማይበልጡ ሰዎች ብቻ እየሄዱ ያነጋግሯቸው ነበር፡፡ ዋናው ሻለቃ መንግስቱ ናቸው፡፡

ጃንሆይ አንዳንድ ጊዜ እንደመቃዠት ያድርጋቸው እንጂ፣ ብዙ ጊዜ በትክክል ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡ መንግስቱ ኃይለማርያም ትዝታቸውን ሲገልፁ፣ "ከስልጣን ከመውረዳቸው በፊትና በኋላ በጠቅላላው ያነጋገርኳቸው ሦስቴ ወይም አራቴ ቢሆን ነው፡፡ ብቻዬን ሳይሆን ከኮሎኔል አጥናፉ ጋር (ያኔ ሻለቃ) እንዲሁም ከሌሎች ጥቂት የደርግ አባሎች ጋር፡፡ በመጀመሪያ የሄድነው አራተኛ ክፍለ ጦር እንደደረሱ ከሌሎች ጓዶቻችን ጋር ሆነን ነው፡፡ እኔ ቀርቤ በአክብሮት አነጋገርኳቸው፡፡ "ግርማዊ ሆይ፣ እዚህ እንድትሆኑ ያደረግነው አሁን

ባለው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታና ችግር ምክንያት ለዕርስዎ ደህንነት ጥበቃ ሲባል ነው፡፡ እና መቼም እንደ ኢዮቤልዩ ቤተመንግስት ባይሆንም የሚያስፈልግዎ ነገር እንደማይጎድልብዎ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በጎደለ ነገር ይጠይቁ" ብያቸው አስገብተናቸው ነው የወጣነው፡፡"

መንግስቱ ጃንሆይ የሚያስቡት ኢትዮጵያን ከፍተኛ ቦታ ላይ አድርሻታለሁ ብለው ነው በሚል መነሻ "እሳቸው የነበሩበትን ስርዓት ለማስታወስ ጉልታዊው ስርዓት ብዬ ስናገር፤ ጉልታዊ ስርዓት አትበል! ጉልታዊውን ስርዓት ከደመሰስነው ጊዜ የለውም" ማለታቸውን ያስታውሳሉ፡፡ ጃንሆይ ከህዝብ ርቀው በመኖራቸው ምክንያት ሰው ስለሳቸው ያለውን አስተያየትና ግምት አያውቁም ማለት ይቻላል የሚሉት መንግስቱ "አንዳንድ ነገር ሲነገራቸው እንዴት ሆኖ? ከየት ነው እንዲህ ያለውን ፈጥራችሁ የምታወሩት? ነበር የሚሉት" በማለት "ስለህዝቡ የኑሮ ደረጃ ስለችግሩ እንኳን ሲነገራቸው "ኢትዮጵያን የት ታውቋትና? ነበር የሚሉን" ሲሉ ያክሉበታል፡፡
" ስለ ለውጥ ስናነሳባቸው "እናንተ ይሄን ውጭ ሄዳችሁ የቀላወጣችሁትን ነገር አምጥታችሁ ነው እዚህ የምትናገሩት፡፡ ይሄንን ህዝብ አለማወቅና አለመረዳት ነው" አሉን፡፡"

ገነት አየለ ትጠይቃለች "ማን መሆንዎን አውቀዋል?"

መንግስቱ "በእሳቸው ግምት አብዮቱን የቀሰቀሱትና አገሪቱን በመምራት ላይ ያሉት ጄኔራል አማን ናቸው፡፡ "ጀኒናር አማን የታለ? መጥቶ ያነጋግረኝ" ነው የሚሉት እንጂ ሻለቃ መንግስቱ ብለው አያውቁም፡፡ እኛም ጄኔራል አማንን ሲሉ፤ ጄኔራል አማንን እናቀርብላቸው ነበር፡፡ ልዕልት እከሌን ሲሉም ይምጡላቸው ነበር የምንለው እንጂ ከልክለን አናውቅም" (ትዘታዎች ቁጥር 1 ገፅ 130)

ጃንሆይ እስር ላይ ሆነው ከአንበሶቻቸው ናፍቆት በስተቀር በሠላም ኑሮአቸውን እየገፉ የነበረ ቢሆንም፤ ድብርቱን አልቻሉትም፡፡ ለዚህ መፍትሄ ይሆን ዘንድም ከጠባቂዎቻቸው ጋር አንዳንድ ቀልዳቀልዶችን በጥያቄና መልስ ዓይነት መወያየት የጀመሩ ይመስላል፡፡ አንድ ቀን ከጠባቂዎቻቸው ውስጥ አንዱ የሆነውን ወታደር "እስቲ ጠመንጃህን ልየው" ይሉታል፡፡ ወታደሩም በአክብሮት ይሰጣቸዋል፡፡ ጃንሆይ በሣቅ ተፍለቀለቁና "አይ ሞኞ፤ ጠባቂያችን ሆነህ እንዴት መሣሪያህን ትሰጠናለህ?" ብለው በፈገግታ ይመልሱለታል፡፡ እነዚህን የመሰሉ ንግግሮች የሚያደርጉት በጊቢያቸው ውስጥ ይንሸራሸሩ በነበረበት ጊዜ መሆኑን መንግስቱ ያስታውሣሉ፡፡

ጃንሆይ እንዲህ ያለ ጭውውት ሲያደርጉ ይቆዩና ወዲያው ደግሞ የመሳት ሁኔታ ያንፀባርቃሉ፡፡እነመንግስቱ ሊያነጋግሯቸው ሲሄዱ፤ "እናንተዬ፤ደጎል ደህና ነው?" ብለው ይጠይቋቸዋል፡፡ቻርለስ ደጎል እ.ኤ.አ



በ1970 ዓ.ም ሲሞት ጃንሆይ ለፈረንሣይ ህዝብ የሐዘን መግለጫ ልከዋል፡፡ይወዱት ስለነበርም በጣም አዝነዋል፡፡ያ ከሆነ ከ4 ዓመት በኋላ ደህና ነው?ብለው መጠየቃቸውና ሌሎች ተመሣሣይ ተደጋጋሚ የመሣት ባህሪያቸው እየባሰ ሲቀጥልም ነው ጤናቸው አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን በቀላሉ ደርጎች መረዳት የቻሉት፡፡

ደርግ አንድ ራሱን የቻለ "የእስር ቤት ጥበቃ ኮሚቴ" አቋቁሟል፤ የሁሉም የጥበቃዎች የበላይ ኃላፊ ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው ነበር፡፡ ሐኪማቸው ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ነበሩ፡፡ ፕሮፌሰሩ ጃንሆይን እየሄዱ ያዩዋቸው ነበር፡፡ የጥበቃ ኮሚቴውም የጤንነታቸውን ሁኔታ ለደርግ በየጊዜው ሪፖርት ያደርጋል፡፡

ከጊዜ በኋላ ህመማቸው እየከፋ ሄደ፡፡ ፊኛቸውን እንደታመሙ ተገለፀ፡፡ ፕሮፌሰር አስራት የጃንሆይ በሽታ አሳሳቢ ስለሆነ፤ "ውጭ አገር ሄደው መታከም አለባቸው" አሉ፡፡ ይህን ሀሳብ ደርግ ተወያየበት፡፡ የማይሞከር ነበር፡፡ ኩዴታ የተከናወነበትን ንጉሠነገስት፣ በቁጥጥር ስር የዋለ መሪ ውጭ ልኮ ማሳከም ምን ያህል ፈተና መሆኑ ለማንም ግልፅ ነው፡፡ ይህንን ለሐኪማቸው አስረዱና፤ "ነገር ግን እዚሁ እንዲታከሙ የሚያስፈልገውን ወጪ፣ የሚያስፈልገውን ትብብር እናድርግ" አሉ መንግስቱ፡፡

ፕሮፌሰር አስራት "የማይቻል ከሆነ ምን ይደረጋል? እዚሁ ህክምናውን እንሞክራለን፡፡ ለህክምና የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችንና አጠቃላይ ሁኔታውን አጥንቼ ልምጣ" በማለት ሄዱ፡፡ ተመልሰውም "የህክምና እቃው ተሟልቶ የሚገኘው ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ነውና እዚያ እንዲታከሙ ይፈቀድልን" አሉ፡፡ አሁንም ሻለቃ መንግስቱ እዚያ ይሂዱ ቢባል የሚፈጠር ግርግር ይኖራል በማል ስጋት "እቃው እዚህ ቢመጣስ?" አሉ፡፡ "መብራት የጠፋ እንደሆንስ?" "ጄኔሬተር መትከል አይቻልም?" "አይሆንም፤ አደገኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ሆስፒታል ካልመጡ አስቸጋሪ ነው"
አሁንም ጉዳዩ ለደርግ ቀርቦ "ሆስፒታል የግድ መግባት ካለባቸው ክቡር ዘበኛ ሆስፒታል ይግቡ" ተብሎ ተወሠነ፡፡እዚያ ገብተው ቀዶ ጥገና ተደርጎላቸው በጥቂቱ አገግመው ደህና ሆነው ተመለሱ፡፡ደርግ የንጉሡ ጤና ዘላቂ እንዳልሆነ ያውቃል፡፡ያቺ ውጭ አገር ሄደው የመታከማቸው ጉዳይ ከተነሳች በኋላ ደርግ (መንግስቱ) ጃንሆይን በሚመለከት ከነበራቸው የተለየ አቋም ለመውሰድ ተገደዱ፡፡በአንድ በኩል "ውጭ አገር ሄደው ታክመው መዳን እየቻሉ አስረው ይዘው ለሞት አበቋቸው" እንዲባሉ አልፈለጉም፡፡ በሌላ በኩል እዚያ ካልሄዱ ሙሉ በሙሉ ጤናቸው እንደማይመለስ አውቀዋል፡፡ስለዚህ በአገር ውስጡ ህክምና ለጊዜውም ቢሆን ስለተሻላቸው ደርግ "የንጉሡ ጤንነት በተደረገላቸው ህክምና

ምክንያት ተመልሷል፣ ደህንነታቸውም የተጠበቀ ሆኗል" ብሎ ከገለፀ በኋላ ጥረቱንና ለንጉሡ ጤንነትም እንደሚጨነቅ ካሳዬ፣ካስገነዘበ በኋላ፤ደግሞ ሳያገረሽና ሊላ አጣብቂኝ ሳይፈጠር በዚህች ክፍተት ውስጥ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ነበረበት፡፡ እስከዚህች አጣብቂኝ ወቅት ድረስ ግን ደርግ ጃንሆይን በአክብሮት ይዟቸው መቆየቱ ግልፅ ነው፡፡

የጃንሆይን አሟሟት በሚመለከት ብዙ ጊዜ "ይባላል፣ ይባላል" የሚሉ ገለፃዎች አሉ፤ በዚህ መጽሐፍ ከ"ይባላል" ለመውጣትና ወደ አንድ ድምዳሜ አንባቢውን ለማድረስ ይሞከራል፡፡

መንግስቱ ኃይለማርያም የጃንሆይን አሟሟት በሚመለከት ለገነት አየለ የሰጡት ቃል ፍጥጥ ያለ ሐሰት ነው፡፡ "... በጥሩ ሁኔታ ታክመው ከዳኑ በኋላ ጥቂት ሳምንታት ቆይተው ሞቱ! ብሎ ዳንኤል ሲነግረኝ ምክንያቱ ሊገባኝ አልቻለም፡፡ እንዴት ሊሆን ቻለ? እንዴት ተሽሏቸው ደህና የነበሩ ሰውዬ በድንገት ሞቱ ትላላችሁ? በማለት ዳንኤልን አፋጥጬ ያዝኩት፡፡..." እያሉ ወሽክተዋል፡፡

ለጣሊያናዊው ጋዜጠኛ ለሪካርዶ ኦሪዚዮ የሰጡት ቃል ግን የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ ሪካርዶ ኦሪዚዮ እ.ኤ.አ በ2003 ዓ.ም ከ8 ወራት መጉላላት በኋላ መንግስቱን ቃለ-ምልልስ ለማድረግ ያቀረበው ጥያቄ ምላሽ አግኝቶ ዙምባቡዌ ሄዶ ቤታቸው ውስጥ ጠይቋቸዋል፡፡የእርሳቸውንና የሌሎችን አምባገነን የቀድሞ መሪዎች ቃለ-ምልልስ አድርጎ የሁሉንም ታሪክ /ኑዛዜ/ አሰባስቦ መጽሐፍ ጽፏል፡፡ ወደ እንግሊዝኛው ተተርጉሞ በዓለም ላይ ተቸብችቧል፡፡ "TALK OF THE DEVIL" የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን፤ "የሠይጣን ኑዛዜ" በሚል ርዕስም በአጥናፉ ሠገድ ኪዳኔ በአማርኛ ተተርጉሞ በእኛ አቆጣጠር በ1996 ዓ.ም ለሕትመት በቅቷል፡፡

ምናልባት መንግስቱ ለገነት አየለ መልስ ሲሰጡ በአማርኛ መዋሸት ቀሏቸው፣ ለሪካርዶ መልስ ሲሰጡ በእንግሊዝኛ መዋሸት ከብዷቸው ይሆናል፡፡ወይም ለአውሮፓውያኑ መዋሸቱ ትርፍ አልባ፣ ለኢትዮጵያውያኑ ትርፍ ያለው ሆኖባቸውም ሊሆን ይችላል፡፡ እሱን እናቆየውና ግን ከገነት አየለ መጽሐፍ ውስጥ ከአልባሾቻቸው አንዱ የተናገረውን እናስቀድም፡፡

"ትዝ እንደሚለኝ ነሐሴ 20 ቀን 1967 ሌላ ጊዜ ተራዬ ሲሆን እንደማደርገው ከንጉሡ መኖሪያ ለማደር ስሄድ ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው ለዛን ዕለት ማደሬ እንደማያስፈልግ ነገሩኝ፡፡ ይህንኑ ለጃንሆይ ለመንገር ጠይቄ ተፈቀደልኝና የታዘዝኩትን ልነግራቸው ገባሁ፡፡

ጊዜው ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ይሆናል፡፡ ወደጌቶቼ ቀርቤ የተባለውን ስነግራቸው ከአልጋቸው ላይ ተነሱና "ቤቱ ጠቧቸው ነው? እንግዲህ ... ውጣላቸው፡፡ ሰፋ አድርገን እንሰራላቸዋለን" ብለው በርከክ አሉና እንባቸውን ከዓይናቸው ላይ እየጠረጉ፤ "አይ አንቺ ኢትዮጵያ!



እውነት በድለንሻል?! እውነት አልደከምንልሽም? ብለው እንባቸውን ፈነጠቁ፡፡ እኔም ሳልወድ በግድ ሌላ አማራጭ ስላልነበረኝ ጌታዬን ጥዬ ወደ ቤቴ ሄድኩኝ፡፡ የማያቸው ለመጨረሻ ጊዜ መሆኑን ግን አልጠረጠርኩም ነበር፡፡ ንጉሡ ሞተው የተገኙ ዕለት የመኝታ ክፍላቸው የመድሐኒት ጠረን ይሸት ነበር፡፡ በንጉሡም አንገት አካባቢ ለቁስል ማሰሪያ የሚያገለግል ፋሻ ተቀምጦ አይቻለሁ" (ቁ1 ገፅ 28)

ቀደም ሲል ያሻው ሰው እየሄደ እንዲጠይቃቸው የተፈቀደላቸው ንጉስ ዛሬ አንድ አገልጋይ ተነፈጋቸው ማለት ነው፡፡ እናም አዘኑ፡፡

ሌላው ከ12 ዓመታት በላይ በዘመነ ኢህአዴግ ታስረው፤ እዚያው ወህኒ እያሉ የደርግን ባለሥልጣናት ሁሉ ያነጋገሩትና ከተፈቱ በኋላ "ምስክርነት" በሚል ርዕስ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ ለሕትመት ያበቁት መጽሐፍ ውስጥ የተካተተው እውነታ ሲሆን፤ የመንግስቱ ኃይለማርያም ጠባቂ የነበረው ልዩ ጦር አዛዥ የነበሩት መቶ አለቃ ወንድሙ አበበ የሰጡት ምስክርነት ነው፡፡ "ንጉሡ የተገደሉት በነሐሴ 20 ቀን 1967 ሲሆን ግብዓተ መሬት የተፈፀመው በተከታዩ ቀን ነሀሴ 21 ነበር፡፡ ግድያው የተፈፀመው ከደብረብርሃን በመጣው ልዩ ጦር አማካኝነት በሻለቃ ዳንኤል አስፋው ነው፡፡ ንጉሡ የተገደሉት ሰመመን ሰጪ መድሐኒት በአፍንጫቸው እንዲያሸቱ ከተደረገ በኋላ በተንተራሱት ትራስ በማፈን ነበር፡፡ እንዲያፍን የተላከው ወታደር ህሊናው እንቢ ብሎት እየተርበተበተ በመቸገሩ ራሱ ዳንኤል አስፋው አፈናውን ፈጽሞታል" በማለት ገልፀዋል፡፡(ገፅ70)

ቀጥለን "የሠይጣን ኑዛዜ" በተሰኘው መጽሐፍ የተካተተውን ገለፃ እናስከትል፡፡ ሪካርዶ ኦሪዚዮ ይህን ጥያቄ ሲያነሳ መንግስቱ ለማስተባበል በሞከሩበት ገለፃ ውስጥ እውነታውን ሲፈነጥቁና ያየናቸውን ሁለት ገለፃዎች ሲያጠናክሩ እናያለን፡፡

"... "አስፈላጊ አልነበረም" አሉ በዛለ ስሜት፡፡ በመቀጠልም "ኃይለስላሴ ሽማግሌ፣ በሽተኛና ከሁሉም በላይ ደግሞ በሁሉም ዘንድ የተጠሉ ነበሩ፡፡ ባለፉት ዘመናት ተራማጅና የዘመናዊ አስተሳሰብ ባለቤት የነበሩ ቢሆንም፤ ህዝቡ እንድናወርዳቸው አጥብቆ በመጠየቁ እኔና ባልደረቦቼ አወረድናቸው፡፡ ልናድናቸው አልቻልንም፡፡"

ታዲያ እንዴት ሞቱ? ለሚለው ጥያቄ መንግስቱ መልስ ለመስጠት ከነበራቸው አብዮታዊ ራዕይ አኳያ ሲታይ፤ እንዲህ ላለው ዝርዝር ጉዳይ ቦታ ሊሰጡት እንደማይችሉ በሚጠቁም ሁኔታ ትከሻቸውን ከፍ ዝቅ ካደረጉ በኋላ ጥያቄውን በማናናቅ "እኔ እስከማውቀው ድረስ አሟሟታቸው ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ በእርግጥ ከባልደረቦቼ መካከል በንጉሡ የተገደሉባቸውን የአባቶቻቸውንና የወንድሞቻቸውን ደም ለመበቀል በባዶ እጃቸው ሳይቀር አንቀው ለመግደል የሚፈልጉ አልነበሩም ብዬ ለመካድ

ግን አይቃጣኝም፡፡ ህክምና ያደርግላቸው የነበረው ዶክተር የጤንነታቸው ሁኔታ እስጊ ደረጃ ላይ መድረሱንም አልነገረኝም፡፡ ስለዚህ ምን እንደተከሰተ በግሌ ለማረጋገጥ አልቻልኩም" አሉ (ገፅ 224)

ይህ ገለፃ የማያሻማ ትርጉም እንዳለው ግልፅ ነው፡፡ መንግስቱ ለጋዜጠኛ ገነት አየለ የሰጡትን "በጭራሽ! በጭራሽ! እኔ አላውቅም!" የሚል ይዘት ያለውን ቃል ስናይ ደግሞ የበለጠ ግልፅ ይሆንልናል፡፡

ምናልባት ጋዜጠኛ ሪካርዶ ኦሪዚዮ ካየነው ምላሽ በኋላ አንድ ተከታይ ጥያቄ መጠየቅ የነበረበት ይመስላል፡፡ "ከባልደረቦቼ መካከል በንጉሡ አባቶቻቸውና ወንድሞቻቸው የተገደሉባቸውን ደም ለመበቀል ሲሉ..." የሚለውን ገለፃ አንስቶ "ለምሳሌ ማን?" ብሎ አልጠየቀም እንጂ ቢጠይቅ መንግስቱ ምን ይመልሱ ነበር? ከደርግ አባላት ውስጥ በጃንሆይ ዘመዱ የተገደለበት አባል ማነው? ቢባሉ መልስ አይኖራቸውም፡፡ በጃንሆይ ጊዜ በተማሪዎች ላይ በፀጥታ ጠባቂዎች አማካኝነት ከተወሰደው እርምጃ በተጨማሪ፣ ሁለት ሰዎች ብቻ በፍርድ ችሎት ተገድለዋል፡፡ በላይ ዘለቀና ጄኔራል መንግስቱ ነዋይ በቃ፡፡ ከዚህም ባለፈ በይባላል ሲወራ እንኳ ገዳዮች ተብለው የሚጠቀሱት ዳንኤልና መንግስቱ እንጂ ሌላ አባል ወደ ጃንሆይ ድርሽ አይል እንደነበር ራሳቸው መንግስቱ ደጋግመው ገልፀዋል፡፡

እናም ጃንሆይ ነሐሴ 20 ቀን 1967 ዓ.ም የጥበቃ ኮሚቴው አሽከሮቻቸውንም ወደቤታቸው ሸኝቶ ብቻቸውን ካስቀረ በኋላ ምሽት ላይ በትራስ አፍኖ የጥበቃው አዛዥ ከጨረሳቸው በኋላ የመሞታቸውን ሪፖርት ለደርጉ አቀረበ፡፡

ጃንሆይ 11 ወራት ተኩል በቁም እስር ካሳለፉ በኋላ በ83 ዓመታቸው ህይወታቸው አለፈ፡፡ ደርግም እፎይ አለ፡፡ ት...ዝ ሲላቸው መሞታቸው ብቻ እፎይ አያስብልም፡፡ ገና የቀብራቸው ጉዳይ ደርጎችን ሌላ ውጥረት ውስጥ ይከታልና፡፡

የጃንሆይ ማረፍ እንደተገለፀ፣ የወቅቱ ፓትሪያሪክና ሌሎች ሁለት ጳጳሳት ወደ መንግስቱ ቢሮ መጥተው "ንጉሡ ካረፉ ስላሴ ቤተ-ክርስቲያን እንዲያርፉና አስፈላጊውን ፀሎተ ፍትሐት እንድናደርግላቸው ይፈቀድልን" አሉ፡፡ መንግስቱ ከባድ ጥያቄ እንደሆነ ያውቁታል፡፡ "አባላቱን አነጋግሬ የሚሉትን እነግራችኋለሁ" ብለው መለሱ፡፡

"በደርጉ ስብሰባ ላይ ይሄ ነገር ቢነሳ አቧራው እንደሚጨስ አውቃለሁ" በማለት የዚያን ጊዜውን ሁኔታ የሚተርኩት መንግስቱ፣ ጉዳዩ ስብሰባ ላይ ሲቀርብ ከአባላቱ የተሰነዘሩትን ልዩ ልዩ ሀሳቦችንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡ አንዱ "ንጉሡን እንደልዩ ፍጡር ከማየት እምነት አልወጣችሁም እንዴ? ሲል ሌላው እሳቸውን ማየት ያለብን እንደተራ ሰው ነው! በየቀኑ ስንቱ ወታደር ይሞት የለ እንዴ? ይላል፡፡ በ83 ዓመት መሞት እድለኝነት ነው ያለም አለ፡፡ ... አንዱ ተነስቶ እንዲህ አለ አሉ፣



"ለመሆኑ ለምንድነው ስላሴ የሚቀበሩት? እሳቸው'ኮ አርበኛ አይደሉም፣ ስላሴ የሚቀበሩት አርበኞች ብቻ ናቸው" (ምናልባት ጃንሆይ በማይጨው ጦርነት የጠላትን አየር ለመጣል አርሊኮን ተኳሽ ሆነው መዋጋታቸውን አያውቅ ይሆናል፡፡ )ብቻ ብዙ ሀሳቦች ተነስተው ተጥለው ንጉሡን በኤፌሴላዊ መንገድ መቅበር ለፖለቲካቸው ስጋት መሆኑን ደምድመዋል፡፡

መንግስቱ በትዝታቸው እንዲህ ይላሉ "አይ እንግዲህ ... አልኩና ፓትሪያሪኩን፣ ይቅርታ ያድርጉልኝ፣ ነገሩ እናንተ እንደምታስቡት አልሆነም፡፡ መልኩን ለውጦ እንዲያውም ሌላ ነገር ነው ያስከተለው፡፡ ንጉሡ አርበኛ አይደሉም፣ እዚያ አያርፉም፡፡ ፍትሐት ስላሉት ደግሞ ጳጳሱስ ቢሆኑ ስንቱ ወታደር በየቀኑ ሲረግፍ ምነው ለእነሱ ፍትሐት ለማድረግ አልጠየቁም? የሚል ነገር ሁሉ ተነስቷል፡፡ ከእርስዎ የምደብቀው ነገር የለም፡፡ ያለው ስሜት ፍፁም እንደምታስቡት አይደለም፡፡ አንድ የፖለቲካ ችግር የሚያስከትል ስለሆነ ይቅርታ አድርጉልኝ፣ ምንም ማድረግ አልችልም አልኳቸውና ተሰናብተው ሄዱ፡፡"

የት ይረፉ ሆነ ጥያቄው ብለው መንግስቱ ገለፃቸውን ይቀጥላሉ፣ "ባዕታ ተባለ፡፡ ባዕታ ገብተው ሲያበቁ ምንም አይነት ክበር፣ ጡሩንባና ጋጋታ ሳይኖር ይረፉ ተባለ፡፡ ይሄንኑ ትዕዛዝ ለእስር ቤቱ ኮሚቴ አስተላለፍኩ፡፡ በዚሁ አከተመ" ብለው ሲያቆሙ ጋዜጠኛ ገነት አየለ "ታዲያ ትዕዛዙ መፈፀሙን አረጋግጠዋል?" ስትል ትጠይቃለች፡፡ መንግስቱ "አይ ትዕዛዜ ፍንክች የማይል ነገር ነው፡፡ ይፈፀማል፡፡ አይፈፀምም ብዬ ጥርጣሬ የለኝም፡፡ ሰውየው አርፈዋል፡፡ መሠረታዊው የቄሶች ጥያቄ መልስ አግኝቷል፡፡ እኔ በጣም የሚያጣድፍና ጊዜ የማይሰጥ ስራ አለብኝ፡፡ ችግር አለ፡፡ ወደዚያ ዞሬያለሁ" ብለው ነው ያስተባበሉት፡፡ ገነት እስከመጨረሻው ብትሞግታቸውም በዚሁ አቋም ድርቅ እንዳሉ ነው የቀጠሉት፡፡

በእርግጥ ግን መንግስቱ ምንም አጣዳፊ ስራ ቢኖርባቸው የዚህን ጉዳይ አፈፃፀም በዓይናቸው ብሌን አይተው ሳያረጋግጡና አፈፃፀሙንም መጨረሻው ድረስ ሳያስጉዙ "ትዕዛዜ መፈፀሙ ስለማይቀር..." ብለው የሚተውት ጉዳይ ነው? "አዝዣለሁ፣ ባዘዝኩት መሠረትም ተፈፅሟል" ብለው አፈፃፀሙን ሳያዩ ፊታቸውን ወደሌላ ስራ ያዞራሉ ብሎ ማሰብ ትልቅ የዋህነት መሆኑን መግለፅ ሳያስፈልግ ማንም በቀላሉ የሚረዳው ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር ነው ተከታዩ የቀብር ስርዓት እውነትነቱ ታምኖበት የተደመደመውና የመንግስቱ ገለፃ ቶርሽ መሆኑ የታወቀው፡፡

ቀደም ሲል ያሟሟታቸውን ሁኔታ የገለፁት የቤተ-መንግስቱ የልዩ ጦር አዛዥ መቶ አለቃ ወንድሙ አበበ ለ"ምስክርነት" መጽሐፍ ፀሐፊ ከተገደሉ በኋላ ስለተከተለው ነገር ሲያብራሩ፣ "በዚያን ወቅት ቤተ-

መንግስቱ ጊቢ ውስጥ የተቀራረቡ፣ ግን የተለያዩ ጥልቅ ጉድጓዶች ጠሩ መቆፈሩን አስታውሳለሁ፡፡ ምሽግ ለማድረግ እንዳይባል አጭር ነው፣ የውሃ ማጠራቀሚያ እንዳይባል ደግሞ ሞላላ ነው፡፡ ጥልቅ የሆኑ አራት ወይም አምስት ጉድጓዶች ተቆፍረው ውለው ሳያድሩ ደግሞ በስሚንቶ ተለስነው ተዘጉ፡፡ በማለት የጉድጓዶቹን አቆፋፈርና መዘጋት ይገልፃሉ፡፡ ከላይ የተገለፀውን ሀሳብ ሻምበል መንግስቱ ገመቹ እውነት መሆኑን አረጋግጠዋል" (ሻምበል መንግስቱ ገመቹ ከፍተኛ የደርግ ባለሥልጣንና የመንግስቱ ቁጥር አንድ ታማኝ መሆናቸው ይታወቃል)

ፀሐፊው ሲቀጥሉም፣ በተለይ የታላቁ ቤተ-መንግስት የጥገና ክፍል ኃላፊ ነበርኩ፣ ጉድጓዶችንም ያስቆፈርኩ እኔ ነኝ የሚሉት መሐንዲስ ጥላሁን ኪዳኔ፣ "ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ እንደሞቱ አውቃለሁ፡፡ የሞቱት ነሐሴ 20 ቀን 1967 ዓ.ም ነበር፡፡ በነሐሴ 21 ቀን ከጠዋቱ 2:30 ሰዓት በመርዕድ ንጉሴ ተጠርቸ የከፌን ጨርቅና የሬሣ ሳጥን እንዳቀርብ ተጠይቄ... ሰጥቻለሁ፡፡ በ7 ሠዓት ላይ ሦስት ጉድጓዶች 3 በ 3 ሜትር አስቆፈርኩ፡፡ አራተኛ ጉድጓድም ተቆፍሯል፡፡ ቦታው በኋላ የፕሬዝዳንቱ ቢሮ ተሰራበት፡፡ አራት ጉድጓድ መቆፈሩ እኛ እንዳናውቅ መሰለኝ፡፡ ጉድጓዶቹን በዳንኤል አስፋው ትዕዛዝ በኮንክሪት ዘጋኋቸው፣ በአጭር ጊዜም በጉድጓዶቹ ላይ ቤት ተሰራ፡፡

ኢህአዴግ ሲገባ ኮሎኔል ስለሺ መኩሪያ ቦታውን ካሳዩ በኋላ ስምንት ሜትር ተቆፍሮ 3 በ 3 ሜትር ቱቦ ተገኘ፣ በኮሎኔሉ መሪነት እንደገና ወደ ውስጥ 3 ሜትር ሲቆፈር የንጉሡ አፅም ተገኘና በሙሉ ወጣ፡፡ በማለት ሰኔ 4 ቀን 1988 ዓ.ም ለዋለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንደኛ ወንጀል ችሎት ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ (የምስክሩን ቃል ያገኘሁት ሻለቃ መላኩ ተፈራ ከማስታወሻ ደብተራቸው ዓለም በቃኝ ውስጥ ጽፈው ሰጥተውኝ ነው)" ይላሉ ፀሐፊው፡፡ (ምስክርነት ገፅ 71)

ከመንግስቱ ቢሮ አጥንት ተቆፍሮ ሲወጣ በቴሌቪዥን የታየ ቢሆንም፣ ባዕታ ነው የተቀበሩት የሚሉት መንግስቱ፣ ይሄ ተራ የኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ ነው ባይ ናቸው፡፡ የጃንሆይ ፍፃሜ ያየነውን አይነት ሆኖ አለፈ፡፡ አፅማቸውም ከጊዜ በኋላ ከዚያ ወጥቶ ስላሴ ቤተ-ክርስቲያን እንዲያርፍ ተደረገ፡፡

በትራስ ታፍነው ሊገደሉ የሰኣታት እድሜ ቀርቷቸው በነበረ ጊዜ ጃንሆይ "እውነት ግን በድለንሻል? እውነት አልደከምንልሽም?" በማለት ተንበርክከው የጠየቁት ሰዎችን አልነበረም፣ ኢትዮጵያን እንጂ፡፡ ኢትዮጵያ ምን መለሰች ብሎ መጠየቅ ሳይገባ ስራቸው ራሱ መልስ እየሰጠ ይገኛል፡፡

በጃንሆይ ፓርላማ እየተሰበሰብን፣ በጃንሆይ ቴአትር ቤት እየተዝናናን፣ በጃንሆይን ስታዲየም እየተጫወትን፣ በጃንሆይ ዘመን የፍትሐብሔር ሕግ እየተዳኘን፣ በጃንሆይ... ብዙ ነገር እየተጠቀምን መሆናችን ማሰቡ ብቻ መልስ ይሆነናል ለማለት ነው፡፡



# ምዕራፍ 85

*የሊቀመናብርቱ ዘመን*

መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም አብዮቱ ከፈነዳ በኋላ ኢትዮጵያ በሊቀመናብርቱ ተመርታለች፡፡ በመጀመሪያ ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም ለሁለት ወራት ሊቀመንበር ሆነው ቆይተው በመንግስቱ ትዕዛዝ ከተገደሉ በኋላ ቀጥሎ ብርጋዴል ጄኔራል ተፈሪ በንቲ ለሁለት ዓመታት ያህል የሊቀመንበርነቱ ቦታ ተሰጥቷቸው መርተዋል፡፡ እሳቸውንም ደርግ ገደለና ተተኪው ሻለቃ መንግስቱ ሆኑ፡፡ እነዚህ ሁለት ጄኔራሎች በጠሩ ዘንድ ተቀባይነት ለማስገኘት ሲባል በሽፋንነት ከፊት እንዲቀድሙ የተደረጉ ይሁኑ እንጂ፣ ከበስተጀርባ መንግስቱ ነበሩ የደርጉ መሪ፡፡ ጄኔራሎቹ የደርግ አባላት አልነበሩም፡፡ የቀሩት የደርግ መስራች ሻለቃ አጥናፉም ተፈሪ ባንቲ በተገደሉ ማግስት ተወግደው መንጌ ብቸኛው ሊቀመንበር ሆነው ዘልቀዋል፡፡

ደርግ ንጉሣዊ አገዛዙን አስወግዶ፣ "የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር" ብሎ ራሱን ሰየመ፡፡ የመጀመሪያ ስራውም አዲሱን ሕገ-መንግስት ማገድ፣ ፓርላማውን መበተንና ማናቸውንም አይነት ሠላማዊ ሰልፍንና የስራ ማቆም አድማን መከልከል ነበር፡፡ "ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለውን መርህ መቃወም የዘመኑ ቁጥር አንድ ወንጀል ሆነ፡፡

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መቋቋም ወዲያው ነበር ተቃውሞ የገጠመው፡፡ በዋናነት የተማሪዎች ቡድን፣ ቀጥሎ "ፎረም" በመባል የሚታወቀው ግራ ዘመም የሆነው የዩኒቨርሲቲ መምህራን ቡድን፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን ሲሆኑ፣ እነዚህም "ዴሞክራሲያ" እና "የሠፊው ህዝብ ድምፅ" በተባሉ መጽሔቶች ዙሪያ ተሰባስበው የግራ ክንፍ ድርጅቶች ሆነው ተቃወሙ፡፡ ከወታደሩ በኩል ደግሞ የክቡር ዘበኛና የወታደር የበረራ ክፍል (አርሚ አቪየሽን) እንዲሁም የመሐንዲስ ክፍል ተቃዋሚ ሆነው ቀረቡ፡፡ የተቃውሞ መነሻቸውም "የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ነው መቋቋም ያለበት" የሚል ነው፡፡ ይህንንም ቀደም ካለው የደርግ ምስረታ ጊዜ ጀምሮ በተለይ የመምህራን ቡድን ለደርግ ያቀርቡት የነበረ ሀሳብ ነው፡፡ ያን ጊዜ "ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም" ሲሉ ቢቆዩም፣ አሁን ከባድ እንደሚሆን ስለተረዱ፣ "ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት" በሚል አሻሻሉት፡፡

ሆኖም የዚህ መፈክር ደጋፊዎች አቋማቸው አንድ ይሁን እንጂ በአመሠራረቱ ላይ የሚያቀርቡት አጀንዳ የተለያየ ነበር፡፡ ከፊሉ "ከሰራተኞች፣ ከተማሪዎች፣ ከመምህራንና ገበሬዎች የሚውጣጣ መንግስት ይሁን" ሲሉ፣ የቀሩት "የየካቲቱ ህዝባዊ ንቅናቄ ባፈራቸው ኮሚቴዎችና ድርጅቶች ላይ ይመስረት" ይላሉ፡፡ ይህ የ"ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት"

መፈክር አተገባበር ጉዳይም በዴሞክራሲያ እና የሰፊው ህዝብ ድምፅ በተሰኙ የፕሬስ ውጤቶች ዙሪያ የተደራጁትን "የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ" (ኢሕአፓ)ን እና "የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ" (መኢሶን)ን ወደፊት የምናያቸውን የእርስ በርስ የስልጣን ፍልሚያ ሊፈጥር ችሏል፡፡

በአብዮቱ ወቅት በአገር ቤት የ"ሰፊው ህዝብ ድምፅ" ላይ በቀረበ ትንቢታዊ ትንታኔ "ወታደራዊ መንግስት ምን ቅን ልቦና ቢኖረው አገሪቱን በአንድ አንባገነን መሪ መዳፍ ስር ይጥላታል" የሚል አቋም የያዘ ጽሁፍ ቢሰነዝርም፤ ይህ የመኢሶን አቋም ከአገር ውጪ ካለው የመኢሶን አመራር ጋር የሚጣጣም አልሆነም፡፡ ምክንያቱም ሰፊውን ህዝብ ለማደራጀት ጊዜ ስለሚያስፈልግ ስልጣኑ በወታደሩ እጅ እንዲቆይለት የውጭ አገሩ ቡድን ይፈልግ ስለነበር ነው፡፡ ከዚህም በላይ ኢህአፓ በብዙሃን ድርጅቶች በመምህራን፣ በተማሪዎችና በሠራተኛው ዘንድ ቀድሞ መሰረፅ ችሏልና የሚቋቋመውን ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት እረከባለሁ ብሎ ያስብ ስለነበርና መኢሶን ገና ይቀረው ስለነበር፤ ወታደሩን ጊዜ መግዣ ሊያደርግ ሽቶታል፡፡

የመኢሶን የውጭ ቡድን አገር ቤት ከገባ በኋላም ከኢህአፓ ጋር ቢፎካከር ውጤት አልባ እንደሚሆን ስለተረዳው ያን የጋራ መፈክር ጥሎ፣ የአገርቤቱን አጋሩንም አስጥሎ ከደርግ ጋር ተንጠላጥሎ /ተለጥፎ/ ስልጣን መያዙን መርጧል፡፡

የኢህአፓና የመኢሶን የጦፈ ክርክር ማርከሳዊ ጭብጥነቱ አንድ ስለሆነ ፉክክሩ "ለርዕዮቱ እኔ ታማኝ ነኝ" ሲል አንዱ፤ ሌላው "እኔ የበለጠ ታማኝ ነኝ" የሚል እንጂ የርዕዮት ልዩነት የላቸውም፡፡ ከዚህ አንፃር ፉክክሩ የስልጣንና የስልጣን ብቻ ተብሎ ይደመደማል፡፡ ደርግ ግን እንኳን ስልጣን አስረክቦ ወደ ካምፕ ለመመለስ ለማጋራት እንኳ የፈለገ አይመስልም፡፡

እርግጥ ነው ደርግ ስደት ላይ ያሉትን ቀደምት የአመፅ እንቅሳቃሽ የነበሩ ምሁራንንና ማኅበራቱን ከአውሮፓም፣ ከአሜሪካም ... ለሁሉም ጥሪ አቅርቧል፡፡ ነገር ግን ምሁራኑን አስቀድሞ ሲጋብዝ ስልጣን ለመልቀቅ ሳይሆን ያስብ የነበረው፤በምን መልኩ ተጠቅሜባቸው ነው ስልጣኔን የማጠናክርባቸው? በሚል ዓላማ መሆኑ ዘግይቶ ገሀድ የወጣ ሀቅ ሆኗል፡፡

ደርግ ጃንሆይን ከስልጣን ከማውረዱ በፊት በምን መልኩ እናውርዳቸው? የሚለውን አጀንዳ ተወያይቶ ውሣኔ ካሳለፈ በኋላ፤ ቀጣይ ውይይቱ ጃንሆይ ከወረዱ በኋላስ ምን ዓይነት መንግስት ይተካ? የሚለው ነበርና በዚህ አጀንዳ የከረረ ክርክር ተደርጓል፡፡ ይህን ጥያቄ የሚመለከቱ



ሀሳቦችንም ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በቡድንም በግለሰብ ደረጃም እየቀረቡለት ሲሰበሰብ ቆይቷል፡፡

በደርግ ስብሰባ ከተነሱ ነጥቦች ውስጥ አንዱ "አፍሪካ ውስጥ የተቋቋሙትን ወታደራዊ መንግስቶች ምሳሌ በማድረግ ህዝቡን አስተባብረን አገራችንን መምራት ያቅተናል እንዴ? ስለዚህ ንጉሡ በንጉስ እንዲተካ ይሁንና ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ተቋቁሞ፤ እኛ በሠራዊቱ የተወከልነው አባላትም ሳንለያይ ለተወሰነ ጊዜ መሪነቱን ይዘን እንቆይ፡፡ በህዝብ የተወከለ መንግስት ሲደራጅ አስረክበን ወደየጦር ክፍላችን እንመለስ" የሚለው ከደርግ አባላት የተሰነዘረው ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ልጅ ሚካኤል እምሩ የመሩት የባለሙያ ቡድን አጥንቶ ያቀረበው እንደሆነ የሚነገርለት የሰለጠነ ሀሳብ ነበር፡፡ ይህን ሀሳብ ከቀናት በፊት የአስተባባሪው ኮሚቴ ሊቀመንበር እንዲሆኑ የተሾሙት ጄኔራል አማን አቀረቡት፡፡ "ከአስተባባሪው ኮሚቴ ውስጥ በድምፅ ብልጫ የሚመረጡ 10 እውቀትና ችሎታ ያላቸው መኮንኖችና 10 ከሲቪል፣ ከታዋቂ ሰዎች ተመርጠው የሁለቱ ጥምር ቡድን መንግስት ኢትዮጵያን ያስተዳድሩ" አሉ ጄኔራል አማን፡፡

ይህ ማለት የደርግ አባላት ተበተኑ ማለት መሆኑ ነው፡፡ይህን ሀሳብ ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም በጽኑ ተቃወሙት፡፡"የደርግ አባላትን በትኖ ወደ ጦር ክፍላቸው መላክ ሠራዊቱን ለሌላ አመፅ ማነሳሳት ይሆናል! መቋቋም ያለበት ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ነው፡፡በሽግግር ወቅት ወታደሩ ስልጣን ለብቻው መያዝ አለበት፡፡ሲቪሎችን ማካፈል ተገቢ አይደለም" ሲሉ፤ጠቅላላው የደርግ አባላት የመንግስቱን ሀሳብ ደግፈው አጨበጨቡ፡፡

ጄኔራል አማን "ሲቪልና ወታደር" ሲሉ ከወታደሩ ቀዳሚ ተመራጭ እንደሚሆኑ ያውቁታል፡፡ ሻለቃ መንግስቱ ከ10 ተመራጮች አንዱ ሊሆኑ እንደሚችሉ ባያጠራጥርም፤ ወደፊት ስልጣንን ለብቻቸው የመያዝ ህልማቸው ግን ይጨናጎላል፡፡ ምናልባትም እውቀት፣ ችሎታና ትምህርት ካላቸው ተመራጮች ጋር ተካተው ሲመዘኑ አንዲት ዝቅ ያለች ቦታ ብቻ ሊያገኙ እንደሚችሉ እሱዋውም ቀጣይነት ላይኖራት እንደሚችል መገመት አይከብዳቸውም፡፡

ሌላው የበታች ሹማምንት የደርግ አባልማ የመንግስቱን አቋም ካልደገፈ ምንም አይነት ቦታ አይኖረውም፡፡ ይህ ስለሆነ የአማን የ"ይበተኑ" አቋም በቀላሉ ተሸነፈ፤ የመንግስቱ የ"አይበተኑም" አቋም በቀላሉ አሸነፈ፡፡

ሻለቃ መንግስቱ ያለእነዚያ ዝቅተኛ ሹማምንት ኃይል፤ ዝቅተኛ ሹማምንቱ ያለሻለቃ መንግስቱ አቋም ህልውና አይኖራቸውም፡፡ ስለዚህ ላእላይና ታህታይ መዋቅሩ እስከመጨረሻው ተሳስረው ከመቀጠል ውጪ

ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም፡፡ ከዚህ በኋላ ጄኔራል አማን ለደርግ፣ ደርግ ለአማን ጥሩ ምልከታ እንዳይኖራቸው ሆነ፡፡ ነገር ግን ለጊዜውም ቢሆን ልዩነታቸውን ውበት አድርገው መቀጠል ነበረባቸውና ቀጥለዋል፡፡

በዚህ መሠረት “የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ” መመስረቱን በአዋጅ ቁጥር 1 1967 ዓ.ም ደንግገው ስራቸውን ቀጥለዋል፡፡

በሻለቃ መንግስቱ አስተባባሪነትም በቀጥታ በደርግ የሚታዘዝ ልዩ ጦር አዘጋጅተዋል፡፡ ከነበሩት አባላት በተጨማሪም ሌሎች ከየጦር ክፍሉ የተውጣጡ በመቶዎች የሚቆጠሩ ንዑስ የደርግ አባላት ተደራጅተው አጋር ሆነዋል፡፡ በውስጥና በውጭ ያሉ ምሁራን በቃላት ጦርነት ሲጠዛጠዙ፤ “የበላይነት ላለው ለእኛ ቡድን ስልጣን ይገባል” እያሉ ሲሸልሉ ደርግ ራሱን አደላድሎ፤ የምሁራኑን ሀሳብ ለራሱ በሚመቸው መንገድ እየተረጎመና ስልጣን የሚሰጥ መስሎ እያማለለ ጥቂት ምሁራንን አስጠግቶ እየተጠቀመባቸው ቀጠለ፡፡ ፍርፋሪ ስልጣን ለመቃረም የነበረው የምሁራን ሽኩቻ ከፍተኛ ነበር፡፡ ለደርግም በእጅጉ ጠቅሞታል፡፡ ደርግ ከህቡዕ ቡድኖች የሚሰነዘረውን የስልጣን ጥያቄ ሲቻል በዘዴ፣ ካልሆነም በኃይል ለማስወገድ ተዘጋጅቷል፡፡

ውክልናው በህዝቡ ዘንድ እውቅና እንዲኖረውም መንግስታዊና ሃይማኖታዊ ተቋሞችን፣ ህዝባዊና የሙያ ድርጅቶችን የሚወክሉ አባላት የሚገኙበት ብሔራዊ የመማክርት ሸንጎ ለይምሰል ሰየመ፡፡ የይምሰል መሆኑን ተረድተው ለተቃውሞ የሚነሱትን መደምሰስ መፍትሄ አደረገው፡፡ ሲጀምርም የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችን አሰረ፡፡ ወዝአደሩ የመሪዎቹን መታሰር ተቃውሞ ሲነሳ በኃይል በተናቸው፡፡ የደርግን ተደላድሎ ስልጣን መያዝ የተቃወሙት ሲቪሎች ብቻ አልነበሩም፡፡ ወደ ሠራዊቱም ተዛምቷል፡፡ ክቡር ዘበኛና የአርሚ አቪየሽን ደርግን ተቃውመዋል፡፡ እነዚህ ክፍሎችም መሪዎቻቸውን በደርግ ተፅዕኖ አሳልፈው ሊሰጡ ተገደዋል፡፡ የመሐንዲስ ክፍሉ ግን በተቃውሞው ስለገፋና እጅ አልሰጥም በማለቱ መስከረም 27 ቀን በሻለቃ መንግስቱ ብቻ ታማኝ እንዲሆን ተደርጎ የተዋቀረውና በእሳቸው ትዕዛዝ ብቻ የሚመራው ወታደር ካምፑን ሰብሮ ገብቶ በከፈተው ጥቃት 5 የመሐንዲስ ጦር አባላት ተገድለው፣ በርካቶች ቆስለው፣ የቀሩት እንዲታሰሩ ተደረገ፡፡ ደርግ ራሱን የአብዮቱ ጠበቂና ብቸኛ አለኝታ አድርጎ ወስዶታልና በዚህ ጉዳይ የወጣበትን ክፍሉን እንኳ እንደማይምር አረጋገጠ፡፡ አብዮቱ በደም ተጀመረ፡፡

በደርግ ውስጥ ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም በአንደበተ ርቱዕነታቸው ተወዳጅ ሆነው ቀጥለዋል፡፡ በተለይ የበታች ሹማምንቱ ከደርግ አባልነት ቀስ በቀስ ወደ መንግስቱ አሽከርነት ተለውጠዋል ቢባል አልተጋነነም፡፡



መንግስቱ ሊለጠፉ ከፈለጉት ምሁራንና ከሰላያቸው ከደጃዝማቹ የሚጎርፉትን ሀሳቦች ለደርግ እያቀረቡ በእጅ ብልጫ ያስወስናል፡፡ መወደድና መከበር ያልቻሉት በጄኔራል አማን ብቻ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ውሎ አድሮም በአማንና በመንግስቱ መካከል በሀሳብ አለመጣጣም መሸካከር ተከሰተ፡፡

የኤርትራ ግዛት ተወላጁ ጄኔራል አማን ሚካኢል አንዶም በራሳቸው የሚተማመኑ፣ የጦር ጀግና፣ ኩሩና አስተዋይ መሆናቸው ይነገርላቸዋል፡፡ በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ በስደት ሱዳን የነበሩና፣ ንጉሡ ከስደት ሲመለሱና በሱዳን በኩል አድርገው ከእንግሊዝ ጦር ጋር እየተዋጉ ሲመጡ አማን ተሳታፊ ነበሩ፡፡ ከነፃነት በኋላ ከኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ጋር ተቀላቅለው አገራቸውን ሲያገለግሉ የቆዩና እስከ ከፍተኛው ሌቴናል ጄኔራልነት የደረሱ ናቸው፡፡ “አሸዋ ልብሱ፣ ኮዳ ትራሱ” እየተባሉ በጦሩ ዘንድ ከፍተኛ አድናቆትና ተወዳጅነት ያተረፉ ከመሆናቸውም በላይ፤ ከፍተኛ ወታደራዊ ትምህርቶችን በምዕራቡ ዓለም የተከታተሉ ናቸው፡፡ በአሜሪካና በሌሎች አገሮች በወታደራዊ አታሼነት ተመድበው ሰርተዋል፡፡ ኮሪያ ለዘመተው ለአንደኛው ቃኘው ሻለቃ አዛዥ ሆነው ዘምተዋል፡፡ በአገር ውስጥም በተለያዩ የምድር ጦር ክፍሎች እየተመደቡ በአዛዥነት አገልግለዋል፡፡ አሁን በደርጉ ዘመን ደግሞ የመከላከያ ሚኒስቴርና ጠቅላይ ኤታማገር ሹም ሆነው የደርግን የሊቀመንበርነት ስልጣንም ይዘዋል፡፡

በጥቅምት ወር 1967 ዓ.ም ወደ ኤርትራ ለጉብኝት እንዲሄዱ ተደረገ፡፡ የኤርትራ ሁኔታ የወቅቱ አሳሳቢ ጉዳይ ነበር፡፡ የሻዕቢያና የጀብሃ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ስጋት የሆነው ከጃንሆይ ዘመን ጀምሮ ነበርና ከአብዮቱ በኋላ የሠላም ጥረት ማድረጉ /መሞከሩ/ ተገቢ ነበር፡፡ የጄኔራል አማን የጉብኝት ዓላማም በዋናነት በግዛቱ ያሉትን የኢትዮጵያ ሠራዊቶች ከተራ ወታደር እስከ አዛዥ በቡድንና በግል ማነጋገርና መገምገም፣ የየግዛቱን ሲቪል ህብረተሰብ ማነጋገር፣ ከአገር ሽማግሌዎች ጋር የኤርትራን ችግር እንዴት መፍታት እንደሚገባ ለመወያየት የታቀደ ሲሆን፤ የአማን የትውልድ አገር መሆኑ ደግሞ ለእቅዱ ስኬታማነት ሚና ይኖረዋል ተብሎ ነው፡፡ እንደተባለውም የኤርትራ ህዝብ በሳባ ስታዲየም ተሰብስቦ የጋለ አቀባበል አድርጎላቸዋል፡፡

በእቅዳቸው መሠረትም የአገር ሽማግሌዎችን እየሰበሰቡ የእርስ በርስ ጦርነቱ ቆሞ ሰላም መውረድ እንዳለበት፣ወላጆችም ልጆቻቸውን ወደ ሠላም የሚመራ ምክር እንዲለግሱ፣ የስልጣን ሱሰኞች የጫሩት እሣት ባፋጣኝ መጥፋት እንዳለበት ገልፀዋል፡፡ ሠራዊታቸውንም አበረታተው ስለሠላም ሰብከዋል፡፡የመጨረሻ ጉብኝታቸውን በደመቀው ስታዲየም ሲያደርጉም የተሰብሳቢውን ህዝብ ልብ የነካ ንግግር እንዲህ በማለት

አሰሙ "በትግርኛ፣ በአማርኛ፣በዓረብኛ ሠላም ይገባችሁ መቀቻለሁ፡፡እኔ የሠላም ምልክት ነኝ፣ ለሠላም የቆምኩ ነኝ፤አማን ማለት ሠላም ማለት ነው፡፡ጥቂት አኩራፊ ታጣቂ ቡድኖች የኢትዮጵያን የወደፊት ዕጣ መወሰን አይችሉም፣የኤርትራና የኢትዮጵያ አንድነት ዘላለማዊ ነው..."

ከጉብኝቱ መልስ የደርግ አባላትን ሰብስበው የጉብኝታቸውን ሁኔታ ካስረዱ በኋላ ውይይት ተደረገ፡፡ አማን የኤርትራ ህዝብ ሠላም እንደሚፈልግና፣ ሠላም ማውረድ እንደሚቻልም ጠቅሰው "መንግስት መከተል ያለበት ሰጥቶ የመቀበልን መርህ ነው" የሚል ድምዳሜ አከሉበት፡፡ ይህንንም ሲሉ የኤርትራ አማፅያንን ትጥቅ ለማስፈታት ቢያንስ የፌዴሬሽን ጥያቄ ማንሳታቸው አይቀርምና ምላሽ ለመስጠት መዘጋጀት ከእኛ ይጠበቃል ለማለት ነው፡፡



ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም በአሥመራ ስታዲየም ከሕዝቡ ለተደረገለት የጋለ አቀባበል አፀፋውን ሲመልስ

የአማን ገለፃ በቀና ትርጓሜ ቢመረመር የኤርትራ አማፅያን ለዓመታት ሲታገሉለት የቆዩት ዓላማ የመገንጠል ጉዳይ ስለሆነ ያለምንም ድርድር ትጥቅ ፍቱ ቢባሉ ምንን መሠረት አድርገው ትጥቅ ይፈታሉ? የንጉሡ መውደቅ አለመውደቅ የአማፅያኑ መሠረታዊ ጥያቄ አይደለም፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ የመጨረሻው መደራደሪያ ከመገንጠል የተሻለውንና የማይከፋውን ፌዴሬሽን መስጠት ይሆናል፡፡ ስለ ሠላም መደራደር ካስፈለገ ምርጫው ያ ብቻ ነበር፡፡ ከዚህ ውጪ ከሆነ ደግሞ አማን የሄዱት ወይም የሚሄዱት ለማስፈራራት ብቻ መሆን ነበረበት፡፡ "እጅ ብትሰጡ ስጡ፣ ያለዚያ ወዮላችሁ" ብሎ ለመመለስ እንደማለት፡፡ ምክንያቱም ለዓመታት የተደራጁና ለእኩይ ዓላማቸው መፈፀም ብዙ ደም ያፈሰሱ ተገንጣዮች በባዶ ሜዳ ሠላማዊ ድርድር የሚያደርጉበት መነሻ አይኖርምና፡፡ ከዚህ አንፃር የጀኔራሉ ሀሳብ ሠላም እንዲወርድ እስከተፈለገ ድረስ አንድ ነገር መደረግ አለበት የሚል ስለሆነ ተገቢነቱ አያጠያይቅም፡፡ ስለሆነም ሊያስጠረጥራቸው ባልቻለ ነበር፡፡ ሆኖም



ምክትል ሊቀመንበሩ ሻለቃ መንግስቱ ሌላ ትርጉም ከመስጠት ወደ ኋላ አላሉም፡፡ በዚህ መሀል ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደሰላሴ "በአስቸኳይ ጦር ካልተላከ ኤርትራ አለቀላት" አሉ፡፡

ወዲያው የሰላም ድርድሩ ቀርቶ ጦር ይላክ? አይላክ? የሚለው ሌላ አጀንዳ ሆነ፡፡ አሁንም ሊቀመናብርቱ ተፋጠጡ፡፡ አማን "ጦር አይላክ፣ ሠላማዊ መንገድ እናስቀድም" ሲሉ መንግስቱ "መላክ አለበት" አሉ፡፡ አሁንም በእጅ ብልጫ አማን ተሸነፉ፡፡ ቀጣዩ አጀንዳ "የትኛው ጦር ይላክ?" የሚለው ሆነ፡፡ አማን "ጅጅጋ ያለው ታንከኛ ጦር ይላክ" ሲሉ መንግስቱ "የአንደኛው ክፍለ ጦር አካል የሆነው አዲስ አበባ ያለው 6ኛ ብርጌድ ነው መላክ ያለበት" አሉ፡፡

በዚህ ጊዜ ሻምበል እንዳለ ተሰማ (በኋላ ሻለቃ) የተባሉት አባል "የታንከኛ ጦር ለሽምቅ ውጊያና ላስቸጋሪ መልከዓ ምድር እንዴት ይጠቅማል? ሶማሊያ ልትወረን እየተዘጋጀች መሆኑ እየታወቀ ያን ጦር ከጅጅጋ ማንሳቱ ተገቢ አይመስልም፡፡ እንደገና ወታደር የሆነ፣ የአገር ፍቅርና ተቆርቋሪነት ያለው፣ የኤርትራንም መሬት ወጣገባነት የሚያውቅ ሰው ታንከኛ ጦር ይላክ የሚል አይመስለኝም..." የሚል ውስጠ ወይራ ንግግራቸውን አሰሙ፡፡ በአባላቱ ውስጥ ተጭሮ የነበረው የጥርጣሬ እሣት ላይ ቤንዚን አርከፈከፉ ማለት ነው፡፡ ጀኔራል አማን በዚህ ንግግር ትዕግስታቸው አለቀ፣ ተቆጡ "እኔ የማደርገውን አውቃለሁ ብዬ አምናለሁ፣ ለ20 ዓመታት ጀኔራል ነኝ፣ የ30 ዓመት ልምድ ያዳበርኩ ጀኔራል መኮንን ነኝ፡፡ ከዚህ ከተሰበሰባችሁት ከማናችሁም ይበልጥ ለኢትዮጵያ መስዋዕትነት ከፍያለሁ፡፡ ኢትዮጵያዊነቴን ማንም እንዲጠይቀው አልፈቅድም!" ማለታቸውን የስብሰባው ተካፋይ የነበሩ አባላት በምስክርነት ቃላቸው ገልፀዋል፡፡ ይሄን ካሉ በኋላ በንዴት ጠረጴዛውን በቡጢ ነርተው "በማሃይም ጫጫታ አገር አትመራም!" አሉና ስብሰባውን ረግጠው ወጡ፡፡ ወደቤታቸው ሄደው ለተለያዩ አዛዥ መኮንኖች በስልክ ይህ ደርግ የሚባል ቡድን ሊያሰራቸው እንዳልቻለና መበተን እንደሚገባው እየገለፁ እንዲተባበሯቸው መጠየቅ ጀመሩ፡፡ ከእነዚህ ውስጥም ለጀኔራል ግዛው በላይነህ የገለፁት ቃል የጃንሆይ ካቢኔ ይጠቀምበት በነበረው የረቀቀ የድምፅ መቆጣጠሪያ መሣሪያ በደህንነቱ ቢሮ ተጠልፎ የአማን ንግግር በደርጉ ስብሰባ እንዲደመጥ ሆነ፡፡ ጀኔራሉ "... ግዛው አገራችን በማንም ዱቄት ሰፋሪና በእነዚህ ቂጣቸውን ባልጠረጉ ጨምላቆች ተመርታ ወደ ጥፋት መሄድ የለባትም፤አንተም ሠራዊትህን አዘጋጅና ተነሳ፤ይሄ ሁሉ ውርደት ነው፡፡ እኔ የጀኔራሎችን ክብርና መብት ለማስጠበቅ ነው፡፡ አንዳንድ ጨቅላ ሻለቆችና ሃምሳ አለቆች..." ሲሉ ጀኔራል ግዛው "ይተው እንጂ ጌታዬ፣ እርስዎን ከዚህ ታላቅ የመሪነት

ቦታ ያስቀመጡት'ኮ እነዚህ ቂጣቸውን ያልጠረጉ ያኗቸው ናቸው..." የሚል መልስ ሰጡ፡፡

አማን ዱቄት ሰፋሪ ያሉት መንግስቱ የመሣሪያ ግምጃ ቤት ኃላፊ ሆነው ይሰሩ ስለነበር ነው፡፡ አማን ጦሩን ለማንቀሳቀስና በደርግ ላይ እንዲነሳ ለማድረግ የጣሩት ጥረት ሁሉ አልተሳካም፡፡ ረፍዶባቸዋል፡፡

እንግዲህ በመጀመሪያ የአማን ፈጥኖ ተወዳጅነት ማግኘት በደርጉ አልተወደደም፡፡ ሻለቃ መንግስቱን የከነከናቸው ይመስላል፡፡ ከዚያ "ደርግ ይበተን" ቀጥሎ "ሰጥቶ መቀበል" እንደገና "ጦር አይላክ" ከዚያም "ታንከኛ ይሂድ" ሲሉና፤ በመጨረሻም ተሳድበው ሲወጡ፤ በዚህም ላይ ኤርትራዊነታቸው ሲደረብና፤ በሳባ ስታዲየም "የኤርትራና የኢትዮጵያ አንድነት ዘላለማዊ ነው" በማለት ያደረጉት ንግግር አንዷን አገር ነጣጥለው ሁለት አድርገው ለየቅል ገለጿቸው የሚል ትርጉም ውስጥ ደርግ ሲገባ፣ በመጨረሻው መጨረሻም ስብሰባውን ረግጠው ወጥተው ጦሩን ለመቀስቀስ ሲሰናዱ የጄኔራሉ ግብ ምን እንደነበር ለመገመት ቢቸግርም፤ ለደርግ በተለይም ለሻለቃ መንግስቱ ምን ማለት እንደሆነ ግን ግልፅ ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ደርግ አማን ላይ እርምጃ ለመውሰድ ከዚህ የበለጠ ምክንያት መጠበቅ ነበረበት ብሎ ማሰብ የደርግን ባህሪ በቅጡ ካለመረዳት የሚመነጭ ነው የሚሆነው፡፡ መንግስቱ የአማንን ጉዳይ እልባት ለመስጠት የሚያስችል መነሻም፤ ድጋፍም፣ ፈፃሚ አካልም አላቸው፡፡ ነገር ግን ከዚያ በፊት ነገሩ መልሶ ቅርፅ መያዝ ነበረበት፡፡

የአማን ስብሰባ ረግጦ መውጣት ለደርግ አስደንጋጭ ዱብ ዕዳ ነበር፡፡ ስለዚህ ቤታቸው ገብተው ቁጭ ያሉትን ሊቀመንበር እንደምንም ተለማምጦ በስራ ገበታቸው እንዲገኙ ማድረግ የግድ ነው፡፡ "ጀግና፣ ኮዳ ትራሱ" እያሉ ራሳቸው ደርጎች እያሞካሹ በቴሌቪዥን በሬዲዮ እያዘመሩለት የነበረውንና መርጠው መሪ ያደረጉትን ሰው ዛሬ እንዲህ መሆኑ ቢታወቅ በጦሩ ውስጥ ምን ሊፈጠር እንደሚችል አስበው ተጨንቀዋል፡፡

ፍርሃት የናጣቸው ሻለቃ መንግስቱ ችግሮችን በውይይት እንፍታ የሚል የልምምጥ ቃልን አስይዘው ጄኔራል ግዛውንና ሻለቃ ብርሃኑ ባየህን በአማላጅነት ላኩ፡፡ አማን በጅ አላሉም፡፡ ቀጥሎ በመረጃ ኃላፊው የሚመሩ ልዑካን በሽምግልና ተላኩ፡፡ አማን ቤታቸው ውስጥ ሆነው "ወግድ!" ብለው መለሱዋቸው፡፡ በመጨረሻ መንግስቱ ራሳቸው መሄድ ነበረባቸውና ሄዱ፡፡ በምን አይነት መደራደሪያ እንደተመለሱ ከማየታችን በፊት መንግስቱ ስለ አማን በትዝታቸው ያሰፈሩትን ገለፃ እናስቀድም፡፡

"... ሰውየው ሁለት ሦስት ጊዜ እንደ ልጅ እያኮረፉ ትተውን ሄደው ነው ቤታቸው የሚቀመጡት፡፡ ሽማግሌ እየያዝኩ እየሄድኩ ነበር የምለምናቸው፡፡ ምን ነካዎት ጄኔራል? እባክዎ ይተው፤ ይች ልክ እንደ



እንቁላል የሆነች አገር ናት'ኮ እጃችን ውስጥ ያለችው፡፡ እኛ ላይ ታሪክ ጥሏታል፤ ብንለቃት'ኮ እንቦጨ የምትል ናት፡፡ እርስዎ እኛን ሰብሳቢ፣ እኛን መካሪ ነዎት እንጂ እኛ እየመጣን ጠዋት ማታ እንዴት ነው? ስላቸው "እኔን የማንም ሃምሳ አለቃና አስር አለቃ አያዘኝም!" አሉ፡፡

"እኔን በበኩሌ ብዙ ጊዜ በሚያንጓ ስልጣን ሊደልሉኝ ሞክረዋል፡፡"ብትፈልግ አንተ ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ብትፈልግ መከላከያ ሚኒስቴር፣የፈለገህን ውሰድ፡፡ይሄን ሃምሳ አለቃውን ምናምኑን ግማሹን ሹመት ስጡት፡፡ወረዳ ገዥ ምናምን እያላችሁ ማሰናበት ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ስራ ይሰራል እንጂ፤ እንዴት ነው በአስር አለቆች አገር የምትመራው? ብለውኛል፡፡

"እንዴት ነው ነገሩ? እርስዎ ምን ቸገረዎት? እርስዎን ያመጣዎ'ኮ ይሄ ኃይል ነው፡፡ ይሄ ኃይል ደግሞ የሚያገለግልበትና የሚፈለግበት ወቅትና ጊዜ አለ፡፡ ከዚያ በኋላ የራሱን ሂደት በራሱ ጨርሶ ይሄዳል፡፡ አሁን እስቲ በመጀመሪያ በዙሪያችን ያሰፈሰፈውን ጠላት እንመክት፡፡

.... ደርጉን በሚመለከት ላለው ነገር እኔ አለሁ፤ እርስዎ ስራዎን ይስሩ ብዬ ስንት ጊዜ ለምኛቸው አቅተውኛል..." ባይ ናቸው መንግስቱ፡፡ ሲቀጥሉም "ለምን እንደዚህ እንዳስቸገሩን ሳይገባን ቀርቶ በኋላ ነው የተገለጠልን፡፡ ኤርትራን የመገንጠል ዓላማ ነው፤ ደርግን የማፍረስ ጉዳይ ነው፡፡ ኃላፊነት የጎደላቸው ሆነው ነው ያገኘኋቸው" ሲሉ ይደመድማሉ መንግስቱ፡፡

የመጨረሻውን የመንግስቱን ልመና ተቀብለው፤ ነገር ግን አሁንም ቅሬታቸው እንዳለ በመግለፅ አንድ መደራደሪያ ያቀርባሉ፡፡ ይህም ሻለቃ መንግስቱ ጥር 7 ቀን 1967 ዓ.ም ጎፋ ሰፈር የሚገኘውን የታንከኛ ክፍል ጎብኝተው ስለ ኢትዮጵያ ትቅደም መርህ ለጦሩ መግለጫ ሰጥተው ነበርና "ይህ ተግባር እኔ ሳላውቅና ሳልፈቅድ የተከናወነ ነው፡፡ (መንግስቱ የጦር ክፍሉን በራሳቸው ስልጣን ነበር ያነጋገሩት) ስለዚህ እኔ ካልተፈለግሁና የእኔ አመራር ቦታ ከሌለው ለምልክትነት የምቀመጥ ሰው አይደለሁም፡፡ በመሆኑም የጎፋ ሠፈር ጉብኝቱም ሆነ መግለጫው በመገናኛ ብዙሃን እንዳይገለፅ ከተደረገ ብቻ ወደ ስራ ልመለስ" አሉ አማን፡፡ መንግስቱ ተስማሙና ጄኔራሉ ወደስራቸው ተመለሱ፡፡

መንግስቱ ቃላቸውን በማጠፋቸውና በእሁዱ የጦር ኃይሎች ፕሮግራም ጉብኝቱ በሚዲያ ሲተላለፍ አማን በማድመጣቸው ይበሳጫሉ፡፡ ለስራ ጉዳይ ወደ አንድ ክፍል ለመሄድ ጉዞ ላይ የነበሩት አማን ዘገባው መተላለፉን ሲሰሙ እቅዳቸውን ሰርዘው ተመለሱና ወደ ቤታቸው ሄዱ፡፡ አልተመለሱም፡፡ በዚህ ጊዜ ነው ከላይ ያየነውን እንቅስቃሴ የጀመሩትና ከአዛገሮች ጋር ትብብርን የሚጠይቁ የስልክ ልውውጦች፣ ስድቦችና

ዛቻዎች የተኾጎደጎዱበት ንግግራቸው ተጠልፎ ለሻለቃ መንግስቱ የተሰጣቸው፡፡

ሻለቃው ጊዜ አላጠፉም፤ ከአዲስ አበባና ከሌላውም ክልል ንዑስ የደርግ አባላትን ባስቸኳይ ጠሩ፡፡ ንዑስ አባላቱም ዋና አባላቱም ፈጥነው በደርግ ጽ/ቤት ተሰበሰቡ፡፡ በመንግስቱ አገላለፅ አጠቃላይ የተሰብሳቢው ቁጥር ስድስት መቶ ይደርሳል፡፡ ጎን ለጎን ደግሞ ከአንደኛው ክፍለ ጦር 6ኛ ብርጌድ የተውጣጡ ወታደሮች ተመርጠው ጄኔራል አማንን እንዲይዙ ትዕዛዝ ተሰጣቸው፡፡ ወታደሮቹ ግን "እንዴት በአማን ላይ አፈሙዝ እንቀስራለን?" በማለት ትዕዛዙን አንቀበልም አሉ፡፡ ደርግ ክው አለ፡፡ አሁንም ለሌላ ክፍሎች ትዕዛዝ ተሰጠ "አማንን የሚያክል ጀግና ምን ሲደረግ? አንችልም!" አሉ፡፡ የአማን ማፈንገጥ፣ የወታደሩን ትዕዛዝ አንቀበልም ማለት የደርግን ሀልውና እንደሚያፈራርሰው የሰጉት አባላት ተስፋ ቆረጡ፡፡ ጦሩ አፈሙዙን ወደ ደርግ ሊያዞር እንደሚችል ታመነ፡፡ ስለዚህ የመጣው ይምጣ ብሎ ባለው የቅርብ ጦር አማንን መደምሰስና የሚመጣውን ለመቀበል ከመዘጋጀት ውጪ ደርግ ሌላ ምርጫ አልነበረውም፡፡ ለደርግ ጥበቃ ተብለው የመጡ ኮማንዶዎችን ከተወሰኑ የደርግ አባላት ጋር በታንክ ታግዞ ሻለቃ ዳንኤል አስፋው ጦርኃይሎች አካባቢ ወደሚገኘው የጄኔራል አማን መኖሪያ ቤት ዘመተ፡፡ ጄኔራሉ እጅ እንዲሰጡ ቢጠየቁም ጀግና እጁን ስለማይሰጥ የጦፈ ውጊያ ገጠሙ፡፡ አንድ ግለሰብ በታንክ የታገዘውን ጦር ገጥመው ጥቂቶችንም ገድለው በመጨረሻ ተገደሉ፡፡

በዚሁ ጊዜ ደርግና ንዑስ የደርግ አባላቱ ስብሰባ ተቀምጠው ስለአማን አስቸጋሪነትና ስለፈፀማቸው ተግባራቶች እየተነተኑ ምን እናድርጋቸው? ተብሎ እየተጠየቀ ነው፡፡ በዚህ መሀል ሻለቃ ዳንኤል የአማንን መገደል ለመንግስቱ በጆሯቸው ሹክ ብሏቸው ይወጣል፡፡ ይህን የሰሙት መንግስቱ የስብሰባውን አጀንዳ በድንጋጤ አሰፉትና ስለታሰሩት የንጉሡ ሹማምንት ጉዳይ አነሱ፡፡

እርግጥ መንግስቱ "የዚያን እለት አጀንዳ የጄኔራል አማን ጉደይ ነበር፡፡ብቸኛው አጀንዳ እሳቸው ነበሩ፡፡ሌላ ስለቀድሞ የኃይለስላሴ መንግስት ባለስልጣኖች የሚል ነገር ጨርሶ አልነበረም፡፡አሁንም ደግሜ ላረጋግጥ የምፈልገው እኔ፣ሌሎች የንዑስ ደርግ አባላት፣ የጦሩ ተወካይ የተባለ ሁሉ አንድ ሳይቀር እንዲገኝ የፈለግሁት ውሣኔው ምንም ይሁን ምን የአማን ጉዳይ ሠራዊቱ ውስጥ የሚያስከትለውን ስሜት ስለማውቅ ሁሉም እጁን እንዲያስገባ ነው፡፡እኔ ይህቺን አስቤ ነው የጠራኋቸው እንጂ ለኃይለስላሴ ሚኒስትሮችና ጄኔራሎች ምን ስብሰባ መጥራት ያስፈልጋል? መርማሪ ኮሚሽን ተቋቁሟል፣በቃ ይሄው ነው..." ብለዋል፡፡እናም ስለአንድ ጄኔራል ስብሰባ መጠራታቸው ያላስደሰታቸው አባላት "የሱን ጉዳይ ተውት



ምን አንድ ጄኔራል ይልቅስ የነዚያን ደም መጣጭ ጉዳይ ዳር ሳናደርስ አንወጣም!"በሚል ተሰብሳቢዎቹ አዳራሹን ቀውጢ እንዳደረጉት ነው የሚገልፁት፡፡

ምንም ይሁን፣ ምንም ይባል ግን የአማን ሞት በሚዲያ በሚገለፅበት ጊዜ ምን ሊፈጠር እንደሚችል በማሰብ ፍርሃት የወረራቸው የደርግ አባላት በተለይ መንግስቱ ጦሩ ቢያምፅና በደርግ ላይ ቢነሳ ደርግም መፍረሱ ነውና፣ ያ ከሆነ አይቀር ደግሞ ያለፈው ስርዓት እንደይመለስ ቢያንስ እነዚያን (በተለምዶ ስልሳዎቹ የሚባሉትን) የቀድሞ ታላላቅ ባለስልጣናት አጥፍቶ መጥፋት የሚሻል መሆኑን እንደመረጡ ግልፅ ነው፡፡ ሻለቃ መንግስቱ ከደቂቃዎች በፊት ብቻቸውን የሰሙትን የአማንን መገደል የተሰብሳቢው ስሜት እየጋለ መሄድን ሲረዱ ስብሰባው ላይ ይፋ አደረጉት፡፡

ከዚህ በኋላ ማለትም ከህዳር 1967 ዓ.ም ጀምሮ የደርግ መንግስት የ"በለው!" አራማጅ ሆነ፡፡ የደርግ መንግስት በ"በለው!" ጀምሮ በ"በለው!" ሊፈፀም ግድ ሆነ፡፡ 60ዎቹ የቀድሞው ባለስልጣናት መንግስቱ እንዳሉት የእለቱ አጀንዳ አልነበሩም፤ ሊሆኑም አይችሉም፡፡ ምክንያቱም የእነሱን ጉዳይ አጣርቶ ለፍርድ የሚያቀርብ መርማሪ ኮሚሽን ተቋቁሟል፡፡ እጅግ በተደራጀ መልኩ እነ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምን የመሳሰሉ ምሁራን ሳይቀሩ የኮሚሽኑ አባላት ሆነው፣ በስርዓት ዳኞች ተሾመው ጉዳያቸው በሕግ እየታየ ነው፡፡ ኮሚሽኑ አጣርቶ የሚደርስበትን ውጤትም ለህዝብ ይፋ እንደሚደረግ ቃል ተገብቷል፡፡

- ነገር ግን የጄኔራል አማን መገደልና በጦሩ ውስጥ የነበራቸው ተሰሚነት፤ እንዲሁም እሳቸውን ለመያዝ የታዘዙት ሁሉ አሻፈረኝ ማለት፣ ይህንንም ተከትሎ የተፈጠረው ፍርሃት ወለድ ምስቅልቅል ነገሮችን ለዋወጠ፡፡ ስለዚህ ደርግ "እቃ እቃ ፍርስርስ፣ አንድ እንጀራ ቁርስርስ" አይነት የልጆች ጨዋታ አድርጎት አረፈ የኮሚሽኑን ጉዳይ፡፡

ከዚያ በኋላማ ምኑ ቅጡ! "በለው፣ በለው፣ በለው!" ተባለ፡፡ ይህን ጉዳይ ራሳቸው መንግስቱ እለቱን እያስታወሱ አዳራሹ ውስጥ የተከሰተውን የዚያችን እለት ሁኔታ ሳይዋሹ ይተርኳታል፡፡

"... ምን የእኛ ነገር ... በለው! ነው" በማለት ስም እየጠቀሱ ትዝታቸውን አካፍለዋል፡፡ ቀንጨብ ቀንጨብ እያደረግን እንየው "... ትዝ ይለኛል መቶ አለቃ እገሌ ይባላል፡፡ ከሦስተኛ ክፍለ ጦር ህክምና ክፍል ነበር የመጣው፡፡ መቼም ተናጋሪ ነው እሣት ነው የሚተፋው፡፡ ብድግ ብሎ ሲናገር ቤቱን በጭብጨባ አናጋው፡፡ ዛሬ ታሪካዊ ቀን ናት፡፡ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ቀን ናት፡፡ ይህቺን ታሪካዊ ቀን እንጠቀምባት፡፡ ይሄን ዶሮ እየተቀለበ የተቀመጠ የወሎ ህዝብ ነብሰ ገዳይ (ረሃቡን) አንድ ውሣኔ ሳንሰጠው መሄድ የለብንም፡፡ አይሸታችሁም እንዴ ዶሮው?

ዛሬም'ኮ ደማችን እየመጠጠ በእስር ስም ተቀምጧል! እያለ ሲል ያ ቤት በጭብጨባ በሁካታ ተናጋ።...”

ሌሎችም እየተነሱ “ምንድነው ስለአንድ ጄኔራል የምትጠሩን? አማን አንድ ጄኔራል ነው ምንም አይደለም በአፍታ እንሸኘዋለን። ህዝቡ'ኮ የወሎን ህዝብ እልቂት ካዬ በኋላ ምንድነው እነኝህን አሳሞች ቁጭ አድርገው የሚቀልቡት? እያለን ነው። ይሄን አንድ ሳናደርግማ አንወጣም። የድጋፍ ጩኸቱ፣ ሁካታው ይቀጥላል...”

ሌላው ይነሳል “እነዚህ ሰዎች ምንድነው ሲሰሩ የኖሩት? በመቶ ሺዎች የሚቆጠር የወሎ ህዝብ በረሃብ ሲረግፍ ዝም ብለው ያዩ ሰዎች ናቸው። የረገፈው'ኮ ፍየል ወይም ዶሮ አይደለም” ይላል። ጥቂት በጣት የሚቆጠሩ አባላት “የለም፤ ለዚህማ መርማሪ ኮሚሽን ተቋቁሟል” ቢሉም ሰሚ የለም ይልቁንም “አፄ ኃይለስላሴ በላይ ዘለቀን የመሰለ አርበኛ በስሙኒ ገመድ እያንጠለጠለ ሲሰቅል የነበረው በየትኛው መርማሪ ኮሚሽን ተጣርቶ ነው?” በሚል መልስ ቀንዱን ይባላል።

በዚህ አይነት ቤቱ በፍፁም ተለወጠ ይላሉ መንግስቱ። “እኛ መቶ ሃያ ነን፤ በዚያ ሁሉ የንዑስ ደርግ አባላት ተዋጥን፤ ተደፈቅን። ጭብጨባ ነው! ቤቱ የሁካታ፣ የፉከራ ቤት ሆነ። ያመዛዛኝና የሕግ ቤት አልሆንም....” እያሉ ይቀጥላሉ። ሕግ የተማሩ የደርግ አባላት “ኸረ ጎበዝ ሕግ እየተጣሰ ...” ብለው ለማረጋጋት ሲሞክሩ “አብዮትና ሕግ መቼ ቀን አብሮ ሂዶ ያውቃል?” የሚል ምላሽ ያቋርጣቸዋል። “እነ እገሌን ያየሽ እንደሆነ ደግሞ በለው ነው! ሽለላ ነው የሚቀራቸው! ህዝቡስ ቢሆን? የዚያን ጊዜ በለው! ነው” (ትዝታዎች ቁ1 ገጽ 145)

ደርግ በስሜታዊነት የወደፊት መንገዱን ከወዲሁ ገለፀው። ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም ቀርቶ በደም ኢትዮጵያ ትቅደም ተተካ።

*የ“በለው” ፍርድና የ60ዎቹ ግድያ*

ውሣኔው የሚያስቅ፤ ፍርዱ የሚያሳቅቅ ነበር። በእርግጥ ከታሳሪዎቹ ከፍተኛ የጃንሆይ ዘመን ባለስልጣናት ውስጥ ብዙዎቹ ንቅዝ ሹማምንት መሆናቸው ይታወቃል። ጥቂቶቹ ግን ንፁህንና አገር ወዳድ እንደነበሩ ብዙዎች ይመሰክራሉ። ምንም ቢሆን ግን ያለፍርድ መገደላቸው በርካቶችን አሳዝኗል። ክሳቸውን ሳያውቁት፣ በጠበቃም ሆነ በራሳቸው ሳይከላከሉ፣ የእምነት የክህደት ቃል ሳይጠየቁ፤ በጥቅሉ የፍትህን አደባባይ ሳይረግጡ ውድ ህይወታቸውን ተነጥቀዋል። አሳቃቂነቱ እዚህ ላይ ሲሆን፤ አስቂኝነቱ ደግሞ የተሰብሳቢዎቹ የድምፅ አሰጣጥ ነው።

የእያንደንዱ እስረኛ ባለስልጣን ስም በየተራ እየተጠራ፤ ስለተጠራው ሰው ደግሞ እያንዳንዱ አባላት ሀሳቡን እንዲሰነዝር ይጠየቅ



ነበር። ለወትሮው ንዑስ የደርግ አባላቱ በማናቸውም አይነት ስብሰባ ድምፅ የመስጠት መብት አልነበራቸውም። እዚህ ላይ ግን መብት ተሰጥቷቸው እንደነበር ይነገራል። ለነገሩ እጅ በማውጣት ድምፅ የመስጠት መብት ባይኖራቸውም፤ በዚህ እለት ግን በድምፅ ጩኸት ብቻ “ይገደል!” ብለው ሞቅ አድርገው ካስተጋቡ ተሰሚነት ነበራቸው፤ አድርገውታልም።

ከአባላቱ ውስጥ ብዙዎቹ እስረኞችን አያውቋቸውም። በስብዕና ቀርቶ በመልክ የማያውቋቸው በርካታ ናቸው። ስለ ሰዎቹ የቀረበላቸው ማስረጃ የለም፤ ስማቸው ብቻ ቀርቦላቸው ነው ድምፅ የሚሰጡት። ዛሬ እንኳን በእስር ላይ ያሉት አባላት ስለተከሳሾች ወንጀል ቢጠየቁ መልስ መስጠት አይችሉም። ግን ድምፅ ሰጥተዋል።

ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም የተከሳሾቹን ስም ዝርዝር ይዘው ያነባሉ። ከወደመጀመሪያው ስም ይጠሩና “እኒህ ሰው እንዲህ እንዲህ አድርገዋል” የሚል አንድ ዓረፍተነገር ከስማቸው ጋር ያነባሉ (ያወራሉ)።ወንጀላቸውን መሆኑ ነው።ግድያውን የምትደግፉ እጃችሁን አውጡ ይባላል እጅ ይወጣል።ማውጣት ያለባቸው አባላቱ ቢሆኑም ንዑስ አባላቱም ሁሉም አዳራሹ ውስጥ ያለው ያወጣል።የድምፅ ቆጠራ በዚያ እለት ማከናወን የሞኝ ተግባር ከመሆኑም በላይ፤እጅ ያላወጣ ከተከሳሾች ጋር እንደሚቀላቀል ስለሚፈራ ያወጣል።እየቆዬ እጅ ከፍ ዝቅ ማድረጉ አሰለቸ፤አንድ ዓረፍተነገር የፈጠራ ወንጀል ጨምሮ ማንበቡ ጊዜ ገዳይ ሆነና መንግስቱ ስም ሲጠሩ አባላቱ “በለው!” ማለት ጀመሩ።

እንዳልካቸው መኮንን “ይሙት!” አክሊሉ ሀብተወልድ “በለው!” ሌተናል ጄኔራል ከበደ ገብሬ “በለው!” ለዑል ራስ አስራተ ካሣ “ይሙት፣ ይሙት!” ራስ መስፍን ስለሽ “ይገደል!” ዶ/ር ተስፋዬ ገብረዝጊ “በለው!” ደጃዝማች ሰለሞን አብርሃ “በለው!” እንዲህ ሆኖ 14· ጄኔራሎች፣ 6 ኮሎኔሎች፣ 8 ደጃዝማች፣ 3 ፊትአውራሪ፣ 2 ራስ የተካተቱባቸውንና ሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣናትንና ሚኒስትሮችን፣ የባህር ኃይል ዋና አዛዡን ሪር አድሚራል እስክንድር ደስታን ጨምሮ (የጃንሆይ የልጅ ልጅ) በእጅ ብልጫና በድምፅ ብልጫ አዳራሽ ውስጥ ተሰብስበው ሞት ፈረዱባቸው።

እነዚህም በተለምዶ 60 የቀደሞው ባለስልጣናት ይባሉ እንጂ፤52ቱ ብቻ ናቸው የጃንሆይ ዘመን ከፍተኛ ባለሥልጣናት። የቀሩት 8ቱ የራሱ የደርግ አባል የነበሩ ሲሆን፤ ወታደራዊ ማሃላቸውን የጣሱ፣ በጦሩ ውስጥ ልዩነት ለመፍጠር የሞከሩ ተብለው የተወነጀሉ ነበሩ።

“... እኔም ሆንኩ የደርግ አባላት ከተገደሉት ሰዎች በጣም ጥቂቶቹን ብቻ ነው የምናውቃቸው። በበኩሌ በሠራዊቱ ውስጥ ከነበሩት ከፍተኛ አዛዦች ጥቂቶቹን ከማወቄ በስተቀር አብዛኛዎቹን ራስ እገሌ፣ ደጃዝማች እገሌ ሲባል ስማቸውን ከምሰማ በስተቀር አላውቃቸውም።...”

የሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም መልስ ነው፡፡ (ትዝታዎች ቁ.1 ገፅ 163) ይሄ ነው አስቂኙ ፍርድ፡፡

ለጥቂት ወራት ያህል ታስረው የቆዩት የቀድሞው ባለስልጣናት ህዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም ሞት ከተበየነባቸው በኋላ ምሽት ላይ ከታሰሩበት ከታላቁ ቤተ-መንግስት ጊቢ ውስጥ በጃንሆይ ጊዜ ለጠጅ ማቀዝቀገር ያገለግሉ ከነበሩት የምድር ቤት ክፍሎች እየተጠሩ እንዲወጡ ከተደረገ በኋላ ሁለት ሁለት ሆነው እየተጣመሩ በካቴና ታስሩና በትልቅ ካሚዮን ተጫኑ፡፡ ደርግ መቼም ፈጣን ነው ሁሉንም ነገር አዘጋጅቷል፡፡ የጫናቸው ካሚዮን ወደ ዋናው ወህኒ ቤት ነበር የሚነጉደው፡፡ ታሳሪዎቹ በውስጣቸው ተስፋ አለ፡፡ ቤተሰብ አይጠይቃቸው ስለነበር ከዚህ በኋላ ጥየቃ ያለበት ቦታ ሊታሰሩ እንደሚችሉ ጠብቀዋል፡፡ ወህኒ ቤቱ ጊቢ ውስጥ ደርሰው ከመኪና ሲወርዱ በውስጣቸው የነበረው ተስፋ ሳያንሰራራ አይቀርም፡፡ ሆኖም ከወረዱ በኋላ እስረኞች ወደሚታሰሩበት ቦታ የሚወስደውን መንገድ ትተው ታጠፉና ድቅድቅ ጭለማ ውስጥ ተደርድረው እንዲቆሙ ተደረገ፡፡ ለመደንገጥ የሚያበቃ ጊዜ አላገኙም፤ በተጠንቀቅ ቆመው ይጠብቋቸው የነበሩ ወታደሮች በእሩምታ ተኩስ ይረሽኗቸዋል፡፡ ወዲያውም እዚያው በቡልዶዘር በተቆፈረ ወጥ ጉድጓድ ውስጥ በጅምላ ተቀብረው አፈሩ ተመልሶ እንደቀድሞው ሜዳ ሆነ፡፡

ህዳር 15 ቀን 1967 ዓ.ም ደርግ በብዙሃን መገናኛ ይህን ጉዳይ ይፋ አደረገ፡፡ "በእስር ላይ የነበሩት የቀድሞው ባለስልጣናት በትናንትናው እለት አማንን ጨምሮ አብዮታዊ እርምጃ ተወስዶባቸዋል!" በማለት ሲገለፅ ድፍን የኢትዮጵያ ህዝብ በአግራሞትና በድንጋጤ ነበር ያደመጠው፡፡

ጂሚ ካርተርማ ይሄን ወሬ እንደሰሙ በድንጋጤ ባሉበት ደርቀው ቀሩ ማለት ይቻላል፡፡ በዚያው ወቅት "የዓለም ሰብዓዊ መብት ጥበቃ መሪ እሆናለሁ" በሚል ማኑፌስቶ የአሜሪካንን ምርጫ አሸንፈው ፕሬዝዳንት የሆኑት ካርተር "ያለምንም ደም" የተሰኘውን የኢትዮጵያ አብዮት በበጎ ዓይን አይተውት ነበር፡፡ ሆኖም ወዲያው በደም መጀመሩን ሲያዩ ክፉኛ ተቃወሙት፡፡ ሳይውሉ ሳያድሩም በኢትዮጵያ ላይ ጠንካራ አቋም በመውሰድ ፊታቸውን አዞሩ፡፡

የኢትዮጵያና የአሜሪካ ጉዳይም በዚሁ ያከትማል፡፡ እንጂማ ደርግ በመጀመሪያ ያንኳኳው የአሜሪካንን ደጃፍ ነበር፡፡ መንግስቱ ሐራሬ ሆነው ለሪካርዶ ኦሪዚዮ እንዲህ ብለውታል፤ "... የቆምኩት ከጎናችሁ ነው፤ ሁለቱ ሀገሮቻችን የረጅም ጊዜ ወዳጆች ናቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ ኢትዮጵያ ከእናንተ ጎን ተሰልፋ ወታደር በመላክ በኮሪያ ጦርነት ተካፍላለች፡፡ አሁን ሀገራችንን እንደገና ለመገንባትና ለማሳደግ የእናንተን እርዳታ እንፈልጋለን፤ በማለት የአሜሪካኖችን በር አንኳኳሁ" አሉና ለጊዜው



ንግግራቸውን አቋርጠው በትዝታ ጭል...ጥ አሉ፡፡ ወዲያው ቀጠሉና "ካርተር በሰጡኝ መልስ የቬትናም ጉዳይ ከአቅም በላይ እንደሆነባቸውና በስትራቴጂ ደረጃም አፍሪካ ላይ ምንም ትኩረት እንደሌላቸው ገለፁልኝ፡፡

"... ቀጥዬ ያንኳኳሁት የቻይናን በር ነበር፡፡ ሆኖም ከቁም ነገር የቆጠረኝ ሰው አላገኘሁም፡፡ መጨረሻ ላይ ፊቴን ወደ ሞስኮ፤ ወደ ሊዎኔድ ብሬዥኔቭ አዞርኩ፡፡ እውነቴን ነው የምልህ ለመጀመሪያ ጊዜ በክሬሚሊን ቤተ-መንግስት እንዴት አድርገው አንገቴን አቅፈው እንደተቀበሉኝ አሁንም ድረስ ትዝ ይለኛል" አሉ፡፡

ሪካርዶ ኦሪዚዮ ትረካውን ይቀጥላል፤ ... "መንግስቱ የዚያን ጊዜውን ሁኔታ በዓይነህሊናቸው እያስታወሱ፤ ዝም እንዳሉ ቀሩ፡፡ አፍሪካዊው ፕሬዝዳንት በዚያን ቀን የብረት መጋረጃ ሀገራት መሪዎች አድርገውት ያዩትንና ከግልገል በግ ፀጉር የተሰራውን የሱፍ ባርኔጣ አድርገው ነበር፡፡ በወቅቱ የነበረው የሞስኮ አየር ከመቀዝቀዙም በላይ ኢትዮጵያ ለመጡት ወጣት መኮንን የፖለቲካው አየር ብዙም የሚሞቅ አልነበረም፡፡

መንግስቱ ይቀጥላሉ "እናም ስለሁኔታው ለብሬዥኔቭ ገልጬ ሳስረዳቸው "መንግስቱ ሀገሬ ከአቶሚክ ቦንብ በስተቀር ያስፈልገኛል የሚሉትን ነገር ሁሉ ልትሰጥዎት ፈቃደኛ ነች" የሚል መልስ ሰጡኝ፡፡ እንግዲህ ግንኙነቱ የተጀመረው በዚህ መልክ ነበር" አሉ መንግስቱ፡፡ ሲቀጥሉም "የሶቭየት እርዳታ በቃላት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በማቴሪያልም ጭምር ነበር፡፡ ከዚያች ቀን በኋላ ብሬዥኔቭ ልክ እንደ አባቴ ሆኑ፡፡ ለ12 ጊዜ የተገናኘን ሲሆን፤ ሁሉም ግንኙነታችን የተደረገው እዚያው ሞስኮ ውስጥ ነበር፡፡ በተገኘንን ቁጥር ችግሬን ከመናገሬ በፊት ምንጊዜም "ጓድ ብሬዥኔቭ ልጅዎ ነኝ፡፡ ውለታዎም ይህ ነው አይባልም" ነበር የምላቸው፡፡ እውነትም ታዲያ ብሬዥኔቭን የማያቸው ልክ እንደወለዱኝ አባቴ ነበር" /Talk of the Devil/ ኢትዮጲያና ሶቭየት በዚህ መልኩ ተጣብቀው ቀሩ፡፡

ደርግ የቀድሞ የጃንሆይ ባለስልጣናትን መገደል ይፋ ካደረገ በኋላ ያሰጋው የህዝብ ተቃውሞ የፈራውን ያህል ሆኖ ሳይደመጥ ቀረ፡፡ የደርግ ቀጣይ ስራ በተገደሉት በጄኔራል አማን ምትክ አንድ አሯሯጭ ከፊት ማስቀደም ነበርና ብርጋዴል ጄኔራል ተፈሪ በንቲን መርጦ የደርግ ሊቀመንበር ብሎ ሾመ፡፡ መንግስቱም በምክትልነታቸው ቀጠሉ፡፡

*የአብዮቱ ፍሬዎች*

የደርግ ታሪክ ገለባ ብቻ ተደርጎ በተደጋጋሚ ይወሳል፡፡ ነገር ግን ገለባው ይብዛ እንጂ በውስጡ ፍሬዎች ነበሩት፡፡

ደርግ ያንን የ"በለው" ፍርድና የአማንን ግድያ ለማለዘብ ሁለት አፋጣኝ ስራዎች ይጠብቁት ነበር፡፡ የመጀመሪያውን በአገር ውስጥና

ከአገር ውጪ በወታደራዊ ተግባራቶች ተሰማርተው አገራቸውን ያገለገሉትንና በሠራዊቱም ዘንድ ተወዳጅነት ያላቸው፣ ነገር ግን እንደ ጄኔራል አማን የስልጣን ጥም የማይንፀባረቅባቸውን የሁለተኛው ክፍለ ጦር አባል ብርጋዴር ጄኔራል ተፈሪ በንቲን በአማን ቦታ መተካት ነበረበትና እሱኑ ተግባራዊ አደረገ፡፡ የኦሮሞ ተወላጅ ስለነበሩም ሰፊውን የኦሮሞ ማኅበረሰብ ድጋፍ ያስገኛሉ ተብሎ ታስቧል፡፡ በዚህ ሹመት የደርግን አካሄድ በጥርጣሬ ዓይን ለማየት የተዘጋጀውን የሚሊቴሪ ክፍል ለማረጋጋት ተቻለ፡፡

በሌላ በኩል ሲቪሉን ህብረተሰብ ዳር እስከ ዳር፣ ከምሁር እስከ ገበሬ የሚያስፈነድቅ ተግባር ጊዜ ሳይሰጥ ማከናወን ነበረበትና እሱኑ ተግባራዊ አደረገ፡፡

በእነ ዶ/ር ሠናይ ልኬ እና ኃይሌ ፊዳ ምክር በመደገፍ ሶሻሊስታዊውን ስርዓት ዘረጋ፡፡ የሠራተኛ አዋጅ አሻሽሎ ካወጣ በኋላ፣ የእድገት በኅብረት የእውቀትና የስራ ዘመቻንም በማወጅ የኢኮኖሚ ፖሊሲውን ቀየሰ፡፡

ታህሳስ 11 ቀን 1967 ዓ.ም "የኢትዮጵያ የእድገት ጎዳና የሚመራው በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ነው" ሲል ይፋ አደረገ፡፡ በዚህ አዋጁ ምሁራኑንና የግራ ክንፍ ኅቡዕ ቡድኖችን ሁሉ በደስታ አዘለለ፡፡አዋጁ ይፋ በሆነ ማግስት የተማረው ወጣት ትውልድ ወደ ገጠሩ እንዲዘምት የቀረበለትን ጥሪ በደስታ ተቀበለ፡፡

ታህሳስ 12 ቀን የእድገት በኅብረት የስራ ዘመቻ የክተት አዋጅ በዓል በድፍን ኢትዮጵያ ተከበረ፡፡ ለዘመቻው 60 ሺ ተማሪዎችን የወከሉ የአዲስ አበባ ዘማቾች እለቱን ለማክበር በጃንሜዳ ተሰለፉ፡፡ በዓሉን በጋራ ለማክበር በጃን ሜዳ ሰልፍ ላይ ሦስቱ ሊቀመናብርት ማለትም ጄኔራል ተፈሪ በንቲ፣ ሻለቃ መንግስቱና ሻለቃ አጥናፉ አባተ ተገኝተዋል፡፡ ያ ሁሉ ህዝብ በአንድ ድምፅ "መንጌ! መንጌ! መንጌ!" ሲል ጮኸ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሊቀመናብርቱ በአደባባይ ታዩ፡፡ መንግስቱም ላንቃው እስኪሰነጠቅ ስማቸውን እየጠራ ለደቂቃዎች ያህል የቆየውን ህዝብ ሲያዩ ልዩ ስሜት ተሰማቸው፡፡

ደርግ የጋራ ውሣኔ አሳልፎ ያንን ግድያ ከፈፀመ በኋላ ስልጣን አስረክቦ ወደ ካምፕ መመለስ ማለት እራስን ለፍርድ ማቅረብ መሆኑን ያውቃል፡፡ እንኳን ይህ ምክንያት ኖሮ ባይኖር እንኳ ስልጣን አስረክቦ የመመለስ እቅድ አልነበረውም፡፡ ስለዚህ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስትነቱን ትቶ ቋሚነቱን አጠናክሮ ከመቀጠል ሌላ ምርጫ ስላልነበረው፣ በተቻለ መጠን የምሁራኑን ሀሳብ የራሱ አድርጎ ወደተግባር መተርጎምና አገሪቱን መምራት ነበረበት፡፡ ጊዜያዊ መንግስትነቱን ግን ለሸፋንም ቢሆን አልቀየረም፡፡ እናም ደርግ ርዕዮቱን ሶሻሊዝም አድርጎ



ሳይውል ሳያድር የገጠሩን ህይወት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመቀየር የነደፈውን እቅድ ተግባራዊ አድርጓል፡፡

ይህ "ብሔራዊ የእድገት በኅብረት ዘመቻ" ዓላማው የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችንና መምህራንን ወደ ገጠር በማዝመት የኢትዮጵያ ትቅደምን መርህ መሠረት ያደረጉ የልማት እንቅስቃሴዎችን እንዲመሩ ማድረግ ነው፡፡

እቅዱ በትክክለኛ ሚዛን ሲቀመጥ ኢትዮጵያን ከኋላቀርነት ለማውጣት የሚረዳና፣ በተለይም በተማረው ክፍል የምክር፣ የትምህርትና የጉልበት ድጋፍ የገበሬው ህይወት የተሻለ እንዲሆን የሚያደርግ ነበር፡፡ ይህን በመረዳትም ነው ብዙሃኑ ምሁራን በደስታ የተቀበሉትና የዘመቱት፡፡ ሆኖም የደርግ የስልጣን ተፋላሚ የሆነው ኢህአፓ ብቻ የእቅዱ ተቃዋሚ ሆነ፡፡ ምክንያቱንም ሲያስቀምጥ፣ "የተማረውን ክፍል በልማት ስም ወደ ገጠሩ በማግለል ደርግ ብቻውን በስልጣን ላይ ለመደላደል ሲል የነደፈው" በማለት ነው፡፡ ኢህአፓ ሰሚ አላገኘም፣ ዘማቾቹ የድጋፍ ሰልፋቸውን ካሳዩ በኋላ ወደ ገጠር ዘመቱ፡፡ የገጠሩን ህይወት የመለወጡን ተግባርም ተያያዙት፡፡



ዘማች ተማሪዎች ተግባራቸውን ሲወጡ

ደርግ የግራ ኃይሎችን ተቃውሞ ወዲያው ለማለዘብ የኢትዮጵያ ትቅደምን መርህ በመከለስ "ዓላማችን ኅብረተሰባዊነት፣ ርዕዮታችን ሶሻሊዝም ነው" ቢልም፣ ብቸኛ ዓላማቸው ስልጣን ብቻ የነበረው ተቃዋሚዎች (ኢህአፓዎች) ሊሰሙት አልቻሉም፡፡

ደርግ እያራመደ ያለው የኢህአፓንና የመኢሶንን ማኑፌስቶ ነው፡፡ መኢሶን ከደርግ (ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን) ተለጥፎ የነበረ ሲሆን፣ ኢህአፓ በውጭ ሆኖ ነበር የሚሞግተው፡፡ ደርግም ከመኢሶን መስራች ምሁራን በሚቀበለው እቅድ ስራውን ቀጥሏል፡፡ የንግድ፣ የኢንደስትሪና የገንዘብ ተቋማትንም ደርግ ወርሷል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም የጃንሆይ ተቃዋሚ የነበሩ ምሁራን ለዘመናት ሲያቀነቅኑት የኖሩትና በጉጉት ይጠብቁት የነበረውን የመሬት ስሪት

አዋጅ ደርግ ይፋ አደረገ፡፡ ይህም ብዙዎቹን ያስፈነደቀ አዋጅ ሆነና፤ በተለይ የገጠሩን ህይወት በመለወጡ ተግባር የተሰማሩትን ዘማቾች የበለጠ በደስታ እንዲሰሩ አደረጋቸው፡፡ ይህ የመሬት ጉዳይ የጃንሆይን መንግስት ለመገልበጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የሞከሩት የእነመንግስቱ ንዋይ ማኑፌስቶ ውስጥ የተካተተ ነበር፤ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች "መሬት ላራሹ" እያሉ የሞቱለት ነበር፡፡ የመጨረሻው የእንደልካቸው ካቢኔም ትኩረት ሰጥቶ እልባት ሊሰጠው ስራ የጀመረበት ሁኔታ ነበር፡፡ በመጨረሻ ደርግ እልባት ሲሰጠው የሚኖረውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ መገመት አይከብድም፡፡

ለዚህም ነው ህዝቡ የተለያዩ የድጋፍ መፈክሮችን ይዞ በአደባባይ ደስታውን የገለፀው፡፡ "የካቲት 25 የሰፊው ህዝብ የልደት ቀን ነው!" "የኢትዮጰያ ትንሳኤ ልደት ዛሬ ነው!" የሚሉ መፈክሮች በደማቁ ህዝባዊ የድጋፍ ሠላማዊ ሰልፍ ላይ ተነበዋል፡፡

የየካቲት 25ቱ አዋጅ በታሪካዊቷ ኢትዮጵያ የመሬት ጥያቄ ጉዳይ ወደር ያልተገኘለት የተሰኘውን ምላሽ ደርግ በመስጠቱ አክራሪ የግራ ክንፍ ተቃዋሚዎችን ሳይቀር ኩምሽሽ ያደረገና የሚቃወሙበትን ነጥብ ያሳጣ ነበር፡፡

አዋጁ የግል የመሬት ይዞታን የሚያስወግድና፣ የገጠር መሬት የማይሸጥ፣ በሊዝ የማይተላለፍ፣ በዋስትና መያዣነት የማይያዝ፣ ገበሬው "በምርት ተግባር ላይ ብቻ" ሊያውለው የሚችል የግል ንብረቱ ሆነ፡፡

አዋጁ የመሬት ይዞታን በአስር ሔክታር ሲወስን፤ ከዚያ የተረፈውንም ቀድሞ በሰው መሬት ላይ በጉልበቱ ያገለግል ለነበረው መሬት አልባ ጭሰኛ በመስጠት መሬት አልባውን ባለመሬት ያደረገ ሆነ፡፡



የመሬት አዋጁን ደግፈው ሰልፍ የወጡ ዜጎች

ለአዋጁ ተግባራዊነትና ስኬታማነት፤ እንዲሁም ዘላቂነት ይረዳ ዘንድም፣ እንደአስፈላጊነቱ የመሬት ድልድል የማድረግ ስልጣን ያላቸውን



የገበሬዎች ማኅበር አቋቋመ፡፡ የመሬት ላራሹን ጥያቄ የመለሰው ታሪካዊው አዋጅ የቀድሞዎቹን የመሬት ከበርቴዎች ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚገባቸውን ጣራ አስተርፎላቸው ሌላውን ወስዶ ለጭሰኞችና ለመሬት አልባዎች ሲሰጥ፤ በተለይ ከአፄ ምኒልክ ጀምሮ እስከ አፄ ኃይለስላሴ ዘመን ድረስ ለሹማምንቱ ይሰጥ የነበረው የመሬት ስጦታ በአገሪቱ ደቡባዊ ክፍል ነበርና፤ በርካታ ጭሰኞችም የነበሩት በዚያ ክልል ስለሆነ በከፍተኛ የደስታ ስሜት ተውጠው፤እስከመጨረሻው የደርግ ደጋፊዎች ሆነው ሲቀጥሉ፤ በተቃራኒው የመሬት ከበርቱ ሆነው ለዘመናት የቆዩት የሰሜኑ ክፍል ሹማምንት ግን የደርግ ተቃዋሚ ሆነው ዘለቁ፡፡ በስተመጨረሻም ፖለቲካዊ ጥያቄ ይዘው ቀድመው የትጥቅ ትግል የጀመሩትን ቡድኖች መቀላቀል ጀመሩ፡፡ መዝመት ያልቻሉትም ድጋፍ ማድረጋቸውን ቀጠሉ፡፡

ደርግ እነዚህን አዋጆች በተግባር ላይ ካዋለ ከጥቂት ወራት በኋላ ሐምሌ 19 ቀን 1967 ዓ.ም ደግሞ የከተማ መሬትንና ትርፍ ቤቶችን የመንግስት ያደረገውን አዋጅ አወጀ፡፡ ይህ አዋጅም የ"ኅብረተሰባዊነት"ን መርህ መሠረት ያደረገ፤ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፍትህን ለማስፈን፣ የዜጎችን እኩልነት ለማምጣት የተወሰደ የደርግ ቅን እርምጃ ነበር፡፡

የቀድሞዎቹ ንቅዝ ሹማምንት ከሕግ ውጪም ሆነ በሕጋዊ መንገድ ካግበሰበሱት ከገጠር መሬት ባለፈ በከተማውም ቦታና ቤት ላይ አስፍተው ይዘው ነበር፡፡ በዚህ ዘመን አገላለፅ "ኪራይ ሰብሳቢነት" የጃንሆይ ዘመን ሹማምንት አንዱ መገለጫቸው ነበር፡፡ ስለዚህ ደርግ ትርፍ ቤቶቹን ወስዶ ለቤት አልባዎች በአዋጁ መሠረት ሰጠ፡፡ ትልልቅ የግል ህንፃዎችንም ወርሶ ኪራያቸው ለአገር ጥቅም በመንግስት በኩል የሚውልበትንና አንዳንዶችንም ለአስተዳደር ስራዎች ይገለገልባቸው ጀመር፡፡ አነስተኛ ትርፍ ቤቶችን ወስዶ ለቤት አልባዎች.ሲያድልም ለገጠሩ መሬት የገበሬ ማኅበራት እንዳቋቋመው ሁሉ፤ለዚህም ቤቶቹን እንዲያስተዳድሩ ስልጣን የተሰጣቸው የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት ማለትም ቀበሌዎችን አደራጅቶ ለቁጥጥር መደባቸው፡፡

እነዚህን የመሳሰሉ የሶሻሊዝም ርዕዮት አምጦ የሚወልዳቸውና የኅብረተሰቡን ኑሮ የሚያሻሽሉ፣ የሐብትን ልዩነት ስፋት ገድበው የሚያቀራርቡ በጎ እርምጃዎች ሲወሰዱ፤ እንደማንኛውም ርዕዮት አፈፃፀማቸው ላይ ልዩ ጥንቃቄ ካልተደረገባቸው ውጤታቸው አጠያያቂ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ ርዕዮቱ በራሱ በአንድ አገር ተግባሪዊ ሲደረግ የሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ይሁንታ ካላገኘ የተጠበቀው ለውጥ አይመጣም፡፡ በኢትዮጵያም የታየው ይሄ ነው፡፡ አብዮት በተከናወነባቸው አገራት ሁሉ አኩራፊ ቡድን ጠፍቶ አያውቅም፡፡ የሶሻሊስት አራማጅ አብዮተኛ መንግስት እነዚያን አኩራፊ ቡድን አገራዊ ፍቅር

እንዲያድርባቸውና፤ በገፍ የያዙት ሐብትና ንብረት ለአገራቸው ተቆርሶ ቢሰጥና ማኅበራዊ ለውጥ ቢመጣ ተጠቃሚዎች ራሳቸው መሆናቸውን ማሳመን ይጠበቅበታል፡፡ ከራስ ጥቅም ይልቅ የሀገርን ጥቅም የማስቀደም ባህል ያላቸው ህዝቦች ያሏት አገር ብቻ ሳያኮርፉ "ይሁን" በማለታቸው በርዕዮቱ ተጠቃሚ ሆነው ያለፉ አገራት ታይተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ግን አኩራፊዎችን ማሳመን አልተቻለም፡፡ አይቻልምም፡፡ ምክንያቱም ኩርፊያው የርዕዮትና ርዕዮቱን ተከትሎ በሚመጣው ጉዳይ ስላልሆነና በስልጣን ብቻ ስለሆነ ነው፡፡ የብዙሃኑ ምናልባትም ከጃንሆይ ዘመን ባለስልጣናትና ሹማምንት በስተቀር የሁሉም ህዝቦች፣ የተደራጁ የግራ ክንፍ ተቃዋሚ ቡድኖች፣ በአገር ውስጥም በውጭም ያሉ የቀድሞው አገዛዝ ተቃዋሚዎች ዓላማና ርዕዮት ደርግ እየተገበረው ያለው ነው፡፡ ከተገንጣይና አስገንጣይ ቡድኖች ውጪ ሁሉም የዚህ መፈክር አራማጅ ነበር፡፡

ስለዚህ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንደሚባለው ሆነ፡፡ ርዕዮቱ በራሱ በአፈፃፀም ችግር የሚፈጥረው ቀውስ አልበቃ ብሎ፤ ጭራሽ የተደራጀ ተቃዋሚ ቡድን በኢትዮጵያ ኖሮ የደርግን የሚደግፍ (ሁሉም ሲመኘው የነበረውን) አዋጅና ተግባር ማጨናገል ደርግን ለመቃወም ከሚተኩሷቸው መሣሪያዎች ያልተናነሰ የማጥቂያ መሣሪያ አደረጉት ኢህአፓዎች፡፡

የደርግ መንግስት የእድገት በኅብረትን እቅድ ተግባራዊ ሲያደርግና ዘማቾቹም በሙሉ ልብ ችግር ያደቀቀውን አርሶ አደር ያሳተፈ ስልት እየተከተሉ ስራቸውን ሲሰሩ፤ ከዘማች ተማሪዎች ውስጥ የተቃዋሚ ኃይሉ ደጋፊዎችም ተካተው ዘምተዋል፡፡ ይህም አልበቃ ብሎ ተማሪዎች ገበሬውን በመለወጡ ተግባር ላይ ሲያተኩሩ፤ የደርግ ባለስልጣናት ደግሞ ቢሮክራሲው ላይ አተኮሩ፡፡

ቀስ በቀስም የዘመቻ ጣቢያዎች ደርግና ደጋፊዎቹ በአንድ ወገን፣ የደርግ ተቃዋሚ የኢህአፓ አባላትና ደጋፊዎቹ በሌላ ወገን ሆነው የሚፋለሙበት ምቹ መድረክ ሆነ፡፡ ዘመቻው እየተራዘመ በሄደ ቁጥርም ፍልሚያው አብሮ እየተጋጋለ ስለሄደ ተቃዋሚዎች የዘመቻ ምድብ ጣቢያቸውን እየለቀቁ የስልጣን ፍልሚያ ለማድረግ ምቹ ወደሆነችው ወደ አዲስ አበባ መምጣት ጀመሩ፡፡ ሙግቱንም ቀጠሉ፡፡ ደርግ የሚከተለውን ርዕዮት መሰረት በማድረግ የወሰዳቸው እርምጃዎች የርዕዮቱ አንድ አካል /አሠራር/ ነውና ከገጠር መሬት ስሪቱ በኋላ አርሶ አደሩ ምርቱን መንግስት በተመነው ዋጋ ለመንግስት ብቻ እንዲያቀርብ ተብሎ ለተቋቋመው የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት ማቅረብ ነበረበት፡፡



የከተማ መሬትንና ትርፍ ቤቶችን በሚመለከት ተግባራዊ የሆነው አዋጅም ብዙዎቹን ተጠቃሚ ማድረጉ ባይዘነጋም፤ ስልጣን የተሰጣቸው ቀበሌዎች ከአስተዳደር ስራቸው ይልቅ ቁጥጥሩ ላይ በረቱ፡፡

በአንድና በሌላ አገላለፅ የደርግ መንግስት፤ የአገር ሐብት ሆነው ሳለ በግለሰብ እጅ ገብተው ቀርተው የነበሩትን ሐብቶች ወደ መንግስት እጅ በማዛወሩና ፍትሐዊ ክፍፍል በማድረጉ ተጠቃሚ የሆነው ብዙሃኑ ህዝብ በደርግ ቁጥጥር ስር መሆን ነበረበት፡፡ ያጠፋውን ቀጪ፣ ታምኖ ያገለገለውን ሸላሚ ደርግ ሆነ፡፡ በመንግስት እጅ የገቡት የኢኮኖሚ አውታሮች የደርግን ስልጣን ለማደላደል ረዱት፡፡

ከገጠሩ ዘመቻ ለቀው የመጡትም ሆኑ በከተማ የነበሩት ተቃዋሚዎች ከርዕዮቱ ጋር ሳይሆን ርዕዮቱን ተከትለው በሚመጡ ችግሮች መነሻነት የጠላትነት ክርክራቸውን ያጧጧፉትም በእነዚህ ክፍተቶች እየሆነ ሄደ፡፡

የመሬት ስሪቱን "ምርታማነት ወይስ ፍትሐዊነት?" ሲሉ ተቹት፡፡ ገበሬው በመሬቱ ላይ ያለው ስልጣን በማምረት ብቻ መወሰኑም "የባለቤትነት ስሜት ካላደረበትና በባለቤትነት የተሰጠውን መሬት ያሻውን ካላደረገው ትርጉም የለውም" የሚል ነቀፋ ጀመሩ፡፡ ከዚህም ባለፈ ከመሬት አዋጁ ጋር በተያያዘ አዲስ የሰፈራ ፕሮግራም መደረጉ የግድ ነበርና፤ ይሄንንም "በሰፋሪው ፈቃደኝነት ላይ ያልተመሠረተ ነው" አሉት፡፡ የሚገርመው ይሄን ሁሉ የተቃውሞ ትችት የሚያዥጎደጉዱት ተቃዋሚዎች ማርክሳዊ መፈክርን ያነገቡ መሆናቸው ነው፡፡ ምንም ቢባል ግን እነዚህ የደርግ ወይም የአብዮቱ ፍሬዎች ብዙሃኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ተጠቃሚ ማድረጋቸው አይዘነጋም፡፡

ከእነዚህ አዋጆች ተግባራዊነት ጋር በተያያዘ የተከሰተው አንኳር ችግር ግን የአገሪቱ ኢኮኖሚ በደርግ መንግስት ቁጥጥር ስር ሆኖ ሲቀጥል የግሉ ዘርፍ እየተሽመደመደ መሄዱ ነው፡፡ (ይህን ያስተዋሉት የቢዝነስ አድሚንስትሬሽን ትምህርት የተከታተሉት ከመንግስቱ ቀጥሎ ስልጣን የነበራቸው ሻለቃ አጥናፉ "ቅይጥ ኢኮኖሚ" /mixed economy/ ይሻለናል ብለው ነበር፡፡ በዚህች ንግግራቸውም ነበር በደርግ የተገደሉት፡፡)

እንግዲህ ከተማን ማዕከል ያደረገው የደርግ እርምጃ በትርፍ ቦታና ቤት ዙሪያ እንደመሆኑ መጠን አዲስ የቤት ቁጥር የተሰጣቸው ተጠቃሚዎችም እንቅስቃሴያቸው ሁሉ በመንግስት ቁጥጥር ሆኖ፤ ያስተዳደር ስልጣን በተሰጣቸው የቀበሌ ሹማምንት መዳፍ ስር ገብተዋል፡፡ ሲሆን በስለላ አሊያ በጥቆማ ቀበሌውን መርዳት ነበረባቸው፡፡ ቀበሌውም ተቃዋሚዎችን ያድናቸው ነበር፡፡

በእነዚህ መሰል መነሻዎችም ነው በቀጣዮቹ ተከታታይ አመታት የኢህአፓ ታጣቂዎች የቀበሌ መሪዎችን፣ የቀበሌ መሪዎች የኢህአፓ

ታጣቂዎችን እያደኑ መግደል ባህላቸው ያደረጉትና ነጭና ቀይ ሽብር ድረስ ያዘለቁት፡፡

ደርግ የጎን ውጋት የሆነበትን ኢህአፓን እርሙን ያወጣ ዘንድ ጥቂት ምሁራንን ከጎኑ አድርጎ በሚያዚያ 12 ቀን 1968 ዓ.ም የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮትን መመሪያ አድርጎ አወጀ፡፡ ይህች ከቻይና አብዮት የተኮረጀች ቀመርም ዓላማና ግቧ በወዝአደሩ፣ በአርሶ አደሩና በንዑስ ከበርቴው አብዮታዊ ጥምረት የሰፊው ህዝብ ጠላቶች ተብለው የተፈረጁትን ፊውዳሊዝምን፣ ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን ድራሻቸውን ማጥፋትና፤ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መመስረት ነው፡፡ ይህም ኢሠፓአኮ፣ ኢሰፓ፣... ወዘተ... እየተባለ ቀጥሎ ወደፊት እንደምናየው በ1980 ዓ.ም እውን መሆን የቻለ ሲሆን፤ተጀምሮ እስኪጨረስም ብቸኛው መሪ መንግስቱ ኃይለማርያም ሆነው እንዲቀሩ ሆኗል፡፡

ሶሻሊስታዊ ስርዓትን መመሪያው አድርጎ በመንግስቱ ኃይለማርያም መሪነት ለ17 ዓመታት የዘለቀው የደርግ አገዛዝ፤ በአብዮቱ ማግስት ቀደም ሲል ያየናቸውን ለውጦች አምጥቷል፤ ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብም ከአብዮቱ የድል ፍሬዎች ተቋዳሽ በመሆኑ ተጠቃሚ ሆኗል፡፡ ደርግ ስልጣን ላይ በቆየባቸው ከ1967-1983 ድረስም እንደ መንግስት ለአገር መስራት ያለበትን ስራ ሠርቷል፡፡ የመሠረተ ልማት አውታሮችን ዘርግቷል፣ የኢንደስትሪ ተቋማትን ገንብቷል፣ ማሃይምነትን ለማስወገድ ልዩ ጥረት አድርጓል፡፡ ጥቂቶቹን ከወዲሁ በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ጠቃቅሶ ለማለፍ ያህል፤ የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ቁ.4/ሀ/ "ለሰፊው ህዝብ እድገትና ለተሟላ ኑሮ የሚያገለግል፣ ለህዝብ ልጆች በሙሉ የሚደርስ፣ ለፀረ ፊውዳል፣ ለፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል የሚያግዝ ነፃ ትምህርት ደረጃ በደረጃ እንዲስፋፋና ማሃይምነት ከአገሪቱ እንዲጠፋ የሚደረግ መሆኑን" ስለሚገልፅ ይህን አዋጅ መሠረት አድርጎ በገጠርም በከተማም ተግባራዊ በማድረግ ከፍተኛ ለውጥ አሳይቷል፡፡ "የማይጽፉ እጆች፣ የማያነቡ ዓይኖች አይኖሩም" በሚል መፈክር በአንድ ዙር የ3 ወር ዘመቻ ብቻ 1,543,678 ሰዎችን ከመሃይምነት አላቋል፡፡ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና በኮሌጆች በመማር ላይ የነበሩትን ተማሪዎች በ10 ዓመት ውስጥ በ33 በመቶ ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡

በሶሻሊስት አገሮች ትምህርት በነፃ ስለሚሰጥም በግል ተይዘው የነበሩትን ሁሉ ወደመንግስት በማዞር የትምህርት ስርጭቱ በነፃ እንዲዳረስ ሆኖ በህዝቡ እንዲተዳደር ሆኗል፡፡ የጤና ጣቢያዎችንና የጤና ኮሌጆችን በማስፋፋትም ከ15 በመቶ አይበልጥ የነበረውን የጤና ሽፋን ወደ 38 በመቶ ከፍ አድርጓል፡፡



የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከ10 በታች የነበረውን ሽፋን ወደ 19 በመቶ አሳድጎታል፡፡ የአንደኛ ደረጃ አውራ ጎዳና መንገድንም ከነበረው ጨምሮ 18ሺ ኪሎ ሜትር አድርሷል፡፡ የአገልግሎት ሽፋኑ በገጠር ባዶ፣ በከተማ 30 በመቶ የነበረውን፣ ደርግ በገጠር 15፣ በከተማ 59 እንዲሆን አድርጓል፡፡

የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫውንም ከነበረበት 50 ሜጋ ዋት 370 ሜጋ ዋት አድርሶታል፡፡ የሙገር ስሚንቶ ፋብሪካን አቋቁሟል፡፡ የአርባ ምንጩ የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት የደርግ መንግስት ውጤት ነው፡፡ የናዝሬት የእርሻ ትራክተር መገጣጠሚያ፣ በአፋር ውስጥ እንፋሎትን ወደ ኃይል የመቀየር (ጅኦ ተርማል) ሞካሪው ደርግ ነው፡፡ በናዝሬቱ የእርሻ ትራክተር መገጣጠሚያ ድርጅት ውስጥም "እሸት" የሚል ስያሜ ያለው የግብርና አውሮፕላን በአገር ውስጥ ተገጣጥሞ ስራ ላይ ውሏል፡፡ የደርግ መንግስት በተለይ የውጭ አገር ምርትን በአገር ውስጥ ለመተካት ሲል ከትንሹ ጨርቃ ጨርቅ እስከ ከፍተኛው የኢንደስትሪ ዘርፍ ድረስ ጠንክሮ ሰርቷል፡፡ የጦር መሣሪያዎችን መገጣጠምና ጥይቶችን እስከማምረትም ደርሷል፡፡ እስከ ሚሳኤል ደረጃ መሄድም እቅዱ ነበር፡፡

በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎችንም በውጭ አገር የቴክኒክ ሙያዎችን ተምረው እንዲመለሱ አድርጓል፡፡ ቀጥሎም 80 ሺ የሚደርሱ የፋብሪካ ሠራተኞች በስራ አመራር፣ በሂሳብ አያያዝ፣ በምርትና በጥገና የሙያ መስኮች በአገር ውስጥ ተምረው ወደ ስራ እንዲሰማሩ አድርጓል፡፡

እነዚህንና ከዚህም ያለፉ በርካታ አገራዊ ስራዎችን ሲሰራ ግን ከምስራቅ የሱማሊያው መንግስት ዚያድ ባሬ ለያዥ ለገራዥ አስቸግሮ ኦጋዴንን ለመንጠቅ ጦር ሰብቆበታል፡፡ ከሰሜን ሻዕቢያ (ሻዕቢያ እስኪደመስሰው ድረስ አብሮት ጀብሃ) ሽምቀው የደርግን መንግስት ፋታ ነስተዋል፡፡ እንደገና በትግራይ ተሃህት(ተጋድሎ ሃርነት ህዝቢ ትግራይ) በኋላ ህወሃት የተሰኘው እየተፈታተኑት ነበር፡፡ በከተማ ውስጥ ኢህአፓ አለ፡፡

በዚህ ሁሉ አጣብቂኝ መሀል ያለው የደርግ መንግስት ግን "እየተዋጋን እናመርታለን፤ እያመረትን እንዋጋለን" የሚለውን መፈክር የሙጥኝ ብሎ ቀጥሏል፡፡

ኢትዮጵያን ለመውረር ያሰፈሰፈውን ኃይል ለመቋቋም ይቻል ዘንድም መንግስቱ በሶቭየት እርዳታ ተደግፈው በአፍሪካ ደረጃ ቁጥር አንድ የተባለ ሠራዊት አደራጅተው አስታጠቁ፡፡ በ12 ቢሊዮን ዶላር (በዚያን ጊዜው ምንዛሬ 24 ቢሊዮን ብር ነው) ጦሩን ሲገነቡ ግን ኢትዮጵያን ለቆት የማያውቀው ረሀብ በዘመናቸው ተከሰተ፡፡ ምንም ለጦርነቱ ቅድሚያ ቢሰጡም፤ እንደ ሁለቱ መንግስታት አይተው ያላዩ አልመሰሉም፡፡ ይልቁንም በተቻለ መጠን, ረሃብተኞችን (በድርቅ

የተጠቁትን ዜጎች) ከወሎና ካካባቢው በአውሮፕላን እያጋዙ ወደ መሀል አገር በማስመጣትና አንቶርጫን (ከኩተቤ በላይ) በመሳሰሉ ጊዜያዊ የመጠለያ ካምፖች እያስጠጉ እህል ውሃ በማቅረብ፣ ከዚያም ወደ ለም የኢትዮጵያ ግዛቶች ወስደው በማስፈርና ኑሮአቸውን እንዲመሠርቱ በማድረግ የቻሉትን ፈጽመውላቸዋል፡፡ ወላጆቻቸውን በድርቁ ያጡ ህፃናትንም ሰብስበው የማሳደጊያ ተቋማትን /ህፃናት አምባ/ እየመሠረቱ አሳድገዋል፣ አስተምረዋል፡፡

ደርግ የድርቅ አደጋውን ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠትም ሞክሯል፡፡ የጣና በለስ ግድብ ፕሮጀክትን ቀርፀው ከጣሊያንም የገንዘብ ችሮታ ተደርጎላቸው ወደ ተግባር ተገብቶ ነበር፡፡ ይህ ፕሮጀክት የኢትዮጵያን ግብርና ለማስፋፋት የረዳና በመቶሺዎች የሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ለም ወደሆነው የአገሪቱ ደቡባዊ ክፍል እንዲሰፍሩ ያደረገ ነው፡፡ ከዚህም አልፎ በጣሊያን እርዳታ በተገነቡ አዳዲስ ግድቦች አማካኝነት 20ሺ ሔክታር መሬት ለማልማት ጭምር ተችሏል፡፡

የደርግ መንግስት ይህን ፕሮጀክት ወደ ተግባር ሲለውጥም ከፍተኛ ገንዘብና ጉልበት አፍስሶበት ነው፡፡ ሆኖም የኤርትራና የትግራይ አማፅያን ወደ አዲስ አበባ ሲገሰግሱ አውድመዋቸዋል፡፡ ሙሉ በሙሉም ከጥቅም ውጪ ሆነዋል፡፡

መንግስቱ ኃይለማርያም ለጣሊያናዊው ጋዜጠኛ ጥያቄ ሐራሬ ሆነው መልስ ሲሰጡ፤ "ለረሃብተኞቹ ትኩረት አልተሰጠም የሚባለው ፈጽሞ ውሸት ነው! ከጣና በለስ ግድብና የገጠሩን ነዋሪ ወደምቹ ቦታ ከማስፈሩ በስተጀርባ የነበረው ስራ ረሃብ ዳግመኛ የማይከሰት ለመሆኑ ማረጋገጫችን ነበር፡፡ እንደገና ልድገመውና በጦርነት ላይ ነበር የምንገኘው፡፡ ጦርነቱን ለመዋጋትና ለማሸነፍ ደግሞ ለጦርነቱ ቅድሚያ መስጠት ነበረብን፡፡"

ይቀጥላሉ መንግስቱ፤ "... እንዴታ! በአፍሪካ ውስጥ እጅግ ጠንካራና ኃይለኛ የተባለ ሠራዊት ገነባሁ፡፡ በአደረጃጀቱ በመላው ዓለም ከሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተርታ ይመደብ የነበረ የፖለቲካ ፓርቲ አደራጀሁ፡፡ አንዲት እናት ህፃን ልጇን ከአደጋ እንደምትጠብቀው ሁሉ እኔም የሀገሬን አንድነት፣ ዳር ድንበርና ሉዓላዊነት ስከላከል ቆይቻለሁ፡፡ ግን ምን ያደርጋል? ድካሜ ሁሉ ከንቱ ሆነ፡፡" ብለዋል፡፡

እናም አብዮቱ ለዘመናት ሲቀነቀን የነበረውን የመሬት ላራሹን የብሶት ጥያቄ በመመለስና የብዙሃኑን ምኞት ዳር በማድረስ ፍሬ ያለው ስራ የሰራ ሲሆን፤ይህም ደርግንና አባላቱን ዛሬ ድረስ የሚያኮራ ተግባር ሆኖ ተመዝግቧል፡፡



*የደርግ ዘመን ፓርቲዎች፣ ውልደትና ሞት*

ከቀደምቱ "ኢህአፓ" እና በኋላ ላይ በደርግ ከተመሰረተው "ኢሠፓ" ውጪ ሌሎች የተቃዋሚና የደጋፊ ቡድኖች "ፓርቲ" የሚለውን መጠሪያ አልተጠቀሙበትም፡፡ "ሊግ" "ድርጅት" "ንቅናቄ" "ኅብረት"... ወዘተ የሚሉትን ነው የመረጡት፡፡ የእነዚህን ቡድኖች ስራና ሴራ በአጭሩ ለማየት ከቀደምቱ ኢህአፓ እንጀምር፡፡ የኢህአፓ ቁንጮ መሪ ቀደም ሲል ያየነው የ"አዞ" ፍልፍል ነው፡፡

አውሮፕላን ጠልፈው ሱዳን፣ ከዚያም አልጀሪያ መግባታቸውን በጃንሆይ ታሪክ ውስጥ አንብበናል፡፡ ዓለም አቀፍ ግንኙነታቸውንም አጠንክረው መቀጠላቸውን አይተናል፡፡ ያኔ ስምንት ሆነው በብርሃነመስቀል ረዳ መሪነት አልጀሪያ የገቡት ቡድኖች በአልጀሪያ መንግስት እርዳታ ከፍልስጤም ነፃ አውጪ ድርጅት /PLO/ ጋር ግንኙነት አድርገው ወታደራዊ ስልጠና ተሰጣቸው፡፡

የሻዕቢያን ተልዕኮ ኢትዮጵያ ውስጥ ለማስፈፀም በሻዕቢያ ሽፋን ደቡብ የመን በመድረስ ቁጥራቸውን በእጥፍ አሳድገው ቀይ ባህርን አቋርጠው ሳህል በረሃ ገቡ፡፡ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ "ምስክርነት" በሚል ርዕስ በ2001 ዓ.ም በፃፉት መፃህፍ ስማቸውን እንዲህ ይዘረዝሩታል፤ "ብርሃነመስቀል ረዳ፣ ቢንያም አዳነ፣ አብዲሳ አያና፣ ኃይለኢየሱስ ወልደሰንበት፣ አዱኛ መንግስቱ፣ አብዱራህማን አህመድ፣ ውብሸት ረታ፣ አበበ /ያባቱ ስም ያልታወቀ/ ተፈሪ ብርሃኔ፣ መሐመድ ማህፉዝ፣ መሐሪ ገብረእግዚአብሔር፣ ሰመረአብ ዮሐንስ፣ ስዩም ከበደ፣ ዘርዓብሩክ አበበ፣ እስክንድር ደምሴና ሌሎች ሆነው ከብርሃነ መስቀል ረዳ በስተቀር ሁሉም በኢህአፓ ስም ሳይሆን በተገንጣዮች ስም ሳህል በረሃ ገቡ፡፡

"ቆይቶም ከተለያዩ አገራት በሶማሊያና በሱዳን ከመጡ ሃያ አምስት የሚሆኑ አባላት አንድ ሐኪም ተጨምሮላቸው ሙሉ ወታደራዊ ትጥቅ ከሻዕቢያ ተሰጥቷቸውና ገንዘብም ታድለው የካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም የመሬት አዋጅ በታወጀበት እለት ለትግል ትግራይ አሲምባ ገቡ፡፡ ብዙ ሳይቆይ 6 ያህሉ አባላት ድርጅታቸውን ከድተው ትግራይ ለነበረው የደርግ መንግስት ባለስልጣን እጅ ሰጡ፡፡ እነተስፋዬ መኮንን እጅ ሲሰጡ እነ ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ፣ ብርሃነመስቀል ረዳ እና እስክንድር ደምሴ በስውር አዲስ አበባ ገብተው ከጀብሃና ከሻዕቢያ፤ ከእነዚህ በስተጀርባ ደግሞ ከአልጀሪያ የተሰጣቸውን የቤት ስራ ለማከናወን ዝግጅት ጀመሩ፡፡..." /ገፅ 143/

ጀብሃንና ሻዕቢያን በዓረባዊ ስሜት የዓረብ አገር መንግስታት ይረዷቸው ነበር፡፡ ይህን ስልጠና ወስደው ኤርትራን ለመገንጠል ቀድመው በሸመቁት ቡድኖች ነው ኢህአፓ የሚመራው፡፡እነክፍሉ ታደሰ አዲስ አበባ ውስጥ ሸምቀው ከኤርትራ በመጣው የሻዕቢያ ነብሰገዳይ

ቡድን መሪ በሆነው በጎይቶም ለባሲ አሰልጣኝነትና የተቀናጀ አመራር ደርግንና የደርግን ተባባሪ እያደኑ በመግደል አዲስ አበባን በደም ጎርፍ አጥለቀለቋት፡፡ከአዲስ አበባም አልፈው በየክልሉ ተመሳሳይ ተግባራቸውን ቀጥለዋል፡፡ወጣቱን በሐሰት ፕሮፓጋንዳ ቀስቅሰው ከጎናቸው በማሰለፍም ስውር ሴራቸውን ያላወቁትን ዜጎች ፈጁ፣ አስፈጁ፡፡

በቅድሚያ የገደሉት ዶ/ር ፍቅሬ መርዕደን ነበር፡፡ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ በመፃህፋቸው፤ "የዶ/ር ፍቅሬ ገዳይ ዛሬ ስሙን ለውጦ በብዓዴን ውስጥ አለ" ይሉናል፡፡

ከአገር ውጪ የነበረው የተማሪ ንቅናቄ አካል አብዮቱ ሲፈነዳ በሁለት አክራሪ ጎራዎች ተሰልፎ ነበር፡፡ እነዚህም የኢህአፓ እና የመኢሶን ድርጅቶች ተከታይ ነበሩ፡፡ ሁለቱ ቡድኖችም በተማሪ ድርጅቶች ሽፋን ደጋፊዎቻቸውን ማብዛትና ማጠናከሩን ተያይዘውት ነበር፡፡ በአብዮቱ ዋዜማ የተማሪዎች ማኅበራት ዱላ ቀረሽ ክርክር ላይ ነበሩ፡፡ የኢህአፓ ወገኖች በአዲስ መልክ የተዋቀረውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽንን (ኢተዓአፌ)ን ሲደግፉ፤ (በአዞዎቹ ቁጥጥር ስር የነበረውን) የመኢሶን ተከታዮች ደግሞ አዞዎቹ ያፈረሱትን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ማኅበር (ኢተዓአማ) እንዲቀጥል ይሟገቱ ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሜን አሜሪካ (ኢተማሰአ) በጃንሆይ ዘመን ታሪክ ውስጥ እንዳየነው የአዞዎቹ የበላይነት ስለነበረበት የፌዴሬሽኑና የኢህአፓ ደጋፊ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በአውሮፓ /ኢተማአ/ ደግሞ ከሁለት ተከፋፍሏል፡፡ እነዚህን የውጭ አገር እንቅስቃሴዎች ደርግ ብዙም ትኩረት አልሰጣቸውም ነበር፡፡ ከአብዮቱ በኋላ ግን ከርዕዮት ክርክር አልፈው ወደ መተላለቅ አምርተዋል፡፡

የውጪ ቡድን ከአገር ውስጥ ቡድኖቹ በርቀትም ቢሆን እየተገናኘ ማርክሳዊ ሌኒናዊ መፈክሮችን ሲያስተጋባ አመታት ተቆጥረዋል፡፡

በአገር ውስጥ ያሉት አብዮቱ እንደፈነዳ በልሳኖቻቸው በዴሞክራሲያ እና በሰፊው ህዝብ ድምፅ አማካኝነት በሚያሰርጓቸው መልዕክቶች የህዝብ ድጋፍ ሲሰበስቡ ቆይተዋል፡፡ ምሁራኑ ከውጭ አገር ወደ አገር ቤት ከእነ ክፍፍል ቁርሿቸው መጥተው እንደተቀላቀሉም ልሳኖቹ የኢህአፓና የመኢሶን መሆናቸው ገሃድ ወጣ፡፡

ኢህአፓ እነ ብርሃነመስቀል ረዳ እና እነክፍሉ ታደሰን ያካተተ ቀንደኛ ተቃዋሚ ሆኖ ቀረበ፡፡ መኢሶን እነ ዶ/ር ወርቁ ፈረደ፤ እነዶ/ር ንግስት አዳነ፣ ዶ/ር መስፍን ካሱ፣ ዶ/ር ነገደ ጎበዜና ዶ/ር ኃይሌ ፊዳ የተካተቱበት ነበር፡፡ በደርግ ምስረታ ማግስት ሌሎችም የግራ ክንፍ ኃይሎች ብቅ ብቅ ይሉ ጀመር፡፡



የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በሰሜን አሜሪካ የአሮጌው (ኢተማሰአ) መሪ በነበረው በዶ/ር ሠናይ ልኬ የሚመራ "ወዝ ሊግ" የተሰኘ ድርጅት ተከተለ፡፡ይህ ቡድን ከውጭ አገር ጀመሮ ቂም የነበረበት ስለሆነ ከደርግ ጋራ ወዳጅ ለመሆን ጊዜ አልፈጀበትም፡፡መኢሶንም በተመሳሳይ ለደርግ እውቅና ሰጥቶ በመለጠፍ ግንባር ቀደም ነበር፡፡
ቀጥሎ "የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች አብዮታዊ ትግል "(ኢጭህአት) የተባለ ቡድን በተለይ የደቡብ ኢትዮጵያን ህዝቦች እወክላለሁ በማለት ብቅ አለ፡፡ከዚያም ከኢህአፓ አፈንግጠው እጅ የሰጡት አባላት አገር ውስጥ ካሉ ጥቂት ህቡዕ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት"ማርክሲስት ሌኒኒስት ሪቮሉሽናሪ ድርጅት"(ማሌሪድ)የተባለ ቡድን መሠረቱ፡፡

ደርግ ግር እያለው ሄደ፡፡ ወዲያውም ፍልሚያውን መቀላቀል እንዳለበት ለደርግ እውቅናና ቅድመ እውቅና ከሰጡት ከወዝሊግ እና መኢሶን አመራር አባላት ባገኘው ምክር፣ እንዲሁም በቀሰሙት ትምህርት በመንዝ፤ በተለይ በወዝ ሊግ አዋላጅነት "አብዮታዊ ሠደድ" የተሰኘ ድርጅት ተወለደ፡፡ ይህም በ1968 ዓ.ም የተደረገ ሲሆን፤ የሰደዱ አባላት የመንግስቱ ወዳጅ የሆኑ መለዮ ለባሾች ናቸው፡፡ በሃምሳ አለቃ /በኋላ ሻምበል/ በለገሠ አስፋው የሚመራ ሆነ፡፡

ከዚህ በኋላ በእለታዊው አዲስ ዘመን ጋዜጣ "አብዮታዊ መድረክ" በሚለው ዓምድ ስር የሁሉም ፓርቲና ድርጅት የብዕር ፍልሚያ ጦፈ፡፡ በዋናነትም መኢሶንና ኢህአፓ የጽሁፍ ችሎታ ባላቸው ምሁራን አባላት አማካኝነት በማርክሳዊ ቃላቶች አሸብርቀው የሚቀርቡ ሀሳቦችን መሰንዘር ቀጠሉ፡፡

የእነ ለገሠ አስፋው (የእነ መንጌ) የሠደድ አባላት አነጣጥሮ መተኮስ እንጂ አንጥሮ መፃፍ ላይ እምብዛም ነበሩና ወሣኝ ወሣኝ ሀሳቦችን ከሁለቱ ተፋላሚ ወገኖች እየቀዱ፣ እየተማሩ፣ ዳር ላይ ሆነው ምኑንም የማያውቁትን ርዕዮት በውል ተረዱት፡፡ ይህን እስከ 1969 ድረስ የዘለቀ የጋዜጣ ትምህርት ይዘውም የርዕዮቱ ተንታኝ፤ ብሎም ተግባሪ ሆኑ፡፡ በእርግጥም የሀሳብ ፍጭቱ ለደርግ ጠቃሚ ነበር፡፡ የብዕር ተፋላሚዎቹም በልዩነት ላይ ሳይሆን አንዱ አንዱን ለማንቋሸሽና እርቃኑን ለማስቀረት የነበረ ሲሆን፤ ውሎ አድሮ ብዕሩ ቀርቶ በጥይት መፋለም ይጀምራሉ፡፡

ደርግ በመሃል የብሔራዊ ዴሞክራሲ አብዮትን በ1968 ሚያዚያ 12 ካወጀ በኋላም ለአዋጁ አስፈፃሚ አካል የሚሆን "ጊዜያዊ የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት" ማቋቋም ነበረበት፡፡ዓላማውም በደርግ አገላለፅ "ሰፊውን ህዝብ ማንቃትና ማደራጀት ነው" ጽ/ቤቱን ለመምራትም 15 አባላት ያሉት ኮሚሽን ሲደራጅ ከሊቀመንበርነት ጀምሮ ያለውን ስልጣን መኢሶን ስለያዘው ድርጅቱን ለማጎልበት ተጠቀመበት፡፡ከኢህአፓ

የማይወዳደር አቅም የነበረው መኢሶን በወራት ውስጥ ጥሩ ለውጥ አሳዬ፡፡ከተሞችን ለመቆጣጠር የሚያስችለውን የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴርን ደርግ ሆነ ብሎ በመኢሶን ስር እንዲሆን በማድረጉም በ1968 መገባደጃ ላይ በተካሄደው ተራ የቀበሌ ምርጫ ደጋፊዎቹን ለማስመረጥ በመቻሉ መኢሶን ደስ ተሰኘ፡፡ነገር ግን ደርግ ይህን ያደረገው ኢህአፓን "እንቁልልጭ" ለማለትና፤"ስልጣን ለህዝብ በተወካዮች አማካኝነት የሚተላለፈው እኔን የአብዮቱን ባለቤት ቀርቦ በመወዳጀት እንጂ በግትርነት አይደለም" በሚል ሾርኒ ለመንካት ነበር፡፡በዚህም ኢህአፓ በግኗል፡፡ስለዚህም ወዲያው ሠራተኛውንና ሌሎች ጥቃቅን ተቃዋሚ ቡድኖችን በመቀስቀስና ደጋፊዎቹን በማነሳሳት የኢህአፓን መፈክር አንግበው ሰልፍ እንዲወጡ አደረገ፡፡ ኢህአፓ "የወዛደሩ ብቸኛ ፓርቲ እኔ ነኝ" ሲል በመከረሙና በአማላይ ቃላቶችም ብዙሃኑን መማረክ በመቻሉ የብሔረተኝነት አላማውን የተረዳውም ያልተረዳውም ተሰለፈለት፡፡ ደርግና የደርግ አሯሯጮች ኢህአፓ መቼም እረፍት እንደማይሰጣቸው ቢረዱትም የወሰዱት የኃይል እርምጃ ግን አልነበረም፡፡

ኢህአፓ በደርግና በአጋሮቹ ላይ የሽምቅ ውጊያን ጨምሮ፤ እያደነ እንደሚገድልም ዛተ፡፡ መስከረም 13 ቀን 1969 ዓ.ም ኢህአፓ መንግስቱ ኃይለማርያምን ለመግደል ያደረጉት ሙከራ ለጥቂት ሳይሳካ ቀረ፡፡በዚህ ተኩስ ክፉኛ የቆሰሉት መንግስቱ ድንጋጤያቸውን በውስጣቸው ይዘው ሙከራውን ለፖለቲካዊ ፕሮፓጋንዳ ተጠቀሙበት፡፡ "አስቡት እኔን የመሰለ አብዮተኛ" እንደማለት፡፡ ጎን ለጎንም የኢህአፓን ፖለቲካዊ ኪሣራ አስገነዘቡበት፡፡

ከጥቂት ቀናት በኋላ ቀደም ሲል ያየነውን የመኢሶን አመራር አባልና የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ባለደረባ የነበሩትን ዶ/ር ፍቅሬ መርዕድን ሠንጋተራ አካባቢ መኪና ውስጥ ቁጭ ብለው ባለቤታቸውን ሲጠብቁ አልሞ መግደልን ሰልጥነውበት፣ ተክነውበት የመጡት የኢህአፓ አባላት ተኩሰው ገደሏቸው፡፡

"ነጭ ሽብር" አሉት፡፡ የነጭ ሽብር ተግባራቸውንም በተጠቀሱት ኢትዮጵያዊ ዶ/ር ጀመሩት፡፡ የመጀመሪያውን ጥይት ያጮኸች ኢህአፓ መሆኗ ግልጽ ነው፡፡ ደርግ ከኢህአፓ የሽብር ተግባር በኋላ "የአንድ አብዮታዊ ህይወት በሺ ፀረ-ህዝቦች ህይወት ይመነዘራል" አለ፡፡ ከዚህ መግለጫ በኋላ የኢህአፓ አባሎችንና ደጋፊዎችን ደርግ በውል ስለማያውቃቸውና አገር ውስጥ ድንበር ሲጠብቅ ስለነበር፤ የፖለቲካ ዲያስፓራዎች እዚያው ይተዋወቃሉና የመኢሶን አባላት ስም ዝርዝራቸውን ለደርግ አቀረቡ፡፡ ደርግም እየለቀመ ማሰር ቀንደኞችንም መረሸን ጀመረ፡፡ ሲቪል ታጣቂዎችንም እያደነ ትጥቅ አስፈታ፡፡ ቀጥሎ በሰርጎ ገብነት የሚጠረጠሩ የራሱ የደርግ አባላትና ደጋፊዎች ለኢህአፓ



እየሰሩ ነው የሚል ነገር መጣ፡፡ የነገሩ እውነትነት ባያጠያይቅም ደርግ "ሠርጎ ገብ" የተባሉትን አባላት በሚመለከት የወሰደው እርምጃ "ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ" የሚባለውን ብሂል የተከተለ ነበር፡፡ ጠቋሚዎቹም የየራሳቸውን የስልጣን ቦታ ለመያዝ ሲሉም ሆነ ያልተዋጠላቸውን ሹም የማስወገጃ መድረክ አድርገውታል፡፡

መንግስቱ የደርግን ህልውና አስጠብቀው ለመቀጠል ቀድመው የተዘጋጁ ነበሩና፤ በቤተመንግስቱ ቅልብ ጦር አኑረዋል፡፡ በኮሎኔል ዳንኤል አስፋው ይመራል፡፡ "መቺ ኃይል" የሚሉትን ቡድንም መስርተዋል፤ በሻለቃ ጌታቸው ሺበሺ ይመራል፡፡ የደርግ አባላቱ ተራ ወታደር 10 አለቃ እየተባሉ "አድሃሪ" ተብለው ስለተተቹም ለእያንዳንዱ አባል በውስጥ አሰራር ማዕረግ እንደ ፈንዲሻ እየተዘገነ እንዲሰጥ አድርገዋል፡፡ በዚህም የእሳቸው ሌተናል ኮሎኔል መሆን አግባብነት ቢኖረውም፤ እያንዳንዱ አባል ከምክትል መቶ አለቃ በላይ እንዲሆን የተደረገው በፍጥነት ነበር፡፡ ከዚህም አልፎ አብዮታዊ ሠደድ አለ፡፡ በጥቅሉ ዙሪያውን አጠባብቀው ሲያበቁ፤ ይህ የኢህአፓ ተግባር አገር የማፍረስ ተልዕኮ መሆኑን በመገንዘብ፤ "ውስጡ መጥራት አለበት" የሚል አቋም ወሰዱ፡፡ ይሄ ሁሉ የስልጣን ህልመኛ ፓርቲ የአብዮቱ ፀር እንደሚሆን ጠረጠሩ፡፡ ዝግጅቱን ያዩት ጄኔራል ተፈሪ በንቲ "እሣት በእሣት አይጠፋምና ብሔራዊ እርቅ ለማድረግ ጥሪ እናቅርብ" ብለው አረፉ፡፡

ወፉ ዛፉ በኢህአፓነት በሚጠረጠርበት በዚያ ጊዜ ይሄን የመሰለ ቃል ከደርጉ ዋና ሊቀመንበር መሠንዘሩ ለኮሎኔል መንግስቱ (ሲፈጥራቸውም ጠርጣሪ ናቸውና) ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ እርግጥ ነው ከጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም በፊትም ለወራት ያህል መጠነኛ አለመግባባት ነበር በተፈሪና በመንግስቱ መካከል፡፡ ሆኖም የዝግጅት ጊዜ አስፈልጓል፡፡ በደርግ ውስጥም ጥርጣሬው ጎልቶ በጎሪጥ መተያየት ተፈጥሯል፡፡ ስለዚህም የደርግ የፖለቲካና የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር የነበሩትን የአየር ኃይል አባሉን ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴን በአብዮቱ ላይ አሲሯል በሚል ክስ በጦር ፍርድ ቤት ቀርበው ተረሽነዋል፡፡ ቀጥሎም በኤርትራ ያለው 2ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ የነበሩት ብርጋዴል ጄኔራል ጌታቸው ናደው ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ተወስዷል፡፡ ጄኔራል ጌታቸው ናደው ልክ እንደ ጄኔራል አማን እጅ አልሰጥም ብለው ቤታቸው ውስጥ ተታኩሰው ነበር የተገደሉት፡፡ ከዚያም መቶ አለቃ በወቅቱ ካሣና መቶ አለቃ ስለሺ በየነ የተባሉ ሁለት የደርግ አባላት ሊወሰድባቸው የታሰበውን እርምጃ ቀድመው በማወቃቸው በሽሽት ላይ እንዳሉ በደርግ የተላከው ጦር አሳዶ ይዞ ገድሏቸዋል፡፡ በተመሣሣይ

ጥርጣሬም የእድገት በኅብረት ዘመቻ አስተባባሪ የነበሩት ሻለቃ ኪሮስ አለማየሁ ተይዘው ታስረው ሳለ ራሳቸውን በእስር ላይ እንዳሉ ገድለዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለም በተጠቀሰው አመት የመጀመሪያው ወራት የደርግ አወቃቀር ላይ መሠረታዊ ለውጥ ተደርጎ ነበርና፤ በዚህም ሁሉም የደርግ አባላት የሚሳተፉበት ሸንጎ ዋናው የስልጣን አካል ሆኖ፤ በተዋረድ ደግሞ የማዕከላዊ ኮሚቴና ቋሚ ኮሚቴ ተቋቋሙ፡፡ በዚህም ዋና ሊቀመንበሩ ዋናውን ሸንጎ በበላይነት መምራት ሲችሉ፤ ምክትሉ መንግስቱ ግን ከደርግ ጋር ያልተያያዘውን የሚንስትሮች ምክር ቤትን በሊቀመንበርነት ከመምራት ያለፈ ስልጣን እንዳይኖራቸው ሆነ፡፡

በተጨማሪም የደርጉ ዋና ፀሐፊ የጽ/ቤቱን ስራ ከመምራት ባለፈ ከአዲሱ አወቃቀር በፊት በሌተናል ኮሎኔል መንግስቱ ስር የነበረውን የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤትንም እንዲቆጣጠሩት ተደረገ፡፡

ይህ አወቃቀር ከግራ ቀኝ ሲታይ መንግስቱና ደጋፊዎቻቸውን አስሮ የማስቀመጥ ዘዴ ሆኖ ስለተገኘ ፍጥጫ ቢፈጠር አይገርምም፡፡ በዋናነት አዲሱን አወቃቀር አቅደው በተግባር እንዲሰራበት ያደረጉት በኢህፓነት የሚጠረጠሩ የተባሉት የደርጉ የኢኮኖሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር የነበሩት ሻምበል  ሞገስ ወ/ሚካኤልና በአዲሱ አወቃቀር የደርጉ ዋና ፀሐፊ የሆነው ሻምበል አለማየሁ ኃይሌ መሆናቸው ነው፡፡ እንደገናም አወቃቀሩ የአብዮቱ ጠባቂ አለኝታ ተደርገው በብዙሃኑ የሚታዩትን፣ የሚፈሩትን መንግስቱን አግልሏል፡፡ ከሁሉም የከፋው ደግሞ በዚህ አሠራር ሠርጎ ገቦች ካሉ እንደልባቸው የመሆን እድል የሚሰጥ መሆኑ ነው፡፡ ተጠርጣሪዎች ይህን አድርገው አስጊውን መንግስቱን ቀፍድደው ስራቸውን ቀጠሉ፡፡ የረሱት ነገር ቢኖር ለመንግስቱ ፍፁም ታማኝ የሆነውና ከሆለታ ትምህርት ቤት ጀምሮ ጓደኝነት የነበራቸው፤ ከደርግ ምስረታ ጀምሮ የመንግስቱ ቀኝ እጅ የሆነው፣ ጃንሆይንም አማንንም ሲጥ ያደረገው ኮሎኔለ ዳንኤል አስፋው የደርግን ህልውና ለማስጠበቅ የተደራጀው የቅልብ ጦሩ የበላይ አዘዥ መሆኑን ነው፡፡ እናም ጠላታቸውን በፍጥነት በማንበርከክ ወደር የማይገኝላቸው መንግስቱ የረቀቀ የማጥቃት ዘዴያቸውን ከደጋፊዎቻቸው ጋር አቅደው ጨረሱ፡፡

ጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም ሁሉም የደርግ አባላትና ሊቀመንበሩ ጀኔራል ተፈሪ በንቲ በስብሰባ ላይ እንዳሉ አንድ መልዕክተኛ ይመጣና መንግስቱ አስቸኳይ የስልክ ጥሪ እንዳላቸው ይገልፃል፤ መንግስቱ አስፈቅደው ይወጣሉ፡፡

ወዲያው ባልተጠበቀ ፍጥነትና ሁኔታ የታጠቁ ወታደሮች በኮሎኔል ዳንኤል አስፋው መሪነት ወደአዳራሹ ገብተው "እጅ ወደ ላይ!" አሉ፡፡ ሁሉም በድንጋጤ እጆቻቸውን በጭንቅላታቸው ላይ አጣምረው አፈጠጡ፡፡ በአንድ አዳራሽ ከታጎሩት አባላት ውስጥ ሰባት ሰዎች



ተመርጠው ስማቸው እየተጠራ ወጡና በአንድ ክፍል ተቆለፉ፡፡ ሌሎቹ አባላት "አይዟችሁ እናንተን አይደለም" ተብለው ተተውና ሰባቱ ወዲያው ተረሸኑ፡፡ ጀኔራል ተፈሪ በንቲ የደርጉ ሊቀመንበር፣ ሻምበል አለማየሁ ኃይሌ በአዲሱ አወቃቀር የደርጉ ዋና ፀሐፊ፣ ሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤል የኢኮኖሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር፣ ሌተናል ኮሎኔል አስራት ደስታ የደርግ የማስታወቂያ ኮሚቴ ሊቀመንበር፣ ሻለቃ ሀሩይ ኃይለስላሴ፣ ሻምበል ተፈራ ደነቀ፣ አስር አለቃ ኃይሉ በላይ የተረሸኑት የጊዜያዊው የደርግ መንግስት ከፍተኛ ባለስለጣናት የነበሩና በኢህአፓ ደጋፊነትና አባልነት ስለተጠረጠሩ ነው፡፡

በቅፅበት መፈንቅለ መንግስቱ በስኬት ቢደመደምም፤ ወዲያው በተፈጠረው የተኩስ ልውውጥ ሽብሩ ቀጠለ፡፡ መንግስቱ ከመፈንቅለ መንግስቱ በኋላ ወደ አዳራሹ ሄደው "አማንን መርጠን ምሩን ብንላቸው አብዮታችን ለመቀልበስ ተነሱ፣ ዛሬ ደግሞ ጀኔራል ተፈሪ በንቲ ለዘብተኛ በመሆናቸው አብዮቱን ለማዳን ርምጃ ተወስዷል፡፡ እኔ ለአብዮቱ ያለኝ አቋም ቁርጠኛ ነው፡፡ አሁን በእርጋታ ስራችሁን መቀጠል ትችላለህ..." እያሉ ሲያረጋጉ የመጨረሻዋን ቃል ሳይጨርሱ የቤተመንግስቱ ጊቢ በተኩስ ሲናጥ መንግስቱ ሮጠው ወጥተው ታንክ ውስጥ ተደበቁ፡፡ ሌላው ባለበት ሆኖ በሽብር ተናጠ፡፡ ጉዳዩን ወዲያው የተረዳው ሻለቃ ዮሐንስ ምትኩ ጊቢ ውስጥ ነበርና የኢህአፓ አባልም ስለነበር ሳይቀድሙኝ ልቅደም ብሎ ተኩስ በመክፈት ዶ/ር ሰናይ ልኬንና ኮሎኔል ዳንኤል አስፋውን ቅል ቅልአቸውን ብሎ አስተኛቸው፡፡ ቀጥሎም መንግስቱን ለመግደል ነበርና ያሰበው ይገኙበታል ወዳለው ቢሮ ገብቶ አጣቸው፡፡ ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን የመንግስቱን ፎቶ ግራፍ በጥይት ቦረዳድሶ ከመውጣቱ በፊት አንድ ታንክ ቢሮውን ደርምሶ ገብቶ ሻለቃ ዮሐንስንም ጨፍልቆ ሲያበቃ ሁሉም ነገር ፀጥ አለ፡፡

የመንግስቱ ድል በወዳጆቻቸው በዶ/ር ሠናይ ልኬና በኮሎኔል ዳንኤል አስፋው መገደል ደበዘዘ፡፡ ፍንቀላው ግን ተሳካ፡፡ ከዚህ በኋላ የመንግስቱ አምባገነንነት የበለጠ እልህ የተሞላበት ሆነ፡፡ የዚህ መፈንቅለ መንግስት አደራጆች መንግስቱ ብቻ ሳይሆኑ የመኢሶን እና የወዝ ሊግ አመራር አባላት የሆኑ ምሁራን ሰፊውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡በዚህ ጊዜ  ነው መንግስቱ "ለምሳ ያሰቡንን ለቁርስ አደረግናቸው" በማለት መግለጫ የሰጡት፡፡

አሁን ደርግ የኢህአፓ ተሚጋች ሆነው "እርቅ" የሚሉትን ሁሉ ደምስሶ ነፃ እርምጃ ለመውሰድ መንገዱን ጠርጓል፡፡ ኮሎኔል መንግስቱ የጀኔራሎችን መጋረጃ ገላልጠው ከፊት ሆኑ፡፡ ከተቀዳሚ ሊቀመንበርነት የደርጉ ዋና ሊቀመንበር ሆኑ፤ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥነቱንም ደርበው ያዙ፡፡ ቀጥሎ አስጊ ያልሆኑት፤ ነገር ግን በየስብሰባው ያውካሉ

የተሰኙት ምክትል የደርጉ ሊቀመንበር ኮሎኔል አጥናፉ አባተ ቀሩ:: አዋኪነታቸው እንዴት ነው? ቢባል በአስተዳደር ጉዳይ እንጂ ለአብዮቱ ፍፁም ታማኝ መሆናቸው ይታወቃል::

አንድ ቀን በስብሰባ ላይ እጃቸውን አውጥተው ሊናገሩ ሲሉ፤ ያ የተለመደ ጭቅጭቃቸው ነው ተብሎ እድል ተነፈጉ:: እሳቸው ግን ተሰብሳቢው አዳራሹን ለቆ እየወጣ ሳለ ጮክ ብለው "ተው ግዴለም ስሙኝ! ይቺ አገር የሚበጃት ቅይጥ ኢኮኖሚ ነው..." ማለታቸውን እስር ላይ የሚገኙ አባላት ደጋግመው ገልፀዋል:: ሰሚ ግን አላገኙም:: ጭራሽ ይሄ አብዮቱን የማወክና የማርክሲዝምን ርዕዮት የሚቃወም ተደርጎ ተፈረጀና ጣት ተቀሰረባቸው:: በዚህም ላይ በተቃዋሚዎች ላይ የሚወሰደው እርምጃ መልክ እንዲኖረው ደጋግመው ያሳስቡ ነበር:: እኚህ ሰው የእነ ተፈሪ በንቲን መረሸንም የሰሙት ለስራ ከሄዱበት ክፍለሃገር ሆነው ነበርና እንደሰሙ በጣም ደንግጠው በቁጣ "ትናንት አማንን ገደልን ዛሬ ደግሞ..." በሚል ቁጨት ላይ ነበሩ:: ወዲያውም በአስቸኳይ ተጠርተው ከነቁጣቸው ቤተመንግስት እንደደረሱ መንግስቱ አረጋግተውና የተረሸኑት በሴራቸው ምክንያት እንደሆነ ገልፀው፤ አለዝበው ሸኟቸው:: የአጥናፉን መናደድ መንግስቱ አልወደዱትም፤ ከ10 ወራት በኋላ በህዳር ወር 1970 ዓ.ም ሆነ ተብሎ በተጠራ የደርጉ ስብሰባ ላይ የአጥናፉ ጉዳይ ተተነተነ:: "እርምጃ ሲወሰድ ይቃወማል፣ የሶሻሊዝምን መሠረታዊ መርሆዎች የሚፃረሩ አስተያየቶች እየሰነዘረ ያውካል..." ተባለና የመንግስቱ አጫፋሪዎች የይረሸን ውሣኔውን ለገሱ:: ተፈርዶባቸው ተረሸኑ:: ፍፁም ስህተት የተሰራው እዚህ ላይ ነው ይላሉ ተፀፃች አባላቱ:: ያለሀጥያቱ ለአገር ጥቅም ሲል በተናገረው የተገደለ ነው ይሉታል:: ብቻ የደርጉ መስራች ተቀጩ::

አበቃ:: መንግስቱ በእሺ ባይ የበታቾቻቸው ብቻ ታጀቡ:: አዲሱን የደርግ አወቃቀርም በራሳቸው ታማኞች ሞሉት:: ግለሰቦች በዚህ መልኩ ከተመነጠሩ በኋላ ቀጣይ ስራ የሆነው ፓርቲዎችን ወይም የፖለቲካ ድርጅቶችን ማጥራት ሆነ::

የግራ ክንፍ ሆነው ነገር ግን ለደርግ በጎ ምልከታ ያላቸው ድርጅቶች ተባብረው በአንድ በኩል ኢህአፓን ለመደቆስ፣ በሌላ በኩል ከደርግ የሚመነጨውን ስልጣን ለመቀራመት ያመች ዘንድ፤ እንዲሁም ከኢህፓ በልጦ ለመፈርጠም ሲሉ "የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ኅብረት (ኢማሌድኅ)ን መሠረቱ:: በየካቲት ወር 1969 ይህን ኅብረት መስርተውም ሰፊውን ህዝብና ተራማጅ ኃይሎችን በማደራጀት ግንባር ቀደም ፓርቲ መመስረት የሚቻለው በዚህ ዘዴ መሆኑን እየገለፁ ተኩራሩ::



ኢማሌድኅ ግን እንደታሰበው ጠንካራ ፓርቲ አምጦ ሊወልድ ቀርቶ ጭራሽ የመበታተኛ መድረክ ሆኖ አረፈው:: በአንድ ጥላ ስር የተሰባሰቡት ድርጅቶች የበላይነትን ለማወጅ እርስ በርስ መፍካከር ጀመሩ:: በተለይ መኢሶን እኔ ነኝ የበላይ የሚል አቋም ይዞ መኩራራት ስራው ሆነ:: በዚህ ሳቢያ ሌላ ግብግብ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ተጀመረ:: እንኳኑ የመከራከሪያ ጉዳይም "ዴሞክራሲያዊ መብቶች በምን ዓይነት ሁኔታ ይፈቀዱ? ያለገደብ ወይንስ በገደብ? አብዮቱ ሲረጋጋ ወይስ አሁኑኑ?" የሚሉ ነበሩ::

በሰፊው የስልጣን መሠረቱን እንደጣለ የተሰማውና በኅብረቱ ውስጥ ከተሰባሰቡት ድርጅቶች አንዱ የሆነው መኢሶን "አሁኑኑ ያለ ገደብ ይፈቀድ" ሲል፤ ሌሎቹ ደግሞ "ሰፊው ህዝብ ሳይደራጅ ገና በእንጭጩ እንዲህ ያለ ተግባር መፈፀም አብዮቱን ለፀረ አብዮተኞች አሳልፎ መስጠት ነው" እያሉ ሞገቱ::

ደርግና ሠደድ የመኢሶን "አሁኑኑ" ባይነትና ሌሎች የእንቡር እንቡር እንቅስቃሴ አላማረውምና "መኢሶን ወዳጅ ብለን ብናስጠጋው እብጠት ተሰማው" በሚል ተወንጅሎ በደርግ ዘንድ የነበረው ተቀባይነት ቀረና ንቀትና ተፅዕኖ ደረሰበት:: ይህን የተረዱትና ጥርስ እንደተነከሰባቸው የገባቸው የመኢሶን አባላት ያለአንዳች ዝግጅት በደርግ ላይ የትጥቅ ትግል አውጀናል ብለው አኩርፈው አዲስ አበባን ለቀው በተለያየ መንገድና በተለያየ አቅጣጫ ነጎዱ:: ግማሹ በጅማ የቀረው በሌላ ተበታትነው ሲጓዙ በደርግ የማሳደድ ዘመቻ ከፊሎቹ ተይዘው ታሰሩ፤ የቀሩት ተገደሉ:: በለስ የቀናቸው አገር ጥለው ሸሹ:: የመኢሶን ታሪክ በዚሁ ያበቃል::

ጥቂት ዘግየት ብሎም ኢጭአት የመኢሶን ዕጣ ገጠመውና በደርግ ተደመሰሰ:: እነዚህን ድርጅቶች በመምታት የደርግ ተባባሪ የነበረው ወዝሊግም በ1971 ዓ.ም ሰደድን ለመቆጣጠር ሠርጎ ገብቷል በሚል ውንጀላ በደርግ ተመታ:: ወይም ተበተነ:: የቀረው ምንም አቅም ያልነበረው ማሌሪድ ነበርና ደርግ እሱን ለማጥፋት አንድ ቀንም አልፈጀበት ተመታ፤ ተበተነ::

ከዚህ በኋላ ማለትም ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ ብቸኛው አውራ ፓርቲ አብዮታዊ ሠደድ ሆነ:: ደርግና ሠደድ ያንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው:: በሠደድ ስም ሲቪሉ ይደራጃል፤ ሲቪሉንም ደርግ ያዘዋል ማለት ነው:: የደርግ ዘመን ፓርቲዎች በአጭሩ ባየነው መልኩ ተወልደው ባየነው መልኩ ከስመዋል:: የቀሩት ስልጣን የያዘው ደርግ እና፤ ተቃዋሚው ኢህአፓ ነው:: እነዚህም የከተማ ጦርነቱን ስራቸው አደረጉት::

የኢህአፓ ነጭ ሽበር

ከአልጀሪያው ቡድን እነ ብርሃነመስቀል ረዳ፣ እያሡ አለማየሁ፣ አብዲሣ አያና፣ ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይ፣ ዶ/ር መኮንን ጆቴ እንዲሁም ከሶቭየት፣ ከአሜሪካና ከምዕራብ አውሮፓ እነ ክፍሉ ታደሰ፣ መሐመድ ማህፉዝን የመሳሰሉ ፖለቲከኞች አንድ ድርጅት ማቋቋማቸውን አውሮፓ ሆነው ይፋ ካደረጉ በኋላ፤ ከአገር ውስጥ ሸማቂ ቡድኖችና ከሲቪል ደጋፊዎቻቸው ጋር በተለያዩ ጊዜ፣ ዓይነትና ሁኔታ ግንኙነት እያደረጉ ከአብዮቱ በኋላ ጠንካራ የግራ ክንፍ ሆነው የስልጣን ትግል አድርገዋል፡፡ በአገር ፍቅር ስሜት ልቡ የነደደውን የኢትዮጵያ ወጣት ለስውር አላማቸው ማስፈፀሚያ ይሆን ዘንድ በፕሮፓጋንዳ ከጎናቸው አሠልፈው የቀይ ሽብር ሰለባ አድርገውታል፡፡ በመጨረሻም ለገዳይ አሳልፈው ሰጥተውት ፈርጥጠዋል፡፡

ነጭ ሽብር የኢህአፓ የግድያ መፈክር ነበር፤ ቀይ ሽብር የደርግ የመልስ ምት መፈክር ነው፡፡ ኢህአፓ ነጭ ሽብርን ባይጀምር ቀይ ሽብር የሚባል ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ባልኖረ ነበር፡፡ የኢህአፓ ዓላማ ምን ነበር? ስንል ምላሹ ሁለት ነው፤ አንደኛ ስልጣን፣ ሁለተኛ ከበስተጀርባ ያሉትን አጋሮች የመገንጠል ጥያቄ በኢትዮጵያ ብሔሮች ሽፋን ማስፈፀም፡፡

ኢህአፓና ደርግ ወይም ሌሎች የዚያ ዘመን የፖለቲካ ድርጅቶች ርዕዮት አንድ ነው፡፡ ሁሉም ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን በጽኑ የሚያወግዙና ሲያወግዙ የኖሩ ማርክሲስቶች ናቸው፡፡ ደርግ ስልጣኑን ለሌላ አካል ያስረክብም አያስረክብም አስተዳደራዊ መዋቅሩን የዘረጋው በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ሲሆን፤ይህም የኢህአፓ የራሱ መሻት የነበረ ነው፡፡

ታዲያ እነዚህ አገር በቀል ቡድኖች ምን አጋጫቸው? ብለን ስንጠይቅ ነው ከላይ የተጠቀሱት ምላሾች ብቸኛ መልስ ሆነው የምናገኛቸው፡፡ ለዚህም ነው በርካታ ምሁራን "ገንጣይና አስገንጣይ" በሚል ታሪኩ ካለፈ በኋላ በየፕሬስ ውጤቱ ሲሞላለጩ የከረሙት፡፡

ደርግ በወቅቱ ስልጣኑን ለኢህአፓ ሰጠ ማለት ኢትዮጵያን ለገንጣይና አስገንጣዮች አሳልፎ ሰጠ የማለት ያህል ነው፡፡ ደርግ የእነዚህን ኃይሎች ተቃውሞ ለማለዘብ ሲል ሲሹት የኖሩትን ርዕዮትና ሀሳባቸውን ሁሉ በተግባር ቢለውጥም ማለዘብ አልቻለም፡፡ ኢህአፓ በደርግ አሰሳ ከከተማ ከተደመሰሰ በኋላም በርሃ ካሉ  ቡድኖች ጋር ተቀላቅሎ ሲታገልና በስተመጨረሻም ደርግ ሲወድቅ ያችኑ ዓላማ ተግባራዊ ማድረግን ነበር የመጀመሪያ ስራው ያደረገው፡፡ እንጅማ በዚያ ወቅት ኢህአፓ ዓላማው ስለኢትዮጵያና ስለህዝቦቿ ከልቡ ተቆርቁሮ ቢሆን ኖሮ በተከታይነት በምናየው በሶማሊያ ወረራ ከሶማሊያ ጎን ተሰልፎ ደርግን ባልወጋ ነበር፡፡



በጠንካራ ዲሲፕሊን የተደራጀውና አንድ አባል ለሦስት ተከታታይ ጊዜያት በስብሰባ ላይ ካልተገኘ እንደሚገደል ለአባላቱ ይፋ ያደረገው ኢህአፓ መንግስቱ ኃይለማርያም ላይ የመግደል ሙከራ ካደረገና በዶ/ር ፍቅሬ መርዕድ ላይ ከዚህ በፊት ያየነውን ግድያ ከፈፀመ ጀምሮ፤ በጊዜያዊ መንግስቱ ባለሥልጣናትና ደጋፊዎች ላይ "ነጭ ሽብርን" አውጆ ተከታታይ ግድያዎችን ፈጽሟል፡፡ ኢህአፓ በወቅቱ የግድያ ኢላማዎቹ ማን ማን እንደሆኑ ጠንቅቆ ያውቃል፤ ደርግ ግን በስተመጨረሻ በመኢሶን አመራር አባላት አማካኝነት የስም ዝርዝር እስኪቀርብለት ድረስ ምንም መረጃ አልነበረውም፡፡ "ቀይ ሽብር" የሚባለውን መፈክርም ደርግ አያውቀውም ነበር፡፡ ከነጭ ሽብር በኋላ ሊያውቀውና ሊፎክርበት ተገደደ፡፡ ስለቀይ ሽብር ብዙ ተብሏል፡፡ የቀይ ሽብር ሰለባዎች ታስበዋል፣ ተዘክረዋል፣ ሐውልትም ታንጾላቸዋል፡፡ ይህ ተገቢ ተግባር መሆኑ ለማንም ግልፅ ከመሆኑም በላይ፤ ለምን ተዘከሩ? የሚል ተቃውሞ አያስነሳም፡፡

ነገር ግን የነጭ ሽብር ሰለባዎችን እንኳን መዘከር ቀርቶ ስማቸውን ያነሳ አካል አለመኖሩ በርካቶችን አሳዝኗል፡፡

ጦርነት ነው፡፡ የወንድማማቾች የፖለቲካ ፀብ የፈጠረው ጦርነት፡፡ የነጭና የቀይ ሽብር ሰለባዎች ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ በኢህአፓም በደርግም በኩል ተሰልፈው በሁለቱም አይነት ሽብሮች በሽዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ተገድለዋል፡፡ በኢህአፓ ጎን የተሰለፉት የቀይ ሽብር ሰለባ ሲሆኑ፤ በደርግ በኩል የተሰለፉት የነጭ ሽብር ሰለባ ሆኑና፤ ደርግ ሲወድቅ ቀይ ሽብርን የፈፀሙት ለፍርድ ቀረቡ፡፡ ነጭ ሽብርና ሰለባዎቹ ግን ከታሪክ ተፍቀው ወጡ፡፡ፍትህ የአሸናፊዎች ደንገጡር ሆነች፡፡

በነጭ ሽብር ከተገደሉት ዜጎች ይልቅ በቀይ ሽብር የተገደሉት በቁጥር ቢበልጡም፤ በነጭ ሽብር ብቻ ግን 1 ሺ 119 ሰዎች እንደተገደሉ የተረጋገጠ ነው፡፡ እንዲያውም ከዚህ በላይ ናቸው የሚሉ በርካታ ምስክሮች አሉ፡፡ በቀይ ሽብር ያለቁትን ልዩ ዐቃቤ ሕግ 6 ሺ ነው ብሏል፡፡ የደርግ አባላት ግን 2ሺ ነው ብለው ይከራከራሉ፡፡ ምንም ቢሆን ቁጥሩ ተቀራራቢ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ የነጭ ሽብር ሰለባዎችን የሚፋረድላቸው አላገኙም፡፡

እነዚህን ኢትዮጵያውያን ታሪክ ረስቷቸዋል፤ ወይም እንዲረሳቸው ልዩ ጥረት ይደረጋል፡፡ የእነሱ ደም ከንቱ ሆኖ የቀረበት ምክንያት ምንድነው ሊባል ነው? ቢባል መልስ የለም፡፡ መጠየቅም ያስኮንናል፡፡ ኢህአፓ የመጀመሪያውን ጥይት ተኩሷል፡፡ ይህ ስልጣን ላይ ባለ መንግስት እይታ ሽብር ፈጠራ ነው፡፡ ሠላማዊ ትግል ግድያ አያካትትምና፡፡ ለአገርና ለህዝብ ተቆርቋሪ የሆነ ድርጅት ደግሞ በከተማ

ውስጥ ሆኖ ሠላማዊ ትግል እያደረኩ ነው ብሎ ጎን ለጎን በግድያ ተግባር መሠማራት ምን ማለት መሆኑ ለማንም አይሰወርም፡፡

በእስር ላይ የሚገኙ የደርግ ባለሥልጣናት በአንድ ነገር በጋራ ይፀፀታሉ፤በ60ዎቹ የጃንሆይ ባለስልጣናት ግድያ፡፡ በቀይ ሽብርስ? ሲባሉ በፍፁም አይፀፀቱም፡፡ "ራሳቸው የጫሩት እሣት ነው" ሲሉ ይመልሳሉ፡፡አሳማኝ መከራከሪያቸው "ነጭ ሽብርስ?" የሚለው ነው፡፡

ሻ/ል ተስፋዬ ርስቱ በ"ምስክርነት" መፃህፋቸው የኢህአፓን የግድያ ተግባር በሚያትቱበት ገጽ ላይ "... የድርጅቱ የፖለቲካ ቢሮ ተለዋጭ አባል የነበረው ጌታቸው ማሩ የእልቂት ድርጊታቸው ትክክል አለመሆኑን በመግለፁ መስፍን ሐረር መንገድ በላይ ዘለቀ በሽመቁበት ቦታ ገድለው ራሱን፣ እጁን፣ እግሩንና ሌላውን አካሉን ለየብቻ ቆራርጠው በጆንያ ከትተው ክፍሉ ታደሰና ተስፋዬ ደበሳይ አውጥተው ሊጥሉት ሲሉ (ለተገንጣይ ስትራቴጂስቶች ሲሉ) ሻለቃ ጌታቸው ሽበሽ የመራው ጦር ደርሶባቸው የተቆራረጠውን አስከሬን ጥለው አምልጠዋል፡፡ ..." በማለት የኢህአፓን ኢሰብአዊ ተግባር ይገልፃሉ፡፡

ሲቀጥሉም "... ለነገሩማ ተስፋዬ ደበሳይ በንግስት አዳነ ጠቋሚነት ፖስታ ቤት አካባቢ ሊያዝ ሲል አምልጦ ከአምባሳደር የመጨረሻ ፎቅ ተወርውሮ ራሱን የገደለው ለኢህአፓ በነበረው ቁርጠኛ እምነት ሳይሆን በታዋቂው የኢትዮጵያ የመረጃ ድርጅት ምርመራ የሻዕቢያን የአዲስ አበባ ግድያና የመረጃ መዋቅር አወጣው ይሆናል ብሎ ሰግቶ እንደነበር እነክፍሉ ታደሰ ገና ሊጠረጥሩ አልቻሉም..." ይሉናል፡፡ (ምስክርነት 2001 ዓ.ም ገፅ 145)

የታችኛው የኢህአፓ አባላት ትግላቸው ኢትዮጵያዊነትን የተላበሰ እንደሆነ አስበውና ተነግሯቸው ይፋለሙ እንጂ፤ ቁንጮ ቁንጮው አመራር የሻዕቢያ እቅድ አስፈፃሚዎች የነበሩ ናቸው፡፡ ፀሐፊው የአሠፋ ጫቦን ገለፃም አካተዋል፤ "ዶ/ር ፍቅሬ መርዕድ ባለቤቱን ሊያመጣ ሄዶ ከሚጠብቅበት ሞርጌጅ ባንክ ህንፃ አጠገብ በኢህአፓ ተገደለ፡፡ በአገራችን በኋላ ቀይ ሽብር፣ ነጭ ሽብር የተባለውን መንገድ የከፈተው የፍቅሬ መገደል ነበር፡፡ ብቻ የመጀመሪያውን ቃታ የሳበ ኢህአፓ ነበር" ሲሉ ያረጋግጣሉ፡፡

የእነክፍሉ ታደሰ አጋር የነበሩትን በመጥቀስም ".... አገሬ ዛሬ ለደረሰባት ንቅዝ የበላው ቤትነት አንድ ደርግ በሚባል ጭራቅ ላይ ብቻ ብንለክክ የሀሊና ንፅህና የምናገኝ አይመስለኝም" በሚል የዚያ ዘመን የ"ነጭ ሽበር" አራማጆች ጥፋታቸውን እያመኑ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በሌላ ወገን የመኢሶን አመራር አባላት ደርግ ላይ ብቻ ጥፋቱ ተደፍድፎ እንዲቀር የካዱ ይኑሩ እንጂ፤ ደርግ ቀይ ሽብርን ተግባራዊ ሲያደርግ የእነሱ እገዛ እንደነበረበት ያመኑ አልጠፉም፡፡ ከላይ የጠቀስናቸው ፀሐፊ



"... የኢህአፓ አባላትን ስም ዝርዝር መኢሶን ለደርግ ባይሰጥና በጋዜጣ ባይወጣ ደርግ የኢህአፓን ነብሰገዳዮች ከህዝብ ባህር ውስጥ ፈልፍሎ ለማውጣት ጊዜ ይፈጅበት ነበር" ይላሉ፡፡ (ገፅ 146)

በጥቅሉ ኢህአፓ ከላይ እስከታች መዋቅር ዘርግቶ በሚስጥራዊ ኮዶች ከአባላቱ ጋር እየተገናኘ የከተማ ውስጥ ትግሉን አጧጡፎ፤ ግድያውንም በነጭ ሽብር መፈክር አጠንክሮ ከመቀጠል ባለፈ፤ አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኝን ባንክ እስከመዝረፍ ድረስ የዘለቀ ተግባር ፈፅሟል፡፡ በአንድ ዙር ዝርፊያ ብቻ ከሾላ ገርጂ ባንክ ግማሽ ሚሊዮን ብር ዘርፏል፡፡ ለምሳሌ በሰኔ ወር 1969 ዓ.ም የአዲስ ከተማ ቁጭራ ባንክን የዘረፈው የሻዕቢያ አባል የሆነው ነይቶም ለባሲ የመራው የኢህአፓ ቡድን ነበር፡፡ በተጨማሪም በትግራይ በኩል ባስገቡት ፈንጂ የአዲስ አበባ መዘጋጃ ቤትና በዋቢሸበሌ ሆቴል አፈንድተው በርካታ ንፁሀን ሲቢሎችን ገድለዋል፡፡ (ትዝታዎች ቁ.1 ገጽ 30)

በዚህና በዚህ መሰል ተግባር ኢህአፓ ደርግን መቀመጫ አሳጣው፡፡እንደመንግስትም ሆነ እንደ ጊዜያዊ መንግስት ደርግ መከላከልና እርምጃ መውሰድ ነበረበት፡፡ነጭ ሽብሩ ተጧጡፎ በመቀጠሉም "አስታጥቁን አታስጨርሱን!" የሚለው ህዝብ በረከተ፡፡

ደርግና መኢሶን ተባብረው ባሳለፉት ውሣኔ ከላይኛው መቺ ጦር ጀምሮ እስከታችኛው የቀበሌ ተመራጮች ድረስ አስታጠቁ፡፡ "ነፃ እርምጃ በኢህአፓ ላይ እንዲወሰድ አወጁ፡፡ "ቀይ ሽብር ይፋፋም!" አሉ፤ ተፋፋመ፡፤ እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ አለ፤ ይኸውም ከኢህአፓ ጥቃት ራሱን እንዲከላከልና እንዲያጠቃበት የታጠቀውን መሣሪያ በተለይ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የነበሩት የቀበሌ ሹሞች በኢህአፓነት ሽፋን በግል ቂም በቀል እና በድንበር ገፋህኝ ... ወዘተ ሕገ-ወጥ ግድያዎች አከናውነዋል፡፡

ደርግና መኢሶን ከላይ እስከታች ካስታጠቁ በኋላም፤ "አብዮቱ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋግሯል" አሉ፡፡ ይህ አዋጅ በ1969 መገባደጃ ይፋ ከሆነ በኋላም ደርግ የነጭ ሽብር አራማጅ የሆኑትን ፀረ ሠላም ኃይሎች እያደነ በመያዝ፣ ከድተው በሚመጡ የኢህአፓ አባላት ጠቋሚነት እየታገዘ መዋቅራቸውን ማፈራረስ ጀመረ፡፡ የተያዙትንና ምስጢር አላወጣ ያሉትንም በከባድ ግርፊያ እያሰቃዩ ማወጣጣት፣ መግደል ስራው አደረገ፡፡ በ1971 ዓ.ም የኢህአፓን መዋቅር ለማፈራረስ እና የመሳሪያ ግምጃ ቤታቸውን ሳይቀር መግረክ ቢቻልም፤ ከወራት በኋላ እንደገና በልዩና በረቀቀ ዘዴ አባላቱ ሊደራጁ ሞክረዋል፡፡ በራሱ በደርግ ውስጥ ሠርጎ ለመግባት ጥረዋል፣ በየጦር ክፍሉም ሠርገው ለመግባትና የበላይ አዛዦችን እስከመመልመል ደርሰዋል፡፡

ባየነው መሠረት ኢህአፓ በራሱ ቀስቃሽነት የጀመረው ነጭ ሽብር ተጋግሎ በመቀጠሉ ደርግ እና መኢሶን የመልስ ምት ለመስጠት ቀይ ሽብር ብለው በማወጃቸው በርካታ አገር ወዳድና ወጣት የኢትዮጵያ ልጆች አልቀዋል፡፡ የመኢሶን ሚና እስከሸፈተበትና ህቡዕ ገባሁ ብሎ እስካወጀበት እስከ ሰኔ 10 ቀን 1969 ድረስ የቆየ ሲሆን፤ ቀሪውን እርምጃ ደርግ ራሱ ቀጥሎበታል፡፡ ስለሆነም በሁለቱም አይነት ሽብር ሠለባ ስለሆኑት ዜጎች ሲነሳ ተጠያቂው ደርግ፣ ኢህአፓና መኢሶን መሆናቸው መታወቅ አለበት፡፡ ከዚሁ ጋርም ስለቀይ ሽብር ሰለባዎች ሲነሳ ስለነጭ ሽብር ሰለባዎችም መዘከር አለበት የሚለው የብዙሃኑ ፍትሐዊ ምልከታ በክፉ ሊታይ እንደማይገባ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ "ክብር ለነጭ ሽብር ሰማዕታት" "ክብር ለቀይ ሽብር ሰማዕታት" ብለናል፡፡

ጓድ ቁጥር· አስራ አንድ ለገነት አየለ ቀይሽብርን በሚመለከት ከገለፁት ውስጥ ተከታዩ ሐተታ ይገኛል፤ "በኢህአፓ በትር በነጭ ሽብር የተጨፈጨፉት በይፋ የሚታወቀው 1,319 ይሁን እንጂ ቁጥራቸው ከዚህ በላይ ነው፡፡ አሁን እኛን በቀይ ሽብር የሚወነጅሉን ለምን የነጭ ሽብርን ሰለባዎች አይፋረዱላቸውም? እነሱ ኢትዮጵያውያን አይደሉም? ወይስ የእነሱ ደም ደመ ከልብ ነው? የቀይ ሽበር ተፋራጅ ኮሚቴ እንደተቋቋመ ሁሉ፤ የነጭ ሽብርም ቢቋቋም ኖሮ ፍትሐዊ ይሆን ነበር፡፡ ቀይ ሽብርን ከመጠሪያው ከቃሉ ጀምሮ ያመጡት እነሱው ራሳቸው ናቸው፡፡ ወታደር ይሄንን ከየት ያውቃል? በሶማሊያ ወረራ ወቅት ኢህአፓ የፈፀመው ክህደት መረሳት የለበትም፡፡ በኤርትራም ችግር ኢህአፓ በግልፅ የወገነው ከጠላቶቻችን ጋር ነበር፡፡ ሻዕቢያን እንደሚደግፍ በይፋ ተናግሯል፡፡ በኢትዮጵያ ሕግ ደግሞ በአገር ላይ የሚፈፀም ክህደት እስከሞት ድረስ ያስቀጣል፡፡…" (ገፅ 31) በመጨረሻ ዋናው አቀናባሪ ተስፋዬ ደበሳይ ያለበት ቦታ በጥቆማ ተደርሶበት ደርግ ሲከበብ ራሱን ከፎቅ ወርውሮ ከሞተ በኋላ ግድያው ጋብ እንዳ። የቀድሞው ሊቀመንበር መንግስቱ ይናገራሉ፡፡ በ1970ዎቹ የመጀመሪያ አመታት ጀምሮም ኢህአፓ እየተሰነጣጠቀ፣ እየተበታተነ ሂደ፡፡ ብርሃነመስቀል ረዳም ከባለቤቱ ጋር ከከተማ ወጥቶ ሲሸሽ ወሎ አካባቢ በገበሬዎች እጅ እንደተገደለ ይነገራል፡፡ ባለቤቱ ወ/ሮ ታደለች ኃይለሚካኤል ነብሰጡር ስለነበሩ የተባሉት ገበሬዎች ሳይገድሏቸው እንደተረፉ እና ለረጅም ዓመታት በእስር ላይ ቆይተው ኢህአዴግ አዲስ አበባ ሲገባ ከእስር ተፈትተው፤ በመጀመሪያ የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ፣ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በኮትዲቫር የኢትዮጵያ አምባሳደር እንደሆኑ በ"መንግስቱ ትዝታዎች" ቁጥር 1 መጽሐፍ በገፅ 190 ተጠቅሶ ይገኛል፡፡

የቀይ ሽብርን ሕገወጥነት በሚመለከት መንግስቱ ሲጠየቁ፤ "እሺ እኛስ እንዲህ ተባልን፡፡ ሌላውስ ምን ሲያደርግ ነበር? ለምን የሌላው ወገን



ስህተት አይታይም? ኢህአፓ በየትኛው ሕግ ተመርታ ኖሯል ሰውን በጠራራ ፀሐይ እየደፋች ስትሂድ የነበረው? በየትኛው ፍርድ ቤት ብይን አግኝታ ነው ሰው ላይ እርምጃ ስትወስድ የነበረው?" በማለት ነው፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን ተደጋግሞ እንደተገለፀው ከስር ያሉ የኢህአፓ ምልምል አባላት አብዛኛዎቹ ለኢትዮጵያ አብዮት እየታገሉ እንደሆነ ነበር የሚያውቁት፡፡ ለዚህም ነው ተበትነው ወደ በረሃ ሲገቡ ብዙዎች ያልጠበቁት ጉዳይ የገጠማቸውና የተገረሙት፡፡ ይህን ጉዳይ ከመንግስቱ ኃይለማርያም ገለፃ ተረድተን እናብቃ፡፡

"… እዚህ ላይ ሁልጊዜ የማይነሳ ወይም ሆን ተብሎ የሚዘለል ጥያቄ አለ፡፡ ኢህአፓ ሠርጎ ገቦችና ከሞላ ጎደል የከተማ ትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ፤ ለዚያውም በሚሰጣቸው ሊስትና ጥቆማ ዒላማ የሚመቱ የተወሰኑ ወጣቶችን በከተማ ውስጥ ስታሰማራ ከተከታዮቿ የሚበልጠው ኢትዮጵያን ለማጥለቅለቅና መንግስትን ለመገልበጥ የተሰበሰበው ኃይሏ የሂደው ትግራይ አሲምባ ነው፡፡

"የት ሂደ ያሁሉ የኢትዮጵያ ወጣት? የት ደረሰ? ማን ፈጀው? ይሄንን የጠየቀ ሰው አለ? የኢህአፓ ዋናው ሠራዊት የነበረው ትግራይ ነበር፡፡ አሲምባ የከተተው ያ ሁሉ የት ደረሰ?

"ልጆቹ የኢህአፓን ዓላማ ለማራመድ ትግራይ ሲሄዱ ያልገባቸው ነገር አለ፡፡ እነሱ አብዮት የሚያካሂዱ፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚታገሉ ነው የመሰላቸው፡፡ ብሔራዊ ስሜት የነበራቸው ናቸው፡፡ እዚያ ሲደርሱ ግን ያጋጠማቸው ጀብሃና ሻዕቢያ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ብሎ ነገር በአጀንዳቸው የሌለ ፍፁም ፀረ ኢትዮጵያ አቋም ያላቸው ገንጣዮች፡፡ እንዴ? ምንድነው ይሄ ነገር? የሚል ጥያቄ ሲያነሱ "አሃ!" ይህቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም" ተብሎ በወያኔ ሠራዊት ተጨፍጭፈዋል፡፡ እተኙበት ቦታ፣ ለ…ሽ ብለው እንደተኙ ሌሊት በደንብ በተዘጋጀ ሠራዊት ጭፍጭፍ አድርገው ፈጅተዋቸዋል፡፡ በዚህ አይነት በግፍ ያለቁት ቁጥር ስንት ነው? ይህን ያነሳ አለ? መለስ ዜናዊ "ኢህአፓ" እያለ ተቆርቋሪ ሆኖ ሲናገር ግርም ነው የሚለኝ፡፡ ወደደም ጠላም ህሊና ካለው ዛሬ ለህሊና ፍርድ ነገ ደግሞ ለህዝብ ፍርድ መቅረቡ የማይቀር ነው፡፡ የትግራይ ህዝብ ይሄንን ያውቃል፡፡ ኢህአፓዎች ሁሉም አላለቁም፡፡ ቢጠየቁ ይናገራሉ፡፡"

ገነት፤ "እና እርሰዎ የሚሉት ወያኔ ነው የፈጃቸው ነው?"

መንግስቱ፤ "ታዲያስ! ወያኔና ሻዕቢያ በአንድነት ነው የፈጇቸው፡፡ "እኛ አሰልጥነንና አስታጥቀን ለዚህ ስናበቃቸው የኢትዮጵያን አንድነት ይጠይቃሉ እንዴ?" ብለው ነው ሙልጭ አድርገው ያጠፏቸው፡፡ እኛ እንደሆነ መጀመሪያ ነገር አሲምባ ሠራዊት የሚባል አልነበረንም፡፡ እዚያ ሂደንስ እናውቃለን እንዴ? የእኛ ሠራዊት የዚያን ጊዜ ያለው ምፅዋና ባሬንቱ ነበር፡፡" (ትዝታዎች ቁጥር 1 ገጽ 207)

እናም የሸማቂ ቡድኑን የደገፉት እዚያው ቀርተው ሲታገሉ፡ ያልደገፉት ወደ ደርግ ተመልሰው ይቅርታ በመጠየቅና ወደ መንግስት ስራዎች ገብተው እስከ ደርግ ፍፃሜ ድረስ ሲቆዩ፣ ጥቂቶቹ ተሰደዋል፡፡ ሌሎቹም ተገድለዋል፡፡ •

## የምስራቁ ጦርነት

ኢጣሊያና እንግሊዝ ተካፍለው ይዘዋት የነበረችው ሶማሊያ፣በ1952 ዓ.ም ነፃ ከወጣች በኋላ የራሷን ነፃ መንግስት መስርታ ከ1953 ጀምሮ በጠቅላይ ሚኒስትር ሸርማኬን ዓሊ ስትመራ ከቆየች በኋላ ኢትዮጰያን የመውረር እቅድ እንደነበራት በተደጋጋሚ ባሳየችው ሙከራ አረጋግጣለች፡፡ነገር ግን በመፈንቅለ መንግስት ስልጣን የያዙትን የዚያድ ባሬን ያህል የተጠናከረ ዘመቻ አልተደረገም፡፡የዚያድ ባሬ መንግስት ከ1969-1973 ዓ.ም በተጠናከረ ዘመቻ ኢትዮጵያን ተፈታትኗል፡፡በ1956 በጃንሆይ ዘመን የወረራ ሙከራ ያደረገችው ሶማሊያ ሙከራዋን የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት በእንጭጩ ማስቀረት ችሏል፡፡

በ1970 ዓ.ም ተመሳሳይ ሙከራ ያደረገው የዚያድ ባሬ መንግስት በድጋሚ ተሸንፎ ተባረረ፡፡ ከዚህ በኋላ የአንድ ዓመት ከፍተኛ ዝግጅት በማድረግ 'የኢትዮጵያ ጦር ፊቱን ወደ ኤርትራ ማዞሩንና ከምስራቁ ግንባር ጦር ተቀንሶ ወደ ሰሜን መዝመቱን በመረዳት የዳግም ወረራ እቅዷን ለማሳካት እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመረች፡፡ በኢትዮጵያ የበረራ ክልል ውስጥም የሶማሊያ አየር ኃይል ከ100 ጊዜ በላይ ጥሶ መግባቱ በጋሃድ ታየ፡፡

የዚያድ ባሬ እቅድና ፍላጎት ታላቋን ሶማሊያ ለመመስረትና በዚህ ምስረታም ኦጋዴን መካተት አለበት የሚል ነው፡፡

"ኦጋዴን በግዛትም፣ በባህልም፣ በቋንቋም፣ በሃይማኖትም ሆነ በዘር ረገድ የሶማሊያ አንድ አካል ነውና ህዝቡም ግዛቱም ወደ ታላቋ ሶማሊያ መጠቅለል አለበት" የሚል አቋም የያዙት ዚያድ ባሬ በተለያዩ አገራት መሪዎች ቢመከሩ፣ ቢዘከሩ እንቢ አሉ፡፡ የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ አገሮችን የግዛት ወሰን ሲከልል ኦጋዴንን የኢትዮጵያ ማድረጉም ሆነ ከዚያ በፊት ከነበሩት ዘመናት ጀምሮ የኢትዮጵያ ግዛት መሆኑን ዚያድ ባሬ ቢያውቁም የወረራ እቅዳቸውን ተግባራዊ ከማድረግ አልተቆጠቡም፡፡

ሶማሊያና ኢትዮጵያ ሶሻሊስት አገሮች የነበሩ በመሆናቸውም የሊቢያው ጋዳፊ፣ የኩባው ፊደል ካስትሮና ሌሎች ሊቀመንበር መንግስቱንና ዚያድ ባሬን ለማግባባት በእጅጉ ጣሩ፡፡ ኢትዮጵያ ያለባትን አጣብቂኝ አገናዝባ ወደ ዲፕሎማሲው ብታጋድልም አልሆነም፡፡ በዚህ መሀል ሶቭየት ማን እንደሚሻላትና ማንን ብትረዳ እንደምትጠቀም ስታወጣ ስታወርድ ቆየች፡፡ በመጨረሻ ዚያድ ባሬ የሶሻሊዝም አራማጅነታቸውን ጥርጣሬ ውስጥ የሚከት እንቅስቃሴዎችን በማሳየታቸው



ሶቭየት ስትረዳቸው ከቆየችው ከሶማሊያና ከኢትዮጰያ ማንን መምረጥ እንዳለባት ተረዳች፡፡ "በቃል ብቻ ሶሻሊስታዊ አገር ናት ከሚሉት ዚያድ ባሬ ይልቅ በተግባር ያረጋገጡት የሊቀመንበር መንግስቱ አገር ትሻለናለች" በሚል ውሣኔ ሶቭየት ለኢትዮጰያ ያልተቆጠበ የማቴሪያል ድጋፍ አደረገች፡፡ (በወቅቱ ኢህአፓ የሶማሊያንና የሻዕቢያን ወረራ ትክክል ነው ብሎ እውቅና የሰጠ ሲሆን፣ ይህንንም ዴሞክራሲያ በተሰኘ ልሳኑ ይፋ አድርጓል፡፡)

የሶማሊያ መንግስት ሠርጎ ገቦችን በኦጋዴን ድንበር እያስገባ የኢትዮጵያን አንዳንድ የመሠረተ ልማት አውታሮች በፈንጂ ማውደምና ሌሎች ተመሣሣይ ተግባራትን ሲያከናውን ቆዬ፡፡ ቀጥሎ መደበኛ ሠራዊታቸውን በኢትዮጵያና በጅቡቲ ድንበር በኩል እስከ ሽንሌ፣ በኦጋዴን በኩል እስከ ቀላፎ፣ በባሌና በሲዳሞ ክፍለሀገሮች በኩል ሞያሌና ነገሌ ቦረና ድረስ በማስገባት ይፋዊ ወረራ አደረጉ፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት የኤርትራው ጦርነት ፋታ ባይሰጠውም በተቻለ መጠን የሱማሊያን ጦር በፍጥነት ለመደምሰስ ይቻል ዘንድ "ዘመቻ ላሸ" የተባለ የውጊያ እቅድ ነደፈ፡፡ ሊቀመንበር መንግስቱ ዘመቻው ተግባራዊ እንዲሆን በህዳር 1972 ዓ.ም ለመከላከያ ሚኒስትር ትዕዛዝ ሰጡ፡፡

ዘመቻው ተገቢ ዝግጅት ከተደረገበት በኋላ በአራት ምዕራፍ ተከፈለና፣ 1. ነሐሴ 22 ቀን 1972 ዓ.ም ተጀምሮ ከሽነሌ ተነስቶ ጅቡቲንና ሶማሊያን ከኢትዮጵያ ጋር የሚያዋስነውን ድንበር አፅድቶ ህዳር 15 ቀን 1973 እንዲጠናቀቅ፣ 2. ወደ ደጋማው የሐረርጌ ክፍል ሠርገው የገቡ የሶማሊያ ታጣቂዎችን ማፅዳት ስለሆነ ከመጀመሪያው ምዕራፍ እኩል በሆነ የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቅ፣ 3. በሁለቱ ምዕራፎች ድል የሚደረጉት ወራሪዎች በዋርዴር፣ በቀብሪደሐርና በጎዴ አውራጃዎች የሚጠራቀሙትን ኃይሎች መምታትና ማባረር ሲሆን፣ ይህም ጠንካራ ዘመቻ ስለሚሆን ነሐሴ 22 ቀን 1972 ዓ.ም ተጀምሮ በታህሳስ ወር 1973 ዓ.ም እንዲጠናቀቅ፣ የሚል ሆነና በታቀደው መሠረት በጀግናው የኢትዮጰያ ጦር ሠራዊት ድል ከሆነ በኋላ 4ኛው ምዕራፈ ቀጠለ፡፡ ይህም በየቦታው ከተደመሰሱት ሠርጎ ገብ ኃይሎች ተርፈው የሸሹትንና ቁጥራቸውም ከ30 ሺ በላይ የሚሆኑትን የሶማሊያ እግረኛና ሜካናይዝድ ኃይሎች ተጠራቅመው የመሸጉበትን 420 ኪሎ ሜትር ስፋት ያለውን ግዛት ነፃ ማውጣት የሚል ነበር፡፡ ይህም በታህሳስ 15 ቀን 1973 ዓ.ም ተጀምሮ 10 ቀናት የፈጀ የምድርና የአየር ውጊያ ተደርጎ በኢትዮጵያ የበላይነት ታህሳስ 15 ቀን 1973 ዓ.ም በድል ተደመደመ፡፡ (ነበር ቁጥር 2)

በዚህ ጦርነት ከሶማሊያ ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያም ከፍተኛ የህይወት መስዋዕትነት ተከፍሏል፡፡የኢህአፓ አባላትም ከሶማሊያ ጎን

ተሰልፈው መዋጋታቸውና መንገድ መሪ ሆነው ሶማሊያን ማገዛቸው በደምብ የሚታወቅ ነው፡፡በተጨማሪም ዚያድ ባሬና የኤርትራ አማፂያን መሪ "እኔ ከዚህ አንተ ከዚያ" በሚል ትስስርም፣ትብብርም አድርገው ነበር፡፡ "ሆኖም ዘመቻ ላሽ" ስኬታማ ሆኖ ወራሪው ጦር እንደ ላሽ ጥርግ ተደርጎ ተወገደ፡፡የዚያድ ባሬ መንግስት ያ ሁሉ ዝግጅት ከንቱ ሲሆንበት ክፉኛ ተበሳጭቶ በመጋቢት ወር 1973 ዓ.ም "ኢትዮጵያ በሶማሊያ ላይ ወረራ አውጃ ጦሯ ወደ ሞቃዲሾ እየገሰገሰ ነውና ከሠራዊትህ ጎን ተሰልፈህ ለአገርህና ለሃይማኖትህ ተዋጋ..." በማለት ለህዝቡ ጥሪ አቀረበ፡፡ ወዲያውም በግንቦት ወር 1973 ዓ.ም የመልሶ ድርጅታቸውን አጠናቀው ለ3ኛ ጊዜ ኢትዮጵያን ወረሩ፡፡የኢትዮጵያ ሠራዊት በ6 ቀናት ውስጥ የሶማሊያን ጦር ብትንትኑን አወጣው፡፡

ከዚህ በኋላም የሠላም ድርድሮች በየመንና በሌሎች አገራት ቢደረጉም ለውጥ የለም፡፡ ዚያድ ባሬ "ኦጋዴን ካልተሰጠችኝ ሠላም ብሎ ነገር የለም!" የሚል ቁርጥ ያለ አቋም ያዙ፡፡ ሊቀመንበር መንግስቱ የሶማሊያ የወረራ እቅድ ለዝንት ዓለም የማይለወጥ መሆኑን በመረዳት "እሾህን በእሾህ" የሚለውን መርህ ለመከተል ወሰኑ፡፡ የደርግ መንግስት በኦጋዴን አካባቢ የነዳጅ ዘይት ቁፋሮ እቅድም ነበረውና ይህም እውን ይሆን ዘንድ የምስራቁ ጦርነት ዛላቂ እልባት ማግኘት ስላለበት፤ ለዚህ ደግሞ የዚያድ ባሬ መንግስት መወገድ ብቸኛው መፍትሄ መሆኑን ተረድቶ እሾህን በእሾህ ቢልም፤ ለተግባራዊነቱ ግን የኢኮኖሚ አቅም አልነበረውም፡፡ ስለዚህ የሁነኛ ወዳጅ እገዛ ያስፈልግ ነበርና ጋዳፊን መምረጥ መፍትሄው ሆነ፡፡

ንጉስ እድሪስን በኃይል አውርደው ስልጣን የያዙት ጋዳፊ አንድ የተባበረ የዓረብ መንግስት የመመስረት እቅድ የያዙት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡እንቅስቃሴያቸውንም ጀምረው ለዓረብ አገራት የነፃነት ታጋዮች እገዛ ማድረግ የጀመሩት በማለዳ ነበር፡፡የሱዳኑ ጄኔራል ጃፋር ኑሜሪ እና የሶማሊያው ዚያድ ባሬ ብቻ የጋዳፊን የእስልምና ተከታይ የሆኑ የአፍሪካ አገራትን የማስተባበርና የበላይ የመሆን እቅድ አልተቀበሉትም ነበርና ፀበኞች ነበሩ፡፡

ሊቢያና ኢትዮጵያ ደግሞ በ1970 ደቡብ የመን ውስጥ የጋራ የሠላም ስምምነት ተፈራርመዋል፡፡ ስለዚህ የመንግስቱን የ"እሾህን በእሾህ" እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ከጋዳፊ ጋር ከነበረው የበለጠ ግንኙነቶችና ምክክሮች ቀጠሉ፡፡ ጋዳፊ የኢትዮጵያን ጥያቄ ወዲያው ተቀበሉት፡፡ ጋዳፊ ለሱዳን አማፅያን በጆን ጋራንግ ይመራ ለነበረው ቡድን እገዛ ያደርጉ ነበር፡፡ በሶማሊያም ተመሳሳይ ተቃዋሚ ቢኖር ሊረዱ ዝግጁ ናቸው፡፡



ጄኔራል ፋራህ አይዲድ የሶማሊያ ምድር ጦር አዛዥ ነበሩ፡፡ ከፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ጋር ስላልተስማሙ ታስረው ቆዩና በ1969 ዓ.ም የሶማሊያ ጦር ኢትዮጵያን ሲወር ያስፈልጉ ስለነበር ተፈቱና አዛዥነታቸውን እንደገና ተረከቡ፡፡ አሁንም በድጋሚ ተጣሉ፡፡ የጥላቻው መንስኤም ኢትዮጵያን መውረር የለብንም የሚል ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ዚያድ ባሬ ከጦር አዛዥነታቸው አንስተው በህንድ የሶማሊያ አምባሳደር አደረጓቸው፡፡

የሁለቱን መቃቃር የሚያውቁት ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያም የሊቢያን ድጋፍ እንደሚያገኙ ካወቁ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ሲነግሯቸው ጄኔራል ፋራህ ወዲያው ወደ አዲስ አበባ መጡ፡፡ "ዚያድ ባሬን ከስልጣን አውርድና አንተ ስልጣን ያዝ፤ ኢትዮጵያና ሶማሊያም ወዳጅ አገር ይሁኑ" አሉ መንግስቱ፡፡ ጄኔራል ፋራህ አይዲድ "እሺ" አሉና ቡደናቸውን አደራጅተው በዚያድ ባሬ መንግስት ላይ የትጥቅ ትግል ጀመሩ፡፡

ኮሎኔል አብዱላሂ የሱፍ በሶማሊያው መሪ በዓሊ ሸርማኬን ላይ መፈንቅለ መንግስት ሞክረው ታስረው የነበረ ሲሆን፤ ዚያድ ባሬ በስልጣን ሲተኩ ከእስር የተለቀቁ ናቸው፡፡ ከዚያድ ባሬ ጋርም ወዲያው ተጋጩና ታሰሩ፡፡ ከዓመታት በኋላ ከእስር እንደተፈቱ በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ጥገኝነት ጠይቀው መኖር ጀምረዋል፡፡

መንግስቱ ኃይለማርያም ድጋፍ እንደሚያደርጉላቸው ቃል ስለገቡላቸው የጄኔራል ዚያድ ባሬን መንግስት ለመጣል የትጥቅ ትግል በ1972 ዓ.ም ጀመሩ፡፡ ከዚያም ባለፈ በሶማሊያ "የሶማሊያ ብሔራዊ ንቅናቄ" (ኤስ.ኤን.ኤም) የተሰኘ ተቃዋሚ ቡድን ነበረና በጄኔራል ፋራህ አይዲድ የሚመራው "የሶማሊያ ብሔራዊ ቅንጅት" (ኤስ.ኤን.ኤ) በኮሎኔል አብዱላሂ የሱፍ የሚመራው "የሶማሊያ መድህን ቅንጅት" (ኤስ. ኤን. ኤም) ሲጨመሩ ሦስት የተለያዩ ተቃዋሚ ቡድኖች ሆነው በዚያድ ባሬ ላይ እንዲነሱ ሆነ፡፡

ለእነዚህ ኃይሎች ኢትዮጵያ ታስፈልጋቸው ነበርና፣ ኢትዮጵያ የመደራጃ መሬት፣ ማረፊያ ቦታ፣ የስልጠናና የህክምና አገልግሎትን ጨምሮ የሰው ኃይል ድጋፍ ሳይቀር ስታደርግላቸው፣ ሊቢያ የስንቅ፣ የትጥቅና ሌሎች ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ ወታደራዊ ቁሳቁሶችን ታሟላ ጀመር፡፡ ኢትዮጵያና ሊቢያ ለአማፅያኑ ነፃ ፓስፖርት፣ ነፃ እንቅስቃሴ፣ ለፕሮፓጋንዳ የሚውሉ ነፃ የሚዲያ አውታሮችን መፍቀድ እንዳለባቸው ተስማምተዋል፡፡

ከሊቢያ የሚመጣውን መሣሪያ ኢትዮጵያ እየተረከበች ታከፋፍላለች፤ በዚህ መልኩ የሱዳንና የሶማሊያ አማፅያን እየተጠናከሩ ሄዱ፡፡

በጄኔራል ፋራህ እና በኮሎኔል አብዱላሂ የሱፍ የሚመሩ ቡድኖች ጠንካራ ተፋላሚ መሆን ቢችሉም፤የኮሎኔል አብዱላሂ ሁኔታ ግን ለሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያም የሚዋጥ አልሆነም፡፡ መንግስቱን ወደ ጎን አድርገው በግላቸው በምስጢር ከጋዳፊ ጋር ብቻ በተደጋጋሚ መገናኘት አዘወተሩ፡፡ ከኢትዮጵያ መንግስት ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም ለመስማት አልቻሉም፡፡ "ኢትዮጵያ የወደፊት ጠላቷን በጉያዋ ሸጉጣ አታሳድግም" አሉና መንግስቱ ኃይለማርያም ወደ እስር ቤት ወረወሯቸው፡፡ ይመሩት በነበረው ቡድን ላይም ዓሊ መሐዲ መሐመድ የተባሉ ሶማሊያዊ እንዲመሩት ተተኩ፡፡ የአብዱላሂ የሱፍን መታሰር ጋዳፊ ተቃወሙና ከመንግስቱ ጋር ተቃቃሩ፡፡ ከዚህ በኋላ ሦስቱ አንጃዎች የጋዳፊንና የመንግስቱን ድጋፍ ተንተርሰው ከግባቸው መድረስ ስለነበረባቸው የሁለቱን አገራት መሪዎች በተናጠል እያባበሉ ቀጠሉ፡፡

ሦስቱ ቡድኖች በሐርጌሳና በሞቃዲሾ በኩል እያጠቁ አብዛኛውን የሶማሊያ መሬት በቁጥጥራቸው ስር አደረጉ፡፡

በሐርጌሳና በሞቃዲሾ መሀል የሚገኘው ሁሉም የመገናኛ መስመር ተቋረጠ፡፡ ስለዚህ የሀርጌሳና የሞቃዲሾ ግንኙነት በአየርና በባህር ብቻ መሆን ነበረበት፡፡ የሶማሊያ ከሁለት የመሰንጠቅ ታሪክም ከዚሁ ጀመረ፡፡

የጋዳፊ ማኩረፍ ለመንግስቱ ኃይለማርያም ከባድ ፈተና ቢሆንም፤ ያለረዳት የተጀመረውን የእሾህን በእሾህ እቅድ ብቻቸውን ዳር ለማድረስ አልተሳናቸውም፡፡

የጄኔራል ፋራህ አይዲድና የዓሊ መሐዲ መሐመድ ቡድኖች በመጨረሻ በጥር ወር 1983 ዓ.ም ሞቃዲሾንም በቁጥጥር ስር አውለው ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬን ከስልጣን አስወገዱ፡፡ የፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም የእሾህን በእሾህ እቅድም በመጨረሻዋ የስልጣን ጊዜያቸው እውን ሆኖ አዩት፡፡ በዚህ ተግባራቸውም ሶማሊያ ኢትዮጵያን የማታሰጋ አገር እንድትሆን አደረጉ፡፡

እነዚያ ሦስት ቡድኖች በጋራ የዚያድ ባሬን መንግስት ያስወግዱ እንጂ ስለቀጣዩ ሂደት ምንም የተወያዩት ነገር አልነበረምና እርስ በርስ ሲናቆሩ ኖሩ፡፡ ሶማሊያም ከሁለት ተከፈለች፣ መንግስት አልባ ሆናም ሁለት አስርት አሳለፈች፡፡ የሶማሊያ ቀውስ ዛሬም ድረስ የቀጠለ ሆኖ ይታያል፡፡ ዚያድ ባሬ ያለሙት ታላቅነት ጭራሽ አገራቱን አሳነሳት ማለት ነው፡፡በዚህ መሠረት የደርግ መንግስት በዘመኑ የተረከባትን አገር ዳር ድንበሯን አስከብሮ የመቆየት ኃላፊነቱን በውጊያም በዘዴም ተወጥቷል፡፡



የሰሜኑ ጦርነት

በምስራቁ ግንባር ድልን የተጎናፀፈው የደርግ ጦር፤ "የምስራቁ ድል በሰሜን ኢትዮጵያም ይደገማል!" ብሎ ፊቱን ወደ ሰሜኑ ግንባር አዞረ፡፡

ባለፈው ምዕራፍ እንዳየነው በኤርትራ የትጥቅ ትግል ቀድሞ የጀመረው ጀብሃ፣ እንዲሁም አፈንግጦ የወጣው ሻዕቢያ የአካባቢው ፀረ ሠላም ኃይሎች ሆነው ቆይተዋል፡፡

ከ1967 ጀምሮ ደርግ በሁለቱም ላይ የከፈተባቸው ዘመቻ እንኳ ኅብረት እንዲፈጥሩ አላደረጋቸውም፡፡ የደርግ ጥቃት ሲመጣባቸው የተናጠል መከላከል ሲያደርጉ፤ ጥቃቱ ጋብ ሲል እርስ በርስ እየተዋጉ ዓመታት ካሳለፉ በኋላ በ1973 ጅብሃ በሻዕቢያ ሙሉ ለሙሉ ተደምስሶ ሻዕቢያ ብቻውን ተጠናክሮ የወጣ ኃይል ሆኗል፡፡

የመጀመሪያው የደርግ ማጥቃት የተሰነዘረው በ1968 "ዘመቻ ራዛ" በሚል የሰሜን ኢትዮጵያ አርሶ አደሮችን አሰባጥሮ ለማዝመት የተደረገው ሙከራ ሲሆን፤ እቅዱ ሙሉ ለሙሉ ባይሰምርም 10 ሺህ የሚሆኑ የሰሜን ወሎ አርሶ አደሮችን አሰባሰቦ ለማዝመት ተችሎ ነበር፡፡ ነገር ግን የህወኀትና የኢህአፓ የታጠቁ ሠራዊቶች "የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት" (ኢሕአሠ) በሰነዘረባቸው ወታደራዊና ፕሮፓጋንዳዊ ጥቃት ተዋክበው እንኳን ኤርትራ ሊደርሱ የትግራይንም ግዛት ማለፍ ሳይችሉ ድሉ ሆነው ተበታትነዋል፡፡ ገበሬዎችን ማዝመት ግድ የሆነው ዋናው ጦር ለምስራቁ ግንባር ያስፈልግ ስለነበር ነው፡፡ ሁለተኛው ጠንካራ ዘመቻ ደግሞ በ1970 ዓ.ም ክረምት ላይ ስምንት ግብረኃይሎች ተዋቅረው እንዲዘምቱ የተደረገበት እርምጃ ሲሆን፤ በዚህ ዘመቻ የደርግ ሠራዊት ጀብሃና ሻዕቢያ ቀደም ብለው የተቆጣጠሩዋቸውን የኤርትራ ዋና ዋና ግዛቶች ለቀው እንዲሸሹ ያደረጋቸው ሆኖ ነበር፡፡

በዚህ ጥቃት ሻዕቢያ አስተማማኝ ደጀኑ ወደሆነው የተፈጥሮ ምሽጉ ወደ ናቅፋ እንዲያፈገፍግ ተገዷል፡፡ ያም ቢሆን የሻዕቢያ አስጊነት ቀጣይ ሆኖ በመገኘቱ ሦስተኛና የመጨረሻ የሆነ መጠነ ሰፊ ዘመቻ በሻዕቢያ ላይ መደረግ ነበረበትና "የቀይ ኮከብ ዘመቻ" ታወጀ፡፡ የዚህ ዘመቻ ዓላማ በየእለቱ እየተጠናከረና በመሐልም ጀብሃን አስወግዶ ትጥቅና የሰው ኃይሉን በምርኮም፣ በእርዳታም አጎልብቶ፣ ሲችል ፊት ለፊት የሚዋጋውን፤ ሳይችል በየከተሞች ላይ ልዩ ልዩ የመሠረተ ልማት አውታሮችን በፈንጅ እየደረመሰ፣ የመንግስት ተቋማትን እያጋዬ፣ የህዝብ መገልገያዎችን እያወደመ፣ ባለስልጣናትን በሠርጎ ገብ ኃይሎች እያፈነ ወደ በረሃ የሚወስደውን ሻዕቢያን ለመጨረሻ ጊዜ መደምሰስ ነው፡፡

የናቅፋ ተራራ በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ብዙ የተወራለትና ታዋቂነቷን ያገኘ የጦር አውድማ ነው፡፡ሻዕቢያ በዓለም ማኅበረሰብ ዘንድ ስሙ ሲነሳ የናቅፋ ተራራም አብሮ ይነሳል፡፡ሻዕቢያ ይህን ቦታ ለቀቀ ማለት ህልውናው ብቻ ሳይሆን ስሙም አይኖርም፡፡ይህን ቦታ ለመያዝ ደግሞ ያለውን ኃይልና ጉልበት ተጠቅሞ ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍሏል፡፡ናቅፋን ቀድሞ የያዘ ጦር ጠላቱን መዋጋት መከላከል ሳይጠበቅበት ቦታው ራሱ ይዋጋለታል፡፡ለዚህም ነው ደርግ ፍፁም የማይመጥነውን ኢምንት ኃይል በምድር ጦርም በአየር ኃይልም ድል ለማድረግ የተሳነው፡፡

የኢትዮጵያ ጊዜያዊ መንግስት በወቅቱ የሱዳኑን መሪ በ1973 ዓ.ም ወደአዲስ አበባ ጠርተው ለሻዕቢያ የሚያደርጉትን ወታደራዊ እርዳታ፣ ነፃ እንቅስቃሴ መፍቀድ፣ ለሥልጠና ቦታ መመደብና እንደማንኛውም ዓረብ አገር ለሻዕቢያ የሚያደርጉትን ድጋፍ እንዲያቆሙ መንግስቱ ሊያግባቧቸው ብዙ ጥረዋል፡፡

ኑሜሪ ግን በቃል እሺ ብለው በተግባር እምቢታቸውን ገፉበት፡፡ ሻዕቢያ ግን ከናቅፋ ተራሮች ወርዶ የመልሶ ማጥቃት ተግባሩን ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ ነው መንግስቱ ጆን ጋራንግን "በርታ" በማለት የራሳቸውን ችግር ደግሞ በራሳቸው ለመፍታት በሻዕቢያ ላይ የመጨረሻ የማጥቃት እርምጃ መውሰድ የሚያስችለውን እቅድ "የቀይ ኮከብ ዘመቻ"ን ተግባራዊ ለማድረግ የተፋጠኑት፡፡

ለአንድ ዓመት ያህል ከፍተኛ ዝግጅት የተካሄደበትና በ1974 ተግባራዊ የሆነው ይህ "የቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ" ኢትዮጵያ በታሪኳ በአንድ ጊዜ የጦርነት ዘመቻ ብቻ ከፍተኛ ገንዘብ የመደበችበት የመጀመሪያው አከሳሪ ዘመቻ ነው፡፡

ራሱን የቻለ ጠንካራ ምክር ቤት የተቋቋመለት ይህ ዘመቻ በስራ አስፈፃሚው በኩል የፖለቲካ ስራ በኅብረተሰቡ ውስጥ፣ የወታደራዊ ዘመቻ እቅድ፣ የኢኮኖሚ ዘመቻ እቅድ፣ የኢንስፔክሽን፣ የወታደራዊ ፖለቲካ ስራ፣ የህዝብ ደህንነት ጥበቃ መመሪያዎች ያለው ሆኖ፤ በሁለት ዋና ዋና ጥቅል እቅዶች ላይ ያተኮረ ነው፡፡

1ኛ. ወታደራዊ ግብ፤ ተገንጣዮችን መደምሰስና በኤርትራ ግዛት ዘላቂ ሠላም ማስፈን፣ 2ኛ. ኢኮኖሚያዊ ግብ፤ በጦርነት የፈራረሱ የመሠረተ ልማት አውታሮችን መልሶ ማቋቋምና፤ አዳዲስ የልማት ተቋሞችን መገንባት የሚሉ ናቸው፡፡

የአገሪቱ አጠቃላይ በጀት ከሠራተኞች የወር ደሞዝ በስተቀር ሁሉም ወደዘመቻው ዞረ፡፡ በዚያ ወቅት አዲስ አበባ ጭልል ብላ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አስመራ ሆነች፡፡ የየሴክተሩ ሙያተኛ ወደ አሥመራ ተጓዘ፡፡



የዘመቻው የአንድ ቀን በጀት ብቻ 1.2 ሚሊዮን ብር ነበር፡፡ የዚያ ዘመን የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ቀውስ መነሻ ምንጩ ይህ ዘመቻ ሆነ፡፡

ወደፊት ለምናየው የኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት የሆነው በዋናነት ይህ ዘመቻ መሆኑን ለመገንዘብ ያህል፤ በብርጋዴር ጄኔራል ተስፋዬ ሐብተማርያም በ1997 ዓ.ም "የጦር ሜዳ ውሎ" በሚል ርዕስ ከተፃፈው መጽሐፍ ውስጥ ለዘመቻው ተብሎ የተከናወነውን ዝግጅት የሚገልፁ ጥቂት ዝርዝሮችን እንይ፡፡

የሰው ኃይል፤ መደበኛ ሠራዊት 120,000፣ የኤርትራ ህዝባዊ ሠራዊት 21,000 ድምር 141,000፣ የአንድ ዓመት ቀለብ ግምቱ ብር 61,874,000 ተመድቦ 404,488 ኩንታል ልዩ ልዩ የምግብ አይነቶች ለጦሩ ታድሏል፡፡

13,309,374 ብር የፊጀ አልባሳት ታድሏል፡፡

ለአንድ ዓመት የነዳጅ ፍጆታ 19,434,982 ብር፣

ለጥርጊያ መንገድ ስራ 613,279 ተመድቦ መንገዱ በፍጥነት ተሰርቷል፡፡

500 ከባድ ተሽከርካሪዎች ተመድበው 100,000 ሠራዊት እና 153,900 ቶን ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች በአንድ ዓመት ከአዲስ አበባ ወደ ኤርትራ ተጓዘዋል፡፡የዚህ ወጪም በገንዘብ ሲተመን 36,678,159 ብር ይሆናል፡፡

መሣሪያ፤ 122 ሚሊ ሜትር እና 130 ሚሊ ሜትር መድፍ -621፣
ቢ ኤም 21 - 37
82 ሚሊ ሜትር ሞርታር- 961
ልዩ ካሊበር ያላቸው መትረየሶች - 5,432
ኤ.ኬ. ኤም 43 ጠመንጃ (ክላሽ) - 90,000
ቲ.55 ታንክ - 159
ብረት ለበሶች - 153
ከባድና ቀላል ተሽከርካሪዎች - 3,000 ሲሆን፤
የ130 ሚሊ ሜትር መድፍ ጥይት - 12,089
የ122 ሚሊ ሜትር መድፍ ጥይት - 43,059
የቢ ኤም 21 ጥይት - 20,729

የኤ ኬ ኤም 47 ጠብመንጃ ጥይት 5 መደባዊ ጭነት፣ ማለትም በድምሩ 54,000,000 ነበር፡፡

የከተማው ጦር ቀለብ፣ አልባሳት፣ ህክምና፣ ነዳጅ፣ ጥይት፣ ደሞዝ ... ወዘተ አገሪቱ ከምትችለው አቅም በላይ እየሆነ ቢሄድም አማራጭ አልነበረም፡፡ ለጦሩ ብቻም ሳይሆን በሽብር ተግባር ከአገርነት ተርታ ወጥታ እንቅስቃሴዋ የቆመው ኤርትራ ዳግም እስትንፋስ መዝራት ስለበረባት መልሶ ግንባታ የግድ ነበርና ለዚህም በጀት ተመድቧል፡፡

የጦር መሣሪያ በገፍ ተገዝቷል፡፡ ለአዲስ ምልምል ሠራዊት ... ወዘተ ... እያለ ቀጥሎ ለአጠቃላይ የቀይ ኮከብ ዘመቻ ብቻ ከ5 ቢሊዮን በላይ የሚገመት ብር ወጪ ተደርጓል፡፡ ይህም ከፊሉ ለልማት ከፊሉ ለጦርነት መሆኑ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የኢትዮጵያውያን ዓይንና ጆሮ ብቻ ሳይሆን ሁሉ ነገራቸው ኤርትራ ላይ ሆነ፡፡

በታቀደው መሠረትም በጦርነት የወደሙ ፋብሪካዎች፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ት/ቤቶች፣ የጤና ተቋሞች፣ መንገዶች፣ ባንክ፣ ውሃና መብራት ... የፈረሱት ተጠግነው ያልነበሩት ተሰርተው •እንቅስቃሴ ጀመሩ፡፡ ሠርቶ አደሩ፣ ላብ አደሩ ወደየስራ መስኩ እንዲመለስ ተደረገ፡፡ ተማሪው ትምህርቱን ቀጠለ፡፡ በሽተኛው ህክምና ማግኘት ጀመረ፡፡

አያሌ ገንዘብ የወጣበት ፌስቲባልና ባዛር በምፅዋ ሠሜናዊ ድንበር "ጉርጉሱም" በተባለ ሥፍራ ተዘጋጅቶ በጓድ ሊቀመንበሩ ተመርቆ ተከፈተ ... በጦርነት የደቀቀችው ከተማ ነብስ ዘራች...፡፡

ጥር 17 ቀን 1974 ዓ.ም ሊቀመንበር መንግስቱ "…. የኤርትራ ህዝብ ሆይ! ልብ ብለህ ስማኝ ... አባቶች፣ እናቶች፣ እህቶች፣ ወንድሞች ... ስል የለበጣ አይደለም፡፡ የፖለቲካ ወይም የዲፕሎማሲ ቋንቋ አይደለም ከሐቅ ነው! ከአንጀት ነው!... የጋራ ችግራችንን፣ የጋራ ስቃያችንን ልናስወግድ፤ ወይም መፍትሄ ልንፈልግ ተሰብስበን እንደሆነ በግልፅና በሐቅ እንነጋገር ..."

"…. ቀደምት አባቶቻችን ስልጣኔን ለዓለም አሻግረው የሰጡበት ድንበር፣ በጠላት ላለማስነጠቅ የከፈሉት መስዋዕትነት፣ ጠብቀው አቆይተው ያስረከቡንን አደራ፣ በጀግንነት የተዋደቁላትንም ምድር ..." እያሉ ተርከው የአሉላ አባ ነጋን ጀብዱ እያስታወሱ ወደ አብዮቱ ዘመን መጥተው የቀይ ኮከብ ዘመቻን ዓላማና ግብ፤ እንዲሁም ቀጣይ ሂደቱን የሚመለከት ሰፊ ገለፃ አድርገው የዘመቻውን ጉባዔ ከፈቱ፡፡ ሊቀመንበሩን ተከትለውም የኢትዮጵያን ህዝብ የሚወክሉ የተባሉ ታላላቅ ሰዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ ባለስልጣናት ... ተመሣሣይ ልብ የሚነካ ንግግር አደረጉ፡፡ የኤርትራ ህዝብም የመኖር ተስፋ ጭላንጭል በማየቱ ተደሰተ፡፡

ጉባዔው በዚህ ሁኔታ ተከፍቶ ሲሰነብትም አጠቃላይ አፈፃፀሙ በሁሉም ገጽታው ታሪካዊ እንዲሆንና የታሪክ አሻራም ትቶ እንዲያልፍ፤ ታሪኩ ለትውልድ ተከትቦ ይቆይና ይተላለፍም ዘንድ ልዩ ዝግጅቱ ተጠናቆ ጋዜጠኞች፣ የኪነጥበብ ሰዎች፣ ደራሲያን፣ የታሪክ ምሁሮች፣ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትና የአገር ሽማግሌዎች ታድመው ጉባኤውን አድምቀዋል፡፡ አንጋፋው ደራሲና ጋዜጠኛ፣ በዓሉ ግርማ አንዱ ነበር፡፡ ያያቸውን ሚስጥሮች ሁሉ በኦሮማይና በቀይ ኮከብ ዘመቻ መጽሐፉ ተርኮታል፡፡ በዓሉ ግርማ በወቅቱ አጠቃላይ ሁኔታውን አይቶ ዘገባውን እንዲያቀርብ በመንግስት ታዞ ነበር የሄደው፡፡ ይህ ታላቅ ብዕረኛ



ያያትን ሁሉ ሲፅፍ በሳንሱር እንደሚወድቅ ቢረዳም እውነታውን ከመፃፍ ወደ ኋላ አላለም፡፡ በመጨረሻ ለፕሮፓጋንዳ ይረዳል ተብሎ የታሰበውን ዘገባ ሲያቀርብ ጽሁፉን ሳንሱር የሚያደርጉ የበላይ አለቆቹ ተቀብለው "እገሌ ይየው" እገሌ ይየው እየተባባሉ ሲዘባቡና ከተለመደው መንግስታዊ አዘጋገብ የተለዬ አይሆንም ብለው በመዘናጋታቸው ጭምር ትኩረት ስላልሰጡት በደንብ ሳይፈተሽ ሂዶ ሂዶ ለህትመት በቃ፡፡ ወይም ባልታሰበ መንገድ ታትሞ ተሰራጨ፡፡ ይህ የፀሐፊው ጥፋት አይደለም፡፡ የፃፈውን ለበላዮቹ ገምጋሚዎች ሰጥቷል፡፡ ገምግሞ መጣልም ሆነ ለህትመት እንዲበቃ መፍቀድ ያለባቸው እነሱ ነበሩ፡፡ ሳይሆን ቀርቶ አምልጦ ታተመ፡፡ "ኦሮማይ" ማለት አበቃለት ማለት ነው፡፡ ደራሲው ባለስልጣናቱን እየጠቀሰ ያየውን ሁሉ አጋለጠ፡፡ ገመናቸውን ያዩ ደነገጡ፡፡ በተለይ ደህንነቱን አፍረጥርጦታል፡፡ እናም ገደሉት....፡፡

ሁሉም ለዘላቂ ውጤት ጓጉቷል፡፡ በተቃራኒውም ዘመቻውን ለማክሸፍ የሚያስችል መረጃ ለጠላት አሳልፎ ለመስጠት ቀብድ የተቀበሉ ጉቦኛ የኢትዮጵያ ልጆች (የጦር አዛዦች) አብረው ነበሩ፡፡ የሻዕቢያ ደጋፊ የሆኑ የውጪ ኃይሎች "ኢትዮጵያ በሻዕቢያ ላይ የመርዝ ጋዝ ልትጠቀም ስለሆነ የመርዝ ጋዝ መከላከያ ጭንብል ለሻዕቢያ እንስጣለን" እያሉ የሐሰት ወሬ ይነዙ ጀመር፡፡

በጉባኤው ላይ "የአስመራ ማኑፌስቶ" ተብሎ የተሰየመው የአቋም መግለጫ የሁሉም ክፍላተ አገር ተወካዮችና በአካባቢው የሚኖሩ የኩናማ፣ የቤኒአመር፣ የአፋርና የሌሎች ብሔረሰብ ተወካዮች በተገኙበት ይፋ ሲደረግም ሁሉንም ያስደሰተ በመሆኑ ተቀባይነቱ አላጠያየቀም፡፡ በጥቅሉ በዘመቻው ጉባዔ ላይ የተነገሩት ንግግሮችና በተግባር የተጀመሩት ስራዎች መላውን የኤርትራ ህዝብ ያጓጓ ሲሆን፤ በተቃራኒው ሻዕቢያ በድንጋጤ የራደበት ክንውን ነበር፡፡

ከጉባኤው በኋላ በሊቀመንበር መንግስቱ ሰብሳቢነት የተነደፈው የወታደራዊ ዘመቻ እቅድ ላይ የክለሳ ውይይት ተካሄደ፡፡ የውይይቱ ዓላማ የአዛዦቹ ቅድመ ዝግጅት ምን እንደሚመስል የሚገልፅ ሪፖርት ማሰማት ነበር፡፡ በጠላት ላይ ጥቃት እንዲሰነዝሩ፣ ደጀን ሆነው እንዲጠብቁና ቁልፍ ቦታዎችን ይዘው እንዲቆዩ ግዳጅ የተሰጣቸው ዕዞችና ክፍለጦሮች ዝግጅታቸውን አጠናቀው በተጠንቀቅ ላይ መሆናቸውን ገለፁ፡፡ ቀድሞ በግብረ ኃይል ተዋቅሮ የነበረው ወደ ዕዝ ተለውጦ ነበርና፤ ውቃው ዕዝ፣ ናደው ዕዝ፣ መብረቅ ዕዝ፣ መከት ዕዝ፣ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ዕዝ በውስጡ በርካታና የተለያዩ ክፍለጦሮችን ያካተተ ሆኖ የተዋቀረ ነው፡፡

በዚህ መሰረት 1. በብርጋዴል ጄኔራል አበራ አበበ የሚታዘዘው ውቃው ዕዝ በአልጌና ግንባር ከቀይ ባህር በኩል በናቅፋ ጀርባ

እንዲያጠቃ፣ 2. ብብርጋዴል ጄኔራል ውበቱ ፀጋዬ የሚታዘዘው ናደው ዕዝ ከከረን ናቅፋ በር በከርከበት ግንባር ከናቅፋ ደቡባዊ ምስራቅ በኩል እንዲያጠቃ፣ 3. በብርጋዴል ጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ የሚታዘዘው መብረቅ ዕዝ ከቃሮራ ናቅፋ በር ግንባር ማለትም ከናቅፋ ሰሜናዊ ምዕራብ በኩል እንዲያጠቃና የሻዕቢያን መውጫ እንዲዘጋ፣ 4. በብርጋዴል ጄኔራል ከበደ ጋሼ የሚታዘዘው መከት ዕዝ የአስመራን ዙሪያ እንዲይጥር፣ 5. የሰሜን ዕዝ ልዩ ልዩ ክፍል የአስመራ ከተማን የውስጥ ጥበቃ እንዲያከናውን የሚል የዘመቻ ትዕዛዝ ተቀብለው ተዘጋጅተዋል፡፡ ከአንድ እስከ ሦስት ያሉት የዘመቻ እቅዶች ግባቸው የናቅፋ ከተማ ናት፡፡

አዛዦቹ ሪፖርታቸውን ሲያሰሙ "ጓድ ሊቀመንበር ዘመቻው ሙሉ በሙሉ ይሳካል፤ ሁሉንም ነገር ለእኛ ይተውት፤ አያስቡ" የሚሉት ቢበረክቱም፤ ጄኔራል አበራ አበበ ግን በተለይ በመብረቅ ዕዝ ስር ያለውን 21ኛ ተራራ ክፍለ ጦር በሚመለከት፤ "ከተቋቋመ አንድ ዓመት ያልሞላው፣ ምንም የውጊያ ልምድ የሌለው፣ ከኦጋዴን ኤርትራ ከገባ ወር ያልሆነው፣ ከኤርትራ መሬትና ከሻዕቢያ የውጊያ ስልት ጋር ትውውቅ ያላደረገ አዲስ ጦር ነው፡፡ ተራራ ክፍለ ጦር ስለተባለ ብቻ ተዓምር ሊሰራ አይችልም፡፡ ተጨማሪ የልምምድ ጊዜ ተሰጥቶት መለማመድ አለበት፡፡ አልጌና ግንባር ያለው ጦርም ቢሆን ለኃይል ማሟያ የተሰጡን አዳዲስ ጦር ስላሉን ተጨማሪ የልምምድ ጊዜ ተሰጥቶን ከታንከኛና ከመድፈኛ ጋር የኅብረት ውጊያ መለማመድ አለብን፡፡ የጦሩ መንፈስ ዝግጁነት በቂ ስላልሆነ ውጊያ ለመጀመር ባንቸኩል ጥሩ ነው" የሚል ሀሳብ አቀረቡ፡፡ መንግስቱ የጄኔራል አበራን ሀሳብ "አልቀበልም" ብለው ዘመቻው በቀጥታ እንዲጀመር አዘዙ፡፡ የካቲት 8 ቀን 1974 ዓ.ም ሊነጋጋ ሲል በሁሉም ግንባር ወደ ናቅፋ የመጠጋት እንቅስቃሴ ተጀመረ፡፡ የናቅፋ ተራሮች በቢ.ኤም.ሮኬት፣ በመድፍ፣ በሞርታር፣ ከሰማይ በሄሊኮፕተርና በጄት በሚወነጩፉ ከባባድ ተኩሶች ተንቀጠቀጠች፡፡ አካባቢው እሳት ለበሰ፡፡

ሻዕቢያ ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሞ ተከላከለ፤ ግን አልቻለምና ናቅፋን ለቆ ሊወጣ ዝግጅት ጀመረ፡፡ ሆኖም ሁሉም መንገድ ታጠረበት፡፡ እዚያው በተከበበበት ሆኖ ማለቅ የመጨረሻው ምርጫ ሆኖበት በአለታማው ተራራ ተለጥፎ መጨፍጨፍ ዕጣው ሆነ፡፡

በሰሜን ምዕራብ በኩል የተንቀሳቀሰው መብረቅ ዕዝ ለወሣኝ ድል ተስፋ የተጣለበት ሲሆን፤ እንዲያጠቃ የተሰጠው ቀጠና ለእግረኛና ለሜካናይዝድ ጦር ውጊያ አመቺ በመሆኑ ግራ ቀኝ ያሉ ተራሮችን አስለቅቆ ከተቆጣጠረና በጠላት ላይ ተፅዕኖ ካደረሰ በኋላ ቀጣዩን ግዳጅ እንዲወጣ ለተመደበው የእግረኛና የሜካናይዝድ ጦር መክፈት ነበረበት፡፡



ይህ ከሆነ ብቻ ነበር ሙሉ ድል ሊገኝ የሚችለው፡፡ ለዚህም ተብሎ እዙ አስፈላጊው የሰው ኃይልና ትጥቅ በበቂ ሁኔታ ነበረው፡፡ ሆኖም ዛሬም ድረስ ባልታወቀ ምክንያት ዕዙ በተሰጠው ትክክለኛ ሰዓት መንቀሳቀስ ባለመቻሉ ጠላት ከሩቅ ያሉትን የሰው ኃይሎች አሰባስቦ እንዲጠናከር ጊዜ ሰጠው፡፡ በዚህች በተፈጠረች የጊዜ ክፍተት ሻዕቢያን ለማገዝ ከሩቅ ቦታ ተነስቶ ተጉዞ የመጣው አንድ ሙሉ የወያኔ ብርጌድ ደረሰለት፡፡የዚህ የወያኔ በርጌድ መሪ አርከበ ዕቁባይ እንደነበሩ በርካቶች ፅፈዋል፡፡በዚህም ሻዕቢያ ነብስ ዘራ፡፡

በመብረቅ ዕዝ ስር ያለውና ግንባር ቀደም የማጥቃት እርምጃ እንዲወስድ ግዳጅ የተሰጠው 21ኛው ተራራ ክፍለ ጦር እንኳን ተራሮችን አስለቅቆ ሊይዝ ቀርቶ፤ ሰብሮ ሊወጣ ባልቻለው የጠላት ቀለበት ውስጥ ገብቶ ተጨፈጨፈ፡፡ ሻዕቢያና ወያኔ በምርኮ ተንበሸበሹ፡፡ ጥቂቶች ብቻ አፈግፍገው ማምለጥ ቻሉ፡፡ ይህ የጦር ክፍል ለምን በተሰጠው ሰዓት እንዳልተንቀሳቀሰ የተለያዩ አስተያየቶች ዛሬም ድረስ ቢነሱም የብዙሃኑ የቀድሞ አዛዦች መንግስቱን ጨምሮ "ሆን ተብሎ የተደረገ ነው" የሚል ነው፡፡ ተራ ወታደሮችም ከዚያ ግንባር ተርፈው የመጡና ዛሬ ድረስ በህይወት ያሉት "መንቀሳቀስ በነበረብን ሰዓት ለመነሳት ዝግጅት እንደጀመርን ሆን ተብሎ አንዳንድ ዝግጅቶች፣ ልምምዶች እንድናደርግ ተደረገ" የሚሉ ናቸው፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ 4 ነገሮች ይጠቀሳሉ፡፡ 1. መንግስቱ ለድል ቸኩለው የተሰጠውን አስተያየት ባለመቀበላቸው፣ 2. በመንግስቱ ላይ ቂም የነበረባቸው አዝማቾች በመኖራቸው፣ 3. መብረቅ ዕዝ ሰዓት አለማክበሩ፣ 4. የወያኔ ጦር ለሻዕቢያ ገስግሶ መድረሱ የሚሉ ናቸው፡፡ ብቻ እንደማይሆን ሆነ፡፡

ከዚህ በኋላ ነገሩ ሁሉ ተበላሽቷልና ከአልጌና በኩል የተነሳው ውቃው ዕዝ በከፍተኛ መስዋዕትነት ከናቅፋ እስከ ሱዳን ጠረፍ የሚደርሰውን ካታር የተባለ ሰንሰለታማ ተራራ ጥግ ደርሶ ለመቆም ተገደደ፡፡ ከከርከበት በኩል እንዲያጠቃ የታዘዘው ናደው ዕዝ በውጤታማ ውጊያ ተጉዞ የናቅፋ ከተማን ለመያዝ 8 ኪሎ ሜትር እንደቀረው መግፋት ተስኖት ቆመ፡፡ያ ሁሉ የአገር ሐብት፣ ያ ሁሉ ጥሪት፣ ያ ሁሉ ወጣት ዜጋ ወደ ትቢያነት ተለወጠ፡፡የቀይ ኮከብ ዘመቻ ትርፉ ኪሳራ ሆነ፡፡ "ኦሮማይ" እንደማለት፡፡ ደራሲው ከውጊያው በፊት በብዕሩ ያሰፈረው ጽሁፍ በጦር ሜዳ ላይ ሲተገበር ታዬ፡፡

በወቅቱ ድልን የጠበቀ ዜጋ ሁሉ አንገቱን ደፋ፤ "እንዴት ሊሆን ቻለ?" ብሎ ያልጠየቀ ዜጋ የለም፡፡ ለውድቀት ምክንያት የሆነው ክስተት እንዲጣራና በዘመቻ ጽ/ቤቱ መምሪያ ተጠንቶ የውሣኔ ሀሳብ እንዲቀርብ ጓድ ሊቀመንበር አዘዙ፡፡ አጣሪ ቡድኑ ለውድቀት ምክንያት ያላቸውን ዘገባዎች አቀረበ፡፡ ዘገባውን ተመርኩዞ የተቋቋመው የጦር ፍርድ ቤት

ባሳለፈው ውሣኔ መሰረትም የመብረቅ ዕዝ አዛዥ ብርጋዴል ጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ላይ የእስር ቅጣት፣ የ21ኛው ተራራ ክፍለ ጦር አዛዥ ኮሎኔል ውብሸት ማሞ የሞት ቅጣት፣ የክፍለ ጦሩ 47ኛው ብርጌድ አዛዥ ሌተናል ኮሎኔል ስለሺ አስፋው ማዕረጋቸው ተገፎ እንዲታሰሩ ሲል ብይን ሰጠ፡፡ ኮሎኔል ውብሸትን በሠራዊቱ ፊት ወስደው ረሸኗቸው፡፡ በጄኔራል ቁምላቸው ላይ መንግስቱ ያሳዩት ርህራሄ ብዙዎችን አስገረመ፡፡

በዚህ ሽንፈት ሊቀመንበሩ ምን ያህል እንደተበሳጩ ማሰብ አይከብድም፡፡ ባየነው መልኩ ቀይ ኮከብ በጥቁር ደመና ተዳፍኖ እንዳለ ዕዞች ይዞታቸውን አጠናክረው ባሉበት ሆነው እንዲደራጁ ተደረገና በተከታታይ ቀይ ኮከብ ሁለት፣ ሦስት… አራት… እየተባለ በተለያዩ የዘመቻ ስያሜዎች የሻዕቢያን ጉዳይ ዳር ለማድረስ በእጅጉ ተሞከረ፡፡ በከባድ ትንቅንቅ አንዴ ሲያስለቅቁ፣ መልሰው ሲለቁ፣ ሲያጠቁ፣ ሲከላከሉ… ቆዩ፤ አልተቻለም፡፡ ለምን? የናቅፋ ተራሮች ለሻዕቢያ ምትክ የሌለው የተፈጥሮ ደጀን ስለሆኗቸው፡፡ እናም ከተጠቀሰው ቢሊዮን ገንዘብ ውስጥ ግማሹ አመድ ቢሆንም ከፊሉ ግን ለኤርትራ ህዝብ ልማት በመዋሉ እንደኪሳራ አይቆጠርም፡፡

የሰሜኑ ጦርነት ሲባል ከሻዕቢያ ጋር ብቻ እንዳልነበር ይታወቃል፡፡ ከሻዕቢያ በኋላ የተነሳው ህወሓት ሌላው የደርግ መንግስት ተቃዋሚ ሆኖ ነፍጥ ያነሳው ገና በማለዳ ነበር፡፡

በምዕራብ ትግራይ ሽሬ አውራጃ፣ ደደቢት በምትባል በረሃማ ቀበሌ የካቲት 11 ቀን 1967 ዓ.ም ጥቂት የዩንቨርስቲ ተማሪዎችና የአካባቢው መሪዎች "ሕወሓት" "ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ"ን መሠረቱ፡፡ ራሳቸውንም ዳግማዊ ወያኔ ሲሉ ሰየሙ፡፡ ህወሓት የሚለውን መጠሪያ ይፋ ከማድረጋቸው በፊትም በተለያዩ ምህፃረ ቃላቶች ይጠሩና ይታወቁ ነበር፡፡

በጃንሆይ ዘመን በተለያዩ የኢትዮጵያ ግዛቶች ላይ የገበሬዎች አመፅ ተቀጣጥሎ እንደነበር አይተናል፡፡ በወቅቱም የገበሬዎችን አመፅ በቀላሉ ማርገብ ተችሏል፡፡ ከእነዚህ ውስጥም የትግሬ ጠቅላይ ግዛት አንዱ ነበር፡፡

በአፄ ዮሐንስ 4ኛ የስልጣን ዘመን የኢትዮጵያ ማዕከል ሆና የቆየችው ትግራይና አካባቢዋ በ1882 ዓ.ም ንጉሠነገስቱ በጦርነት ላይ ከተሰውበት ጊዜ ጀምሮ፤ የትግራይ መሣፍንትና መኳንንት የሆኑት ሁሉ የቀያሞውን አይነት ክብርና ተሰሚነት ማግኘት አልቻሉም፡፡ ዳር አገር በመሆናቸውም የፖለቲካ ተሳትፏቸውና ተጠቃሚነታቸው የቀዘቀዘ ሆኖ ነበር፡፡ ያም ቢሆን ለኩርፊያና ለሽፍትነት የሚጋብዝ ባለመሆኑ ለረጅም ጊዜ በግዛቱ ላይ ሠላም ሰፍኖ ቆይቷል፡፡



ከኢጣሊያ ዳግም ወረራ በፊት ግን በመንግስትና በራያና አዘቦ ህዝብ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት፣ እሱንም ተከትሎ የደረሰው ደም መቃባት ለአካባቢው ሠላም መደፍረስ የመጀመሪያው ሆኗል፡፡ ከንግስት ዘውዲቱ የግዛት ዘመን ጀምሮ ማዕከላዊ መንግስቱን ሲፈታተንና በየጊዜውም ከሚላክበት ጦር ጋር በሽፍትነት ይፋለም የነበረው የራያና አዘቦ ህዝብ ይህን ተግባሩን በቀጠለበት ሁኔታ የኢጣሊያ ወረራ ተከሰተ፡፡ በዚህም ማዕከላዊ መንግስቱን ለመበቀል ምቹ ሁኔታ ተፈጠረላቸው፡፡ከማይጨው ጦርነት ሸሽቶ ይመጣ በነበረው የኢትዮጵያ ጦር ላይ ያደረሱት ግፍም የሚረሳ አይደለም፡፡
ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ሙሉ ለሙሉ ለቃ ከወጣች በኋላም የጃንሆይ መንግስት እስኪደላደል ድረስ በነበረው የጊዜ ክፍተትና ጣሊያኖች ትተውት የሄዱትን መሣሪያ በገፍ ማግኘት ቀላል ስለነበር በነፃነት ማግስት የመጀመሪያውን የተደራጀ አመፅ ማካሄድ ቻሉ፡፡ ይህም በነፃነት ማግስት በትግሬ ጠቅላይ ግዛት የተቀሰቀሰው የመጀመሪያው የ"ወያኔ" አመፅ ነው፡፡

የራያና አዘቦ ህዝብ አመፁን የለኮሰውም እንደመጀመሪያ ተግባሩ በአፋሮች ላይ ከፍተኛ ዝርፊያ በመፈፀም ሲሆን፤ በዚህም የማዕከላዊ መንግስቱን የበቀል እርምጃ በራሱ ላይ አስከተለ፡፡ የመንግስት ማጥቃትና የአማፅያኑ የመከላከል ተግባር እየተጋጋለ ሄዶ በመጨረሻ አማፅያኑ ከመከላከል ወደማጥቃት አመሩ፡፡ ይህ ሁኔታ ከተራ የሽፍትነት አመፅ ወደ ፖለቲካዊ አመፅ ተሸጋገረ፡፡

አማፅያኑ የመጀመሪያ ድላቸውን ያገኙት ግንቦት 14 ቀን 1935 ዓ.ም በተንቤን አውራጃ "አዲ አቡን" በተባለ ስፍራ ነው፡፡ ከዚያም በተከታታይ መቀሌ አጠገብ የሚገኙትን ቅዊሓንና እንዳ እየሱስን በቁጥጥር ስር አዋሉ፡፡ በመጨረሻም የጠቅላይ ግዛቱን ዋና ከተማ መቀሌን ሙሉ ለሙሉ ያዟት፡፡

ለዚህ ድል የረዳቸው ዋና ምክንያት የህዝቡን ቅሬታ ዘውጋዊ ወይም ጎሳዊ ርዕዮት በመስጠት ማስተባበር የቻለው የብላታ ኀይለማርያም ረዳ አመራር ነው፡፡

የአመፁ ስፋት፣ ጥልቀትና እድገት መንግስትን ክፉኛ ስላስደነገጠው በአርበኝነቱ ዘመን በፈፀሙት ጀብድ ስመጥርነትን ያተረፉትን ራስ አበበ አረጋይን የጦር አዝማች አድርጎ ላከ፡፡ ከሁኔታው አስጊነት አንፃርም በወቅቱ በኢትዮጵያ ከነበሩ የእንግሊዝ ጦር ባለስልጣኖችን እርዳታ መጠየቅ አስፈልጎ ነበር፡፡ በእንግሊዝ ይሁንታም የጦር አውሮፕላኖች ማግኘት ተችሎ ቀዳማዊ ወያኔን በምድርና በአየር ውጊያ ማሸነፍ ተቻለ፡፡ መስከረም 25 ቀን 1936 ዓ.ም ሙሉ ለሙሉ ድል የሆነው የአማፅያኑ ጦር ተበታተነ፡፡

ቀዳማዊ ወያኔ ትግሉን የጀመረው ምስራቃዊ ትግራይን መነሻ በማድረግ ነበር፡፡ ዳግማዊ ወያኔ ደግሞ ከመረብ ወንዝ በስተደቡብ በሚገኘው በምዕራብ ትግራይ መነሻውን አድርጎ ከ31 ዓመታት በኋላ የአርነት ንቅናቄውን እንደዋዛ ጀምሮ እየተጠናከረ ቀጥሏል፡፡

የመጀመሪያው ወያኔ ርዕዮቱን ዘውጋዊ አድርጎ የተነሳ ሲሆን፤ ሁለተኛው ወያኔ ደግሞ ከኢትዮጵያ የተማሪዎች ንቅናቄ በወረሰውና "የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል" በሚለው መርህ የሚመራ ነበር፡፡ቀዳማዊ ወያኔናዳግማዊ ወያኔ የሚመሳሰሉበት ሁኔታ ኖሮ ሳይሆን፤ህወሓት ለራሱ ፕሮፖጋንዳ ታሪካዊ መሰረት ለመስጠት የፈጠረው ነው፡፡

አካባቢው ዳር አገር በመሆኑ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ለማድረግ ምቹ ቢሆንም፤ በአካባቢው ኅብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት የግድ ነበርና፤ ለዚህ የሚረዳ በቂ ምክንያት በጠቅላይ ግዛቱ ውስጥ መኖሩ ለዳግማዊ ወያኔ የበለጠ ምቹ ሁኔታ ፈጠረለት፡፡ ይህም ከ1950ዎቹ አጋማሽ አመታት ጀምሮ በግዛቱ ውስጥ የተከሰተው ተደጋጋሚ ድርቅና የኢኮኖሚ ችግር ነው፡፡ ከዚህም በላይ የቀድሞ ባለባት ሹማምንት የፖለቲካ ማዕከላዊነት በማጣታቸው ምክንያት ሲሰማቸው የቆየው ቁጭት ስለነበር፤ በጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦች የመሰረቱትን የነፃነት ንቅናቄ በግዛቱ የሚኖረው ሁሉም ወገን የየራሱን መነሻ ምክንያት መሰረት በማድረግ ለመደገፍና ለማበረታታት ዝግጁ ነበር፡፡ ለዚህም ነው በተመሠረተ በአጭር ጊዜ ውስጥ በቂ የሚባል የሰው ኃይል፣ የስንቅና የትጥቅ አቅርቦቱ ሳይቸግረው ባለበት ፈጥኖ ተደራጅቶ የደርግ መንግስትን መፈታተን የቻለው፡፡

ህወሓት ይዞት የተነሳውን "የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል" የሚለውን የሌኒን መርህ ግን ለትግራይ ህዝብ ከማስረዳት ይልቅ ከእሱ ቀድሞ የመገንጠል ዓላማ ይዞ ለተነሳው ለሻዕቢያ መግለፅ ይቀለው ነበር፡፡ ያደረገውም ያንን ነው፡፡ሆኖም ሻዕቢያ የትግራይን የመገንጠል ትግል የኔን ትግል ያዳክምብኛል በሚል የወያኔን የመገንጠል ዓላማ ማኑፌስቶ እንዲያሰወግድ አስገድዶታል፡፡

ለወያኔ የአካባቢውን ህዝብ ድጋፍ ለማግኘት የኢኮኖሚ ችግር ሰለባ መሆኑን መግለፅ ብቻውን በቂ ስለነበር የርዕዮት ትንተና ውስጥ መግባት አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ለሻዕቢያ ግን ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ስለዚህ የ"ገንጣይ" እና "አስገንጣይ" ጥምረት መስርቶ መደጋገፉ ለሁለቱ ቡድኖች ወሣኝ በመሆኑ፤ ከልዩነታቸው ይልቅ አንድነታቸው ጠንክሮ በመቀጠሉ በመጨረሻ የየግል ግቦቻቸውን ዳር ማድረስ ችለዋል፡፡



ደርግ ጊዜያዊ መንግስት በሆነ ማግስት የወሰዳቸው እርምጃዎች፤በተለይም የ60ዎቹ ግድያና ሌሎች በፍርደ ገምድልነት የተደረጉ ነገሮች መደራረባቸውም ለሸመቁ ተቃዋሚዎች ድጋፍና ትኩረት አስገኝቶላቸዋል፡፡የአገር ውስጥ ብቻም ሳይሆን የውጭ አገራት ድጋፍን በተከታታይ አመታት ሊያገኙ የቻሉት የደርግ አምባገነንነት በየጊዜው እየጎላ በመሄዱ ነው፡፡

ደርግ ለአብዮቱ ሲል የሚወስዳቸው ጥንቃቄ አልባ እርምጃዎች በአብዮቱ ደጋፊዎች ዘንድ ተወዳጅ ያደርገኛል ብሎ ሲያስብ ራሱን ለጠላት ፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ አድርጎ ማቅረቡን ለደቂቃ አስቦት አያውቅም፡፡

ህወሓት "ወያኔ" የሚለውን ወኔ ቀስቃሽ ስያሜ ይዞ የትጥቅ ትግል ሲጀምር ልክ እንደሻዕቢያ የመጀመሪያ ስራው ያደረገው በግዛቱ ውስጥ የበላይነቱን ማረጋገጥ ነበር፡፡ ስለዚህም በቅድሚያ ከሦስት ተቀናቃኝ ድረጅቶች ጋር መፋለም ነበረበት፡፡ በመጀመሪያ ከእሱ ቀድሞ የተደራጀውን "የትግራይ አርነት ግንባር"ን ማስወገድ ቻለ፡፡ ይህን ግንባር ለማስወገድ ብዙ ድካም አልነበረውም፡፡ ሁለተኛውን "የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት" በእንግሊዝኛ ምህፃረ ቃሉ "ኢዲዩ"ን ግን ብርቱ የሆነ ውጊያና ከፍተኛ የህይወት መስዋዕትነት በመክፈል ነው መደምሰስ የቻለው፡፡

ኢዲዩን ከምዕራብ ትግራይ ጠራርጎ ካስወጣ በኋላ ቀጣዩን ፍልሚያ ያደረገው በሰሜን ምስራቅ ትግራይ አሲምባ በምትባለው ተራራማ ቦታ ከመሸገው ከኢህአፓ ሠራዊት ጋር ነበር፡፡ ኢህአፓ በከተማው ትግል ስኬታማ መሆን ሳይችል ሲቀር ወደ ገጠር አምርቶ አሲምባ ላይ ቢመሸግም ለአካባቢው እንግዳ ነው፡፡ ኢህአፓ አሲምባን የመረጠው በሁለት ምክንያቶች ሲሆን፤ አንዱ ከመንግስት ጥቃት ለመሸሽ፣ ሌላው በትግራይ ያለው ሸማቂ ቡድን የኅብረብሔራዊነት ዓላማ ካለው አብሮ ለመቀናጀትና ለመታገል ነው፡፡

ህወንትም ኢህአፓም ግራ ዘመም ከሆነው ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ አብራክ የወጡ ድርጅቶች ይሁኑ እንጂ፤ ዓላማና ግባቸው እጅግ የተራራቀ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ገሃድ በሆነው ትግላቸው ውስጥ ስውር የሆነ የየግል ዓላማ ነበራቸው፡፡

የትግሉን ይዘት በሚመለከት ኢህአፓ "በኅብረብሔራዊ ድርጅት የሚመራ የመደብ ትግል"ን በቀዳሚነትና በአፅንኦት ሲያስቀምጥ፤ ሕውሓት ግን "ትግሉ ሊሰምር የሚችለው የተለያዩ ጭቁን ብሔር ብሔረሰቦች በራሳቸው ድርጅት አማካኝነት ትግላቸውን ጀምረው ከዚያ በኋላ የኅብረት ግንባር ሲፈጥሩ ነው" የሚል አቋም ያዘ፡፡ ከዚህ ልዩነት በተጨማሪም ሕወሓት ሙሉ እምነቱን በገጠር የትጥቅ ትግል ላይ

ሲያሳርፍ፤ ኢህአፓ ደግሞ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረው በከተማ ነው ብሎ ስላሰበ በከተማ የትጥቅ ትግል ላይ እምነቱን አሳድሯል፡፡በተጨማሪም ኢህአፓ እንደ ነጭ ማርክሲስትነቱ አርሶአደሩ አብዮታዊ ሀይል አይደለም ላብ አደሩ እንጅ ብሎ በማመኑ ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ ግን (የሻዕቢያን ከጀርባ ሆኖ በሰርጎ ገቦቹ አማካኝነት ኢህአፓን መጠቀሚያ ማድረጉን ሳንዘነጋ) ዋናው ልዩነታቸው በህወሓት ውስጥ የነበረው የመገንጠል መሻትና "በኢህአፓ ውስጥ የነበረው መገንጠልን ያለመሻት የፀባቸው መንስዔ ነው፡፡

በዚህ ልዩነት ሕወሓት የኢህአፓን አባላት ቢቻል በእሱ አቋም እንዲስማሙ አድርጎ ማሳመንና መቀላቀል፣ ካልተቻለ ያመኑለትን መርጦ ወስዶ የቀሩትን መደምሰስ፣ ካልሆነም ከአካባቢው ማባረር ነበረበት፡፡ ያደረገውም ይሄንኑ ነው፡፡

በዚህ መሠረት ገሚሱ የኢህአፓ አባላት ተደመሰሰ፡፡ጥቂቶቹ ተባባሪ ሆነው ተቀላቀሉ፡፡ የቀሩት ጓዛቸውን ጠቅልለው ወደ ጎንደርና ወደ ወሎ አፈገፈጉ፡፡ አንዳንዶቹም የከተማ ሽብራቸውን ቀጠሉ፤ሌሎችም ለደርግ እጃቸውን ሰጥተው ከደርግ ጋር መስራት ጀመሩ፡፡ደርግም ምልስ የኢህአፓ አባላትን እጁን ዘርግቶ ተቀበላቸው፤የድርጅታቸውን ሚስጥር አወጡ፤በደርግ ተይዘው የሚታሰሩ አባላትን መርማሪ ሆነው እስኪሰሩ ድረስ ለደርግ ታማኝ ሆነው ዘለቁ፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለም የየራሳቸውን ብሔር እንዲያደራጁ ወደየክልላቸው ቀድመው የተላኩ ምልምሎች የተገኙት በዚህ አጋጣሚ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡

በዚህ ዓይነት በትግራይ ግዛት ውስጥ ብቸኛው የትጥቅ ትግል አራማጅ ህወሃት ሆነ፡፡ እነዚህ ጅምር የነፃነት ንቅናቄዎችና የውስጥ ፍጭቶች ለሻዕቢያ ሠርግና ምላሹ ነበሩ፡፡ ኅብረብሔራዊነት፣ ብሔረተኝነት ወዘተ … ለሻዕቢያ ምኑም አይደሉም፡፡ ብቻ ኢትዮጵያ ውስጥ ሽብሩም፣ ተቃውሞውም፣ ፍጅቱም ይፋፋምለት እንጂ ሌላው ሁሉ ነገር አያገባውምም፣ አይገባውምም፡፡ የእሱ ስራ በኢትዮጵያውያን የግራ ኃይሎች ውስጥ የራሱን ዓላማ ማስፈፀም የሚችልበት፣ የመገንጠል ግቡን የሚያፋጥኑለትን ልዑካን ማሰማራት ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ምቹ ሆኖ ያገኘው ከሕወሓት ይልቅ ኢህአፓን ነበር፡፡

መጀመሪያ ላይ ደርግ ሕወሓትን ከመጤፍ አልቆጠረውም ነበር፡፡ ለድርጅቱ መፈጠር ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎችን ትኩረት በመንፈግ አንድ የሻዕቢያ ተቀፅላ ቡድን አድርጎ ነበር የወሰደው፡፡ ስለዚህም ደርግ ሙሉ ኃይሉን ያዘመተበት ሻዕቢያ ከተመታ ሕወሓትም አብሮ ይከስማል ብሎ ጥርጣሬ አልባ ግምት ውስጥ ገባ፡፡

ነገር ግን ሕውሓትና ሻዕቢያ አንድ አልነበሩም፡፡ አንድነታቸው ሰፊ፣ ልዩነታቸው ጠባብ የሆኑ የተነጣጠሉ ቡድኖች ናቸው፡፡ ይልቁንም



ሻዕቢያ መጀመሪያ ላይ ከሕወሓት ይልቅ ቀድሞ ወደጎለበተው ወደ ኢህአፓ ነበር ያተኮረውና በኅብረት ለማመፅ ሁኔታዎችን ያመቻቸው፡፡ ሆኖም ኢህአፓ ከትግራይ ተጠራርጎ ሲወጣ ፊቱን ወደ ሕወሓት አዞረ፡፡

ሕውሓት በመላ ትግራይ የበላይነቱን ካሰፈነ በኋላ የተመሠረተው ግንኙነትም የፍቅር ሳይሆን የጥቅም ብቻ ነበር፡፡ የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ አንድ ህዝቦችን ለመከፋፈል ሲል ተክሎት በሄደው መርዛማ ችግኝ ምክንያት በሁለቱ የመረብ ወንዝ ተዋሳኝ ወንድማማች ህዝቦች መካከል ከመቃቃርም አልፎ በጣም በጥቂቱ መናናቅም ይታይ ነበር፡፡ ሆኖም ከጃንሆይ ዘመን ጀምሮ የተፈጠረው ውህደት ተለያይተውና ተቃቅረው የነበሩ ህዝቦችን አንድ አድርጎ ወደ ቀድሞው ፍቅራቸው መልሷቸው ነበር፡፡ በዚህ መሠረት በሁለቱ ህዝቦች መካከል አንዳች ልዩነት አለመኖሩን ስንረዳ፤ የሁለቱ ህዝቦች ተቆርቋሪ ሆነው የትጥቅ ትግል በጀመሩ የስልጣን ተፋላሚዎች ዘንድ ግን የተካረሩም ባይሆኑ ልዩነቶች አልጠፉም፡፡

ሕወሓት "ብሔር ብሔረሰቦች" ሲል ሻዕቢያ ግን በኤርትራ ትግል ውስጥ ብሔር ብሔረሰብ የሚባል አጀንዳ ፈፅሞ የለም ባይ ነበር፡፡ ሕወሓት ሶቭየት ኅብረት ለደርግ በምታደርገው እገዛ ምክንያት ጠንካራ ፀረ ሶቭየት አቋም ሲወስድ፤ ሻዕቢያ ግን ፀረ ሶቭየት አቋም አልያዘም፡፡

የሕወሓት የጦር ስልት በደፈጣ ውጊያ ላይ ሲያተኩር፤ ሻዕቢያ ግን መደበኛ ውጊያን መርጧል፡፡ በዚህም ሕወሓት ሻዕቢያን ተቻኩሎ ወደ መደበኛ ጦርነት በመግባቱ ክፉኛ ይተቸው ነበር፡፡ "ሳንደራጅ አታስጨርሰን፤ ተረጋጋ" መሆኑ ነው፡፡

እነዚህን በመሳሰሉ የሀሳብና የዘዴ ልዩነቶች ሲተቻቹ ከቆዩ በኋላ፣ የደርግ የማጥቃት እርምጃ እየጠነከረ ሲሄድና በተለይም ከቀይ ኮከብ ዘመቻው ከ1974 ጀምሮ በነበሩት ተከታታይ አመታት፤ የነበራቸውን ጥቃቅን ልዩነቶች ሁሉ እርግፍ አድርገው ትተው በጋራ ርብርብ፣ በጋራ ጠላታቸው በደርግ መንግስት ላይ ተነሱ፡፡ ውድቀቱን ለማፋጠንም በቁርጠኝነት ተፋለሙ፡፡

እነሱን ለማጥፋት ደርግ የወሰዳቸው ተደጋጋሚ እርምጃዎች ከሸፉበት፡፡ ቢቸግረው ለኤርትራና ለትግራይ የራስ ገዝ አስተዳደር ስልጣን ሊሰጥ ሞከረ፡፡ ይህን ግን የኃይል ሚዛኑ ወደነሱ ማዘንበሉን የተረዱት ሁለቱ ቡድኖች ሊቀበሉት አልፈቀዱም፡፡

ሻዕቢያና ሕወሓት ሲመች በጥምረት ሳይመች በተናጠል ደርግን በፅኑ ሲፋለሙ እነሱ ተሳዳጅ ደርግ አሳዳጅ ሆኖ የዘለቀው ለጥቂት ዓመታት ነው፤ እያደር ግን ደርግ ተሳዳጅ እነሱ አሳዳጅ ሆነው ተገኙ፡፡

ግራ የተጋባው ደርግ አብዮታዊ ሠራዊቱን እንደገና በአዲስ መልክ አደራጅቶ በአራት ዕዞችና በውስጡም የተለያዩ ኮሮችን አቅፎ የሚይዝ

ከማድረጉም በላይ "የሦስት ማዕዘን ዕዝ" በሚል 1ኛ አዛዥ፣ 2ኛ የፖለቲካ ኃላፊ፣ 3ኛ የወታደራዊ ደፀንነት ኃላፊ የሚባሉ ባለሥልጣኖችን በጦሩ ላይ ሹሞ ዝብርቅርቁን አወጣው፡፡

የዕዙ ማዕከል ዋና አዛዡ ቢሆንም የፖለቲካና የወታደራዊ ደህንነት ኃላፊዎች በዋና አዛዡ ስራ ላይ በቀጥታ ጣልቃ መግባት ይችላሉ፡፡ በተለይ የፖለቲካ ኃላፊው በአዛዡ ላይ ጣልቃ መግባት ብቻ ሳይሆን ትዕዛዙንም መሻር ይችላል፡፡ ይህ ያልተለመደ አደረጃጀት ሙያና ችሎታው ያለውን አዛዥ ሙያው የሌላቸው ኃለፊዎች ሊገድቡት እንዲችሉ ከማድረጉም በላይ፤ የእኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ፉክክሩን ዋና ስራቸው አድርገው እንዲቀጥሉ በር ከፈተ፡፡ ሽንፈት ሲደርስም የሱ ችግር ነው፣ የእኔ አይደለም ተብሎ መጠቋቆም ሆነ፡፡ ሠራዊቱ ዋና አዛዡን ለይቶ ማወቅ ተሳነው፡፡

ይህ አይነቱ ከሶቭየት የተኮረጀ የቀዩ ጦር ስልት ዓላማው አፈንጋጭነት እንዳይፈጠርና በአንድ አዛዥ ክህደት ችግር እንዳይደርስ አጥብቆ ለመያዝ ነበር፡፡ ሆኖም በእኛ አገር ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ ቅድመ ዝግድቶች ይቀሩ ነበር፡፡ የታሰበው ሳይሆን ቀርቶ አደረጃጀቱ የጣት መቀሳሰሪያና የአጥፊና ጠፊ መድረክ ሆኖ ቁጭ አለ፡፡

ሻዕቢያን ከኤርትራ፣ ሕወሓትን ከትግራይ ለመደምሰስና ሙሉውን የኢትዮጵያ ድንበር ለማስከበር ይቻል ዘንድ ሠራዊቱ በሰው ኃይል ጠንክሮና በዕዝ ደረጃ ራሱን ችሎ እንዲደራጅ፣ ግዳጁን የመወጣት ብቃትም እንዲኖረው ታስቦ የተደራጀው አብዮታዊ ሠራዊት፤ 1. አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት በሜጀር ጀኔራል ደምሴ ቡልቶ አዛዥነት፣ የዕዝ ቀጠናው ምስራቅ ኢትዮጵያ ሆኖ የሰው ኃይሉ 30,498፣ 2. ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት በሜጀር ጀኔራል ረጋሳ ጅማ አዛዥነት የዕዝ ቀጠናው ኤርትራ ራስ ገዝ ሆኖ የሰው ኃይሉ 124,024፣ 3. ሦስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት በሜጀር ጀኔራል ሙላቱ ነጋሽ አዛዥነት የዕዝ ቀጠናው ትግራይ፣ ጎንደርና ወሎ ሆኖ የሰው ኃይሉ 107,407፣ 4. አራተኛው አብዮታዊ ሠራዊት በሜጀር ጀኔራል ጌታቸው ሽበሺ አዛዥነት የዕዝ ቀጠናው ምዕራብና መሀል ኢትዮጵያ ሆኖ የሰው ኃይሉ 20,700 ተደርጎ፣ በስራቸው ልዩ ልዩ ኮሮችና ክፍለ ጦሮች አቅፈው ተደራጁ፡፡

ሦስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት በጀኔራል ሙላቱ ነጋሽ ዋና አዛዥነት ከተቋቋመ በኋላ በትግራይ ላይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታወጀ፡፡ ሻምበል ለገሰ አስፋው የትግራይ ራስ ገዝ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አስተዳደር የበላይ አስተዳዳሪ ሆኖ ተሾመ፡፡ በአዋጁ አማካኝነት በቀጥታ የሠራዊቱ የበላይ አዛዥ ሆነ ማለት ነው፡፡

ለገሠ አስፋው ተሹሞ ሄዶ መቀሌ እንደደረሰ በፍጥነት ሦስተኛውን አብዮታዊ ሠራዊት "በቁልፍ ወታደራዊ ቦታዎች ላይ ጠላት



ሠፍሯል፣ ሠራዊታችን፣ በሚገባ ተደራጅቷል፣ ስለዚህ ከየአቅጣጫው ተወርውሮ ይምታው!" ሲል አዘዘ፡፡

ሕወሓትም በበኩሉ፤ "ጦሩ ሲወረወር ተሰወር" የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶ ስልታዊ ማፈገፈግ አደረገ፡፡ በዚህ አይነት የሚለቀቁ ቦታዎችን በተነጣይ ክፍል እያስጠበቁ ሲገሰግሱ የሠራዊቱ ኃይል እያነሰ ቢበታተንም ድል ያልሆነ ድል መሰል ተግባር ሆኖ ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ሽፋን ተሰጠው፡፡ ምርኮ ተብለው ጥቂት መሣሪያዎች በመገናኛ ብዙሃን ታዩ፡፡ ቀጣይነት ግን አልነበረውም፡፡ ይልቁንም በጀኔራሉና በሻምበሉ መካከል የነበረው የታዥነትና የአዛዥነት አለመጣጣም እየተካረረ ሄዶ በየጦር ግንባሩ የሚታየውን ችግር አስተውሎ የጋራ የመፍትሄ እርምጃ መውሰድ ተሳናቸው፡፡

ብዙም ሳይቆይ የቁርጡ ቀን ደረሰና በ1980 ዓ.ም ከህዳር 27 እስከ 30 ባሉት ሦስት ተከታታይ ቀናት ሻዕቢያ በሳህል አውራጃ ውስጥ በሚገኙ የናደው ዕዝ ክፍለ ጦሮች ላይ ጠንካራ በትሩን አሳረፈ፡፡ በ15ኛው ክፍለ ጦርና በ22ኛው ተራራ ክፍለ ጦር ላይ ያረፈው ምት ከቀይ ኮከብ ዘመቻ በኋላ የመጀመሪያው ከባድ ውጊያ ሆኖ "አፋቤት የተባለውን ቁልፍ ወታደሪዊ ቦታ ሻዕቢያ በቁጥጥሩ ስር አደረገው፡፡

በዚህ ወቅት የናደው ዕዝ አዛዥ ብርጋደር ጀኔራል ታሪኩ ዐይኔ ለአለቆቻቸው ሳያሳውቁ ሠራዊታቸውን ትተው አስመራ ከተማ ነበሩ፡፡

እኚህ ጀኔራል ወደ ሳህል ተመድበው ከመሄዳቸው በፊት መቀሌ አካባቢ ለሰፈረው ጦር አዛዥ ሆነው በ1970ዎቹ ይሰሩ ነበር፡፡ በዚያ ወቅት ወያኔ "ዘመቻ አግአዚ" (አግአዚ ኦፕሬሽን) ብሎ በሰየመው እስረኞችን የማስለቀቅ ድንገተኛ ወረራው ሲከሰት በወህኒ ቤቱ ዙሪያ የሚገኘው የጥበቃ ኃይል ከአቅም በላይ የሆነ ወረራ እንደመጣባቸው ገልፀው፤ እርዳታቸውን ሲጠይቁ ጀኔራሉ "የወህኒ ቤት ጠባቂ አይደለሁም" የሚል መልስ ሰጥተው በመቅረታቸው የወያኔ ኃይል ያለ ችግር ወህኒውን ጥሶ ገብቶ የራሱን ሰዎች ስም እየጠራ በ15 ደቂቃ ውስጥ ይዞ ሄዷል፡፡ (ነበር ቁጥር 2)

በተጨማሪም የሊቀመንበሩንም ሆነ የሌሎች አዛዦቻቸውን ትዕዛዝ "አላመንኩበትም" እያሉ ከመፈፀም ይቆጠቡ እንደነበርና በሁሉም ዘንድ ጥርስ ውስጥ የገቡ ጀኔራል መሆናቸው ይነገርላቸዋል፡፡ አሁን ደግሞ የአፋ ቤት ውድቀት የመጣው በጀኔራል ታሪኩ ዐይኔ ጥፋት ነው ተባለና ያለፍርድ ተረሸኑ፡፡ እንዲሁም ብ/ር/ጀ/ል ከበደ ጋሼ ድል ከሆኑ ሁለት ክፍለ ጦሮች ውስጥ አንዱን ይመሩ ስለነበር በጥፋተኝነት ሙሉ ማዕረጋቸው እንዲገፈፍ ተደረገ፡፡ እንዲህ ያለው ተግባር በጦሩ ፊት በተግባር መፈፀሙ ደግሞ የጦሩን ስሜት የሚጎዳና ሞራሉንም የሚነካ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

በአፋቤት ጦርነት 20 ሺህ የደርግ ሠራዊት በአንድ ጊዜ ያለቀ ሲሆን፤ ስፍር ቁጥር የሌለው የጦር መሣሪያ በሻዕቢያ እጅ ገባ፡፡ ይህ ቦታ ለሻዕቢያ መጀመሪያ ወደ ምፅዋ፣ እንዲሁም ወደ አስመራ መረማመጃ ሆነው፡፡ በጦርነቱ የወደፊት አቅጣጫ ላይም ለሻዕቢያ ድል መፋጠን ትልቁን ሚና ተጫውቷል፡፡ በርካታ መኮንኖች በመማረካቸውም ሚስጥሩን ሁሉ፣ የሠራዊቱን አሠፋፈር ሳይቀር በቀላሉ ለመረዳት ለሻዕቢያ ጠቅሞታል፡፡

ሻዕቢያ እስከ መጋቢት ወር ድረስ አፋቤትን የማፅዳትና ሙሉ ለሙሉ የግሉ ለማድረግ በወሰደው ተከታታይ የማጥቃት እርምጃ ከነሙሉ የጦር ግምጃ ቤቷ ተረከባት፡፡ ዘጠኝ የሶቭየት የጦር አማካሪዎችን ጨምሮ ማረከ፣ የናደው ዕዝ በተጠቀሰው ወር ተናደ፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ኤርትራን ሊነጠቅ ምንም እንዳልቀረው እየተረዳ ነበር፡፡

በትግራይ ላይ የተሰማራው የሶስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት 604ኛ ኮር የሕወሓትን ስልታዊ ማፈግፈግ መነሻ አድርጎ ሲገሰግስና ቅጥ ባጣ ሁኔታ እየሳሳ ሲሄድ፤ በተናጠል ምት እየተደመሰሰ ራሱን መከላከል በማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡

በየካቲት ወር 1981 ዓ.ም በሻዕቢያ ሜካናይዝድ ጦር ታግዞ በምዕራብ ትግራይ የምትገኘውን ሽሬ እንዳስላሴን በከፍተኛ መስዋዕትነት መቆጣጠር ቻለ፡፡ 40 ሺ ወታደር የያዘው 604ኛ ኮር ሙሉ ለሙሉ ተደመሰሰ፡፡ ሕወሓት የምስረታውን የልደት ቀንን ጠብቆ የካቲት 11 ያደረሰው የ18 ሰዓታት ጥቃት ሽሬን መቆጣጠር ሲያስችለው፤ ብርጋዴል ጄኔራል ከንፈና ብርጋጀል ጄኔራል ገሞራውን ጨምሮ በርካታ መኮንኖችን መማረክም ችሏል፡፡ በኢትዮጵያ ጦርነት ውስጥ ጄኔራል ሲማረክ ይህ የመጀመሪያው ነበር፡፡

የአፋ ቤት ድል ለሻዕቢያ ወሣኝ የድል ምዕራፍ እንደሆነው ሁሉ ለሕወሓትም የሽሬ ድል ተመሳሳይ ገፅታ ነበረው፡፡

ቀጥሎ ተመሳሳይ ሽንፈትና ኪሳራ እዳይደርስ በሚል ከየካቲት 18 ጀምሮ የደርግ ሰራዊት ያለውጊያ ከመቀሌ መውጣት ጀመረና ግማሹ ወደ አስመራ፣ ግማሹ ወደ ሰሜን ወሎ ጓዙን ጠቅልሎ እንዲሄድ ተደረገ፡፡ በሚስጥር የተከናወነው ሽሽት በ15 ቀናት ተጠናቆ የካቲት 22 ቀን 1981 ሙሉ ለሙሉ መቀሌ ተለቀቀች፡፡

የደርግ መንግስት ያለአንዳች ውጊያ ለሕወሓት የትግራይን ግዛት አስረከበ፡፡ የሚገርመው ቦታውን ለማስከበር ሰፍሮ የነበረው ጦር "ዘመቻ ቅጣው" በሚል ስያሜ የዘመተ መሆኑ ነው፡፡ ሳይቀጣም፣ ሳይቀጣም ሹልክ አለ፡፡

ከዚህ በኋላ ሕወሓት ትግራይን ደጀን አድርጎ ዘመቻውን ወደ መሐል አገር አስፋፋ፡፡ የትግራይ ወጣትም ወደ እነሱ ከቀድሞው የበለጠ



እየተቀላቀላቸው የሰው ኃይላቸውን አሳደጉ፡፡ ትግራይን ነፃ አወጣለሁ ብሎ የተነሳው ድርጅት አገር አቀፍ የሆነ ሌላ አጀንዳ ማውጣት ግድ ሆነበት፡፡

ከ"ኢሠፓአኮ" ወደ "ኢሠፓ"

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግስት ደርግ ከምስራቁና ከሰሜኑ ጦርነት ጎን ለጎን ስልጣኑ ሕጋዊ ከለላ ያለውና፤ በህዝብ ተሹሞ የተሰየመ መንግስት ሊያስመስለው የሚችል ተግባር ለመፈፀም ደፋ ቀና ይል ነበር፡፡

ይህም በየካቲት ወር 1972 ዓ.ም ተጀምሮ በ6 ወራት ውስጥ እንዲዋቀር የተደረገውን "የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን" (ኢሠፓአኮ)ን መመስረት ሲሆን፤ አደራጅ ኮሚሽኑ ከተዋቀረ በኋላ ደግሞ አምጦ የሚወልደው "የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ፓርቲ" (ኢሠፓ) የመጨረሻው አውራ ፓርቲ ይሆንና፤ የደርጉን ሊቀመንበር ሌተናል ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምን ብቸኛ መሪ አድርጎ እስከፍፃሜው እንዲዘልቁ ማድረግ ዓላማና ግቡ ነው፡፡

ዓላማው ከግቡ ይደርስ ዘንድም ገና ከጅምሩ በጽኑ መሠረት ላይ መገንባት ነበረበትና የኮሚሽኑ ምስረታ አዋጅ ይፋ ከመደረጉ በፊት በክፍላተ አገራት፣ በአውራጃና በወረዳዎች ላይ ታማኝ ታማኝ የመንግስቱ ተጠሪዎች ከታህሳስ ወር ጀምሮ ቅድመ ስራቸውን እንዲያከናውኑ ተመደቡ፡፡

በየቦታው ቢሮዎችን ማዘጋጀት፣ ተገቢ ሰዎችን መመልመል፣ መሰናክል ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉትን ማጥራት፣ የመንግስቱን መልካም ስብዕና ማንፀባረቅ... የሚሉት ከቅድመ ስራዎች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በኋላ በ"ኢማሌድኅ" ጥላ ስር ተሰባስበው ከነበሩ ድርጅቶች ውስጥ በአባልነት ይሳተፉ ከነበሩ ግለሰቦች ጀምሮ፤ የፖለቲካ ተሳትፎ እስከሌላቸው ግለሰቦች ድረስ፣ ምሁራን፣ የኪነጥበብ ሰዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የፊጠራ ባለቤቶች፣ አምባሳደሮች፣ ሚኒስትሮች፣ ከጦር ኃይሉም፣ ከፖሊስ ሠራዊትም ፣ጡረተኛ አርበኞችም ... ሳይቀሩ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በ ኢሠፓአኮ መስራች ጉባዔ ላይ እንዲሳተፉ ተደረገ፡፡

እነዚህ ከድፍን ኢትዮጵያ ተመርጠው በጉባዔው ለመገኘት የተጋበዙ ዜጎች ቁጥራቸው 2ሺ ሲሆን፤ በታላቁ ቤተመንግስት ጊቢ ውስጥ ባለው የምኒልክ አዳራሽ ጳጉሜ 1 ቀን 1972 ዓ.ም ከጠዋት ጀምረው በመስራች ጉባኤው ላይ በጋራ ተገኝተው ያዳራሹን ግድግዳና ኮርኒስ በጋለ ጭብጨባ ሲያናጉት ዋሉ፡፡

ጉባዔው በማግስቱም ቀጠለና 93 ቋሚ፣ 30 ተለዋጭ አባላት ያሉት ማዕከላዊ ኮሚቴውን ሰየመ፡፡ ከቋሚ የማዕከላዊ አባላት ውስጥ 60ዎቹ መለዮ ለባሾች (ፖሊስን ጨምሮ) እንዲሆኑ ሲደረግ፣ 33ቱ

በአፋቤት ጦርነት 20 ሺህ የደርግ ሠራዊት በአንድ ጊዜ ያለቀ ሲሆን፤ ስፍር ቁጥር የሌለው የጦር መሣሪያ በሻዕቢያ እጅ ገባ። ይህ ቦታ ለሻዕቢያ መጀመሪያ ወደ ምፅዋ፣ እንዲሁም ወደ አስመራ መረማመጃ ሆነው። በጦርነቱ የወደፊት አቅጣጫ ላይም ለሻዕቢያ ድል መፋጠን ትልቁን ሚና ተጫውቷል። በርካታ መኮንኖች በመማረካቸውም ሚስጥሩን ሁሉ፣ የሠራዊቱን አሠፋፈር ሳይቀር በቀላሉ ለመረዳት ለሻዕቢያ ጠቅሞታል።

ሻዕቢያ እስከ መጋቢት ወር ድረስ አፋቤትን የማፅዳትና ሙሉ ለሙሉ የግሉ ለማድረግ በወሰደው ተከታታይ የማጥቃት እርምጃ ከነሙሉ የጦር ግምጃ ቤቷ ተረከባት። ዘጠኝ የሶቭየት የጦር አማካሪዎችን ጨምሮ ማረከ፣ የናደው ዕዝ በተጠቀሰው ወር ተናደ። የኢትዮጵያ መንግስት ኤርትራን ሊነጠቅ ምንም እንዳልቀረው እየተረዳ ነበር።

በትግራይ ላይ የተሰማራው የሶስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት 604ኛ ኮር የሕወሓትን ስልታዊ ማፈግፈግ መነሻ አድርጎ ሲገሰግስና ቅጥ ባጣ ሁኔታ እየሳሳ ሲሄድ፤ በተናጠል ምት እየተደመሰሰ ራሱን መከላከል በማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ።

በየካቲት ወር 1981 ዓ.ም በሻዕቢያ ሜካናይዝድ ጦር ታግዞ በምዕራብ ትግራይ የምትገኘውን ሽሬ እንዳስላሴን በከፍተኛ መስዋዕትነት መቆጣጠር ቻለ። 40 ሺ ወታደር የያዘው 604ኛ ኮር ሙሉ ለሙሉ ተደመሰሰ። ሕወሓት የምስረታውን የልደት ቀንን ጠብቆ የካቲት 11 ያደረሰው የ18 ሰዓታት ጥቃት ሽሬን መቆጣጠር ሲያስችለው፤ ብርጋዴል ጄኔራል ክንፈና ብርጋጄል ጄኔራል ገሞራውን ጨምሮ በርካታ መኮንኖችን መማረክም ችሏል። በኢትዮጵያ ጦርነት ውስጥ ጄኔራል ሲማረክ ይህ የመጀመሪያው ነበር።

የአፋ ቤት ድል ለሻዕቢያ ወሣኝ የድል ምዕራፍ እንደሆነው ሁሉ ለሕወሓትም የሽሬ ድል ተመሳሳይ ገፅታ ነበረው።

ቀጥሎ ተመሳሳይ ሽንፈትና ኪሳራ እዳይደርስ በሚል ከየካቲት 18 ጀምሮ የደርግ ሰራዊት ያለውጊያ ከመቀሌ መውጣት ጀመረና ግማሹ ወደ አስመራ፣ ግማሹ ወደ ሰሜን ወሎ ጓዙን ጠቅልሎ እንዲሄድ ተደረገ። በሚስጥር የተከናወነው ሽሽት በ15 ቀናት ተጠናቆ የካቲት 22 ቀን 1981 ሙሉ ለሙሉ መቀሌ ተለቀቀች።

የደርግ መንግስት ያለአንዳች ውጊያ ለሕወሓት የትግራይን ግዛት አስረከበ። የሚገርመው ቦታውን ለማስከበር ሰፍሮ የነበረው ጦር "ዘመቻ ቅጣው" በሚል ስያሜ የዘመተ መሆኑ ነው። ሳይቀጣም፣ ሳይቀጣም ሹልክ አለ።

ከዚህ በኋላ ሕወሓት ትግራይን ደጀን አድርጎ ዘመቻውን ወደ መሐል አገር አስፋፋ። የትግራይ ወጣትም ወደ እነሱ ከቀድሞው የበለጠ



እየተቀላቀላቸው የሰው ኃይላቸውን አሳደጉ። ትግራይን ነፃ አወጣለሁ ብሎ የተነሳው ድርጅት አገር አቀፍ የሆነ ሌላ አጀንዳ ማውጣት ግድ ሆነበት።

ከ"ኢሠፓአኮ" ወደ "ኢሠፓ"

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግስት ደርግ ከምስራቁና ከሰሜኑ ጦርነት ጎን ለጎን ስልጣኑ ሕጋዊ ከለላ ያለውና፤ በህዝብ ተሹሞ የተሰየመ መንግስት ሊያስመስለው የሚችል ተግባር ለመፈፀም ደፋ ቀና ይል ነበር።

ይህም በየካቲት ወር 1972 ዓ.ም ተጀምሮ በ6 ወራት ውስጥ እንዲዋቀር የተደረገውን "የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን" (ኢሠፓአኮ)ን መመስረት ሲሆን፤ አደራጅ ኮሚሽኑ ከተዋቀረ በኋላ ደግሞ እምጦ የሚወልደው "የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ፓርቲ" (ኢሠፓ) የመጨረሻው አውራ ፓርቲ ይሆንና፤ የደርጉን ሊቀመንበር ሌተናል ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምን ብቸኛ መሪ አድርጎ እስከፍፃሜው እንዲዘልቁ ማድረግ ዓላማና ግቡ ነው።

ዓላማው ከግቡ ይደርስ ዘንድም ገና ከጅምሩ በጽኑ መሠረት ላይ መገንባት ነበረበትና የኮሚሽኑ ምስረታ አዋጅ ይፋ ከመደረጉ በፊት በክፍላተ አገራት፣ በአውራጃና በወረዳዎች ላይ ታማኝ ታማኝ የመንግስቱ ተጠሪዎች ከታህሳስ ወር ጀምሮ ቅድመ ስራቸውን እንዲያከናውኑ ተመደቡ።

በየቦታው ቢሮዎችን ማዘጋጀት፣ ተገቢ ሰዎችን መመልመል፣ መሰናክል ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉትን ማጥራት፣ የመንግስቱን መልካም ስብዕና ማንፀባረቅ... የሚሉት ከቅድመ ስራዎች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው።

ከዚህ በኋላ በ"ኢማሌድኅ" ጥላ ስር ተሰባስበው ከነበሩ ድርጅቶች ውስጥ በአባልነት ይሳተፉ ከነበሩ ግለሰቦች ጀምሮ፤ የፖለቲካ ተሳትፎ እስከሌላቸው ግለሰቦች ድረስ፣ ምሁራን፣ የኪነጥበብ ሰዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የፈጠራ ባለቤቶች፣ አምባሳደሮች፣ ሚኒስትሮች፣ ከጦር ኃይሉም፣ ከፖሊስ ሠራዊትም ፣ጡረተኛ አርበኞችም ... ሳይቀሩ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በ ኢሠፓአኮ መስራች ጉባዔ ላይ እንዲሳተፉ ተደረገ።

እነዚህ ከድፍን ኢትዮጵያ ተመርጠው በጉባዔው ለመገኘት የተጋበዙ ዜጎች ቁጥራቸው 2ሺ ሲሆን፤ በታላቁ ቤተመንግስት ጊቢ ውስጥ ባለው የምኒልክ አዳራሽ ጳጉሜ 1 ቀን 1972 ዓ.ም ከጠዋት ጀምረው በመስራች ጉባኤው ላይ በጋራ ተገኝተው ያዳራሹን ግድግዳና ኮርኒስ በጋለ ጭብጨባ ሲያናጉት ዋሉ።

ጉባዔው በማግስቱም ቀጠለና 93 ቋሚ፣ 30 ተለዋጭ አባላት ያሉት ማዕከላዊ ኮሚቴውን ሰየመ። ከቋሚ የማዕከላዊ አባላት ውስጥ 60ዎቹ መለዮ ለባሾች (ፖሊስን ጨምሮ) እንዲሆኑ ሲደረግ፣ 33ቱ

ሲቪሎች ነበሩ፡፡በዚህም የአማን አንዶምን የመጀመሪያ ዕቅድ ደርግ በመጨረሻ በከፊል መተግበሩን እንረዳለን፡፡

ከተለዋጭ አባላቱ ውስጥ ደግሞ 21ዱ መለዮ ለባሽ፣ 9ኙ ሲቪሎች ናቸው፡፡ በተለዋጮቹ ውስጥ 2ቱ፣ በቋሚዎቹ ውስጥ 26ቱ የደርግ አባላት እንዲሆኑ ተደረገ፡፡ ሁሉንም አባላት በዕጩነት ያቀረቡት ሊቀመንበር መንግስቱ የነበሩ ሲሆን፤ ያለአንዳች ተቃውሞ ይሁንታ ማግኘቱን ቆመው በጋራ ጭብጨባ ያረጋገጡት ደግሞ ሁሉም ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡

ኢሠፓአኮ ከተመሠረተ በኋላ ባደረገው የመጀመሪያ ስብሰባም የአደራጅ ኮሚሽኑ ሊቀመንበር አድርጎ መንግስቱን መምረጡን ለጠቅላላ ጉባዔው ሲያበስር ያ ከፍተኛ ድምፅ ያለው የጋለ ጭብጨባ ያለማቋረጥ ተስተጋባ፡፡

ኮሎኔል መንግስቱ በደርግ ሊቀመንበርነታቸው ላይ የኢሠፓን ሊቀመንበርነት ደርበው ያዙ፡፡ ከዚህ በኋላ ሊቀመንበሩና የመስራች ጉባዔ አባላቱ በሲቪልና በወታደራዊ ሰልፍ የደመቀውን የአብዮቱን 5ኛ ዓመት በዓል በአብዮት አደባባይ አክብረው ወደየመጡበት ተመለሱ፡፡ ወደየመጡበት . የተመለሱት የመስራች ጉባዔ አባላት በየክልላቸው ኢሠፓአኮን አቀነቀኑ፡፡ ሊቀመንበር መንግስቱም በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የማዕከላዊ ኮሚቴውን ስራ አስፈፃሚዎች (የፖሊት ቢሮ አባላትን) መርጠው በየዘርፉ መደቡ፡፡

1. ሻምበል ለገሠ አስፋው - የድርጅት ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
2. ሻምበል ፍቅረስላሴ ወግደረስ - የርዕዮተዓለም ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
3. ኮሎኔል ተካ ቱሉ - የዲሲፒሊንና ቁጥጥር ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
4. አቶ ታዬ ጉርሙ - የኅብረት ስራ ማኅበራት ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ
5. ኮሎኔል ብርሃኑ ባይህ - የውጭ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
6. ኮሎኔል ውብሸት ደሴ - የአስተዳደርና ፋይናንስ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ
7. ኮሎኔል ገብረየስ ወልደሃና - የአብዮታዊ ጦር ዋና ፖለቲካ አስተዳደር ኃላፊ
8. ሻለቃ ተካልኝ ባልቻ - የማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ኃላፊ ሆነው ተመድበው ስራቸውን ቀጠሉ፡፡

ኢሠፓአኮ በዚህ መልኩ ተዋቅሮ ሲያበቃ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሁሉ በስሩ ሆኑ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ወሬ ስለ ኢሠፓአኮ እንዲሆን ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ስራ ተሰራ፡፡ ሲቪልና ወታደሩ እየተናናቀ፣ እንዲሁም ሌሎች የውስጥ ችግሮችን ይዞ ለመቀጠል



ከመገደዱም ባለፈ፤ አደራጅ ኮሚሽኑ የፀነሰው ፓርቲ ነውና አብሮ ለመወለድ ሲባል የሚደረገው ሹክቻ የበረታ ነበር፡፡ በዚህም ላይ የሰሜንና የምስራቁ ጦርነት አለ፣ የኢህአፓ ሠርጎ ገቦችን መከላከልም ሌላ ፈተና ነበር፡፡ የክፍለሃገራት ኮሚቴዎችን ፅብ ማርገብና መሸምገልም ተጨማሪ ስራ ሆኗል፡፡ ምንም ቢሆን ግን ኮሚሽኑን ተንከባክቦ ዳር ማድረስ አላዳገተም፡፡

ኢሠፓአኮ ከፍተኛ በጀት ተመድቦለትና የህዝብ ድጋፍም አግኝቶ ጠቅላላ ጉባዔ፣ ማዕከላዊ ኮሚቴ፣ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ የክፍላተሃገር ኮሚቴ እና በየቀበሌው ማኅበራትና መስሪያ ቤቶች የተዋቀሩ መሠረታዊ ድርጅቶች እንዲኖሩት ተደርጎና ራሱን የቻለ የአሠራር መዋቅር ተዘርግቶለት፣ ከቀበሌ እስከ አጠቃላይ ምክር ቤት ባለው የአመራር ቦታ ላይ ይመጥናል የተባለ እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ዜጋ ከየአቅጣጫው ተሰብስቦ በዕጩነት ተመዘገበ፡፡ ከሞላ ጎደል የዕጩዎች መመዘኛ አጭር የህይወት ታሪክና ለአብዮቱ ያደረጉት አስተዋፅኦ የሚል ነበር፡፡

ዕጩዎችን ለማበጠር የተሰየሙት ኮሚቴዎችም "የአብዮታዊ ሠደድ" አባላት የበረከቱበት ነው፡፡ በደርግ የበላይነት እየተዳፈኑ የነበሩ የዘመኑ ፓርቲዎችም በዚያ ወቅት ገና ተደመሰሰው አልከሰሙም ነበርና በተቻላቸው መጠን ዕጩዎቻቸውን አቅርበዋል፡፡ የዕጩዎች ዝርዝር ከተጠናቀቀ በኋላም ምርጫው በቀበሌ፣ ቀጥሎ በከፍተኛ፣ በመጨረሻም በአጠቃላይ ምክር ቤት ተካሂዶ በሁሉም ከተሞች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተጠናቀቀ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የሠራተኛና የገበሬ ማኅበራት ተደራጁ፡፡

በዚህ መሠረት ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን በአንድ በኢሠፓአኮ አመራር መዳፍ ስር ማድረግ ተቻለ፡፡ "የኢሠፓአኮ ተልዕኮ በሰፊው ህዝብ የጋራ ርብርቦሽ ይሳካል" የሚል መፈክር ያላሰማ ዜጋ ፀረ አብዮተኛ ተብሎ ይፈረጃል፡፡ የኮሚሽኑ ልሳን "ሠርቶ አደር" ጋዜጣ ሙሉ ገፁ ስለኢሠፓአኮ የሚያትት ሆነ፡፡

እንዲህ ሆኖ የፓርቲው መወለጃ ጊዜ እስኪቃረብ የተጀመሩ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች እንዲፋጠኑ፣ አስፈላጊ ዝግጅቶች እንዲደረጉ፣ የሌኒንና የቅማላችን ሐውልቶች ግንባታቸው አልቆ በጌጣጌጥ እንዲንቆጠቆጡ ተደረገ፡፡

ኢሠፓአኮ በተመሠረተ በ4ኛ ዓመቱ በ1977 "የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር" ፓርቲን (ኢሠፓ)ን ሲወልድ በጥቂቱ በዓሉን የወሎው ድርቅ አደበዘዘው እንጂ፤ አጠቃላይ የከተማዋ በመብራትና በባንዲራ ማሸብረቅና ሌላው ሁሉ ዝግጅት የቀድሞውን የእነጃንሆይን የንግስ በዓል

የሚያስታውስ ሆኖ ነው የታየው፡፡ እንዲህ ያማረችው ከተማ የመላ አገሪቱን የፓርቲ ተወካዮችና የውጭ አገር እንግዶችን በክብር ተቀበለች፡፡

ይህ የንግስ በዓል በአብዮቱ 10ኛ ዓመት የድል በዓል ወቅት በደማቅ ስነስርዓት ከመከበሩ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ጳጉሜ 1 ቀን 1976 ዓ.ም የፓርቲው መስራች ጉባዔ ተሰብስበው ለኢሠፓ ምስረታ እውቅና ሰጥተዋል፡፡ በጉባዔው ላይ ከ2ሺ በላይ የኢሠፓአኮ አባላትና ከ350 በላይ ታዛቢዎች ተገኝተዋል፡፡ የኢሠፓአኮ ተመራጭ አባላት ከሠራተኛው፣ ከገበሬውና ከወታደሩ የተወጣጡ ይሁኑ እንጂ 60 በመቶው አባላት ከመለዮ ለባሹ የተውጣጡ ናቸው፡፡ ... ያው እንደተለመደው ስለሆነ ዝርዝር ውስጥ መግባት ሳያስፈልግ በእለቱ የዕጩዎች ስም ዝርዝር ለቋሚ ማዕከላዊ ኮሚቴና ለተለዋጭ አባላት የታሰቡ ሰዎች ቀረቡ፡፡ ምርጫውም ለብዙሃን መገናኛ የሚሆኑ ቀረፃዎች እስኪከናወኑ ድረስ እውነተኛነቱን ተላብሶ ሲካሄድ ቆየና የድምፅ መስጫ ሳጥኖች የምርጫ አስፈፃሚ ሆነው ለተመደቡት ለኮሎኔል ብርሃኑ ባይህ ተሰጠ፡፡ ከ3 ሰዓት በኋላ የቆጠራ ውጤቱ ተነበበ፡፡በዚህ መሠረት ኮሎኔል መንግስቱ ቁልፍ የሆነውን የፓርቲ ዋና ፀሐፊነት ከመያዛቸውም በላይ፤ ሁለት መቶ አባላት ያሉት የማዕከላዊ ኮሚቴና አስራ ስምንት አባላት ያሉት የፖሊት ቢሮ ሊቀመንበር ሆነው ቁጭ ማለታቸው ተረጋገጠ፡፡

ከኢሠፓአኮው ምስረታ ጋር ተመሣሣይ በሆነ መልኩም የፖሊት ቢሮው አባላት ለመንግስቱ ታማኝነታቸውን ያረጋገጡና በመንግስቱ አቅራቢነት የተመረጡ የደርግ አባላት፣ ቴክኖክራቶችና የማርክሲዝም ሌኒኒዝም አቀንቃኞች ነበሩ፡፡

በዚህ መልኩ ኢሠፓአኮ ኢሠፓን ወለደ፡፡ ፓርቲው ሶሻሊስታዊ ሠነዶችን አፅድቆ ስራውን ቀጠለ፡፡ መንግስቱም እቅዳቸው እየሰመረ በመቀጠሉ ደስ ተሰኙ፡፡ ሆኖም ከአባላቱ በኩል ሁለት ተቃውሞ ነበር፡፡ አንዱ በምርጫው ድራማዊ ክንውን ካኮረፉት በኩል የተደመጠ ማጉረምረም ሲሆን፤ ሌላው የአገሪቱ ዜጎች በረሃብ እየተቀጠፉ ይህን ያህል ከፍተኛ ገንዘብ ለፓርቲ ምስረታ ተብሎ በመመደቡ ነው፡፡

በእርግጥም መንግስቱ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ትኩረታቸው ፓርቲው ላይ ነበርና ይህንኑ ዳር ካደረሱ በኋላ ነው በፍጥነት ወደ ድርቁ ጉዳይ ፊታቸውን ያዞሩትና ቀደም ሲል "የአብዮቱ ፍሬዎች" በሚል ርዕስ ስር ተካትቶ ያየነውን የመፍትሄ እርምጃ መውሰድ የጀመሩት፡፡

በተረፈ በምርጫው ፍትሐዊ አለመሆን የተደመጠውን ጉርምርምታ ከመጤፍ አልቆጠሩትም፡፡ እናም ከዚህ ጊዜ በኋላ "ከጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያም አብዮታዊ አመራር ጋር ወደፊት!" ተባለ፡፡ ሊቀመንበር መንግስቱ አሁን የቀራቸው ሁለት ያህል ቀላል ስራዎች ናቸው፡፡



ሕገ-መንግስቱን ማስረቀቅና ማፅደቅ፣ ሪፐብሊኩን አውጆ ህዝባዊ ምርጫ ማከናወን፡፡ ምርጫውንም አሸንፈው ፕሬዝዳንት መሆንና እስከመጨረሻው መንገስ፡፡ እነዚህን ተግባራት ከማከናወናቸው በፊት ግን በፓርቲው ምስረታ ማግስት የተከሰተው ከባድ የኢኮኖሚ ቀውስ ኢሠፓን አላራምድ ስላለ አንዳንድ እርምጃዎችን መውሰድ ቀዳሚ ተግባር መሆኑ የግድ ሆኖ ተገኘ፡፡ ሰማያዊ ካኪ መልበስም የመጣው የኢኮኖሚ ቀውሱን ተከትሎ ነውና እሱኑ ወደማየት እንለፍ፡፡

የኢኮኖሚ ተሐድሶ

ወቅቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ለድርቅ አደጋ የተጋለጡበትና፤ ድርቁን ተከትሎ በተከሰተው ረሃብም በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ለአሠቃቂ ሞት የተዳረጉበት ወቅት ነው፡፡ ይህንን ዛሬም ድረስ አልለቅ ያለ የጎን ውጋት ለማስወገድ ኢትዮጵያ አቅም አልነበራትም፣ አሁንም ያላትም፣ (ወደፊት ይኖራት ይሆናል እንጂ፤) ስለዚህ ወደለጋሽ አገራት አኮፋዳ ይዞ መዞር የግድ ነበርና መንግስቱ ይህን አድርገው የነብስ አድን ስራ ሠርተዋል፡፡ ነገር ግን በወቅቱ ብዙ አገሮች በርዕዮት መለያየት ምክንያት ፊታቸውን አዞሩ፡፡

በዚህም ላይ በርሃ ያሉ ተቃዋሚዎች ደርግ ጃንሆይን ሲጥል እንዳደረገው ሁሉ ረሃቡንና የፓርቲ ምስረታ ግብዣውን እያቀናጁ ለፕሮፓጋንዳ ስለተጠቀሙበት የተፈለገው እርዳታ በተፈለገው መጠን ሊገኝ አልቻለም፡፡ የተፈጠረውን ክፍተት በራስ ጥረት ለመሙላት ሲባልም እቅድ ነድፎ የነብስ አድን ስራውን ለመስራት የሚያስችል "የተፈጥሮ ችግር መቋቋሚያ ኮሚቴ" ተቋቁሞ እርዳታውን ለተጎጂዎች ማሰራጨትና፣ ተጎጂዎችን ወደ ሌላ ሠፈራ ማጓጓዝ ተጀመረ፡፡ ለዚህም ኮሎኔል ብርሃኑ ባይህ የእርዳታ ገንዘብና ቁሳቁስ አሰባሳቢ፣ ሻምበል ለገሠ አስፋው የሠፈራ መርሐ ግብር አስፈፃሚ ዘርፎች ኃላፊ ሆነው ተመድበው በየክፍላተአገሩ እስከቀበሌ ድረስ በተዋረድ የሚሰሩ ሰዎች ተመድበው በህዳር ወር 1977 ዓ.ም ስራቸውን ጀምረዋል፡፡ ሂደቱን አጠናክሮ በመቀጠልም ከትንሹ ስንዴ እደላ እስከ ትልቁ የጣና በለስ ግድብ የዘለቀ የመፍትሄ እርምጃ ተወስዷል፡፡

ድርቁ ያስከተለው ችግር ወደ ከተማም ተዛምቶ በአዲስ አበባ ሳይቀር ከፍተኛ የእህል እጥረት ተከሰተ፡፡ በሚያስደነግጥ ሁኔታ አንድ ኩንታል ጤፍ 400 ብር (አራት መቶ ብር) ተሸጠ፡፡ ዳቦ ጠፋ፣ አትክልት የለም፡፡ የውሃ እጥረትም ተፈጠረ፡፡ በዚህ ምክንያት በየካቲት ወር 1977 የኮሌራ ወረርሽኝ የከተማውን ህዝብ አጠቃ፡፡

ወረርሽኙ የፖለቲካ ኪሣራ እንዳያስከትል "አጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት" የሚል መጠሪያውን መንግስት "አተት" በሚል ምህፃረቃል ሸፈነው፡፡ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር በወሰደው ፈጣን የመከላከል ርምጃ 700

ሠዎች ብቻ ገድሎ በሽታውን መግታት ተቻለ፡፡ እንዲህ እያለ የአገሪቱ ኢኮኖሚ በፍጥነት እያሽቆለቆለ ሲሄድ መንግስት ለህዝቡ የተለያዩ ምክሮችንና የተመጠነ ኑሮ ማልመድ እንደሚገባ ማስተማር ጀመረ፡፡ "ቁጠባን ልመዱ" ሲል አስጠነቀቀ፡፡

ጓድ ሊቀመንበር ራሳቸውን አርአያ አድርገው ማሳየት ነበረባቸውና … ያው የወታደር ልብሳቸውን ካወለቁ ቆይተው ነበርና በምትኩ ሱፍና ክረባት አድርገው ይታዩ ስለነበር አሁን ደግሞ የአገር ውስጥ ምርት የሆነውን ሠማያዊ ካኪ ኮምፕሌቱን ገጥመው መጡ፡፡

"አለው አለውና

በካኪው ላይ ጠና …" የሚል ስንኝ ተቋጠረ፡፡ ከካኪ ወደ ሱፍ፣ ከሱፍ ወደ ካኪ ማለት ነው፡፡ ወዲያው የፓርቲው አባላትና ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ይህንኑ ጥቁር ሠማያዊ ካኪ እንዲለብስ የሚያስገድድ ደንብ ወጣ፡፡ ተግባራዊም ሆነ፡፡ ያጉረመረሙት ብዙ ቢሆኑም ግን፤ "አሁን ካኪ ተለብሶ ምን ለውጥ ሊመጣ ነው?" ቢሉም ተግባራዊ ከመሆን አልዳነም፡፡የሀ ልብስ ሶስት አይነት ደረጃዎችና ቀለማት ነበሩት፡፡ ቀጥሎ ለመንግስት ስራም ሆነ ለግል ማንኛውም አውቶሞቢልና ሌሎች የቅንጦት እቃዎች ከውጭ እንዳይገቡ ታገደ፡፡

የመንግስት ተሽከርካሪዎች በባለሥልጣናቱ በግል መያዛቸው ቀርቶ በጣም አስፈላጊ ሲሆን በሹፌር እንዲጓጓዙ፣ የግል አውቶሞቢል እሁድ ቀን እንዳይሽከረከር፣ ነዳጅ በኩፖን እጅግ አስፈላጊ ለሆነ ጉዳይ ሲፈለግ ብቻ እንዲሸጥ፣ ውድ ዋጋ ያላቸው ጨርቃጨርቆች ተገዝተው ከውጪ እንዳይመጡ፣ነዳጅ፣የሞተር ዘይትና ቅባት ለምርት፣ ለወታደራዊ አገልግሎት፤ እንዲሁም ለህዝብ መጓጓዣ ተግባር ብቻ በእቅድና በቁጠባ እንዲውል፣ የተጋነነ የመኖሪያ ቤት አሠራር ስርዓት እንዲይዝ፣እያንዳንዱ ዜጋ በድርቅ ለተጎዱ ወገኖቹ መልሶ ማቋቋሚያ የሚሆን ቋሚ የገንዘብ መዋጮ እንዲያደርግ፣በመጠለያ ጣቢያ የሚገኙትን ተጎጂዎች ለመርዳት ጥያቄ የሚቀርብለት ዜጋ በማንኛውም የስራ ዓይነት በፈረቃ መሳተፍ ግዴታው እንደሆነ የሚደነግግ ደንብ ወጥቶ በስራ ላይ እንዲውል ተደረገ፡፡

እነዚህን የመሰሉ ሕጎች አውጥቶ በመንግስት ብቻ ጉዳዩ ሳይያዝና በብሔራዊ ደረጃ ችግሩን ለህዝብ ገልጾ፣ አቅምን አገናዝቦ የተመጠነ ኑሮ መኖር ግዴታ መሆኑን አውጆ፤ በተለይም በገቢና ወጪ ንግድ ላይ የተከሰተውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ችግር ለመቅረፍ የሞከረ መንግስት "ረሃብ ደብቋል" እየተባለ መታማቱ ተገቢ አይመስልም፡፡ ከዚህ ይልቅ "ትኩረት የሰጠው ዘግይቶ ነው" በሚለው ማማቱ የተሻለ ይሆናል፡፡

ፓርቲው በአዋጅ የያዘውን አገር የመምራት ስልጣን መሠረት አድርጎ የመንግስትነት ኃላፊነቱን በውጊያም፣ በኢኮኖሚ ግንባታም በሌሎችም ዘርፎች ሁሉ ከመዋከቡ ጎን ለጎን የተቻለውን ጥሯል፡፡



የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ያሽቆለቆለው በድርቅ ምክንያት ብቻ አልነበረም፡፡ በዋናነት በጦርነት ነው፡፡ የራስ ወዳድ ግለሰቦች ንቅዘትም አብሮ ይጠቀሳል፡፡ በጦርነት የፈሰሰው ገንዘብ ግን እጅግ ከፍተኛ የሆነውን ድርሻ ይይዛል፡፡ ይህም የአገር ዳር ድንበር ጉዳይ እስከሆነ ድረስ ደርግ ከጃንሆይ የተረከባትን ድፍን ኢትዮጵያን ጠብቆ የመቆየት ኃላፊነት አለበትና እንደመንግስት በዘርፉ ፈሰስ ማድረግ ነበረበት፡፡ "አገሪቱን በጦርነት ዘፍቆ ህዝቡን ለረሃብ አጋለጠ" ይባላል፡፡ ማነው ጦርነት የፈለገው? ደርግ? ይሄ አባባል መመርመር ያለበት ነው፡፡ ምክንያቱም ጤናማ አስተሳሰብ አይመስልም፡፡ በጥቂቱ ከላይ የተጠቃቀሱትን አይነት የኢኮኖሚ ተሐድሶ በማድረግ በወቅቱ የነበረውን ችግር በመጠኑ ማሻሻል ተችሏል፡፡

ሁኔታው በዚህ በቀጠለበት ወቅት በፓርቲው የማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት ውስጥ በተለይ የወታደርና የሲቪሉ ፍጥጫና መናናቅ እየተካረረ ሄደ፡፡ በነብስ አድን ስራው ላይ ይታይ የነበረው የጋራ ርብርብ ፓርቲው የወታደርና የሲቪል እየተባለ በሽኩቻ ውስጥ መሆኑ ቀርቶ ውህደት እየተፈጠረ ነው ወደሚል እሳቤ አምርቶ የነበረ ቢሆንም፤ ብዙም ሳይቆይ የስልጣን ትግል ተጀመረ፡፡

አንዱ ቡድን ኃያሉ የወታደር ቡድን ሆነና፤ ሌላው ቡድን ስልጣን ከወታደሩ ለመንጠቅ ይገዳደራል የተባለው አራት ሲቪል ግለሰቦችን ያቀፈ ቡድን ሆኖ ቁርቁሱ ቀጠለ፡፡ "ጋንግስ ኦፍ ፎር" (አራቱ ነውጠኞች) ተብለው የተፈረጁት በቁጥር እንጂ በስም ተለይተው አይታወቁም፡፡ ብቻ ግን ጓድ ሊቀመንበር መፍጠን ነበረባቸው፡፡ ፓርቲው (ኢሠፓ) ከተመሠረተ ከሦስት ዓመት በኋላ የሊቀመንበሩ የመጨረሻ ዓላማ ግቡን ሲመታ እናያለን፡፡

ሕገ መንግስትና ምርጫ

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በአብዮቱ ወቅት በገባው ቃል መሠረት ስልጣኑን ለህዝብ ለማስረከብ በዝግጅት ላይ መሆኑን በአብዮቱ 11ኛ ዓመት የልደት በዓል ላይ መስከረም 2 ቀን 1978 ዓ.ም በአብዮት አደባባይ ለተሰበሰበው ህዝብ ጠቁሞ ነበር፡፡

ይህን ለማድረግ የመጀመሪያው ስራ ሕገመንግስት ማርቀቅ ነበርና የአርቃቂ ኮሚሽኑ አባል ሊሆኑ የሚችሉ ዕጩዎችን መመልመል ተጀመረ፡፡ ለዚህና ለቀጣዩ ሂደት ሲባልም "የብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲቲዩት" የተባለ የአገሪቱ ምርጥ ምርጥ ምሁራን የተሰባሰቡበት ተቋም እንዲመሰረት ተደርጎ ነበርና፤ ተቋሙ ያካሄደውን ጥናትና የጥናቱንም ውጤት በመመርኮዝ ሂደቱ እንዲቀጥልና ውጤታማ ግብ ላይ እንዲደረስ ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡

በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑና አብዮቱን የሚደግፉ ዜጎች ተሳታፊ እንዲሆኑ የተደረገበት 'ምልመላም ከህዝባዊ ማኅበራት፣ ከሙያ ማኅበራት፣ በአካባቢያቸው ከታወቁ ሰዎች፣ ከፓርቲ አባላት፣ ከሃይማኖት መሪዎች፣ ከጦር ሠራዊት፣ ከፖሊስ፣ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች፣ እንዲሁም ከሕግ ባለሙያዎች የተውጣጡ 344 አባላት ያሉት የሕገመንግስት አርቃቂ ኮሚሽን ማቋቋም ተቻለ፡፡ ስራውንም በዚያው ዓመት የካቲት 7 ቀን ጀመረ፡፡ ህዝቡ እንዲወያይበት ስለታቀደም አራት ወራት የፈጀ የአወያዮች ስልጠናና የመወያያ መድረኮችን የማመቻቸት ስራ ተሠራ፡፡

ረቂቁ በአማርኛ ከተዘጋጀ በኋላ ሁሉም ብሔረሰብ በቋንቋው እንዲወያይበት በሚል በኦሮምኛ፣ በትግርኛ፣ በሲዳምኛ፣ በወላይትኛ፣ በሶማልኛ፣ በአፋር፣ ሐድያ፣ ከንባታ፣ ጌዲኦ፣ ኩናማ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ሳሆ እና በስልጥኛ ተተርጉሞ ለወይይት ተሰራጨ፡፡

ምሽግ ውስጥ ካሉት ወታደሮች ጀምሮ ውጪ አገር ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሳይቀር ለሁሉም ዜጎች እንዲደርስና አስተያየት እንዲሰጥበት ከተደረገ በኋላ ከአወያዮች ዘገባ ጋር ወደ አርቃቂ ኮሚሽኑ ተመለሰ፡፡

ኮሚሽኑ "አስተያየቶችንና የማሻሻያ ሀሳቦችን ተቀብዬ አስተካክዬ ጨርሻለሁ" በሚል ጳጉሜ 1 ቀን 1978 ዓ.ም ለጓድ ሊቀመንበሩ አስረከበ፡፡

በ17 ምዕራፎች የተከፈለውና 119 አንቀጾች ያሉት ሕገ-መንግስት ጥር 24 ቀን 1979 ዓ.ም የህዝብ ውሣኔ ያገኘ ሲሆን፤ እንደ ኮሚሽኑ ዘገባ ከተመዘገበው ህዝብ 81 በመቶው "ተቀብለናል" የሚል ነበርና ሕገመንግስቱ በሪፈረንደም ፀደቀ፡፡

ሕገመንግስቱ በሚደነግገው መሠረትም የመንግስት ከፍተኛ አካል ነው ለተባለው ለብሔራዊ ሸንጎ አባልነት ምርጫ መካሄድ ነበረበት፡፡ ለዚህም "የምርጫ ኮሚሽን" ሚያዚያ 14 ቀን 1979 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡ የዚህ ብሔራዊ ሸንጎ (የእንደራሴዎች ሸንጎ) አባል ሆኖ ለመመረጥ የፓርቲው ዝቅተኛ አባላት መብት አላቸው፡፡ በዚህም በፓርቲው የተደገፉ ዕጩዎች አሸናፊ እንዲሆኑና የብሔራዊ ሸንጎው አባል እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡የአውራጃ ፓርቲ ኮሚቴዎች ለህዝብ እንደራሴነት ይመጥናሉ ያሏቸውን ግለሰቦች ስም ዝርዝር በመመዘኛው መሠረት አጣርተው ለክፍለሀገር ኮሚቴዎች ሲያሳልፉ፤እዚያም አስፈላጊው ማጣራት ተደርጎና "እገሌን በእገሌ ለውጥ" በሚል ወደ አውራጃ ስም ዝርዝሩ ተመልሶ፤ የተለወጡትም "ለምን ተለወጥን?" የሚል ክርክራቸው ውድቅ ተደርጎ፣ የተጣራው ዝርዝር ለማዕከላዊ ኮሚቴ ድርጅት ጉዳይ መምሪያ ተላከ፡፡ ማዕከላዊ ኮሚቴውም የደረሰውን ስም ዝርዝር አይቶ፤የሚሰርዘውን ሠርዞና



በሌሎች ዕጩዎች ተክቶ ለመጨረሻ ስራ ወደ አውራጃ ኮሚቴዎች መለሰው፡፡ በዚህ ጊዜ ነው የበታች የሆኑ የአውራጃ የፓርቲ አባላቱና፤ የፓርቲው የበላይ አካላት ጥምረታዊ የፓርቲ ስራ እየሰሩ እንዳልሆነና፤ፓርቲው የይምሰል መሆኑ ለብዙዎች ግልፅ የሆነው፡፡የበታች የሆኑ የፓርቲው አባላት በዕጩነት የመዘገቧቸውን ተራ የፓርቲ አባላት የላይኛው ክፍል እየሰረዘ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን ተካበት፡፡

ከዚህም በላይ በህዝብ ዘንድ ተደማጭነትን ያስተርፋሉ ተብሎ የታመነባቸው ግለሰቦች ባይፈልጉትም በዕጩነት እንዲቀርቡ ግፊት ተደርጎባቸዋል፡፡ ለአብነትም ብፁዕ አቡነ ተክለሃይማኖት ይጠቀሳሉ፡፡ "አልፈልግም" ብለው ቢከራከሩም በብዙ ማግባባት እሺ አሰኝተው ቅፅ እንዲሞሉ ሲደረግ "ብሔር" የሚል ነገር ሲያዩ "እኔ ብሔር ብሎ ነገር አላውቅም እምቢ ያልኩትም ለዚህ ነው፤ እኔ የምወክለው ምዕመኑን ብቻ ነው" ብለው ጥለው ሊወጡ ሲሉ፤ "ግድ የለም እሱን ይተውትና ሌላውን ይሙሉ" ተብለው የሚያምኑበትን ብቻ ሞልተው እንደሄዱ በ"ነበር" ቁጥር 2 ላይ ተጠቅሷል፡፡

በዚህ ዓይነት የዕጩ እንደራሴዎች ቅድመ ዝግጅት ከተጠናቀቀ በኋላ 150 ሺ አባላት ያሏቸው ከ ክፍለሀገር እስከ ቀበሌ የምርጫ ጣቢያ ድረስ ምርጫውን የሚያስተባብሩ "የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች" በድፍን ኢትዮጵያ ተቋቋሙ፡፡

የምርጫ ኮሚሽኑ ዝግጅቱን አጠናቆ የዕጩ እንደራሴዎችን ዝርዝር ተቀብሎ ካፀደቀና የምርጫ አፈፃፀምና የዕጩዎች ማስታወቂያ መመሪያዎችን ካዘጋጀ በኋላ ለእያንዳንዱ ዕጩ የምርጫ ምልክት ብሎ ራሱ የሰየመላቸውን "ዝሆን፣ አንበሳና ጎሽ" ሰጣቸው፡፡ በተለመደው አሠራር መሠረት አንድ ዕጩ መወዳደር ያለበት በሚኖርበት ወረዳ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን በአዲስ አበባ የፓርቲ አባላትና የመንግስት ባለሥልጣናት በጣም ብዙዎቹ ቦሌ አካባቢ ይኖሩ ስለነበር ችግር ተፈጠረ፡፡

መቼም ቀድሞ ያለቀለት ምርጫ ቢሆንም (እንደማንኛውም የአፍሪካ አገራት ምርጫ) ለደንቡ ያህል ነውና የቦሌዎቹን ባለሥልጣናት ወደ ሌሎች ወረዳዎች መበተን የግድ ሆነ፡፡ በማይኖሩበት ቀበሌ ሄደው ተመረጡ ማለት ነው፡፡

የዝሆን ምልክት የያዘ ዕጩ ማሸነፍ እንዳለበት ቀድሞ ተወስኗል፡፡ ግን አንበሳና ጎሹ እንዲያው በስህተት ሊያሸንፉ ቢችሉስ? በሚል መነሻና በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች ሊመረጡ ይችላሉ ተብለው የተፈሩ ዕጩዎች ስለነበሩ፤ ከዕጩ እንደራሴነት ራሳቸውን እንዲያገሉ ተደረገ፡፡

በከፍተኛ (ወረዳ) 14 ቀበሌ 18 በነበረው የምርጫ ጣቢያ ላይ ዕጩ ሆነው ከቀረቡ 3 ሰዎች ውስጥ አንዱ ጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ

ኃይለማርያም ናቸው፡፡ የፕሬዝዳንትነት ወንበሩ የትም እንደማይሄድ ቢያውቁትም ግን፤ ከዚያ በፊት ከዚህ ቀዉሌ በእንደራሴነት ምርጫ ማለፍ አለባቸው፡፡

እንደማንኛውም ዕጩ እንደራሴም በቀበሌው ህዝብ ፊት ቀርበው ራሳቸውን አስተዋውቀዋል፡፡ እናም አንዳች አስገ ነገር እንዳይከሰት የጎሽና የአንበሳ ምልክት ባለቤቶች በደረሰባቸው ተፅዕኖ ምክንያት "ከእሳቸው ጋር በዕጩነት በመቅረቤ ብቻ ታሪካዊ ኩራት ይሰማኛል፣ ልወዳደራቸውና ልመጥናቸው ስለማልችል ብቻ ግን ራሴን በፈቃዴ ከምርጫው አግልያለሁ" እያሉ ወጡ፡፡ የቀበሌው ብቸኛ ዕጩ እንደራሴ ሆነው ጓድ መንግስቱ ብቻቸውን ተወዳድረው ብቻቸውን ተመርጠው አለፉ፡፡

የምርጫውን አጠቃላይ ድባብ በሚመለከት የ"ነበር" ፀሐፊ ዘነበ ፈለቀ በቁጥር 2 መጽሐፋቸው በገፅ 109 ያሰፈሩትን ብናይ ሁኔታውን በአጭሩ ለመገንዘብ ይረዳናል፡፡

"... እንዲህ ሆኖ በሌሎች ምርጫ ጣቢያዎችም ተመሣሣይ እርምጃ ተወስዷል፡፡ ሆኖም አንዳንድ ጣቢያዎች ላይ ጠንካራ እንቢታ ገጥሟል፡፡ ለምሳሌ እኔ ምርጫ ባስፈፀምኩበት ቀጠና ከፍተኛ 17 ቀበሌ 17 ላይ የዝሆን ምልክት የያዙት ኮማንደር የኋላእሸት ግርማ ነበሩ፡፡ የአንበሳውን ምልክት የያዘው የትምህርት ሚኒስትር ኢሠፓ መሠረታዊ ድርጅት ፀሐፊ መብራቱ ገብረንጉስ ነበር፡፡ ከእርሳቸው ይልቅ እርሱ በቀበሌው ህዝብ የታወቀ በመሆኑ፤ "ዝሆኑን ይጥለዋል" በሚል ስጋት ከዕጩነት ራሱን እንዲያገል የምርጫ ጣቢያው አስተባባሪ ኮሚቴ ጠየቀው፡፡ መብራቱ ሆዬ "ኧረ ምን ሲደረግ? ምርጫ ብላችኋል፤ ብላችኋል! የህዝብ ድምፅ ይለየን እንጂ ራሴን አላገልም" ብሎ በፅናት ቆመ፡፡

ቢለመን፣ ቢለመን አሻፈረኝ በማለቱ ወደኔ ላኩት፡፡ "ጓድ መብራቱ ... ምን መሰለህ .... ብዬ ላግባባው ከመጀመሬ "ጓድ ዘነበ ብዙ አትድከም፡፡ እስከላይ ድረስ ሄጄ (እስከ ማዕከላዊ ኮሚቴው) ያለሁበት ፓርቲ የእኩል ፓርቲ መሆኑን ቁርጡን ማወቅ እሻለሁ" ብሎ እንቅጩን ነገረኝ፡፡ .... እላይ ደርሶ ምን እንደተባለ ባላውቅም፤ ከፍቶት ተመለሰ፡፡ ከዚያም ከምርጫው ራሱን አገለለ፡፡..." ይሉናል የዓይን እማኙ፡፡

ምናለ ግን አፍሪካ ውስጥ ቀድሞ ለታወቀ አሸናፊ ምርጫ እየተባለ ያ ሁሉ ጋጋታ፣ ለጋጋታው ሲባል ያ ሁሉ ሚሊዮን ብር ባይባክን? ያስብላል፡፡ ወይስ የአፍሪካ መሪዎች ህዝቡ ሴራችንን አያውቅም የእውነት ይመስለዋል ብለው ያስባሉ? ዘወትር ሲገርመኝ የሚኖር የግል ጥያቄዬ ነው፡፡ መልስ አልባ ጥያቄ!



እዚህ ላይ እግረመንገዴን አንድ ፈገግ ያሰኘኝን ገጠመኝ ላስፍር፡፡ በ2002 ዓ.ም ምርጫ በኢትዮጵያ ከተካሄደ በኋላ የኢትዮጵያ ፓርቲዎች (ብዛታቸው 93 ነበር) ሁሉም በየጽ/ቤታቸው የምርጫውን አጠቃላይ ሂደት የሚመለከቱ መግለጫዎች ይሰጡ ነበር፡፡ በጥምረት በተመሠረተውና መድረክ በተሰኘው ፓርቲ ውስጥ አመራር አባል የሆኑት ዶ/ር መረራ ጉዲናን ፓርቲው መግለጫ ከመስጠቱ በፊት ለሥራ ተገኝቼ ነበርና "ምርጫው እንዴት ነበር ዶ/ር?" አልኳቸው፡፡ "የምን መርጫ?" አሉኝ፡፡ "እንዴ የአሁኑ ምርጫ ነዋ፤ እናንተ ኢህአዴግን በብርቱ የተፈታተናችሁበት የትናንቱ ምርጫ" ስላቸው፤ "ታዲያ ቅርጫ በላ! ምን ምርጫ ትላለህ? ቅርጫ አይደለም እንዴ? ቅርጫ እንኳን ስርዓት አለው" ነበር መልሳቸው፡፡ ይህችን አገላለፅ ስብሰባው ከተጀመረ በኋላም ደጋግመው እያሏት የተገኘውን ጋዜጠኛ ሁሉ በሣቅ ሲያፈርሱት ቆዩ፡፡ ምርጫና ቅርጫ የዚያ ወቅት ሰሞነኛ ጥምር ቃላት ሆነው ሰነበቱ፡፡

ስንመለስ ሰኔ 7 ቀን 1979 ዓ.ም ከንጋቱ 12 ሰዓት የጀመረው ምርጫ ምሽት 12 ሰዓት አበቃ፡፡ የውጭና የአገር ውስጥ ጋዜጠኞች እየተዟዟሩ ሁኔታውን ዘገቡ፡፡ ቀድመው ያሸነፉት የዝሆን ዕጩዎች በካርድ ቆጠራ በድጋሚ አሸነፉ፡፡

ከዚያም ጳጉሜ 4 ቀን 1979 ዓ.ም የብሔራዊ ሸንጎ መስራች ጉባዔ በከፍተኛ ድምቀት ተከፈተ፡፡ 2ሺ የሚሆኑ ጉባኤውን የሚያደምቁ ከአገር ውስጥ የፓርቲ አባላት፣ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ምሁራን፣ መለዮ ለባሽ ጉባዔው ሲከፈት የተገኙ ሲሆን፤ ከውጭ አገር በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት የግብፁን ሆስኒ ሙባረክ ጨምሮ፤ የታንዛኒያ፣ የናይጄሪያ፣ የዛምቢያ፣ የቶጎ፣ የሊቢያ፣ የሳዑዲዓረቢያ፣ የኩዌትና የሌሎች አገሮች መንግስታት ተወካዮች የሆኑ የልዑካን ቡድኖች በክብር እንግድነት ተገኙ፡፡

የመታሰቢያ ስጦታቸውን ሲያበረክቱም በወቅቱ ሻዕቢያን እየረዳች ኢትዮጵያን ታሳርድ የነበረችው አገር የሳዑዲዓረቢያ ተወካይ ለመንግስቱ ያበረከቱት ስጦታ ጎራዴ ነበር፡፡ "እኛ የምንሰጥዎ ከንጉሣችን የተላከ የሳዑዲ ጎራዴ ነው!" ብለው በጩኸት ከተናገሩ በኋላ ጎራዴውን ከአፎቱ መዥረጥ አድርገው ለጓድ ሊቀመንበር ሰጧቸው አሉ፡፡ እረደው ይሁን፣ እያረድናችሁ ነው ይሁን ትርጉሙን በውል ባይረዱትም መንግስቱ ስጦታውን ተቀበሉ፡፡ ከተሰብሳቢው ጉርምርምታ ተደመጠ፡፡

በእለቱ ጓድ ሊቀመንበር መንግስቱ ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምረው እስከዚያች ታሪካዊ ያሏት ቀን ድረስ የነበረውን የኢትዮጵያ ታሪካዊ ገፅታ 4 ሰዓት በፈጀ ሐተታቸው አቀረቡ፡፡

ሲቀጥሉም፤ "... ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተደደር ደርግ ህዝባዊ አደራ በተቀበለበት በዚያ ቀውጢ ወቅት በገባው ቃል መሠረት ስልጣን

ለታሪክ ሰሪውና ከታሪክ ጋር ለሚዘልቀው ለሠርቶ አደሩ ህዝብ እነሆ ሊያስረክብ ነው፡፡ ደርግ ባለፉት የትግልና የድል አመታት ለተከናወኑት አብዮታዊ ተግባራት ከሁሉም በላይ የድርጊቶቹም ሆነ የውጤቶቹ ባለቤት ለሆነው ለሠርቶ አደሩ ህዝብ ያለውን ጥልቅና ታላቅ አክብሮት እየገለፀ፡ ለወደፊቱም ህዝቡ ለኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አመራር፣ በኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግንባታ የእድገት ትልሙን ሙሉ በሙሉ ዳር እንደሚያደርስ ከልብ ይመኛል፡፡…" አሉ፡፡

በዚህም የስልጣን ምርኩዝ ሆኖ ያገለገላቸውን "ደርግ" የተባለ ቡድን መክሰሙን አረዱ፡፡ የደርግ አባላት መክሰም የጀመሩት ከኢሠፓ ምስረታ ጀምሮ የነበረ ቢሆንም፤ ይፋ የወጣው እና በሕገመንግስቱ መሠረትም መኖር እንደሌለበት ግልፅ የሆነው በዚሁ ጊዜ ነው፤ ይህ ማለት ግን አባላቱ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ከሚገባቸው ስልጣን ጋር ይዘው ስለዘለቁ መክሰም ሊባል አይችልም፡፡ ከቡድናዊ ባለሥልጣንነት ወደተናጠላዊ ሹማምንትነት ተለወጡ የሚለው የተሻለ ይገልፃቸዋል፡፡

ከሊቀመንበሩ ንግግር በኋላ የነበረውን ጊዜም ልዩ ልዩ ሕገመንግስቱን ተንተርሰው የወጡ አዋጆችን በማፅደቅ ነበር ያለፈው፡፡ በዚህም በ813 እንደራሴዎች አማካኝነት ስልጣኑን ተግባራዊ እንደሚያደርግና፤ ዋናው የመንግስት ምክር ቤት እንደሆነ፤ የመንግስት ምክርቤቱም የጉባኤና የስራ አስፈፃሚ አካል የተሰኙ የስራ ዘርፎች እንዳሉት ተገለፀ፡፡ በሕገ መንግስቱ መሠረትም፤

- የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢሕዴሪ) ብሔረሰቦች በእኩልነት የሚኖሩበት ብሔራዊ መንግስት ነው፡፡
- ሠርቶ አደሩ ህዝብ የስልጣን ባለቤትነቱን ተግባራዊ የሚያደርገው በምርጫ በሚያቋቁመው ብሔራዊ ሸንጎና የአካባቢ ሸንጎዎች አማካይነት ይሆናል፡፡
- ብሔረሰቦች በሸንጎው መወከላቸው ይረጋገጣል፡፡
- ኢሕዴሪ በዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊኒት፣ በሶሻሊስት ሕጋዊነትና፤ ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት መርህ የሚመራ መንግስት ነው፡፡
- የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ኢሠፓ የመንግስትና የመላው ህዝብ መሪ ኃይል ነው፡፡
- የውጭ ፖሊሲው በወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት፣ በሠላም አብሮ መኖርና በገለልተኝነት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡
- ኢህዴሪ በራስ ገዝና በአስተዳደር አካባቢዎች የሚዋቀር አሃዳዊ መንግስት ነው፡፡
- ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን አካል ብሔራዊ ሸንጎው ነው፡፡



ብሔራዊ ሸንጎው ዋና ባልሥልጣን መሆኑን ካወጀ በኋላ የራሱን ስብሰባ አድርጎ በመሪነት ላይ መሪነት፣ በመሪነት ላይ መሪነት እየተቀዳጁ እዚህ የደረሱትን ሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማርያምን "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ፕሬዝዳንት" አድርጎ መርጦ እንደሾማቸው ይፋ አደረገ፡፡

ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም በዕለቱ ሳቃቸውን መቆጣጠር እያቃታቸው፤ "… ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ህዝብ በመረጠው ፕሬዝዳንት ተመራች!" በማለት የእንጨት መዶሻዋን አንስተው ጠረጴዛዋን ኳ አደረጓት፡፡

ሸንጎው የኢህዴሪን ልዩ ልዩ የስልጣን አካላት ያዋቀረ ሲሆን፤ እነዚህም፤ የመንግስት ምክር ቤት፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ እና የቁጥጥር አካላት ናቸው፡፡

በዚህም መሠረት መንግስቱ ኃይለማርያም የምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት፣ ሻምበል ፍቅረስላሴ ወግደረስ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ አቶ አሰፋ ሊበን የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት ሆነው ሲሾሙ፤ ሌሎች የደርግ አባል የነበሩና ያልነበሩ መለዮ ለባሾችና ሲቪሎች በሚኒስትርነት፣ በምክር ቤቱ አባልነት፣ በምክትል ፕሬዝዳንትነትና በምክትል ጠቅላይ ሚንስትርነት፣ እንዲሁም በልዩ ልዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ እንዱሾሙ ሆነው በጦርነት አጣብቂኝ ውስጥ ገብታ ውጥረት የነገሰባትን ኢትዮጵያን ማስተዳደር ቀጠሉ፡፡

የሌተናል ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም የመጨረሻው የስልጣን ጣራ ላይ የመውጣት ህልም እውን ሆኖ በ1980 ዓ.ም ግቡን መምታት ቻለ፡፡ ስለዚህም 13ኛው የድል በዓል ላይ ስልጣን ህዝቡ ተረክቧልና፣ ወይም ስልጣን የህዝብ ሆኗልና … የዚያ ዓመት መስከረም ሁለት ከሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ ደምቆ ተከበረ፡፡

*መፈንቅለ መንግስቱ እና ያስከተለው መዘዝ*

ግቦት 8 ቀን 1981 ዓ.ም ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም ወደሚወዷት ምስራቅ ጀርመን ለስራ ጉብኝት ብለው ሄዱ፡፡ የኢሠፓ የፖሊት ቢሮ አባላት፣ የመንግስት ምክር ቤት አባላት፣ ሚኒስትሮችና ጄኔራሎች ኤርፖርት ድረስ ሄደው በተለመደው መሽቆጥቆጥ በክብር ሸኝተዋቸው ተመለሱ፡፡

መንግስቱ ግትር ሆነዋል፣ ጠሩ እየተሸነፈ ነው፣ የጄኔራሎች የጦር እቅድ በመንግስቱ ዘንድ ብዙም ተቀባይነት አያገኝም፣ የተለየ ሀሳብ የሚያቀርብ የጦር አዛዥ በጥርጣሬ ዓይን ይታያል፣ ሊቀመንበሩ የመረጡትና ወደተግባር እንዲተረጎም የሚሹት የዘመቻ ስልት በሶቭየት ህብረት የጦር አማካሪዎች የሚቀርበውን የወረቀት ላይ የዘመቻ ንድፍን

ነው፡፡ ከፍተኛ የጦር ጄኔራሎች በበታቾቻቸው በደርግ አባላት ይታዘዛሉ፡፡ አንድ መቶ አለቃ ወይም ሻምበል አንድን ጄኔራል ያዛል፣ መንግስቱ በታማኝነት እንጂ በሙያ ብቃት ማመንና መሾም አልፈጠረባቸውም፡ የተናቁም ይመስላቸዋል፣ ከዚሁ ጋርም የደርግ አባል የሆኑ የበታች ሹማምንት ቁምነገሩ የበላይና የበታችነት ጉዳይ ሳይሆን የመንግስቱ ታማኝና ቀኝ እጅ ሆኖ መገኘቱን በመረዳታቸው በማዕረግ የሚበልጧቸውን ታላላቅ የጦር ጀግኖች ይንቋቸዋል፡፡

በእነዚህና እነዚህን በመሣሠሉ መነሻ ምክንያቶች በርከት ያሉ ጄኔራሎች የመንግስቱን አገዛዝ ጠልተውታል፡፡ ፊት ለፊት መጋፈጥ የማይሞከር በመሆኑም ያለው ምርጫ መፈንቅለ መንግስት ማድረግ ነበርና በዚህ ጉዳይ በተለያዩ ቦታዎች ተሰብስበው መመካከር ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡

የጉዳዩ ጀማሪና ጠንሳሽ ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ ነበሩ፡፡ እቅዱ ከሁለትና ሦስት ዓመት በፊት ተነድፎ ሲብላላ የቆየ ነው፡፡ በተለይ መንግስቱ በኤርትራ ያለው ጦር በተሸነፈ ቁጥር ችግሩ የጄኔራሎች ነው ብለው በማመናቸው ብዙዎችን ከነበሩበት ቦታ እያነሱና ዝቅ፣ ከፍ እያደረጉ መሾም መሻር የጀመሩት ከ1978 ጀምሮ ሲሆን፤ ለአብነት ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይን ከአየር ኃይል ዋና አዛዥነታቸው አንስተው የኢንደስትሪ ሚኒስቴር ሚንስትር እንዲሆኑ አድርገዋል፡፡ ይህ መሰሉ ሹም ሽር ለአመታት ተከታትሎ የተከናወነ እንደመሆኑ መጠንና በጄኔራሎቹም ዘንድ ስላልተወደደ ጥርስ ነከሳው ከተጠቀሰው ጊዜ የጀመረና ሲብላላ የኖረ፤ ነገር ግን በ1981 ግንቦት ወር ሊተገበር የተሞከረ ነው፡፡

የዚችን እለት የመጨረሻ የአድማ ስብሰባ ለማድረግ የተመረጠው ቦታ በመከላከያ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ጊቢ ውስጥ የሚገኝና ከሚኒስትሩ ከሜጀር ጄኔራል ኃይለጊዮርጊስ ቢሮ አጠገብ ያለው አነስተኛ የመሰብሰቢያ ክፍል ነው፡፡

በእለቱ ባልተለመደ ሁኔታ ይህ ጊቢ የጄኔራሎች መጠራቀሚያ ሆታ ታዬ፡፡ አድመኞቹም በቀጠሯቸው መሠረት አንድ በአንድ ወደዚያች ክፍል ገቡ፡፡ በስብሰባው ላይም የተገኙት፤

1. ሜ/ጀ/ል መርዕድ ንጉሴ - የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም
2. ሜ/ጀ/ል ኃይሉ ገብረሚካኤል - የምድር ጦር ዋና አዛዥ
3. ሜ/ጀ/ል አምሃ ደስታ - የአየር ኃይል ዋና አዛዥ
4. ሪረ አድሚራል ተስፋዬ ብርሃኑ - የባህር ኃይል ዋና አዛዥ
5. ሜ/ጀ/ል አለማየሁ ደስታ - የምድር ጦር ምክትል አዛዥ
6. ሜ/ጀ/ል ወርቁ ዘውዴ - የፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ



7. ሜ/ጀ/ል አብዱላሂ ዑመር - የመከላከያ ሚ/ር አስተዳደር መምሪያ ኃላፊ
8. ሜ/ጀ/ል ፋንታ በላይ - የኢንደስትሪ ሚኒስትር
9. ሜ/ጀ/ል አበራ አበበ - የጦር ኃይሎች ምክትል ኤታማዦር ሹም
10. ሜ/ጀ/ል ተስፋዬ ትርፌ - የአብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ኃላፊ
11. ብ/ጀ/ል ሰለሞን ጋሻው - የአየር ኃይል ኤታማዦር ሹም
12. ብ/ጀ/ል ደሣለኝ አበበ - የጦር ኃይሎች አካዳሚ አዛዥ
13. ብ/ጀ/ል እርቅይሁን ባይሳ - የ67ኛው ኮር ዋና አዛዥ
14. ብ/ጀ/ል ተስፋዬ ደስታ - የአየር ኃይል ዘመቻ መኮንን
15. ብ/ጀ/ል ነጋሽ ወልደየስ - የ608ኛው ኮር ዋና አዛዥ
16. ብ/ጀ/ል እንግዳ ወልደአምላክ - የ606ኛው ኮር ዋና አዛዥ
17. ብ/ጀ/ል ገናናው መንግስቱ - የ6ኛው አየር ምድር አዛዥ
18. ኮሞዶር ኃይሌ ወልደማርያም - የጦር ኃይሎች ዘመቻ መምሪያ ባልደረባ ናቸው፡፡(ነበር ቁ.2)

በስብሰባው የተገኙት እነዚህ ብቻ ይሁኑ እንጂ ከየጦር ክፍሉ የተመለመሉ አዛዦችም የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ ለመፈፀም ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ተሰብስበው የመጀመሪያ ውሣኔ ያደረጉት ሊቀመንበሩን ቀይ ባህር ሲደርሱ ፕሌኑን በሚሳኤል መምታትና ማሰናበት የሚል የነበረ ቢሆንም፤ ከመንግስቱ ውጪ የተሳፈሩ በርካታ ንፁሃን ሰቪሎች ስላሉ እነሱንም አብሮ መግደል ተገቢ አይደለም የሚል ሀሳብ ስለተነሳ ውሣኔው ተሻረና፤ ከዚህ ይልቅ በወጡበት ማስቀረት እንደሚሻል ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡

ዋና ሰብሳቢው ሜጀር ጄኔራል ፋንታ በላይ ነበሩ፤ ነገር ግን ወደ ስብሰባው የመጡት ዘግይተው ነበርና የሰብሳቢነቱን ቦታ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ንጉሴ ይዘውታል፡፡ ጄኔራል ፋንታ በላይ ወደ ስብሰባው ገብተው ሲያዩ ቦታው ተይዟል፡፡ ጄኔራል መርዕድ ዋና ሰብሳቢው ሲመጡ ቦታውን መልቀቅ ሲገባቸው ፀጥ አሉ፡፡ ቢታይ፣ ቢታይ መርዕድ ለፋንታ ሊለቁ ቀርቶ የመልቀቅ አዝማሚያም ሳያሳዩ ስብሰባውን መምራት ቀጠሉ፡፡

መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ የተሰባሰቡት ጄኔራሎች እዚያው በዚያው ሌላ መፈንቅለ መንግስት አደረጉ፡፡ ስልጣን ሠይጣን ነዋ! አስቂኝነቱም እዚህ ላይ ነው፡፡ እናም በዚያች ጠባብ ቢሮ ኩዴታ የተከናወነባቸው ጄኔራል ፋንታ በላይ በሁኔታው ተበሳጭተው ስብሰባውን ጥለው ወጡና በር ላይ እጃቸውን ኪሳቸው ከተው መንጎራደድ ጀመሩ፡፡ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ንጉሴ ቦታውን የያዙት "ይምሩት" የሚል ፈቃድ

አግኝተው አይደለም፣ በማዕረግ በመብለጣቸውም አይደለም። ሲመሩት የቆዩት ጄኔራል ስለዘገዩ ብቻ ኗው።

ከጅምሩ መንግስቱን ለመሸኘት ሽመገኘት እየነበረባቸው ሳይገኙ የቀሩ ጄኔራሎች በመኖራቸው ምክንያት ጠርጣራው የደህንነት ሚኒስትር ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴ የቀሩትን ጄኔራሎች የሚከታተል ቡድን አሰራጭተው ተጀምሮ እስኪጨረስ የነበረውን ሁኔታ ይከታተሉ ነበር። የመፈንቅለ መንግስት አድማ መሆኑን እንዳረጋገጡም የመንግስቱ ቀኝ እጅ ለሆነው ለሻምበል (በኋላ ሻለቃ) መንግስቱ ገመቹና ለሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን አሳውቀዋቸዋል።

እነዚህ ሦስቱ ተመካክረው የፓርቲው ፖሊት ቢሮ አባላትና የመንግስት ምክር ቤት አባላትን፣ እንዲሁም በቅርብ የተገኙትን ሚኒስትሮች ወደ ቤተመንግስት ከጠሯቸው በኋላ በጋራ ምክክር "ሰው ልከን ፍላጎታቸውን እንወቅ" የሚል አቋም ይዘው ኮሎኔል ደበላ ዲንሳንና ኮሎኔል ሃዲስ ተድላን መርጠው ከአንድ ፖሊስ ጋር ላኳቸው።

መልዕክተኞቹም "... የያዛችሁት ጉዳይ ደም መፋሰስ እንዳያስከትል በጋራ እንምከርበት ... ፍላጎታችሁስ ምንድነው?" ብለው ጥያቄያቸውኝ ለጄኔራል መርዕድ ንጉሴ አቀረቡ። ጄኔራሉም፤ "ጉዳያችን ከሰውየው ነው። እናንተን አይመለከትም፤ ነገሩም ያለቀለት ስለሆነ ምክክር አያስፈልግም" ብለው እንቅጩን ነገሯቸው ይሉናል፤ በቅርበት ሆነው ጉዳዩን የመከታተል እድል የነበራቸው የ"ነበር" ፀሐፊ ዘነበ ፈለቀ።

ሁኔታው ቀጥሏል፤ሁለት የአየር ኃይል ጀቶች በአዲስ አበባ ሰማይ ላይ እስገምግመው አልፈዋል።ጄኔራሎቹም ጉዳዩ እንደተሳካ ቆጥረው ተረጋግተው ተሰብስበዋል።

በእቅዱ መሠረትም ሜጀር ጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔና የ202ኛው አየርወለድ ክፍለ ጦር ኤታማጀዦር ሹም ኮሎኔለ ካሣዬ ታደሰ አንድ አንቶኖቭ አውሮፕላን ሙሉ የአየር ወለድ ወታደሮች ይዘው ከአስመራ ተነስተው ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ደርሰዋል።

ይህንንም በደህንነቱ ለጥበቃ ቦሌ የተመደበው ሰው ለደህንነቱ ለኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴ በመስከ ሬዲዮ ገለጸ። ኮሎኔል ተስፋዬ፤ "ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን በማን ትዕዛዝ መጣህ ብሎ ጠይቆሃል ብለህ ንገረው" ሲሉት ይህንኑ ለጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ሲገልፅ፤ ጄኔራሉ "ጄኔራል ተስፋዬ የሚባል አዛዥ አላውቅም! ለምን እንደመጣሁ ሊጠይቀኝ እንደማይችል ንገረው" ሲሉ መለሱለት።

ሜጀር ጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ በተያዘው እቅድ መሠረት በተዘጋጀላቸው መጓጓዣ ጠራቸውን ጭነው ወደ አርሚ አቪየሽን ተጓዙ። እንደደረሱም የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያንና አርሚ አቪየሽንን ከምድር ጦር ዋና አዛዥ ከሜጀር ጄኔራል ኃይሉ ገብረሚካኤል ከስብሰባው



በፊት በተገለፀላቸው መሠረት በቁጥጥር ስር አዋሉና ከሜጀር ጄኔራል አበራ አበበ የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ መጠባበቅ ጀመሩ።
ይህ በእንዲህ እንዳለ ለስብሰባ በተመረጠው ጊቢ ውስጥ ያለው ሁኔታ ደግሞ ጄኔራል ፋንታ በላይ ደጃፉ ላይ መንጎራደዳቸውን እንደቀጠሉ ሲሆን፤ጄኔራል መርዕድ ንጉሤም የመሪነት ቦታውን እንደያዙ የተለያዩ ውሳኔዎችን እያሳለፉ ነበር።ጥቂት የኮር አዛገሮች እየተጠሩ በስብሰባው ላይ እንዲገኙ ሲደረግ፤የመንግስቱ ታማኝ የተባሉትን የማዕከላዊ ዕዝ አዛዥ የነበሩትን ሜጀር ጄኔራል ዘለቀ በየነ የደርግ አባልም ስለነበሩ "ለስራ ጉዳይ ይፈለጋሉ" ተብለው ተጠርተው በአንድ ክፍል እንዲታሰሩና እንዲቆለፍባቸው ተደረገ።

በዚህ መሀል ከመሰብሰቢያ ክፍሏ ውጪ ያለውን ሁኔታ እንዲቃኙ የተላኩት ሜጀር ጄኔራል አበራ አበበ በመከላከያ ሚኒስትር ጊቢ ውስጥ የነበሩትን ወታደሮችና ሲቪል ሠራተኞች ሰብስበው "ጨቋኙና አምባገነኑ መንግስት ወድቋል! ከዚህ በኋላ..." እያሉ የመፈንቅለ መንግስቱን ሁኔታ በንባብ እያሰሙ ሞቅ ያለ ጭብጨባ እየተቀበሉ ነበር። ምኑም ሳይያዝ፣ የሚዲያ አውታሮችን በቁጥጥር ስር ሳያውሉ፣ ገና አንድ እርምጃ እንኳ ሳይጓዙ ጊቢው ውስጥ ላሉ ሃያና ሰላሳ ሠራተኞች ይህን የመሰለ መግለጫ እየሰጡ ማስጨብጨባቸው ሌላው አስቂኝ ገጽታ ነው።
እነዚህ ጄኔራሎች መንግስቱ ከዚህች ሰዓት ጀምሮ ከስልጣን መወገዱንና የመንግስት ለውጥ መደረጉን የገለፁት ለማን ነው? ብንል ለራሳቸውና ለእነዚያ ጥቂት ግለሰቦች ነው መልሱ። በተቃራኒው ግን ኤርትራ ያሉት በአስመራ ሬዲዮ ጣቢያ ለህዝብ ይፋ አድርገው ነበር።

የግለሰቦችን ጭብጨባ ሰምተው ከቢሮአቸው የወጡት የመከላከያ ሚኒስትሩ ሜጀር ጄኔራል ኃይለጊዮርጊስ ፈቃዳቸውን ያልተጠየቁበት ስብሰባ በቢሯቸው አጠገብ መካሄዱ ገርሟቸው ወደ ቦታው ሊያመሩ በሚራመዱበት ጊዜ ጄኔራል አበራ አበበ ለአንድ የጥበቃ መኮንን "ጥብቅ ጥበቃ ይደረግ" የሚል ትዕዛዝ ሲሰጡ ሰሙና "እኔ በማላውቀው ጉዳይ ላይ የሚካሄድ ጥብቅ ጥበቃ ምንድነው?" በማለት ርምጃቸውን ገታ አድርገው ጠየቁ። በዚህ ጊዜ እያንበቡ ያስጨበጭቡ የነበሩት ጄኔራል አበራ አበበ፤ "አንቱ ሰውዬ ተውኝ ብልዎ አልተውኝ አሉ አይደለም?" በማለት የቆየ ቁርሾ እንደነበራቸው በሚጠቁም አነጋገር ሲቆጡ፤ ሚንስትሩ በቁጣ ሽጉጣቸውን መዘገ ሲያደርጉ ጄኔራል አበራ አበበ ቀድመው ተኩሱና ጣሏቸው። የመከላከያ ሚንስትሩ ሜጀር ጄኔራል ኃይለጊዮርጊስ በዚችው ጥይት ህይወታቸው አለፈ።

የኃይል ስምሪቱን ለማስተባበርና የስብሰባውንም ደህንነት የማስጠበቅ ኃላፊነት የተሰጣቸው ጄኔራል አበራ አበበ አንድ ነብስ

አጥፍተው፤ ሁኔታውንም ለተሰብሳቢዎች ሳይገልፁ፤ ሂጃለሁም ሳይሉ ጊቢውን ለቀው እግሬ አውጪኝ ሓሉ።

ተሰብሳቢዎቹ ያወቁት ጉዳይ የለም፤ ስብሰባውን ቀጥለዋል።ከአስመራ ይመጣል ብለው የሚጠብቁት የአየር ወለድ ጦር በምን ሁኔታ ላይ እንዳለና መድረስ አለመድረሱን አያውቁም።

ጄኔራል አበራ አበበ ጥለው እንደሸሹ አያውቁም፣ ከአስመራ ይዘዋቸው የመጡትን አየርወለዶች ጄኔራል ቁምላቸው ምን እንደሚያሂቸው አያውቁም፤ ምክንያቱም የጄኔራል አበራን ትዕዛዝ በመጠባበቅ ላይ ናቸውና። ጄኔራል ቁምላቸው ቀጣይ ትዕዛዙ ለምን እንደዘገየ አያውቁም፣ አየር ወለዶችም ስላልተገለፀላቸው ለምን እንደመጡ አያውቁም። በቃ አያውቁም ባያውቁም ሆነ ነገሩ ሁሉ።

የፖሊስ ጠቅላይ አዛዥ ሜጀር ጄኔራል ወርቁ ዘውዴ ነገሩ አላምር ብሏቸው ይሁን፣ ጥበቃውን ለማጠናከር ይሁን በማይታወቅ ሁኔታ ስብሰባውን ጥለው ወጡ። ከዚህ በኋላ ማንም አልወጣም። ወዲያው እሩብ ጉዳይ ለሰባት ሲሆን በሻምበል መንግስቱ ገመቹ የተመራው የቤተመንግስቱ ቅልብ ጦር የመስሪያ ቤቱን ጊቢ ዙሪያውን አጠረው። የልዩ ጥበቃ ብርጌዱ ጦር ከበባውን እንዳደረገም ማንም እንዳይወጣ፣ ማንም እንዳይገባ የሚል ትዕዛዝ ከሻምበል መንግስቱ ገመቹ ተሰጠና ይሄው ትዕዛዝ ተግባራዊ ሆነ።

ሻምበል መንግስቱ ገመቹ ይህን በድል እንዳጠናቀቀውና የቀረው በምድር ጦር ውስጥ አርሚ አቭየሺን የመሸገው ኃይል እንደሆነ ለሌተናል ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ገለፀ። ቀጥል ተባለ። ቀጠለ።

በዚህ መሐል ሁለተኛው ዙር የአየር ወለድ ጦር ከአስመራ ተነስቶ ቦሌ ደረሰ። ይህንንም እዚያ የነበረው ጠባቂ በታዘዘው መሠረት ለደህንነቱ ለኮሎኔል ተስፋዬ ገለፀ። አለቃቸውን ጠይቆ እንደተረዳውም ከጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ብቻ ትዕዛዝ ተቀበሉ ተብለው የተላኩ መሆናቸውን ጨምሮ ነበር በመስክ ሬዲዮ መረጃ ያስተላለፈው።

ይህን ገለፃ በያዘው ሬዲዮ ከደህንነቱ እኩል ያዳምጥ የነበረው ሻምበል መንግስቱ ገመቹ በደህንነት ሚኒስትሩ እና በመረጃ አቀባዩ የሬዲዮ ንግግር ጣልቃ ይገባና "እንድም ነገር አትንገራቸው፤ እንሄዳለን ወደሚሉበት ይሂዱ" ብሎ ትዕዛዝ አስተላለፈና አብሮት የነበረውን ሻለቃ ሽለማ ኤልማናን "አብዮት አደባባይ ላይ ጠብቀህ አስቁማቸውና ጄኔራል ቁምላቸው ታላቁ ቤተመንግስት እንደሚገኙ ነግረህ ወደዚያው ይዘሃቸው ሂድ" ብሎ አዘዘው። ሻምበል መንግስቱ ገመቹ እነዚህን ትዕዛዞች ከሰጠ በኋላ የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያንና አርሚ አቭየሽንን ይዘው ትዕዛዝ ይጠባበቁ የነበሩትን "ወንድሞች ጥቂት ችግር ነበር፤ አሁን ችግሩ ተወግዷል፤ ስለደከማችሁ መሣሪያችሁን አስቀምጡና ረፍት አድርጉ"



አላቸው። መሣሪያቸውን ከግምጃ ቤት እንዲያስቀምጡ ካደረገ በኋላ "የመጣችሁት ለተሳሳተ ተግባር መጠቀሚያ እንድትሆኑ ነበር። ነገሩ እስከሚጣራ በጥበቃ ስር ሆናችሁ እዚህ ትቆያላችሁ" በማለት በቁም እስር አቆያቸው። ይሄን ተግባር ፈፅሞ ሲመለስ ሻለቃ ሽለማ በታዘዙት መሠረት በሁለተኛው ዙር የመጣውን አየርወለድ ወደ ቤተመንግስት መርተው አስገብተዋቸው ነበር።

በሁለት ዙር የመጡት ከታገቱ በኋላ ሦስተኛው አንቶኖቭ አዲስ አበባ ደርሶ ለማረፍ እያንዣበበ እንዳለ "ለተሳሳተ ተግባር የተላኩ ወታደሮችን መጫንህ ስለተረጋገጠ፤ ወደመጣህበት ተመለስ። እንቢ ካልክ ባለህበት እንደምትጋይ እወቅ" የሚል ማስጠንቀቂያ ለአብራሪው ሲነገረው ወደመጣበት ተመለሰ።

በዚያች ዕለት አገሪቱን እየመሯት የዋሉት ሻምበል መንግስቱ ገመቹና ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴ ነበሩ ለማለት ይቻላል። የአድመኞቹን የግንኙነት መስመር በማቋረጥ ደህንነቱ ኮሎኔል ተስፋዬ፣ የአድመኞቹን አጋዥ ወታደሮችና የአዛዦችን የትብብር መረብ በመበጣጠስ ሻምበል መንግስቱ መተኪያ የሌለው ሚና ተጫውተዋል።

ከስብሰባው ውጪ ሆነው ጦር እንዲያስተባብሩ የተመደቡት ጄኔራል ቁምላቸው ደጀኔ ጥቂት ወታደሮችን ይዘው በግራ መጋባት ሲጠባበቁ ከቀኑ 10 ሰዓት በአንድ መቶ አለቃ የሚመሩ በሻምበል መንግስቱ የተላኩ የልዩ ጥበቃ ብርጌድ ወታደሮች እርሳቸው ወዳሉበት ሄዱ። እነዚህ ወታደሮች አካባቢውን እንዲቃኙ ቀድመው ተላኩ እንጂ ሌላ ትዕዛዝ ያልተሰጣቸው ነበሩና ሄደው ከጄኔራል ቁምላቸው ሠራዊት ጋር ተላተሙ። ጄኔራሉ ይህን ምንነቱን ያላወቁትን ወታደር አብረዋቸው በነበሩት ወታደሮች አስከብበው ትጥቁንም አስፈትተው ባዶ ቤት ውስጥ አዘጉባቸው። እነርሱን ተከትለው የሄዱ ሌሎች ወታደሮችም በታንክ ታግዘው ወደ ቦታው ሲያመሩ ጄኔራሉ በተመሳሳይ አስከብበው ታንካቸውንም ማርከው በግራ መጋባት መጠባበቃቸውን ቀጠሉ።

ሜጀር ጄኔራል ቁምላቸው ያለውጊያ እነዚህን ወታደሮችና ታንካቸውንም ጭምር በቀላሉ መማረክ ቢችሉም ከበላዮቻቸው ጋር የነበረው ግንኙነት በመቋረጡና ቀጣይ ስራቸውንም ባለማወቃቸው ምንም ሊያደርጉ አልቻሉም።

ምሽት 12 ሰዓት ላይ ሻምበል መንግስቱ ገመቹ እንደተከበበ ወደዋለው ወደ መከላከያ ጊቢ አምርቶ በድምፅ ማጉያ ጊቢው እንደተከበበና በውስጡ የሚገኝ ዘበኛ፣ ሲቪል ሠራተኛ፣ ባለሥልጣን፣ ጄኔራል ሁሉም እጁን ጭንቅላቱ ላይ አጣምሮ በሁለተኛው በር እንዲወጣ አሳሰበ። ሁሉም በአምባሳደር ቴአትር ቤት በኩል ባለው በር እጅ ወደ ላይ አድርገው ሲወጡ፤ ብርጋዴል ጄኔራል አምሃ ደስታ እዚያው